
ፍትሕን በራሴ
3ተኛ
ዕትም
18+
እውነተኛ ታሪክ
በሊዛ ተሾመ

# ፍትሕን በራሴ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልቦለድ)

በ

ሊዛ ተሾመ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ

©መብቱ በሕግ ተጠበቀ ነው።

## ምስጋና

የጥበቦች ሁሉ ባለቤት ለሆነው ልዑል!
እና
በመጽሐፉ ላይ እጃቸው ላለበት ሁሉ!

መታሰቢያነቱ
የወሲብ ጥቃት ለደረሰባቸው

የመጀመርያ ሥራ፡- አሜከላ ያደማው ፍቅር

ዋና አከፋፋይ
ዮሐንስ መጽሐፍት
አውቶብስ ተራ
+251-922-430617

የዕሁፍ ሥራ
ጅናስ ቢዝነስ ሴንተር
+251-912-056803

ለአስተያየትዎ
ሲባ
ፖ.ሣ.ቁ 46490
አዲስ አበባ፡-ኢትዮጵያ
Email: life57happens@hotmial.com

# መግቢያ

ውድና የተከበራችሁ አንባብያን ዳግም በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል፡፡ መቼም በመጀመርያ ሥራዬ «አሜከላ ያደማው ፍቅር!» በሚለው ልቦለድ እንደተዋወቅን እርግጠኛ ነኝ፡፡ አሁን ደግሞ «ፍትሕን በራሴ!» የሚለውን በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልቦለድ እንሆ! ስለመፅሐፉ በጥቂቱ ካላችሁኝ… ፊደል ሳልመርጥ መግለፅ የፈለግኩትን በተመቸኝ አማርኛ እና ፊደል አስቀምጫለሁ፡፡ እነ"ሰ"ም ሆኑ እነ"ሀ" እስከ ዘመዶቻቸው አሉ ለማለት ፈልጌ ነው፡፡ በተጨማሪም በታሪኩ ውስጥ ወሲብ እና ፍቅር ግብግብ ሲገጥሙ እናያለን፡፡ ፍቅር እና ጥቅምም ጥሎኞች ናቸው! ፍቅር፣ ኃይማኖት የግል መሆኑን አይከድም! በአለመቻል በሽታ የተጠቁም ሰዎች መፍቴሔ አጥተው ሲሰቃዩ እናያለን፡፡ ኧረ ሞትንም የተጠሙ ሰዎች አሉ! የፍትሕ እጦት ያስከራቸው ደግሞ ፍትሕን ፍለጋ ጦር ሲመዙ እናያለን፡፡ ሴት ወንድን ወደ ስሪያ ሜዳ እየመራች በወሲብ አለንጋ ስትገርፍ ማየትም ቀላል ነው! ሌላው «የወንድ ብልት በ አደፍርስ» እንዲሁም «የሴት ብልት በ ድንቅነሽ» መሰየማቸውን በትህትና እገልፃለሁ፡፡

በተረፈ ውስጥ እንገናኝ……..!

# ክፍል አንድ

## ድብቁ አላማ

ህይወት በእራሷ መንገድ ሰውን የሚያህል ክቡር ፍጡር እየመራች፣ ከፈለገች ከገደል፣ ካማራት ከምድራዊ ሲኦል፣ በይ ካላት ደግሞ ከምድራዊ ገነት የምትከት፣ ከባድ የቁማር ሊቅ ናት! ህይወት ከሰው ጋር ቁማር መጫወት የምትጀምረው ገና ከእናቱ መህፀን ብቅ ከማለቱ በአዋላጅ እጅ ጭንቅላቱ ተጨምድዶ ከሚጎተትበት ቁማራዊ ክዋኔ ይጀምራል፡፡ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ!» የሚለው የታላቁ መጽሐፍ ቃል እስኪፈፀም ድረስ ህይወት ለማሸነፍ ቁማሩን ረከዛ ትጫወታለች፡፡ የታገላት ከምድራዊ ገነት የመግባት እድል ሲኖረው፣ የቁማሩ ስልት ያልገባው ድግሞ፣ ምድራዊ ሲኦል ገብቶ እድሜውን ሙሉ እከኩን እንዳከከ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ የሚለውን ቃል እውነትነት ያረጋግጣል፡፡

እኔ እንደ ህይወት የቁማር ሊቅ ባልሆንም፣ «ጥሩ ተጫዋች ነኝ!» ህይወት ለማሸነፍ፤ እኔ ደግሞ የጭዋታው መሪ ለመሆን  ቁማሩ እንዳለ ሆኖ ወደ ተፈበረኩበት መመለስ የውዴታ ግዴታዬ ነው፡፡ በምድር ላይ እስካለሁ ድረስ ደግሞ ነዋሪ እንጂ አኗኗሪ መሆን አልፈልግም፡፡ ማግኘት የምፈልገውን ነገር ለማግኘት ከሞት ጋር ቡጢ መግጠም ካለብኝ አደርገዋለሁ፡፡ የልጅነት ህልሜ ደራሲ መሆን ነበር፤ ደራሲ አምሮት ካንትይገኝ መባል፤ ህልም ከእንቅልፍ ሲነቁ የሚጠፋ ነገር ነው፣ አምሮት ካንትይገኝ ግን ከነብልሀቷ ወደ ፊት ትቀጥላለች፡፡

ወደ 'ዚች የውሸት ካምፕ ከመጣሁ ጀምሮ የደስታ ጐረቤት እንጂ እመቤት ሆኜ አላውቅም፡፡ የትውልድ ሀገሬን ድሬዳዋን ለቅቄ አዲስ አበባ ስገባ አጐቴ ቤት ነበር ያረፍኩት፡፡ እድሜ ለአጎቴ ሚስት! አጐቴ ቤት የተቀመጥኩበት 4 ወር ስድስት ዜሮዎችን ያስከተለ 4 የችግር አይነት ያየሁበት የቀናት ጥርቅም ነበር፡፡ የተወለድኩበትን የፍቅር ከተማ ከለቀቅኩ ዛሬ አንደኛ ዓመቴን ይዣለሁ፡፡

ከጓደኞቼ ትእግስት እና ማህደር ጋር የተዋወቅነው ባሌም ጓደኛዬም ለማለት ከሚቸግረኝ ወንድ ጋር የማዘውትርበት መቃሚያ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ትእግስት እና ማህደር ከተለያዩ ወንዶች ጋር እየመጡ መቃሚያ ቤቱን ያደምቁት ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ጓደኝነታችን እየጠበቀ መጣ፡፡ የሁለቱ ሥራ በጨለማ ተውጣ ሰው ሰራሽ መብራት ያስዋባትን ካሣንችስ አምራ እና ደምቃ እንድትታይ ተውበው በጐዳናዋ ላይ መንሸራሸር ነው፡፡

ካሣንችስን የሚያሣምሯት ከዋክብት የእኔ ጓደኞች ከሆኑ ጀምሮ፣ ከትውልድ መንደሬ እያክለፈለፈ ያመጣኝ፣ ድብቁ አላማዬ፣ የሚሣካበት ቀን ቅርብ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ እየተቀጣጠርን በተለያዩ መዝናኛ ቦታዎች መገባበዝ ከጀመርን ወራት ተቆጥረዋል፡፡ ከእነሱ ኑሮ የኔን የተሻለ የሚያደርገው ምንልባት ለቤት ኪራይ እና ለምግብ አለማሰቤ ይሆናል፡፡ በተረፈ የኔም ኑሮ ያቅለሸልሻል፡፡

በአጐቴ ሚስት መርዛማ ምላስ ተነድፌ መድኃኒት ሳጣ፣ ከድሬዳዋ ስመጣ የተዋወቅኩት ጥቁር ድንክ ቦርጫም የኮሌጅ አስተማሪ ቤት

ማክሰኞ ጠዋት ቲጂ እድል ስቃላት ተደስታ ገባች፡፡ ማዱን ግን ፊት ነስታት ስለነበር አዝና ነው የገባችው፡፡ ማርኮ ደውሎ እራት ስለጋበዘን እኔ እና ቲጂ ልብስ ስንለካ ስናወልቅ ሠዓቱን ገፋነው፡፡ መጨረሻ ላይ ጀርባው ክፍት ጡት የሚያሣይ ረጅም ቀይ ቀሚስ ከማህደር ተውሼ ለበስኩ፡፡ ቲጂ አጭር ጥቁር ቀሚሷን ለበሰች፡፡ እኔ ብዙ መቀባባት ባይመቸኝም፣ ቀይ ሊፕስቲክ ለከንፈሬ፣ ጥቁር ኩል ለዐይኔ አልነፈግኩትም፡፡ ቲጂ የቀለም ማስታወቂያ የምትሠራ ይመስል ፊቷን በሜካፕ አጨናንቃው ከቤት ወጣን፡፡

በኮንትራት ታክሲ ዞና ብለን የተባልነው ቦታ ደረስን፣ ቀኑ ቅዳሜ በመሆኑ የምግብ አዳራሹ ውስጥ በጣም ብዙ ሰው አለ፣ የነጭ መዓት የአገሬን ክትፎ ሊና ጠጅ ያስገባል፡፡ ሰውነቴ የሰዉን አይን መቋቋም አልቻለም፤ እግሬ ተሳሰረብኝ፣ እጄን አላበኝ፣ ኡምቤርቶ ወደ ተገተርንበት ሲመጣ ትንሽ ተንፈስ አልኩ፡፡ እንገቴ ስር ስሞኝ፣ እጁን ቀጠን ያለ ወገቤ ላይ አሣርፎ፣ ወደ ቦታቸው ወሠደን፡፡ እራቱ በሀበሻ ልብስ ባሸበረቁ አስተናጋጆች በክብር ቀረበልን፡፡ ቀይ ወይን የዘወትር ምርጫዬ ስለነበር ወይን አዘዝኩ፡፡ ቲጂ ምርጫዬን ተጋራች፡፡ በሀገራችን ባህላዊ ጭፈራና ዘፈን እየተዝናናን እራታችንን በላን፡፡ ወይኑ ገብቶ ስራውን መስራት ጀምሯል፡፡ በሆነ ባልሆነው መሣቅ ስራዬ ሆነ፡፡ ኡምቤርቶ አልጋ ላይ ሆነን ብንጫወት የተሻለ እንደሆነ በጆሮዬ ሹክ አለኝ፡፡ እንቢ ድሮ ቀረ! በኮንትራት ታክሲ ወደ አረፈበት ሆቴል አመራን፡፡

መኝታ ክፍሉ እንደገባን በር መቆለፊያ ጊዜ አልነበረንም፡፡ ግርግዳው ላይ አጣበቀኝ፡፡ ፓንቴን ማን ያውልቀው? ተስገበገብና! የልብሴ እጣ ፋንታም አሣስቦኝ ነበር፡፡ ያውም የተወሰ! አይቼው የማላውቀው አሳሳም ስለገጠመኝ ይሁን ስለተመቸኝ አላውቅም ከንፈሬን ከከንፈሩ ላይ ለማላቀቅ አልፈለግኩም፡፡ ኡምቤርቶ ልዩ ነው! የውስጡን ትኩሣት በጅሮዬ ልክ ከሙቀቱ እየዘፈቀ ትንፋሽ አሣጣኝ፡፡ በስቃዬ እረክቶ እፎይታን ሰጠኝ፡፡ ያማረ አልጋ የናፈቀው ገላዬ የወደቀበትን ሳያውቅ ነጋ፡፡

ጠዋት የማታው ሠላማዊ ጦርነት ተደግሞ፣ ቁርሣችንን ልንበላ ወደ እንግዳ መቀበያው ስንወርድ፣ ቲጂ እና ማርኮ ቁርሣቸውን እየበሉ አገኘናቸው፤ እኛም የራሳችንን ቁርስ አዘዝን፡፡ ቲጂ የደበራት ትመስላለች፡፡ ያልተመቻት ነገር ምን እንደሆነ ጠየኳት፡፡ ማርኮ በቂጥሽ ካልሰጠሽኝ እያለ ሲያስቸግራት እንዳደረ ነገረችኝ፡፡ ዘገነነኝ!

የኡምቤርቶን ሰማያዊ ዓይኖች ወድጃቸዋለው፡፡ ግንባርህ ላይ ካልተደፋሁ የሚል ውብ ፀጉር ባለቤትም ነው፡፡ ሰውነቱ በስፖርት የዳበረ ነው፡፡ ቁመት ሲታደል ቀድሞ ብሎ የተገኘ መሆኑን ቁመቱ ይመሰክራል፡፡ ብቻ የጐደለው ነገር የለም! ማርኮ ቁመናው በጣም ያምራል፡፡ ግን ቅልብልብ አይኖቹን አልወዳቸውም፡፡ የሴት መቀመጫ ካላየህ አይንህ ይጠፋል የተባለ ይመስል ከሄዶች ከመጣችው ጋር ዓይኑ ይንከራተታል፡፡ "መቀመጫ" የሚለው ሙሉ ስም የሚገባው ለቲጂ ቂጥ ነው፡፡ አይን አዋጅ ላለበት ሰው ግን ቆርጠው በትሪ ቢያቀርቡለት እንኳ አይኑ ከመቅበዝበዝ አይድንም፡፡ ለነገሩ ሰውየው ጉዳዩ ከቂጥ ላይ

ስለሆነ አይፈረድበትም፡፡ ዳግም እንደ ምንገናኝ ተስፋ እያደረግን፣ እኔ እና ቲጂ ተሰናብተናቸው ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

እቤት ስንገባ ማህደር አመዱን የጣለ ከሠል ላይ አፉ የተሸራረፈ ጀበና ጥዷ ሲጋራዋን ታቦላለች፡፡ ነጩ፣ የኒኬል ሰሀን ላይ የተደረደሩት አራት እሮጌ ሲኒዎች እንዳልተቀዳባቸው ይመሰክራሉ፡፡ ቀሚሷን ባስቸኳይ እንዳወልቅ ቆጣ ብላ አዘዘችኝ፡፡ ደንገጥ በዬ ማውለቅ ጀመርኩ፡፡

«ቲጂ እስቲ ብር አበድሪኝ!» አለች ማህደር፡፡

«ውይ ማዱዬ የለኝም!» አለቻት ቲጂ፡፡

«ሕንጭ ጋር አይደል እንዴ ያደርሽው?» አለቻት ቆጣ ብላ፡፡

«ቀሚስሽን ልግዛሽ!» አልኳት ፈጠን ብዬ፡፡ እድሜ ለኡምቤርቶ ቦርሳዬ ውስጥ አስር የመቶ ብር ኖቶች ተኝተዋል፡፡

«200 ብር አምጪ!» አለችኝ በደንብ ያልፈላና ያልሰከነ ቡናዋን እየቀዳች፡፡

«መቶ ትውሰደው! ምክንያቱም በጣም ብዙ ጊዜ ለብሰሽዋል፣ ብርም አላወጣሽበትም፡፡» አለቻት ቲጂ፡፡ ማህደር ተስማማች!

«የዚህን ቀሚስ ጉድ ልንገርሽ!» አለችኝ ቲጂ፡፡ ማህደር ሳቋን ለቀቀችው፡፡

«አንድ የውጪ ዜጋ ደንበኛ ነበረኝ፡፡ የፍቅረኞች ቀን የሚከበርበት ቀን ሲደርስ ባህሌ ባይሆንም እሱን ላስደስተው ብዬ ቀይ ቀሚስ ልግዛ ወደ ሀያሁለት ማዞሪያ ከእጅሬዋ ጋር ተያይዘን ሄድን፡፡ አጅሬት 'ዚች ቀሚስ ላይ አይኗን ጣለች፡፡ ብር ግን የላትም! ልለካ ብላ ጠቅልላ ቦርሣው ውስጥ ከከተተች በኋላ እንደ ጤነኛ ሰው ከሱቁ ሹል

ብላ ወጣች፡፡ እኔ ገንዘቤን አሟጥጬ ስለብስ እሷ የፍቅረኞችን ቀን በሰረቀችው ልብስ አከበረች፡፡» አለች ቲጂ፡፡

«ከቻልሽ መግዛት፤ ካልቻልሽ መስረቅ፡፡» አለች ማህደር፡፡

ህይወት ባለ አማራጭ ናት! ነው ነገሩ፡፡ የጠፋው ከሰል ላይ የተጣደው ጀበና ሁለተኛ ቡና ከማፍላት ዳነ፡፡ ምሳችንን በርበሬ ያለው የቲማቲም ስላጣ ጉሮሮ በሚያርድ እንጀራ በላን፡፡ እድሜ ለኡምቤርቶ የጫት እና የሲጋራ የቻልኩት እኔ ነኝ፡፡ እነሱ ከጥማቸው ለመርካት እየደጋገሙ ሲጋራ ሲያጨሱ፤ እኔ ለሙድ ሣብ ሣብ እያደረግኩ ጭሡን አቦላለሁ፤ የሆድ የሆዳችንን እያወጋን ስሷ ፋራሽ ላይ ቂጣችንን ስናለፋ ውለን ሲመሽ እኔ እና ቲጂ አጫጭር ቀሚስ ለብሰን ነጮቹ ወዳረፉበት ሆቴል ሄድን፡፡

ቆንጆው ኡምቤርቶ አልጋ ላይ ጋደም ብሎ ዐይኑን ላፕቶፑ ላይ ተክሏል። ከወገቡ በላይ እራቁቱን ነው፡፡ እንገቱ ስር ሳምኩት፡፡ ከከናፍሮቼ ከተቋደሰ በኋላ ትራሡን አስተካክሎ እንድተኛ ጋበዘኝ፡፡ ግብዣው አስፈላጊ ነውና ልብሴን አውልቄ አልጋው ላይ ወጣሁ፡፡ ዓይኖቹ ልብን የሚያቀልጥ እሣት መርጨት ጀመሩ፡፡ ከግንባሬ እስከ እግር ጥፍሬ ሳሙኝ፡፡ እጆቼ የለበሰውን ቁምጣ ለማውለቅ መታገል ሲጀመሩ እጁ ጭኖቼ መሀል ገባ፡፡ እንደ ወሲብ ዓለም የሚያስደስት ነገር ምን አለ? ቁምጣውን አውልቆ ወረወረው፡፡ አደፍርሱ ተገትሯል! በእጄ ጨበጥኩት! ግሏል! ጥንካሬው ደስ ይላል፡፡ እግሮቼ በፍቃደኝነት ይበልጥ ተራራቁ፡፡ አደፍርስ እና ድንቅነሽ ሲገናኙ ዓለም የእኔ ብቻ የሆነች መሰለኝ! ፈጣሪ ለሰው ልጆች ከፈጠራቸው አስደሣች ነገሮች

በሙሉ፣ በአንደኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ያለበት «ወሲብና ወሲብ ብቻ!» ወሲብ ሀጢያት አይደለም!!

እኔ እና ኡምቤርቶ ተጣጥመናል፡፡ በስም የማውቀው ሆቴል ቤቴ ሆነ፡፡ ግን ደግሞ ቤት መከራየት አማረኝ! ገርጂ አካባቢ ከሚገኙ የጋራ መኖርያ ቤቶች መሀል፣ ባለሁለት መኝታ ክፍል ተገኘለኝ፡፡ የቤቱ ባለቤት ቤቱን ለመሸጥ ፈልገው ገዢ ስላልተገኘ ተከራይ ማፈላለግ እንደጀመሩ ደላላው ሹክ አለኝ፡፡ እንኳን ለመግዛት ለመከራየት የሚያስችል ገቢ የለኝም፡፡ ለኡምቤርቶ አማከርኩት፡፡ ክራዩን በእኔ ጣይው አለኝ፡፡ አንድ ሀሳብ ተቃለለልኝ!

ለቲጂ እና ለማህደር አንደኛውን መኝታ ክፍል አከራየኋቸው፡፡ ኡምቤርቶ የመኝታ ቤት እቃ ሲገዛልኝ፣ ትእግስት ማርኮ በሠጣት ብር ያገለገለ ሶፋ እና ማቀዝቀዣ፣ ማህደር ደግሞ ያገለገለ ቴሌቪዥን እስከ ማስቀመጫው ገዛች፡፡ እንደየአቅማችን የእቃ ቤት እቃዎችን አሟላን፡፡ ሁለቱ መኝታ ክፍላቸውን ባገለገለ እቃ አሳመሩት፡፡ ቲጂ ካሚንችስን ከተወቻት ሰንብታለች፡፡ ማህደር ግን ደህና የሚረዳት ሰው ስላላገኘች አልፎ አልፎ በካሚንችስ ጉዳና ስትንሸራሸር አምሽታ እድል ከቀናት እየሣቀች ካልተሣካላት አኩርፋ ትመጣለች፡፡

አርብ ሠዓቱ ልክ 6፡15 ሲል እኔ እና ቲጂ መርካቶ ደረስን፡፡ አንድ የኤሌክትሮኒክስ መሸጫ መደብር ፊት ለፊት ቁመት ሎጋ ወጣት የሙስሊም ቆብ ደፍቶ እጁን እያወናጨፈ ስልክ ያወራል፡፡ ቲጂን ትቻት ወደ እሱ ገሰገስኩ፡፡ ያላየሁት መስዬ አላዩ ላይ ወጣሁ፡፡

ሞባይሉ ወደቀ። እሣት የለበሱ አይኖቹን ተከለብኝ። ረጋ ብዬ ሞባይሉን አንስቼ ሰጠሁት። መንጭቆ ተቀበለኝ።

«እያየሽ አተሂጂም? ነጃሳ! ኤፍሬም ኡዱ የማደርግበትን ውሀ አምጣለኝ። ቶሎ በል!» አለ ቁመተ ለጋው ወጣት። የታዘዘው ወጣት እየሮጠ ወደ ውስጥ ገባ።

«ነጃሳ ነው ያልከው?» አልኩት ኮስተር ብዬ።

«አቦ እናትሽ ትበዳ!... ጥፊ ከፊቴ! ምን ትመስላለች?» አለኝ። እዎ! ሲቆጣም ያምራል!

«እራስህን በምን ሒሣብ ነው የምታየው ባክህ?» አልኩት የተናደድኩ ለማስመሰል እየሞከርኩ።

«አንተ የሠላት ሠዓት አለፈኮ አትሂድም?» አለችው ሂጃብ የለበሰች ተለቅ ያለች ሴት ሱቁ በር ላይ ቆማ።

«ኡዱ አድርጌ ከዛ ነጃሳ ልጅሽ ጋር እያወራሁ፣ ይቺ ፈረስ ደግሞ እላዬ ላይ ወጣችብኝ!... እንደገና ኡዱ ላደርግ ነው!...» አላት ብስጭት ብሎ።

«የተናደድክ የምታስመስለው ንዴት እንደሚያምርብህ ስለምታውቅ መሆኑን ስለማውቅ ብዙ አትልፋ ታምራለህ!» ብዬው ከጠቀስኩት በኋላ ልገዛ የመጣሁትን እቃ ትቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

እርግጠኛ ነኝ ከጭንቅላቱ እንደማልጠፋ! ወንዶች ያልጠበቁትን ነገር የምታደርግ ሴት ቀልባቸውን መቆጣጠር ትችላለች። ደፋር ሴት ትስባቸዋለች። ሆን ብዬ ያደረኩት ነገር ስኬታማ መሆኑን የማውቀው

ድጋሚ ያገኙሁት ቀን ነው፡፡ እቤት እንደገባን፣ ቲጂ ባልታጠበ እጇ እንጀራ አቅርባ፣ ካልተሞቀ ሽሮ ጋር ይዛ መጣች፡፡ እርቦኝ ስለነበረ የሽሮውን መቀዝቀዝ ባላየ ምሳዬን በላሁ፡፡ መርካቶ የሄድኩት ሞባይል ለመግዛት ነበር፡፡ ግን…

«ደግሞ ነጃሳ ይላል! እራሱ ነው ነጃሳ!» አልኩ እምልጠኝ፡፡

«የነጀሽውማ አንቺ ነሽ! ውስጥሽ ስለእሱ እያሰበ መሆን አለበት፡፡ መቼም በጤናሽ ሰውየው በሌለበት ከመሬት ተነስተሽ አትሳደቢም፡፡» አለች ቲጂ፡፡

«ማነው?» አለች ማህደር እስፍስፉ፡፡

«እንዱ ጢባራም አስቀያሚ!» አልኳት፡፡

«አስቀያሚ አይተሽ አታውቂም!» ቲጂ ተውረገረገች፡፡

ቆንጆማ ቆንጆ ነው!… ግን ደግሞ አስቀያሚ ነው!… እመሻሹ ላይ ሞባይሉን ለመግዛት ሀያሁለት መዞርያ ያሉትን ሱቆች ስንጎበኝ ቆይተን፣ ቀልቤን የሳበውን ባለካሜራ ሞባይል ገዛን፡፡ ቀን መርካቶ ያገኘሁት ወጣት እየተጐማለለ እኛ ወዳለንበት ሱቁ ገባ፡፡ ምርጥ አጋጣሚ! ከባለሱቁ ጋር ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ የት ነው የማውቃት? ብሎ ነው መሠለኝ ትኩር ብሎ ተመለከተኝ፡፡ ቀን ያየኝ በቱታ ነበር፡፡ በሰዓቱ የለበስኩት ደግሞ የሰውነቴን ቅርፅ የሚያጎላ ልብስ ነው፡፡ ብዙ ካሠላሠለ በኋላ አገኘኝ፡፡

«ሞጥሚጣ!» አለኝ፡፡

«አንተ ደንበኛዬን አታስቀይምብኝ!» አለ ባለ ሱቁ፡፡

«ደግሞ አሁን ምን ይሁን ነው የምትለው?» አለችው ቲጂ ፡፡

«የቀኑ ጢባራም ይሄ ነው?» አለች ማህደር አይኗን ጎልጉላ፡፡

«አብዲ እባላለሁ! ጢባራም ነው አለችሽ?» አለ ሳቅ ብሎ፡፡

«ማህደር እባላለሁ! ማዱ ብለህ ብትጠራኝ ደግሞ ደስ ይለኛል! በጣም ታምራለህ! ጢባር ሲያንስህ ነው!» አለችው እየተቅለሰለሰች፡፡

«እመስግናለሁ! ማዱ!» አላት ኮራ ብሎ፡፡

«እኔ ደግሞ ሚካኤል እባላለሁ! ለምን ሻይ ቡና አንልም? የሞባይልሽን አጠቃቀም በጣም ባሳይሽ ደስ ይለኛል፡፡» አለኝ ባለ ሱቁ፡፡

«ግብዣ አይናቅም! እኔ በበኩሌ ተቀብያለሁ፡፡» አለች ማህደር አብዲ ላይ እንደተጣበቀች፡፡

ቲጂ ቆንጠጥ ስታደርገኝ፣ እሺም እምቢም ሳልል ተከተልኳቸው፡፡ ቀን መስኪድ ለመሄድ ሲጣደፍ የነበረው ሰውዬ፣ የክርስቲያን ስጋ ጥስቅ አድርጐ ቢራ ከለሰበት፡፡ ያለ የሌለውን እየቀባጣጠረ ሲያስገለፍጣቸው አመሸ፡፡ እኔ ፊቴ ሳይፈታ ሰፈራችን ደረስን፡፡ አብዲ ተብየው ካላደረ ስኳችሁ ብሎ ሰፈራችን ድረስ መምጣቱ ሳያንስው፣ ቤታችሁን ልይላችሁ ብሎ በፈጣጣ እቤት ገብቶ፣ ክፍሎቻችንን ጐብኝቶ፣ እኔን ከምንም ሳይቆጥረኝ፣ ከጓደኞቹ ጋር ሲጫወት አምሽቶ ወጥቶ ሄደ፡፡

በሦስተኛው ቀን ጠዋት ላይ ስልኬ ሲጠራ ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡ ቁጥሩን አላውቀውም፡፡ ከእንቅልፌ ጋር ያቆራረጠኝ ደዋይ እንቅልፍ ባደከመው ድምፄ እየተዝናና ሲያስለፈልፈኝ ከቆየ በኋላ «አብዲ ነኝ!» አለኝ፡፡ ደነገጥኩ! ለካ እጅሬ ስልክ ቁጥሬን ከቲጂ ወስዶ ነበር! መቃሚያ ቤት

ሲያገኘኝ እንደሚፈልግ ሲነግረኝ በፍፁም አልችልም አልኩት፡፡ በስንት ልመና ሀሳቤን አስቀየረኝ፤ መጀመሪያም ቢሆን መለመን ፈልጌ እንጂ መች እሱን ማግኘት ጠላሁ!?... በቦታው ሚካኤል ተብየው ባለሱቅ ስለሚገኝ ቲጂ እና እኔ ድርያችንን ለብሰን ከተባልነው ሁዓት ሰላሣ ደቂቃ አሳልፈን መቃሚያ ቤቱ ውስጥ ተገኘን፡፡ ሰላሣዋ ደቂቃ ሆን ተብላ ያለፈች ናት፡፡ ወንዶችን ጥያቄ ውስጥ መክተት ለሴቶች ጠቀሜታ አለውና!

ሺሻ እየሣብን ጫት ስንቅም አመሸን፡፡ እራት አብዲ ጋበዘን፡፡ ሦስቱ ቢራቸውን እኔ ቀይ ወይን እየጠጣሁ ሰዓቱን ገፋነው፡፡ ቲጂ እና ሚካኤል አልጋ ይዘው አደሩ፡፡ አብዲ የእንደር ጥያቄ ከአፉ አላወጣም፡፡ ቢጠይቀኝም እሺ እንደማልለው እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ግን ሁለታችንም አብሮ የማደር ፍላጐት እንደነበርን ዓይኖቻችን ይመሰክሩ ነበር፡፡ ቤቴ ስንደርስ አንገቴ ስር ስሞኝ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡

አብዲ የለኮሰውን እሣት ለማጥፋት ልብሴን ቀያይሬ ወደ ኡምቤርቶ ከነፍኩ፡፡ የፈረደበት ላፕቶፕ ላይ ተጥዷል፡፡ ልብሴን አውልቄ እርቃኔን አልጋው ላይ ወጣሁ፡፡ አላሳፈረኝም! የወሲብን ዓለም እንደ እንዝርት እያሽከረከረ አስቃኘኝ፡፡ ሰላም ያለው እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ ጠዋት ቁርሴን በልቼ ልክ ስራ እንዳለበት ሰው እየተጣደፍኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡ ቤቴ ስገባ አብዲ ሳሎን ቁጭ ብሎ ከማህደር የሚፈስለትን ወሬ ይቀዳል፡፡ ተናደድኩ! መናደድ ሳይሆን... ብቻ ጥሩ ስሜት አልተሰማኝም፡፡

«አዳር ጥሩ ነበር?» አለኝ አብዲ፡፡

«በጣም!» አልኩት ኮስተር ብዬ፡፡

«ቁርስ እንድታባይኝ ነበር አመጣጤ፣ አንቺ...»

«አስፈላጊ አይመስለኝም!» ቱግ ያደረገኝን ነገር ባውቀው ደስ ይለኝ ነበር፡፡

«እኔ አባልቼዋለው!» አለች ማህደር እጁን እየዳበሰች፡፡

«አመሰግናለሁ የኔ ቆንጆ!» አላት እጇን እየሳመ፡፡ ድርጊታቸውን ላለማየት አይኔን መሬት ላይ ተክዬ «ሊተኛ! ተጫወቱ!» አልኳቸው፡፡

«ቁጭ ብለሽ ነው እንዴ ያደርሽው?» አለኝ ከተቀመጠበት ተነስቶ እጆቹን ኪሱ ውስጥ እየከተተ፡፡

ስፊው ደረቱ ዓይኔ ወስጥ ተቀረቀረ፡፡ እስተያየቱ የሴትን ልብ ይማርካል፡፡ አብዲ!? መልስ ሳልሰጠው መኝታ ክፍሌ ገብቼ በሩን ጠረቀምኩት፡፡ ማስታወሻዬን ከትራሴ ስር አውጥቼ ትላንትናዬን ሞነጫጭሬ ትንሽ ጋደም አልኩ፡፡ ግን ልቤ ሳሎን ነበር፡፡ በሩን ከፍቼ ጭንቅላቴን አሾለኩ፡፡ ማዶ ብቻዋን ናት! የምትምገውን ሲጋራ ቀምቺያት ሁለቴ ስቤ መለስኩላት፡፡

«እኔ አብዲን ወድጄዋለው! አንቺስ?» አለችኝ፡፡

«እሱ አንቺን ካለ...» ተናግሬ ሳልጨርስ ቲጂ ከተፍ አለች፡፡ ማህደር ወደ ቲጂ ዞረች፡፡ «ጅናባሽን ለትለት ብለሽ ምሳ ስሪ!... ተረኛ ነሽ!» አለቻት፡፡

ቤቱን ስናፀዳም ሆነ ምግብ ስናበስል በተራ ነው፡፡ የቲጂ ተራ ደረሰና ፍርፍር ሰርቶ ለማቅረብ አንድ ሠዓት ፈጀባት፡፡ በዘይት የተጥለቀለቀ

የድርቆሽ ፍርፍር ከበላን በኋላ እንዙር የሚል ሀሳብ ከማህደር ፈለቀ፡፡ ሦስታችንም ቀይ ቀሚስ ለበስን፡፡ ቦርሣችን እና ጫማችንም ቀይ እንዲሆን መረጥን፡፡ ሁለ ነገራችንን በቀይ ቀለም አስውበን ሚካፕ ላይ ተለያየን፡፡ እኔ ብዙም የሚካፕ ተጠቃሚ አይደለሁም፡፡ መቀባት ካማረኝ ዓይኔን በጥቁር እርሣስ ኩሉ፤ ከንፈሬን በቀይ ሊፕስቲክ አደምቀዋለው፡፡ ቲጂና እና ማህደር በጣም ሚካፕ ያበዛሉ፡፡ ፀጉራቸው ላይ የሚቀጥሉት የዊግ አይነት መብዛት፣ የቀለሙ ማስጠላት፣ ኡ!...

ቦሌ ከሚገኙ ካፌዎች ውስጥ ለጠበሳ የሚመቸውን ቦታ መረጥን፡፡ ለማህደር እጅ ኪሡን የሚያስረክብ ለማዳ አሞራ ካገኘን ብለን እንጂ እኛስ ችግር ደህና ሰንብት ካልን ዘግይተናል፡፡ ችግር ተጣብቆ አለቅ ያላት ማህደር ከሁለታችን በእድሜ ታንሣለች፡፡ እኛ ሀያዎቹ ውስጥ ስንሆን እሷ ገና አስራ ዘጠኝ ዓመቷ ነው፡፡ የቀይ ቆንጆ ናት! እንደ እሷ የሚያበሣጨኝ ሰው የለም፤ ግን በጣም እወዳታለሁ፡፡ የዋህ ስለሆነች ታሣዝነኛለች፡፡ ቲጂን መግለፅ አስቸጋሪ ነው፤ ልቧን ማግኘት የማይሞከር ነገር ነው፡፡ ጭዋታዋ በጥርስዋ ነው፡፡ የፀይም ቆንጆ ናት!

የገባንበት ካፌ በሰው ተጨናንቋል፡፡ ባዶ ቦታ ስላላገኘን ቡና የሚጠጡ ሁለት ወጣት አሞራዎች ጋር ተዳበልን፡፡ አንደኛው ቀኝ ጆሮው ላይ ዳይመንድ መሠል አርቴፊሻል ለጥፏል፡፡ ፀጉሩ በቢጫ ቀለም የተለወሰ ነው፡፡ የሚያምሩ ትናንሽ አይኖቹን እያንከራተተ ከንፈራሙ ጓደኛው የሚፈተፍትለትን ወሬ እየኮመኮመ፤ የሚያማምሩ ጥርሶቹን ብልጭ ያደርጋል፡፡

«ዛሬ የፍቅረኞች ቀን ነው እንዴ?... » አለ ከንፈራሙ፡፡

«ተሳስተሀል! ቀይ ልብስ የሚወድ ዛር ስላለብን ነው በቀይ ያሸበረቅነው፡፡» አልኩት፡፡

«ያንቺ ዛር ለየት ይላል መሠለኝ!... » አለ ባለ ቢጫ ፀጉር፡፡

«እንዴት?» አልኩት ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ፡፡

«ሁለቱ የተቀቡት የሚያብረቀርቅ ኖራ የሚመስል ሊፕስቲክ ነው፡፡ ያንቺ ከንፈር ግን በቀይ ሊፕስቲክ ያበደ ነው፡፡» አለ ከንፈራሙ አይኑን ከንፈሬ ላይ ተክሎ፡፡

«ባለቀሚስ ብቻ ሣይሆን ባለ ሊፕስቲክም ነው ለማለት ፈልጉ ነው፡፡» አለ ባለ ሎቲው ጥርሱን ለአመል ብልጭ አድርጎ፡፡

«ግን ማን እንበል?» አለች ማህደር፡፡

ከንፈራሙ ፈጠን ብሎ «እኔ ሀይላይ! እሱ ደግሞ ሰለሞን፡፡» አለ፡፡

«እኔ ማዱ፤ እሷ ኤሚ፤ ጥርሰ ፍንጭቷ ደግሞ ቲጂ፣ ታምራላችሁ፣ በተለይ ባለሎቲው፡፡» ማህደር ተቅለበለበች፡፡

«ሰሊ ሀገን ሆነ እንጂ በጣም ያምራል፡፡» አልኩ፡፡

«ሆ! በሉ እኔ ልሂድ!» ብሎ ሰለሞን እየተጣደፈ ከካፌው ወጣ፡፡

«ሲት አትመስጠውም! ጌ ነው! ማለቱ ግብረ ሠዶማዊ... እርሱት በቃ!...» አለ ሀይላይ እንደማፈር ብሎ፡፡

«ይህን የመሰለ ቆንጆ? ቆይ ምን አይነት እርካታ ነው የሚሰጠው?» አልኩት፡፡

«ጌዎችኮ ቆንጆዎች ናቸው፡፡» አለች ማዱ፡፡

«አፈር ያስበላውና መግደል ነበር፡፡» አለች ቲጂ፡፡

«በአንድ ሺህ ብር ነው አሉ የተበሳው! ደግሞ እኮ የደህና ቤተሰብ ልጅ'ኮ ነው! ቤተሠቦቹ ጌ መሆኑን ሲያውቁ ከቤት አባረሩት! አሁን መተዳደሪያው ቂጡ ነው!» አለ ሀይላይ እያንገሸገሸው፡፡

ወንዶች ቂጣቸውን ተበስተው ካለቁ ብር ፍለጋ ሳይሆን ወንድ ፍለጋ ስደት እንጀምራለን፡፡ ቲጂ እና ማህደር ተጠቃቅሰው ተነስተው ሄዱ፡፡ ሀይላይ ስለ ስለሞን ጓዳ በስፊው እንዲተርክልኝ ፈልጌ ነበር፡፡ እጅሬ ግን ትረካውን በሌላ ቀን እንደሚቀጥልልኝ ቃል ገብቶ፣ ስልክ ቁጥሬን ጠየቀኝ፡፡ ሰጠሁት፡፡ ሀይላይ ሎተሪ እንደወጣለት ሰው እየተፍለቀለቀ ተሰናብቶኝ ሄደ፡፡

ሀይላይ ከሄደ በኋላ ብቻዬን ስቁለጨለጭ ቲጂ የወንዱንም የሴቱንም አይን እንደማግኔት የሚስበውን መቀመጫዋን እያገላበጠች መጣች፡፡ ፊት ለፊታችን ተቀምጠው አፍ ለአፍ ገጥመው የሚያወሩት ጥንዶች፣ እጮኛሞች መሆናቸውን አስታውሳኝ፣ ወንዱን በአይኗ ልሳ ቀድማው ሽንት ቤት እንደጠበቀችውና እንደ ተከተላት ነገረችኝ፡፡ አስፈሰፍኩ!

«ወንዶች ሽንት ቤት ይበኝ ገባ፣ ከዛ ሣመኝ፣ ከዛ ከንፈሩ ሲጣፍጥ፣ ከዛ ሰው ይመጣብናል ብለን ፈራን፣ ከዛ ስልኩን ሠጠኝ፣ ከዛ መጣሁ፣ ግን አቆምኩበት!» አለች ቲጂ አይኗን እያስለመለመች፡፡

«ብታቆሚበት ምን ዋጋ አለው? እጮኛው ናት አድለች!» አልኳት፡፡

«ጎገ ማርኮ ካልደወለልኝ አገኘውና ወንድነቱ ይፈተሽል!»

«እናተ ልብስ ሰርቄ መጣሁ!» ብላ ማህደር የሰረቀችውን ልብስ ቦርሳዋን በቀጭኑ ከፍታ አሳየችን፡፡

አመዴ ቡን አለ፡፡ ቶሎ ሒሳብ ከፍለን ከካፌው ወጣን፡፡ የልብስ ሌባዋ ሂኖክ የሚባለው ስንጥር ፍቅረኛዋ ናፍቆኛል ብላ ከእኛ ተለየች፡፡ እኔ እና ቲጂ ወደ ቤት ተመለስን፡፡ ቴሌቪዥን ስናይ አምሽተን ልንተኛ ስንል ቲጂ ስለአብዲ እንስታ ስትነዘንዘኝ ቆየች፡፡ «ሀብታም ነው፣ ደረቱ፣ ቁመቱ፣ መልኩ፣ ሀበሻነቱ፣ ይወድሻል፣ ጋጨው፣ ማህደር ልትቀድምሽ ነው፡፡» ያላለችኝ ነገር አልነበረም፡፡ ሲደክመኝ ትቻት መኝታ ክፍሌ ገባሁ፡፡ በሩን ቆልፌ መብራቱን ካጠፋሁ በኋላ ትራሴን አቅፌ ትላንትናዬን በሀሳብ መነፅር አየሁት፡፡ አመመኝ! ትላንትናዬ ያመኛል! ግን...

*አማርረውና እህህ.... አምላኬ በፀና*
*ተመስገን እላለሁ መልሼ እንደገና*
*ብዙ የሰው ፍጡር እንደዚህ ነውና*
*እህህ...እህ ሂሂሂ...እህህ...እህህህ...*

አይደል ያለችው አስቴር አወቀ፡፡

ቀኑ ስንት ነው? ማነው? ወሩስ? አላውቅም!... ግን አዲስ ቀን ነው፡፡ አማን አውለኝ! ብዬ ነው ከአልጋዬ የወረድኩት፡፡ ምግብ የማብሰሉም ሆነ የቤቱ ፅዳት የእኔ ተራ ነው፡፡ ቤቱን አፀዳድቼ እንደጨረስኩ ማህደር እየተወላከፈች ገባች፡፡ ሰዓት የማይፈጅ ቁርስ ከጦስኝ ሻይ ጋር ለሶስታችንም አቀረብኩ፡፡ በደቂቃ ወስጥ ፊታችን የቀረበው ሰህን

አላየሁም አለ፡፡ የሶስታችንም ሆድ ቢሆን መች አየሁ አለ? ምሳ መስራት ጀመርኩ፡፡ ሽንኩርት ስከትፍ ያፈሰስኩትን እንባ ለአንድ ወገኔ ብረጨው ሀዘኔ መሪር መሆኑን ይገልጽልኝ ነበር፡፡ ምሳው ከደረሰ በኋላ ገላዬን በቀዝቃዛ ውሀ ለቅለቅ ብዬ ምሳ አቀረብኩ፡፡ ምሳው ከሚጣፍጥ ወሬ ጋር ተበላ፡፡

ከሰዓት በኋላ ማዱ እስኪ የምትኖረው እህቷን ለመጠየቅ ሄደች፡፡ ቲጂ ጋሽ ከዛን ለማግኘት ታጥባ ታጥና ወጣች፡፡ እኔ አንድ መፅሐፍ አዟሪ መንገድ ላይ ካልገዛሽኝ ብሎ ሲጨቀጭቀኝ ደስ እንዲለው ብዬ የገዛሁትን የትርጉም መፅሐፍ እንዳይደብረኝ ብዬ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ቀስ በቀስ ታሪኩ እየመሠጠኝ መጣ፡፡ ብዙ ገፆችን አነበብኩ፡፡ ለነገሩማ በልጅነቴ አባቴ እቤት ሳይኖር ደርድሮ ያስቀመጣቸውን የትርጉም መፅሐፍት ከትምህርት ቤት መልስ እየተደበቅኩ አነብ ነበር፡፡ ወደ ልጅነቴ ተመለስኩና «አመመኝ!» ያለፈው ሕይወቴ ለአሁኑ ሕይወቴ ጉልበት መሆኑን አልከድም፡፡ ግን ያመኛል!... እኔ አሁን ማሰብ ያለብኝ ስለድብቁ አላማዬ ነው፡፡ በሩ በሀይል ሲንኳኳ እንባዬን አብሼ ከፈትኩ፡፡ ያልጠበቅኩት ሰው! አብዲ! ቲጂ እቤት መሆኗን ደውላ እንደነገረችው ነገረኝ፡፡ ሳልፈልግ አስለፈለፈኝ! ሳልፈልግ አሳቀኝ! አመሻሹ ላይ እራት ሊጋብዘኝ ወደ ታወቀ ሬስቶራንት ይዞኝ ሄደ፡፡

የቦታው ድባብ ደስ ይላል፡፡ አብዲ ምላሱን ቆልፎ በዐይኑ ነበር የሚያናግረኝ፡፡ እራቱ እንዳለቀ ፍቃዴን ሣይጠይቅ መኪናውን እያሽከረከረ ሀያት ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ይዞኝ ከነፈ፡፡ ግቢውን የሚጠብቁለት ሽምግል ያሉ ሰው የተቀበሉን በፉከራ ነበር፡፡ «አጅሬ

ጠጅ ነው!» አለኝ አብዲ፡፡ እየተመላለሰች ቤቱን የምታፀዳለትና አንዳንዴም እቤት ከዋለ ምግብ የምታበስልለት ሠራተኛው ደግሞ በእንጉርጉሮ ታዝናናዋለች፡፡ የቤቱ ስዳት መንፈስን ያረካል፡፡ የእቃው ጥራትና ውበት ሌላ ነው፡፡ በመሣሪያ ብቻ የተቀነባበረ ለስላሣ ሙዚቃ ከፍቶ፣ ወይን ቀድቶ ከሠጠኝ በኋላ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ፡፡

እኔ ስለሚለብሳቸው ልብሶች፣ ሽቶው፣ ንፅህናው፣ እያሰብኩ፣ በፓንት ብቻ ከመኝታ ክፍሉ ወደ ሳሎን ወረደ፡፡ እደፍርሱ ገና ሣይቆም ፓንቱን ወጥሮታል፡፡ ሳላስበው በረጅሙ ተነፈስኩ፡፡ ብርጭቆዬን ተቀብሎ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው፡፡ ልብሴን ረጋ ብሎ አውልቆ ጨረሰ፡፡ በፓንት ብቻ ቀረሁ፡፡ እንደ ሎሚ እንዲጨምቀኝ ተመኘሁ፡፡

ቴሌቪዥኑ ላይ የተቀመጠውን ጩቤ አንስቶ እያገላበጠ ተጠጋኝ፡፡ የልቤ ምት ጨመረ፡፡ «ብስላም ነው?» አልኩት፡፡ መልስ ሳይሰጠኝ በጩበጠው ጩቤ ፓንቴን በአንደኛው ጐን በጠሰው፡፡ አይኖቹን አየኋቸው፡፡ አቅም አነሠኝ! የአንደኛውን ጐን ደገመው፡፡ ፓንቴ መሬት ላይ ወደቀ፡፡

ጩቤውን ቦታው መለሶ ይስመኛል ብዬ ስጠብቅ እንገቴ ስር ተቀብሮ ጠረኔን ከማገ በኋላ ፓንቱን አወለቀ፡፡ እደፍርሱ ከእንቅልፉ ነቅቶ የሚንጠራራ ጐረምሳ መሰሏል፡፡ ምራቁን ዋጥኩ፡፡ የሴት እንባ ይሁን ዝናብ ያሳደገው… አላውቅም! የፈረንጅ ፅድ የመሰለ ፀጉር ደረቱ ላይ ተጋድሟል፡፡ በቸኮሌት የቆዳ ቀለም የተሸፈነ ገላ አለው፡፡ ስመኘው የነበረው ደረት ሰፊ ቁመት ሎጋ ቀብራራ የሀበሻ ወንድ ፊት ለፊቴ

እርቃኑን ቆሟል። ህልም እንዳይሆን ተመኘሁ። አደፍርሱ ከመወጠሩ የተነሳ የፈጠጠ ወፍራም ደምስር ተጋድሞበታል። አው!... ምራቄን ዋጥኩ! ወገቤን ስቦ ደረቱ ላይ ለጠፈኝ። አይኔን ጨፍኜ ጠረኑን ማግኩት። ስላም አለው!!

በስዕል ደረጃ ጭንቅላቴ ውስጥ የተቀመጠው የአዳም ዘር ነብስ ዘርቶ ወገቤን ይዞ ቆሟል። እንደ እንቁላል አልተጠነቀቀልኝም። በሰፊ መዳፉ ጡቴን እየጨመቀ፣ እያገላበጠ ጋለበኝ። ዓለም መዳፌ ውስጥ የተቀመጠች መሠለኝ። ህልሜን እውን ሆኖ አየሁት! «መንጠባረር ሲያንሰው ነው!» ከሣሎን መኝታ ቤት፣ ከሶፋ አልጋ፣ ከአልጋ መሬት፣ እንደ እንርዝት ሲያሽከረክረኝ አደረ። ረፋዱ ላይ አሪፍ ቁርስ ሰርቶ ቀሰቀሰኝ። እየተሰራረቅን እየተያየን የቀረበውን ቁርስ ቀምሰን ወጣን። ሰፈር አድርሶኝ ወደ ሥራው ሄደ። መኪናው ከዓይኔ እስኪሰወር ድረስ ግን ተገትሬ ነበር።

ቤቴ እንደገባሁ ለጓደኞቼ ቀደዳዬን ጀመርኩ።

«ጉዴ ፈላ! ሰው ሲፈጠር የሆነ... የሆነ ነገር አየጐድለውም?»
«ኤምዩ ፍቅር እንዳይዝሽ!» አለችኝ ቲጂ።
«ምንልባት ፀባይ ሊጐለው ይችላል!» አለች ማህደር።
«ወሲብ ላይ ከተመቸኝ ስለ ፀባዩ አልጨነቅም!»
«አሁን ኡምቤርቶን እንዴት ልታገኚው ነው?» አለችኝ ቲጂ።
«አልገባኝም?»
«እንገትሽን በመስታወት እይው።» አለች ማዷ።

እንገቴ በልዟል!

«አላገኘሁትም! እኔ አሁን ማሰብ የምፈልገው ስለ አብዲ ብቻ ነው!» አልኩ ኮራ ብዬ።

«ቀደምሽኝ እንጂ የኔ ነበር!» አለች ማጂ። የተናደደች ትመስላለች።

«ማዱ በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ! አብዲ በመዳፌ ውስጥ እንደ ሎሚ እየታሸ የሚኖር ክንፍ የሌለው እሞራ ነው። ስለዚህ አይንሽን አንሺ!» አልኳት።

ኡምቤርቶ ሲቀጥረኝ ሠበብ እየፈጠርኩ አስራ አምስት ቀን ሙሉ አብዲ ቤት ቁጭ አልኩ። ጠዋት ላይ ሱቁ ደረስ ብሎ እስኪመጣ ተጣጥቤ ቁርሴን በልቼ አልጋ ውስጥ እጠብቀዋለው፤ ይመጣል፤ አልጋ ውስጥ ስንለኳኮስ ስንነድ እንውላለን። ሲሰኞች መሆናችንን ያለምንም ምስክር አምነን ተቀብለናል። አንዳንዴ እኛ ሳንሆን ወሲብ እራሱ ይቆጣጠረንና ገደብ የሌለው ብልግና ስንፈፅም እንውላለን።

ኡምቤርቶን ትቼ ኑሮዬን መምራት ለኔ አስቸጋሪ እንደሆነ ስለተረዳሁ ይሁን... አብዲን ስለጠገብኩት... አላውቅም ለምን እንደሆነ!? ወደ ቤቱ ተመልሼ የበለዘ አንገቴን ሻዝሊን እየቀባሁ አምስት ቀን ሙሉ አከምኩት። ኡምቤርቶ ክፍለሀገር ወንድሜን ለመጠየቅ መሄዴን ስለሚያውቅ፣ የፈጠርኩትን ውሸት አሳማኝ ለማድረግ፤ «ክፍለ ሀገር ያለው አጎቴ ስለሞተ ለቅሶ መድረስ አለብኝ።» የሚል ሁለተኛ ውሸት ፈጥሬ፤ አብዲን ተሰናብቼ ወደ አዋሣ ሄድኩ። ኡምቤርቶጋ ደውዬ

«አዋሳ መጥተህ ካላየሁህ በናፍቆት መሞቴ ነው፡፡» አልኩት፡፡ ሶስተኛ ውሸት! እየከነፈ መጣልኝ፡፡

በሰበቡ አዋሳን ተዋወቅኳት፡፡ «ታምራለች!» ኡምቤርቶም ቢሆን በጣም ነው የወደዳት፡፡ «ባይወዳት ነው የሚገርመኝ!» እንዴን ስራ ፊት ሦስት የመቶ ብር ኖቶች ሸጉጬለት፣ ወንድሜ ነው ብዬ ለኡምቤርቶ አስተዋወቅኩት፡፡ ውሸቱ እውነት ሆነ! 20 ቀን ሙሉ ድምፃችንን አጥፍተን አዋሣ ተቀመጥን፡፡ አዲስ አበባ ደግሞ ናፈቀችኝ፡፡ አብዲንም ባገኘው ደስ ይለኛል፡፡ አዋሣን ተሠናብተን ሸገር ከሠዓት በኋላ ደረስን፡፡ እሱ ወደ አረፈበት ሆቴል እኔ ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡

የእንኳን ደህና መጣችሁ የእራት ግብዣ እንዳለብን ኡምቤርቶ ደውሎ ነገረኝ፡፡ አልፈለግኩም ነበር ግን ጋባዥ ማርኮ ስለሆነ ቲጂን ለማስደሰት ስል ግብዣውን ተቀበልኩ፡፡ እግራን በሰበረው! እራት በልተን ከሬስቶራንቱ ስንወጣ አብዲ እና ሚካኤል ሲገቡ ተገናኘን፡፡ ኡምቤርቶ እጄን ይዞ ቦርሣዬን እንጠልጥሏል፡፡ አብዲ ከላይ እስከታች ተመለከቶኝ ምንም ሳይናገረኝ ወደ ውስጥ ገባ፡፡

«ታውቂዋለሽ?» የሚል ጥያቄ ከኡምቤርቶ ቀረበልኝ፡፡

«ኢላውቀውም!»

«በውበትሽ ተማርኮ ይሆናል!»

ይሻለኝ ነበረ...!

ከአራት ቀን በኋላ ምሽት ላይ ሣሎን ቁጭ ብዬ ከማዴ ጋር ካርታ እየተጫወትኩ በሩ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ማህደር ፊጠን ብላ ከፈተች፡፡

አብዷ ነው፡፡ የለበስኩት አጭር ቁምጣ ላይረዝም ወደታች መጎተት ጀመርኩ፡፡ ልብሴን ለመቀየር ጊዜ እንኳ ሣይሰጠኝ ወደ ቤቱ ወስዶ ልብሴን አውልቆ በቀበቶ ገረፈኝ፡፡

«ሁለተኛ ከዛ ነጫጭባ ጋር ልይሽና...»

«ነጫጭባ የምትለው ሰው... ቤት ተከራይቶ ያስቀመጠኝ ወንድ ነው፡፡ የምተዳደረውም እሱ በሚሠጠኝ ገንዘብ ነው፡፡ ስለዚህ የሚያገባህ ነገር የለም!» አልኩት እያለቀስኩ፡፡

«እረ!... ድጋሚ ከእሱ ጋር ልይሽና ያኔ እኔ እና አንቺ ነን፡፡ እሱንም ቢሆን አለቀውም፡፡»

«ሴትን ልጅ መምታት ወንድነት መስሎሀል!?... አሁን በሩን ክፈትልኝ እሄዳለሁ፡፡»

ይውጣላት ብሎ ልብሴን የመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ከቶ ውሀ ለቀቀበት፤ ፊት ለፊት ያገኘሁትን የፀጉር ሻንቦ እንስቼ ወረወርኩበት፡፡ ሣትኩት! ፀጉሬን ጨምድዶ አልጋው ላይ ወርውሮኝ ወደ ሳሎን ሄደ፡፡ እልቅሼ ሲወጣልኝ መብራቱን አጥፍቼ አልጋው ውስጥ ገባሁ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ቀዝቃዛ ወተት በብርጭቆ ይዞልኝ መጣ፡፡ አልጠጣም ብዬ ድርቅ አልኩ፡፡ «ፀጉርሽ ላይ እለቀዋለው!» አለኝ፡፡ ሊያስፈራራኝ እንዳልሆነ ማውቅ ደግሞ የእኔ ግዴታ ስለሆነ ጠጣሁ፡፡ ይቅርታ እንኳ ሳይለኝ ጀርባውን ሰጥቶኝ ተኛ፡፡ ግን ሣንፈልግ መነካካት ጀመርን፡፡ የሁለታችንም የንዴት ግለት የወሲብ ጥም ለቀቀብን፡፡ የጤና ይሆን?

ሰላማዊ ጦርነት ተጀመረ፡፡ የገረፈውን ገላ፣ በስሜት መአበል እየቀዘፈ፣ ፍቅር በሚረጩ መዳፎቹ ዳበሰው፡፡

«አባዲ…»

«ወዬ…»

«በእናትህ አትምታኝ!…»

«ከተናደድኩ… ወላሂ!… እገልሻለሁ!…»

የአቅሟ ጠላት የሆነውን አይኑን ስመለከት፣ አንገቷን እየዳበሰ ከንፈሩን ሠጠኝ፡፡ የእናቱን ጡት ያገኘ ህፃን ይመስል እየተስገበገበ መጠጥኩት፡፡ ውሻ ነኝ! ከግንባሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ ሳምኩት፡፡ ነከስኩት! አሁንም አልጠገብኩትም፡፡ አቅም አነሰኝና በጀርባዬ ተንጋለልኩ፡፡ ጭኖቼ መሀል ገባ፡፡ ከዛ በኋላ የሆነውን ለማስታወስ እቸገራለሁ፡፡ ምክንያቱም ገሎ እስኪያድነኝ ድረስ እራሴን አላውቅምና አብዲ ሰይጣናዊ ሰው ነው!!

መንጋቱ አይቀርም ነጋና አዲስ ቀን ለማየት በቃሁ፡፡ የተገረፈው ቆዳ ገላዬ አንዳንድ ቦታ በልዟል፡፡ ልብሴም በውሀ ተነክሮ እንዳደረ ነው፡፡ የእሱን ሸሚዝ ለብሼ በውሀ የተነከረ ልብሴን በፌስታል አንጠልጥዬ ወደ ሳሎን ወረድኩ፡፡ የተጠበሰ እንቁላል ሽታ ተቀበለኝ፡፡አእርቦኝ ስለነበረ ብዬ እስኪለኝ አልጠበኩም፡፡ ቁርሳችንን በልተን እንደጨረስን እንደተለመደ ቤቴ አድርሶኝ ወደ ስራው ሄደ፡፡

እቤት ስገባ ማዱ ሶፋው ላይ ተቀምጣ ታለቅሳለች፡፡ ብቻዋን ተቀምጣ ስታለቅስ ማግኘት የተለመደ ነገር ነው፡፡ ወዲያው ደግሞ ትስቃለች፡፡

«መፍትሔ የሌለው ነገር ቢኖር ሞት ብቻ ነው፡፡» አልኳት፡፡

«ሞት ነው የሚያስለቅሰኝ!» አለች እየተነፋረቀች፡፡

«ታዲያ ከሞት የሚቀር ማን አለ?»

«የእኔ የቁም ሞት ነዋ!»

«የቁም ሞትን ለማሸነፍ ከፈለግሽ... ጠንካራ ሴት ሁኚ!»

«ዛሬ ደግሞ በሸሚዝ ነው የላከሽ?...» ፈገግ አለች፡፡

ለቅሶው ተረሳ!

«ቲሸስ?» አልኳት ድምጿ ሲጠፋብኝ፡፡

«ማርኮ አዋሣ ይዟት ሄደ! እኔ ነኝ እንጂ የሚወስደኝ የሌለኝ!»

«ማታ ማታ መንገድ ላይ መገተር ይቅርብሽ! ተይው!»

«ብሩስ? ሄኒ እንደሆን ደሞዝ ሲቀበል መቶ ብር ብቻ ነው የሚሰጠኝ፡፡» እንገቷን ደፋች፡፡

መንገድ ላይ ተገትሮ የሰካራም ቆርቆሮ ማስቆም ባላውቀውም አስቀያሚ ሥራ ነው፡፡ መልካም ነገር ማድረግ ለራስ ነውና! ስለቤቱ ክራይ እንዳታስብ ነገርኳት፡፡ ደስ አላት! እኔ መልካም መሆን ባልፈልግም ትዝታዬ መልካም እንድሆን ያስገድደኛል፡፡ መጥፎም እንድሆን ያበረታታኛል፡፡ ቢሆንም የተከፋ ሰው ማየት አልፈልግም!

በዕለተ ሀሙስ አብዲ ያልጠበኩትን ነገር አድርጎ አስደነገጠኝ፡፡ ከሠፈሬ ብዙም ሣይርቅ ሡቅ ተከራይቶ፣ በተለያዩ የመዋቢያ እቃዎች ሱቁን ሞለቶ፣ ቁልፉን አስረከበኝ፡፡ ሊቀጥረኝ መሠለኝ ግን ለእኔ በስጦታ መልክ ያበረከተው መሆኑን ሲነግረኝ... ማልቀስም መሣቅም አምሮኝ ነበር፡፡ ከኡምቤርቶ ለማራቅ የተጠቀመበት ዘዴ መሆኑም

ገብቶኛል፡፡ ከሱቁ ጎን ያለው የልብስ መሸጫ ሱቅ ባለቤት፣ አዜብ የምትባል ስራ ያጣች ዘመድ እንዳለቻት ስትነግረኝ፣ በእሷ ተያዥነት ቀጠርኳት፡፡ ማን ይታሰራል?

የአብዲ አለማ እኔን ከኡምቤርቶ መለየት ቢሆንም አልተሳካለትም፡፡ በቂ ምክንያት ሳይኖር ሲሳይን መገፍተር ሞኝነት ነው፡፡ ኡምቤርቶ በሚሰጠኝ ገንዘብ ደግሞ የመቃሚያ ፍራሽ እስከ ትራሶቹ ገዛሁ፡፡ ቦርሳዬ ከቀይ እና ከቢጫ ብር ሌላ አያውቅም ነበር፡፡ አሁን የአረንጓዴ ብሮች ማጠራቀሚያ ሆኗል፡፡ የኔ እና የህይወት ቁማር ጭዋታ ይቀጥላል!...

ዛሬ በጠዋት የተነሣሁት እንግዶች ስለሚመጡብኝ ነው፡፡ የእኔ በጥዋት ከረፋዱ 4:00 ላይ ነው፡፡ ወገቢ እስኪበጠስ ቤቴን አፅድቼ አብዲ ከጅቡቲ ባስመጣልኝ መስከቲ አጠንኩት፡፡ ቡና አቀራርቢ፣ አረንጓዴ አበባ ጣል ጣል ያደረገበት መደቡ ጥቁር ድሪያ ለብሼ፣ ፀጉሬን ጀርባዬ ላይ በተንኩት፡፡ ያንተከተኳትን ሽሮ በቁራሽ እንጀራ ከተመስኩ በኋላ ቡናውን መቁላት ስጀምር፣ ሰለሞን እና ህይላይ በጋዜጣ የተጠቀለለ ጫት ይዘው ገቡ፡፡ ቡናውን ቆልቼ ስፈርስ ሰለሞን ካልወገጥኩ ብሎ ሙቀጫ ውስጥ የፈመርኩትን ቡና ይዞ ወጣ፡፡

«የሴት ሥራ ስለሚወድ ነው! ለነገሩ ሴት ነኝ ብሎ አይደል የሚያስበው…» አለ ህይላይ፡፡

«ቡና መውቀጥን የሴት ሥራ ያደረገው ማነው?»

«መህበረሰቡ!»

«ሰለሞን ጥሩ ልጅ ይመስላል!... በዛ ላይ ያሳዝናል!...»

«ይሄ ምኑ ያሳዝናል? የሲኦል ዲቃላ!...»

ስሊ ሲመጣ ወሬ ቀየርን፡፡ ሀይላይ በትክክል ሰለሞንን ይጠላዋል፡፡ ቡናው እንዳበቃ መሀላችው ተቀምጬ፣ ሀይላይ አጤሬራ እያደረገ የሚሠጠኝን ጫት ጉንጬ ውስጥ እየወተፍኩ፣ የማያቋርጥ ወሬውን አቀዳለሁ፡፡ ስሊ ብዙም አያወራም፡፡ የጫቱን እንጨት የሚሠባብሩት ረጃጅም ጣቶቹ ያምራሉ፡፡ ሀይላይ መፀዳጃ ቤት ሲገባ ጠብቄ የስሌን ሞባይል ከፍራሹ ላይ አንስቼ ወደ ሞባይሌ ደወልኩ፡፡

«ዘመድ መሆን አይቻልም?»

«ኧረ ምን ጣጣ አለው?! ደግሞ.... » ተናግሮ ሳይጨርስ ሀይላይ ሲመጣ ዝም አለ፡፡ እንዳታዋራት የተባለ ይመስላል፡፡

«ስሌ ዝምታ ወርቅ ነው እያለ ነው!» አልኩ ጨዋታ የፈጠርኩ መስሎኝ፡፡

«እንደ ሴት መሽኮርመም እና መቅለስለስ አሁን ያመጣው ፀባይ ነው፡፡» አለ ሀይላይ፡፡

«ፍቅረኛህ ደህና ናት?» አልኩት ወሬ ለመቀየር፡፡

«የማን? የእኔ? አለው አለሽ እንዴ?» ሀይላይ ተንተባተበ፡፡

«አንተን የመሰለ ቆንጆ እንዴት እስከዛሬ አይኖረውም?»

«አንቺ ፍቅረኛዬ እንድትሆኚ ነው የምፈልገው!»

«አሰበኸዋል የ19 ዓመት ገረምሳ...» ተናግሬ ሳልጨርስ አቋረጠኝ፡፡

«ጭንቅላቱ የ10 ዓመት፣ እድሜው 40፣ የሆነ ሰው ነው የምትፈልገው? ዝም ትላለህ እንዴ? ነው የቀባጠርኩላት ነገር አለ?» ብሎ ሰለሞን ላይ አፈጠጠ፡፡

«እንቢ ካለች መጫኑ...» ሰሊ መልሶ ዝም አለ፡፡

«ውይ የእኔ ቆንጆ እኔ እንኳ ትደኛ አለኝ፡፡ ባይሆን እህትነቱን ከተቀበልክ ዝግጁ ነኝ፡፡» እልኩት ትከሻውን እየዳበስኩ፡፡

ሀይላይ አልተዋጠለትም፡፡ ጫቱ ሲያልቅ ትንሽ ተጫውተው ወጥተው ሄዱ፡፡ ምርቃናዬ ሳይጠፋ ቶሎ ቶሎ ብዬ ቤቱን ካስተካከልኩ በኋላ የምሽት ዜና ለመመልከት ቴሌቪዥኑን ከፈትኩ፡፡ የሴቶች ጉዳይ፣ ለሴቶች፣ ሴቶቻችን... «የአፍሪካ ፖለቲከኞች ወንበራቸውን ለማጠንከር የሚጠቀሙበት ባዶ ቃል!!» በሩ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ውስጤ በደስታ ፈነደቀ፡፡ በሀይል ማንኳኳት የእብዲ አንዱ መለያው ነው፡፡ እየሮጥኩ ከፈትኩለት፡፡

«መርቅነሻል! ከማን ጋር ነው ስትቅሚ የነበረው?» አለኝ፡፡

«ከሰው ጋር!» ተኮሳተርኩ፡፡

«መቼም አውሬ ስጋ ትቶ ጫት አልጀመረም፡፡»

«አታውቃቸውም!»

«ያ አላህ! ንገሪኝና አላውቃቸውም ልበል ሽ፡፡» አፈጠጠብኝ፡፡

«ሀይላይ እና ሰለሞን... እና ሰብለና ስርጉት» ዘባረቅኩ፡፡

«ሀይላይ፣ ሰለሞን፣ ስርጉት፣ ሡብለ...» አሰላሰለ፡፡

«አልኩህኮ ጭቅጭቅ ስለምትወድ ነው እንጂ...»

«አትንደቅደቂ!» ገላመጠኝ፡፡

ማዱ እና ቲጂ ውጪ ስለሚያድሩ እኔ የግዴታ እቤቴ ማደር ነበረብኝ፡፡ አብዲ ግን አልተዋጠለትምና በሬን ቆልፌ ተከተልኩት፡፡ ሰፈራችን ካለው የክርስቲያን ስጋ ቤት አንድ ኪሎ ስጋ ገዝተን ወደ ቤቱ ሄድን፡፡ እንደገባሁ የሚጣፍጥ ጥብስ ሠራሁ፡፡ ግማሹን ለግቢው ጠባቂ ከሁለት ቢራ ጋር ሰጣቸው፡፡ ቤተክርስቲያን መሳም የሚገባቸውን ሽማግሌ ጠጪ አድርጓቸዋል፡፡ ጠጅ ሳይቀር እየገዛ ያመጣላቸዋል፡፡ እሣቸውም እያቅራሩ ግቢውን ይጠብቃሉ፡፡ እሱ ቢስሚላ! እኔ በስመአብ! ብለን መብላት ጀመርን፡፡

«መጀመርያ የተገናኘን ቀን፣ ኡዱ ስታደርግ የነበረው፤ መስጊድ ለመሄድ ወይስ ሰጋጅ ለመምሰል?» አልኩት ትዝ ብሎኝ፡፡

«አርብ ነው ለኔ ስትል መስጊድ ሂድና ስገድ ብላ እናቴ ቆብ ገዝታልኝ መጣች፡፡ እሺ ብዬ ኡዱ አድርጌ እንደጨረስኩ ውጪ ያለው ወንድሜ ደወለልኝ፡፡ ከእሱ ጋር ስጨቃጨቅ አንቺ መጣሽና ወጣሽብኝ፡፡ ብሽቅ ነው ያልኩት እሺ! ከዛ በኋላም ቢሆን እናቴ ደስ እንዲላት መስጊድ ሂድኩ ብዬ ሌላ ቦታ ቆይቼ ሰዉ ከሠላት ሲመለስ ወደ ሱቅ ተመለስኩ፡፡» ሥራው ግን ዐልቶታል፡፡

«ሰው መስለህቸው ነው የሚደክሙት!»

«ድሬዳዋ እያለሁኮ አንድቀን ከመስጊድ ቀርቼ አላውቅም፡፡»

«አሁን ማን ከለከለህ?»

«አሁንማ እድሜ ላንቺ!... ለየልኝ!....»

እኔን ደግሞ ከቤተክርስትያን ማን ይሆን ያስቀረኝ? ሴት ልጅ የቤቷን እቃ ማሟላት በጣም ደስ ያሰኛታልና አባዲን ዲሽ ከሱቅህ አምጣልኝ አልኩት፡፡ እንቢ አለኝ! እንደማይጨንብኝ ስለማውቅ አለመንኩትም፡፡ የበላንበትን እንኳ ሳናነሳ እጃችን ታጥበን እሱ ውስኪ እኔ ወይን ቀድቼ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄድን፡፡ አብዲ ልብሱን አወላልቆ፣ ላፕቶፑን አብርቶ፣ አልጋው ላይ ተቀመጠ፡፡

«ንቀት ነው?»

«አዎ!» አለኝ ላፕቶፑ ላይ እንዳቀረቀረ፡፡

ከወይኔ እየተጐነጨሁ በሞባይሌ ያነሳሁትን የኡምቤርቶን ፎቶ ማየት ጀመርኩ፡፡ አብዲ ትንሽ ቆይቶ ላፕቶፑን ሲያጠፋ ፈጠን ብዬ ሞባይሌን አጥፍቼ ወደ መፀዳጃ ቤት ገባሁ፡፡ ጥርሴን ቦርሼ ስመለስ ሞባይሌን ይነካካል፡፡ ደግነቱ ስልኬ ባለ ቁልፍ ነው፡፡ ስላልፈለገ ነው እንጂ አስከፍቶ ጉዴን አይቶ ሲቀጠቅጠኝ ያድር ነበር፡፡ መፀዳጃ ቤት ገብቶ ገላውን ታጥቦ እስኪወጣ ልብሴን አወላልቄ በፓንት እና በጡት መያዥ ጠበኩት፡፡ እርቃኑን ፀጉሩን አነስ ባለች ፎጣ እያደረቀ መጣ፡፡

«ፓንት እና ጡት መያገርያሽን አውልቂና ጣይ፡፡»

«አንተ ምን ትሰራለህ?» አልኩት፡፡

ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ጡት መያገሪዬን አወለቀው፡፡ እጁን ወደ ፓንቴ ሲሠድ ፓንቴን ያዝኩበት፡፡ ሁለቱንም እጄን ቆነጠጠኝ፡፡ ፓንቴን ለቅቄ እጄን ማሸት ጀመርኩ፡፡ «ምነው? ያኘርው እንጂ!...» አለኝ ከመሬት የሚደባልቁ አይኖቹን ተክሎብኝ፡፡ ፓንቴን በሁለቱም ጐን በእጁ በጠሰው፣ መማታት ፈልጓል ያ እንዳይሆን ደግሞ ፀባየኛ ሆንኩ፣

እሱ የፈለገው የሚንቀጠቀጡ ከናፍሮቼን በጣቶቹ መነካካት፣ ሲቃ የተሞላበት ልመናዬን መስማት፣ ምክንያት ቢያጣ የታችኛው ከንፈሬን ነከሰኝ፡፡ በጣም አሞኛል! ግን እንባዬን ዋጥ አደረኩት፡፡ ጀርባውን ሰጥቶኝ ተኛ፣ እኔም ጀርባዬን ሰጥቼው ተኛሁ፣ ሰላሳ ጊዜ ይገላበጣል፡፡ እንዳልሰማ ዝም! ቀስ በቀስ እንቅልፍ ወሰደን፡፡ ጠዋት ቀድሞኝ ተነስቶ ቁርስ አቅርቦ ቀሰቀሰኝ፡፡ ተጣጥቤ ቁርስ አብረን ከበላን በኋላ ምንም ቃል ሳይተነፍስ እቤቱ አደረሰኝ፡፡

ቤቱ ማንም ስለሌለ ይደብራል፡፡ የአስቴር አወቀን ካሴት ለቴፑ አጉርሼ፣ ውብ ድምጿን እየሰማሁ፣ እልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ፣ አዳሬን ማስታወሻዬ ላይ አሰፈርኩ፡፡ ሰዓቱ ነጐደ፡፡ ያደረ ሽሮ መብላት ስላልፈለኩ ዘይት እና በርበሬ መትቼ በእንጀራ ጐረስኩ፡፡ የበላሁት እንዲሰራ በረንዳ ላይ ቆሜ አላፊ አግዳሚውን ትንሽ ከተመለከትኩ በኋላ ልገባ ስል ቲጂ እየተጣደፈች ቀድማኝ ገባች፡፡ ተከተልኳት! ትራስ ተደግፋ ታለቅሳለች፡፡

አሁን አሁን ሴት ልጅ ለለቅሶ የተፈጠረች እየመሰለኝ ነው፡፡ ቲጂ እሮሮዋን ማሰማት ጀመረች!...

«እኔ መረ...ረኝ መረረ...ኝ!» ኝን ተጫነቻት፡፡

«ከነጩ፣ ከጥቁሩ፣ ከተገረዘው፣ ካልተገረዘው ጋር መዝለል ምርር አለኝ!»

«ማርኮ አልተገረዘም?» አልኳት፡፡

«ተገርዟል!»

«ተጣላችሁ?»

ማምጣት ለምን አስፈለገው? እኔ የተፈጠርኩት ለ'ራሴና ለ'ራሴ ብቻ ነው። አለም ውሸታም ናት! ስለዚህ የውሸት እየሳቅኩ የውሸት መኖር ለምጃለሁ። እችልበታለሁም!!

አብዲ ከእሱ ሌላ ወንድ ቀሚሴን እንዳይገልብው ሱቅ ከፈተልኝ። የወሲብ ጥሜን ለማርካትም ታጥቆ የተነሣ የወሲብ ጌታ ነው። ግን እኔ ወሲብም ሆነ ብር ጠግቤም አላውቅም!... መጥገብም የለብኝም! ኡምቤርቶ እንደሚለው ከሆነ ከእኔ ፍቅር ይዞታል። እኔ ፍቅር አላውቅም። ስለፍቅር የማውቀው "የሦስት ፊደላት ጥርቅም" መሆኑን ብቻ ነው። ለቤት ኪራይና ለአንዳንድ ነገሮች ይሁንሽ ብሎ ቦርሣዬ ውስጥ ከማስቀመጥ ቦዝኖ አያውቅም። ወሲብ ላይ አብዲን መሆን ባይችልም የሙሉ ወንድነት መአረግ አያሣጣውም። ሁለቱም ያረኩኛል! ግን ለአብዲ ለምን እንደማደላ ለህኪም አላማከርኩም። በሁለቱ ብር፣ በሁለቱ ወሲብ፣ የውሸት እየሣቅኩ፣ የእውነት እቀበላለሁ። አሪፍ የቂማር ተጫዋችነቴን መዓረግም ከፍ አደርጋለሁ።

የእጄ ሰዓት እንደ እኔ ካልዋሸች ከምሽቱ አንድ ሰዓት ትላለች። ጥቁር ጠባብ ቦዲ በረጅም ሰፊ አረንጓዴ ጉርድ ለበስኩ፤ ከሰውነቴ ጋር ተጣጥሟል። ፀጉሬን ሙጥጥ አድርጌ ካስያዝኩ በኋላ፣ ተረከዘ ረጅም ጥቁር ጫማዬን ተጫምቼ፣ የአይኔን መቁጠሪያ የሚመስል አረንጓዴ ጥቁር ቦርሳዬን አንጠልጥዬ የአንገት ጌጥ አንገቴ ላይ አጠለቅኩ፤ ጥቁር ቦርሳዬን አንጠልጥዬ ከወጣሁ በኋላ፣ ቦርሣዬ ውስጥ ከማስቀምጠው ሽቶ አንገቴ ስር ረጨሁ። «እም!» ብሬን ይጭነቀው ቆሜ ታክሲ መጠብቅ አልፈልግም፤ ኮንትራት ታክሲ ይገፍ ወደ ሜክሲኮ ሄድኩ።

ኡምቤርቶ በቦታው ቀደም ብሎ ተገኝቷል፡፡ ፊት ለፊቱ ካለው ጠረጴዛ ላይ የኮካ ጠርሙስ እያገላበጠ እሣት የሚተፉ አይኖቹን የተከለብኝ ሰው ደግሞ አይኔ ካልተሳሳተ አብዲ ነው፡፡ ልቤ ደረቴን ፈንቅሎ የሚወጣ መሠለኝ፡፡ ወደ ማን መሄድ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡ ኡምቤርቶ የቆምኩበት ድረስ መጥቶ አቀፈኝ፡፡ አብዲ ምንም ሳይናገር ወጥቶ ሄደ፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት በተመሳሳይ ቦታ እንዴት ሊገናኙ ቻሉ? ስልኬ ጮኸ፡፡

አብዲ ነው!...

እየፈራሁ አነሳሁት!

«ከ10 ደቂቃ በኋላ ቤትሽ ባላገኝሽ ለሚፈጠረው ነገር ተጠያቂ አልሆንም፡፡ የኡምቤርቶ ህይወት በእጅሽ ናት!» ስልኩ ተዘጋ፡፡

«መሄድ አለብኝ! ወንድሜ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ የመኪና አደጋ ደረሰበት ብለው ነው የደወሉልኝ፡፡» አልኩት ለኡምቤርቶ፡፡

«አብሬሽ እሄዳለሁ!» ከተቀመጠበት ተነሳ፡፡

«አይሆንም!» ሣይታወቀኝ ጮህኩበት፡፡

ስምንት የመቶ ብር ኖቶች ሰጠኝ፡፡

«የያዝኩት ይህን ብቻ ነው! ካነሠሽ ደውይልኝና ያለሽበት ቦታ ድረስ እመጣለሁ፡፡ እራስሽን ጠብቂ!» አለኝ፡፡

ኡምቤርቶ አሳዘነኝ! እቅፍ አድርጌ አንገቱ ስር ስሜው ከሬስቶራንቱ ወጣሁ፡፡ የያዝኩት ኮንትራት ታክሲ መሀል መንገድ ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ የተሠጠኝ ደቂቃ እያለቀ ነው፡፡ ታክሲው ተጉርጉሮ እና

ተገፍቶ በስንት መከራ ጉዞ ጀመረ፡፡ 'ቤት የደረስኩት ከተሰጠኝ ደቂቃ አሳልፌ ነበረ፡፡ አብዲ ከቲጂ ጋር ቁጭ ብሎ ጣቢያ እየቀያየረ ቴሌቪዥን ያያል፡፡

«ኤሚዬ ዲሽ ተገጠመልን! ዲቪዲም መጥቶልናል! በይ ዛሬ በደንብ ስጪው፡፡» አለችኝ ቲጂ፡፡

አብዲ እንደቆምኩ እጄን እየጎተተ ወደ መኪናው ይዞኝ ሂደ፡፡ እቤቱ እንደገባን የሣሎኑን በር ቆልፎ ቁልፉን ይዞ ወደ መኝታ ክፍሉ ሂደ፡፡ ምን ሊያደርገኝ ይሆን? እያልኩ ስንቆራጠጥ በፓንት መጣ፡፡

«አብዲ እራት ልንበላ ብቻ ነው የተገናኘነው፡፡»

«አፍሽን ዘግተሽ ልብስሽን አውልቂ!»

ልብሴን አውልቄ በጡት መያዣና በፓንት ቀረሁ፡፡

«እሱንም አውልቂ!»

አወለቅኩ፡፡

«.... ገንዘብ ስለሌለኝ ነው አልሽ ሱቅ ከፈትኩልሽ፡፡ ያም አይበቃሽም ብዬ ብር ከመስጠት አልተቆጠብኩም፡፡ አሁን ደግሞ ምን ፍለጋ ይሆን ከኡምቤርቶ ጋር የምትገናኚው?»

«ምንም! ማለቴ እራት ልጋብዝሽ ስላ...»

አቋረጠኝ፡፡

«አሁንማ ምን እንደጎደለሽ በሚገባ አውቄዋለሁ!»

እየጐተተ ወደ መኝታ ክፍሉ ወሠደኝ፡፡ እባካችሁ አድኑኝ እያልኩ በልቤ የጠራኋቸውን ታቦቶች ብዛት አሁን አላስታውስም፡፡ አልጋው ላይ ሲወረውረኝ የትራስጌው እንጨት ጭንቅላቴን መታኝ፡፡

«እህ! የሚል ነገር እንኳ ብሰማ እገልሻለሁ፡፡»

ጭኖቼን ፈልቅቆ የተገተረ አደፍርሱን ሰነቀረብኝ፡፡

«አህ!... እይ!... አባዬ ስሞት!... አሳመም...! » አለቀስኩ፡፡

«አንድ እንባ እንዳላይ ዋጪት!»

«አመመኝ!»

«ዋጪት!»

«እሺ አውጣው!»

«እንዲህ እያሳመመሽ ይሆናል ከእሱ መለየት ያልቻልሽው ብዬኮ ነው!»

«አይ እሱ አያማ...ምመኝም፡፡»

«ታዲያ ምን ፍለጋ ነው?»

«እራት ልበላ!»

«ያ አላህ! አትቀሽብኝ፡፡» እንገቴን ነከሠኝ፡፡

«.... አባዬ በማርያም ተወኝ!»

«አልተ...ውሽም!» በስስት ተመለከተኝ፡፡

አንገቴ ስር ተሸጉጦ ከቆየ በኋላ በስሱ ነከሰኝ፡፡

«አንቺን መተው አለመቻሌ ደግሞ ያናድደኛል!»

አደፍርሱን ቀስ ብሎ መዘዘው፡፡

«ግን እመነኝ እኔ እና እሱ እራት ለመብላ...»

ሳላስበው አደፍርሱን ሰነቀረብኝ፡፡ ላ ብዬ ቀረሁ፡፡ አይኖቹ እባክሽ አትዋሺ የሚሉ ይመስላሉ፡፡ እጆቹ ጡቶቼ ላይ አርፈዋል፡፡

«ልግደልሽ?»

«ግደለኝ!» አልኩት ከልቤ፡፡

«እፈራለሁ!»

«ለምን?»

«እኔም እንዳልሞት!»

ከወገቡ በታች ያለው እንቅስቅቃሴ እርጋታ የተሞላበት ነበር፡፡

«አንድ ጥያቄ እጠይቅሻለሁ ግን እንዳትዋሽኝ!»

«አብዲ ሙት አልዋሽህም!»

«እራት በልታችሁ አብራችሁ ልታድሩ ነበር አይደል?»

ውሸት ለእኔ እውነት ነው!

«አብዲ ሙት አልነበረም!» የግራ ጣቶቼን ይዞ ወደ ኋላ አጠፋቸው፡፡

«አይ አንተ...አንተ አይ...አብዲ የማል'ኮ... እኔ ልርሙህ ነው! እሺ. አዎ ልናድር ነበር!»

አደፍርሱን ግማሹን ከመዘዘው በኋላ በሀይል ከተተው፡፡ አመመኝ! ግን ደግሞ... ግን ደግሞ...

«ላውጣው?» አለኝ መቅለጤን አይቶ፡፡

«እታ…ው…ጣው!» አልኩት ይበልጥ ወደ እሱ እየተጠጋሁ፡፡

ይበልጥ እንዲጠጋኝ፣ እንዲያስቃየኝ፣ እንዲነክሰኝ፣ እየፈለግኩ… አደፍርሱን መዞ ጆርባውን ሰጥቶኝ ተኛ፡፡ ጆርባውን ሰጥቶኝ ተኛ፡፡ እሺ! እኔስ ይቅርብኝ፤ ለእራሱ፤ ለእራሱ ሲል ብንጨርስ ቆይ ምን አለበት? አፌን በትራሱ አፍኜ ጮሁኩ!

# ክፍል ሁለት

## በቀል

የማህደር ከቤት መጥፋት እንዴ ያሣሠበኝ ነገር ነው፡፡ ችግር ቢገጥማት በውስጧ አፍና ከማልቀስ ውጪ አትናገርም፡፡ «እቃዎቿ የሚቀመጡበትን ኮሜድኖ ለምን ከፍተን አናየውም?» የሚል ሀሳብ ቲጂ አቀረበች፡፡ ደስ አላለኝም! ግን የማዱን ችግር አገኘዋለው ብዬ ስላሰብኩ በተመሳሳይ ቁልፍ ከፈትነው፡፡ የመድኃኒት አይነት፣ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀቶች፣ የህክምና ካርዶች፣ ያልታጠቡ ፓንቶች፣ አንድ ካርድ ላይ ግን አይኖቼ ተጣብቀው ቀሩ! ቲጂ ቀምታኝ አገላብጣ ካየችው በኋላ አፏን ይዛ መለሰችልኝ፡፡ ካርዱን ቦታው መልሼ ኮሜዲኖውን ለመቆለፍ ትግል ጀመርኩ፡፡ አይቆለፍም! ቁልፉም ተቀርቅሮ አይወጣም! ማዱ በር ስትከፍት ተሰማን፡፡

እንደ ጤነኛ ሰው አልጋው ላይ ተቀምጠን ጠበቅናት፡፡ ስትገባ አይኖቿ በቀጥታ ያረፉት ኮሚዲኖው ላይ የተንጠለጠለው ቁልፍ ላይ ነበር፡፡ ቦርሣዋን ከፍታ የእራሷን ቁልፍ ፈለገች፡፡ አለ! ማቀስ ጀመረች፡፡

«ማዱ አታልቅሺ! ስትጠፊ ጊዜ ምን አልባት የሄድሽበትን ዕፈሽ አስቀምጠሽ ከሆነ ብዬ ነው፡፡ እኔ ነኝ የከፈትኩት!» አልኳት፡፡

«አይደለም! እቃዬን ለመበርበር የተጠቀማችሁት ዘዴ ነው፡፡»

«ስለምንወድሽ ነው!» አለቻት ቲጂ፡፡

«አወቃችሁት አይደል?.... ቤቱን ለቅቄላችሁ እሄዳለሁ!...»

እጇን እየጐተተችኩ መኝታ ክፍሌ ይዣት ገባሁ፡፡ ማዴ አልጋዬ ላይ ተቀምጣ እንደ ክረምት ዝናብ እንባዋን አወረደችው፡፡ የሚያለቅሳትን ሰው ሲያባብሉት አልቅስ እንደተባለ ስለሚቆጥረው ይብሰባታል ብዬ ዝም አልኳት፡፡ ሲደክማት ይሁን እንባዋ አልቆ ዝም አለች፡፡

«መደበቋ ግን አስፈላጊ ነበር?» አልኳት፡፡

«መጠቋቆሚያ መሆን አልፈልግም፡፡»

«ደሞኮ ካለ ኮንዶም ነው የምትጠቀሚው፡፡»

«የበከለኝ የአዳም ዘር እስከሆነ ድረስ፣ ይህን ቅንዘረኛ ወንድ አለቅመዋለሁ!»

«በቀል ነው?»

«በቀል!»

ፊቷ ላይ ጭካኔ እና ቆራጥነት ይነበባል፡፡ ሴት ልጅ ጨካኝና ቆራጥ ስትሆን፣ እፍ! የሆነ የማላውቀው ስሜት ወረረኝ፡፡

«ላማሽ ስለማልፈልግ ቫይረሱ በደሜ ውስጥ እንደሚገኝ አልነገርኩሽም፡፡ ላለኝ ራስወዳድ ወንድ ሲያንሰው ነው፡፡ እንደውም አደፍርሳቸውን እየቆራረጥኩ መጣል ነበረብኝ፡፡» አለች ጥርሷን ነክሳ፡፡

ህይወት በበቀል የተሞላች ናት!!

«ስህተትሽ ምኑ ጋር እንደሆነ ላስረዳሽ! አንድ ወንድ ስትበክል አስር ሴት ታጠፊያለሽ፡፡ ካንቺ ጋር ሲማግጥ የሚውል ወንድ ሁሉ ሚስት ወይም ፍቅረኛ ትኖረዋለች፡፡ ስለዚህ ለሴቷ ስትይ…»

«የኔ ቁስልስ? አመርቅዞ የሚጠዘጥዘኝ ቁስል በምን ይዳን?»

መልስ የለኝም!

«ግን መድኃኒቱን በትክክል ትወስጃለሽ?»

«እዎ!»

«... የቂማሩ ተሸናፊ እንዳትሆኚ ሪከዘሽ ተጫወቺ፡፡ አለበለዚያ ህይወት ፈጣን እና ብልጥ ናት ታሸንፍሻለች!» ,

ከኮሜዲኖዋ ውስጥ ከህክምና ጣቢያ ቫይረሱን መቋቋሚያ መድኃኒት የምታመጣበትን ካርድ ባናይ ኖሮ የኤድስ በሽታ ተጠቂ መሆኗን አናውቅም ነበር፡፡ ይገርማል! የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደሟ ውስጥ መኖር ከጀመረ ሦስት ድፍን አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ግን አንድም ቀን መድኃኒት ስትውጥ አይቻት አላውቅም፡፡

ማዱ እንደተለመደው የፈረደበትን ሜካፕ ተለቅልቃ ከለባበሰች በኋላ ሲጋራዋን እየማገች ወደ እደን ሄደች። ቲጂ ለንቦጯዋን ዘርግታ ቤቱን ታፀዳለች፡፡ ከመቀመጥ ብዬ ተነስቼ ምግብ ማብሰል ጀመርኩ፡፡ ስንፍና የሚባል በሽታ ስለተጠናወተን ደህና ምግብ አናበስልም፡፡ ብሎ ድካም የሌለበት ሽሮ እና ፍርፍር ብቻ ሆኗል የዘወትር ምግባችን፡፡ ምሳችንን ከበላን በኋላ ለሁለት አዋጥተን የምንከፍላት የቤት ሠራተኛ ፍለጋ ወጣን፡፡ ለኩድራ ደንበኞችን እማማ ስፍራዬ ሠራተኛ እንዲፈልጉልን ስንነግራቸው ልጃቸውን እንድንቀጥርላቸው ለመኑን፡፡ እሺ! ብለን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

በበነገታው እማማ ስፍራዬ በጥዋት ልጃቸውን ይዘው እቤት ድረስ መጡ፡፡ ልጃቸው መቅደስ የ10ኛ ክፍል የማታ ተማሪ ናት፡፡ ሥራ ጀመረች፡፡ መቅደስ ቤት ስታፀዳም ሆነ ምግብ ስታበስል ጐበዝ ናት፡፡ እኔም ከቤት ፅዳትና ከሽንኩርት ከተፋ ተገላገልኩ፡፡ ገና ተረኛ መሆኔን ሳስበው እራሴን ነበር የሚያመኝ፡፡

ወግ ይድረሰኝ ሱቅ ልዋል ብዬ ቁርሴን በልቼ ወጣሁ፤ አዜብ ሱቁን አልከፈተችም፤ ዘመዷን ስጠይቃት፤ አምስት ቀን ሙሉ እንዳልገባች ነገረችኝ፤ ተበማጭቼ ቁልፉን ልቀበላት የቤቷን አቅጣጫ ጠይቄ ወደ ስፈሯ ታክሲ ይዤ ሄድኩ፡፡ ባሏ የታወቀ አናጢ እና ጠጃም ስለነበር እንድ ጫማ የሚያስውብ ወጣት ቤቷን አሣየኝ፡፡

አዜብ ፊቷ በልዟል! አይኗ በርበሬ መስሎ አብጧል፡፡ ከዚህ በፊት ስካራም ባሏ እንደሚደበድባት ስለነገረችኝ የእሱ የስራ ውጤት መሆኑ ገባኝ፡፡ ቤቷ ውስጥ ሁለት ሰዎች የሚያፋቅር አልጋ፤ የእቃ መደርደሪያ፤ መከተፊያ፤ አሮጌ ቡታጋዝ፤ አግዳሚ ወንበር፤ የወየበ የውሃ ጀሪካን፤ ጥግ ጥግ ይዘው ተቀምጠዋል፡፡ ቤቱ አፈር አፈር ይሸታል፡፡ አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጥኩ፡፡ አዜብ ወደ አንድ ጐን ያጋደለች በርጩማ ላይ ፊት ለፊቴ ተቀመጠች፡፡

«ደግሞ አሁን በምን ተጣላችሁ?» አልኳት፡፡

መቼም የቤት ነገር መነፋረቅ ነው!... እንባዋን አስቀድማ ትረካዋን ቀጠለች....

«እቤት እንደገባሁ ለእራት ትኩስ ሽሮ ሠርቼ ልጠብቀው ብዬ ስጣደፍ መጣ፡፡ ጥምብዝ ብሎ ሠክሯል፡፡ ሽሮው ሲደርስ አቅርቤ የእጅ መታጠቢያ ውሀ ይገፍ ጐንበስ አልኩ፡፡ በጥፊ ደረገመብኝ፡፡ ቆሌዬ ግፍፍ አለ!... ያቀረብኩትን ምግብ ገለበጠው፡፡ ምናልባት ንዴቱ ከበረደለት ብዬ «እንዳልከዪ አርግሃለሁ!» አልኩት፡፡ «ምን? ከኔ? ከኔ ነው ያረገኸኝው?» አለኝ፡፡ ደነገጥኩ! «አንቺ ሽርሙጣ ለማንም እግርሽን ከፍተሽ ሲሸናብሽ... ላንተ ነው ያረገዝኩት ትይኛለሽ?» ሲለኝ ስለሰከረ ነው ብዬ ዝም አልኩት፡፡ ከተቀመጠበት ተነስቶ በእርግጫና በጥፊ አጣደፈኝ፡፡ ጐረቤት እንዳይሰማ አፌን በእጄ አፍኜ አለቀስኩ፡፡ ይባስ ብሎ ቢላዋ አንስቶ ሆዴን ለመቅደድ መታገል ጀመረ፡፡ ጮሁኩ! ጐረቤት ተሠበሠበ፡፡ ወንዶች ታግለው አስጣሉኝ፡፡ በሩ ተቆልፎ ቢሆንማ ዛሬ አታገኝኝም ነበር፡፡ ስንጯጯህ የሰማ መንገደኛ ፖሊስ አንቆ ጣቢያ ወሠደው፡፡ የእኔ ትንሿ ህይወት እንዲህ ናት!» አዜብ አቀረቀረች፡፡

ቆይ ወንዶች አላበዙትም? ለምንድነው በጉልበታቸው የሚያስቡት? ወንዶችን እየረገጠች የምትገዛ ሴት የትኛው ገዳም ገብታ ይሆን? እኩልነት! የታል? ወሬ ብቻ! እንዳውም እኩልነት የሚባለው ዲስኩር ከመጣ ጀምሮ ወንዶች ጠግበዋል! እኔ ሳስበው ሴቶች እኩል ናቸው የሚለው ቃል... በወንዶች ቋንቋ... ሴቶች ይረገጡ የሚል ትርጉም ሳይኖረው አይቀርም፡፡ ሲሻላት ሡቁን እንድትከፍት ነግሪያት ለታክሲ አስር ብር አስቀርቼ ቢጫ ብር ሠጥቻት ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡

ያም፣ ይሄም፡ ጋዜጣው፡ ሚዲያው፡ ሴቶች!... ሴቶች!... ወሬ ብቻ! ኢትዮጵያ! ስምሽ መጣፊጡ ኑሮሽ መምረሩ!... የጥንት ወንዶች ልጆችሽ የነብር ጆሮ በስተው፣ ድንበርሽን ከልክስክስ ውሾች ለመጠበቅ ከአንበሳ ጋር እየተጋፉ በዱር በገደሉ ሲሮጡ ውለው፣ ወንድነታቸውን ሲያስመሠክሩ፤ የዚህ ዘመን ወንዶች ግን የሴት ቀሚስ ሲገልቡ ይውሉና፣ የሴትን አይን አውጥተው፣ በአሲድ እያጠቡ «ወንድ ነኝ!» እያሉ በአደባባይ ያሽካካሉ!... እማማ ወንዶች ልጆችሽኮ በሴት ለቀማቸው ብቻ አላረፉም፡፡ ወንድ የወንድ ጀርባ ላይ እየጋሰበ፡ ዘሩን ለወንድ ፊንጢጣ እየመገበ፡ ወንድ ወንድን ለማግባት ቀለበት አሰረ፡፡

ችግር የማልሠማበት እና የማላይበት አገር በዚች ውሸታም ዓለም ውስጥ አገኝ ይሆን? ውስጤ ተረበሸ! ሰለሞን ጋር ደውዬ እንዲያዳብረኝ ለመንኩት፡፡ እንቢ አላለም፡፡ በቀዝቃዛ ውሀ ተነከርኩ፡፡ ትንሽ ቀለል አለኝ፡፡ ጫት ገዝቼ እስክመለስ መትደስ ቡና አቀራርባ ከሠል እያይዛ ጠበቀችኝ፡፡ ያቀረበችልኝን ምግብ ቀምሼ መቃሚያ ፍራሹ ላይ ተሰየምኩ፡፡ ሰለሞን ዘይት ውስጥ የተነከረ የሚመስል ከንፈሩን እያብለጨለጨ መጣ፡፡ ገላውን በሽቶ የታጠበው እስኪመስል የተቀባው ሽቶ ቤቱን አወደው፡፡ ቡናችንን እየጠጣን ጫታችንን በስመ መቃም ብለን ጀመርን፡፡

«ህይወት ምን ትመስላለች?» አልኩት፡፡

«ቀለም የላትም!»

«እርግጠኛ ነህ?»

«አንዳንድ ሰዎች የህይወት ቀለም የሰው ልጅ ነው ይላሉ፡፡»

«አንተስ?»

«የላትም ከሚሉት ውስጥ ነኝ!»

«ለምን?»

«ስለማላውቃት!»

«እንዴት አታውቃትም?» አልኩት ሳቅ ብዬ፡፡

«እናትዬ ና ብለሽ ስትጠሪኝ የመጣሁት እኔን ለመርሳት እንጂ…» በስጨት አለ፡፡

«ሰው እራሡን መርሳት ይችላል?»

«አዎ! እኔነቴ ትክክለኛ የምኖረው ህይወት ነው!»

«አሁን እየኖርከው ያለውስ?»

«እሱ የውሸት ነው! እራሴን ለመደበቅ የተጠቀምኩበት ዋሻ ነው!»

«እውነተኛ ህይወትህስ?»

«ለቅሶና ሀዘን!» ትናንሽ ውብ አይኖቹ እንባ አቀረሩ፡፡

ወንድ ለቅሶ እና ሀዘን ያውቃል?

«ብቸኛ ነኝ! የሚወደኝ ሰው የለም! የሚቀርቡኝ በማንነቴ ይሳለቁብኛል! እናቴ እንኳ ጠልታኝ ልታየኝ አትፈልግም፡፡ እኔነቴን እየጠላሁት ወድጄው እየኖርኩት ነውና የእውነት የሚቀርበኝ ሰው ተጠምቻለሁ! እባክሽ አትፀየፊኝ!»

ከዓይኖቹ የሚወርዱት የእንባ ዘለላዎች እየተንከባለሉ እኔ ልብ ውስጥ ተንጠባጠቡ፡፡ ወንድ ልጅ ሲያስለቅስ እንጂ ሲያለቅስ አይቼ ስለማላውቅ ተገረምኩ፡፡ ሰለሞን ፊቱን ደብቆ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡

በውሸታም ዓለም ውስጥ እየተኖረ እውነትን ፍለጋ መባዘን ለምን አስፈለገ? ሰው ማግኘት የሚቻለውን ነገር ቢመኝ ምን አለበት? የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥኩት፡፡ ሠማዩ ጠቁሯል፡፡ አንድ ብቸኛ ኮከብ ፈንጠር ብሎ ተቀምጧል፡፡ ራቅ ብለው ደግሞ ሠማዩን ያስዋቡት ከዋክብት በብቸኛው ኮከብ የሚሳለቁ መሰለኝ፡፡ ብቸኝነት ከዋክብትም ጋር አለ እንዴ? አልኩ ድምፄን ከፍ አድርጌ፡፡ የመለሠልኝ የለም! ብቻዬን ነኝ፡፡ ጉንጩን የወጠረውን ጫት ተፍቼ፣ ለባብሼ ኡምቤርቶ ወደ አረፈበት ሆቴል ሄድኩ፡፡

ምን ሀሳብ አለበት! እግሩን ዘርግቶ ላፕቶፑ ላይ ረክሿል፡፡ ሲያየኝ በጣም ተደሠተ፡፡ ዓይኖቹን ጨፍኖ የታችኛውን ከንፈሬን መጠጠው፡፡ ለእሱ የእውነት የሚመስለው የውሸት ፈገግታ ለገስኩት፡፡ እራት አዘዘ፡፡ የመብላት ፍላጐት ባይኖረኝም በግድ ጐሠጐስኩ፡፡ እራት የቢራ ጠርሙስ ከደረደርኩ በኋላ የኡምቤርቶ ሁለተኛ ጠርሙስ እስኪጋባ ድረስ ጠብቄ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄድን፡፡ የዝሙት መንፈስ እየጋለበ ጭንቅላቴን ተቆጣጠረው፡፡ ብልግና ተጀመረ...

ሴሠኛ አለ አብዲ! አንዳንዴ ያደረግኩት የቀባጠርኩት ሁሉ በስሜት ግለት ብቻ እንደተደረገ መቁጠር አልፈልግም፡፡ ምክንያቱም የምፈልገውን ለማግኘት ስል እልም ብዬ የስሜት ባህር ውስጥ የጠለኩ የማስመሰል ችሎታዬን እጠቀማለሁና፡፡ ያኔ ኪሳቸው ኪሴ ይሆናል፡፡ የውሸት ስሜ የእውነት እሳማለሁ፡፡ ጨዋታው የውሸት ሠጥቶ የእውነት መቀበል ይሆናል! ይሄ ችሎታ ለተሠጣቸው እንጂ ለተነፈጋቸው አይሠራም! ለኡምቤርቶ ናፍቆት እንቅልፍ ነስቶኝ ላየው እንደመጣሁ

ደረቱ ላይ ተጋድሜ ነገርኩት፡፡ «እኔም ናፍቀሽኛል የእኔ ጣፋጭ!» አለኝ ፀጉሬን እየዳበሰ፡፡

ሞኝ! እኔ የመጣሁት የቤት ኪራዬን ሂሳብ ለመቀበል ነው፡፡ ጠዋት ለቤት ኪራይ እና ለአንዳንድ ነገር ይሁንሽ ብሎ ቦርሳዬ ውስጥ በዛ ያሉ አረንጓዴ የብር ኖቶችን አስቀመጠልኝ፡፡ አከራዬ መጥተው ያጡኛል ብዬ እየተጣደፍኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡ የምፈልገውን ካገኘሁ ምን እሰራለሁ? እሱ እንደሆነ 24 ሰዓት አብሬው ብቀመጥ አይሰለችም፡፡

ታማኙ ጓደኛዬ ማስታወሻዬ ሆይ.... አዲስ አበባ ድረስ ያመጣኝ ድብቁ አላማዬ ግቡን እንዳይመታ ትልቅ እንቅፋት ገጥሞታል፡፡ አለመቻል የሚባል እንቅፋት! ቲጂ ጫማዋን በእጇ አንጠልጥላ መኝታ ክፍሌ በር ላይ ቆማለች፤ ፊቷ የተረበሸ ከተማ መስሏል፤ እንደተገተረች ማልቀስ ጀመረች፤ ማስታወሻዬን ትራሴ ስር ሸጉጬ፣ ደግፌ አልጋዬ ላይ አስቀመጥኳት፤ ተስፈንጥራ ተነሣች፡፡

«ምን ሆነሽ ነው?»

«እ... ወይኔ እናቴ! ማርኮ...ማ..ርኮ»

«ምን ሆነ?» ደነገጥኩ፡፡

«ደ...ደፈረኝ!»

«ደፈረኝ?»

«በፊንጢጣዬ... በቂጤ ...ኤሚዬ....»

ቀስ ብዬ አልጋዬ ላይ ተቀመጥኩ፡፡

«እንደሚያገባኝ ቃል ገባልኝ!... ከዛ ሞክሬ ካመመሽ እተውሻለሁ ሲለኝ... እሺ አልኩት ከዛ...»

«አሁን የምታለቅሽው ስለ አመመሽ... ወይስ?»

«የሆነው ነገር እንዴ ሆኗል!... ግን መቀመጥ አልቻልኩም፡፡ በጣም አመመኝ!»

«ታዲያ ደፈረኝ ብለሽ አታውሪያ!» አናደደችኝ፡፡

«ባያመኝ ችግር የለውም! ያገባኛል! ላገባ ነው...!»

«ቃል ስለገባልሽ አመንሽው?»

«ፈረንጅ ነው'ኮ!» አለች ኮራ ብላ፡፡

ግን ወንድ ነው! ለማግባት ብላ የቂጧን ቀለበት አስፈልቅቃ መጣች፡፡ አምላኬ! ለማግባት? ቲጂን ከመኝታ ክፍሌ አስወጥቼ አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ ማዱ በሩን በርግዳ ገባች፡፡ ጥምብዝ ብላ ሰክራለች፡፡ እነሱ ተበስተው እና ሰክረው ሲመጡ እኔ ሰላሜን አጣለሁ፡፡ ማዱ አልጋዬ ላይ ከነጫማዋ ወጥታ ተጋደመች፡፡ የለበሠችው ሱሪ እና ሸሚዝ የወንድ ነው፡፡ ከቁም ሣጥኔ ጋቢ አውጥቼ አለበስኳት፡፡ ቆንጆዬ ፊቷ ደስታ እንደራቀው ያስታውቃል፡፡ አቅፍያት ተኛሁ፤ እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ፡፡ አመሻሹ ላይ ስልኬ ሲጠራ ነቃሁ፡፡ ኡምቤርቶ ነው የደወለው፡፡ ተነስቼ ገላዬን ተጣጥቤ ልብሴን ለባበስኩ፡፡ ማህደር ከእንቅልፏ አልነቃችም፡፡ ልቀሰቅሳት ስላልፈለግኩ ማስታወሻዬን ደብቄ ከቤቴ ወጣሁ፡፡

ኡምቤርቶ ያረፈበት ሆቴል በር ላይ ተገትሮ ጠበቀኝ፡፡ ወጣ ብለን እራት እንድንበላ ፈልጎ ነበር፡፡ አብዲ ያየኛል ብዬ ስለፈራሁ እምቢ

አልኩት፡፡ አላስገደደኝም፡፡ እዛው እራታችንን በልተን ወደ መኝታ ክፍሉ ሄድን፡፡

«እግብቼሽ አገሬ ልወስድሽ እፈልጋለሁ፡፡» አለኝ፡፡

«እኔን?» አልኩት ሳቅ ብዬ፡፡

«አጠገባችን ሌላ ሰው አለ እንዴ?»

«አንተም የኔን ቂጥ መብላት አምሮህ ይሆን?» አልኩ በሆዴ፡፡

«ምነው ዝም አልሽ?»

«ሚስትህ መሆን አልችልም!»

«ምክንያት?»

«ከአገሬ መውጣት አልፈልግም!»

«እመኚኝ ጥሩ ባል እሆንሻለሁ!»

«ግን ጥሩ ሚስት መሆን አልችልም!»

ጀርባዬን ሠጥቼው ተኛሁ፡፡ «አስቢበት!» ብሎኝ መብራቱን አጠፋው፡፡ ትንሽ ከተገላበጠ በኋላ «አፈቅርሻለሁ!» አለ፡፡ እንዳልሰማ ዝም አልኩ፡፡ ተኝታለች ብሎ ነው መሰለኝ ግንባሬን ስሞኝ አቅፎኝ ተኛ፡፡ እንቅልፌ በስንት ልመና መጣ፡፡

ጠዋት ተነስቼ ካልጋው ሳይወርድ ተሠናብቼው ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡ እቤት ስገባ ማዱ እና ቲጂ የወሲብ ፊልም አፋቸውን ከፍተው ያያሉ፡፡ መቅደስን ቁርስ እንድታቀርብልኝ ነግሪያት ፊልሙ ላይ አይኔን ተከልኩ፡፡ ሰውነቱ የሚያምር ጥቁር፣ ፀጉሯን በአጭሩ የተቆረጠች ነጭ፣ ሶፋ ላይ አስፈንድዶ ይጋልባል፡፡

«እናንተ አደፍርሱ የአብዲን ነው የሚያክለው!» አልኩ፡፡

«እና?» አለች ቲጂ፡፡

«እና ምን? ምንም!»

«እውነት?» አለችኝ ማዱ፡፡

«ያማረኝ መስሏችሁ ነው?» ተኮሳተርኩ፡፡

«አይ የረጠብሽ መስሎን ነው...» አለች ቲጂ፡፡

«የሄኒ ቆለጥ ከማጠሯ መቅጠኗ!» አለች ማዱ፡፡

«የአቤነዘር ደግሞ አሁራ ጣት!» አለች ቲጂ፡፡

«ሥራው ላይ ብቃት ካለው... ማጠር መቅጠኑ እኮ ችግር የሚፈጥር አይመስለኝም! » አልኳቸው፡፡

«አቤነዘርን የተውኩት እቃው ስላጠረ መሰላችሁ? ፅዳቱን ስለማይጠብቅ ነው! የሚያጨሰው ሲጋራ ከንፈሩን ኩበት አድርጎታል፤ ጥርሱን አይፍቅ፤ ኧረ ተዉኝ!» አለች ቲጂ እየቀፈፋት፡፡

«እኔ ብሆን አንድም ቀን አብሬው አላድርም!» አልኳት፡፡

«እልፈልግሀም ብዬ ስተወው ምን ብሎ ቢያስወራብኝ ጥሩ ነው?!... አሳሳም ስለማታውቅ አስጠላችኝ! ተውኳት!»
ሣስታችንም ሣቅን፡፡

«የአብዲ ትልቅ ነው! ማለት መጠነኛ! ማለቴ ወፍራም!... ማለቴ ደስ ይላል!... ማለቴ... » ቃላት ውድ ሆኑብኝ እና ዝም አልኩ፡፡

«ፈረደበት!» አለች ቲጂ፡፡

«ማዱዬ! ስንት ወንድ በክልሽ?» አልኳት ፀጉሯን እየዳበስኩ፡፡

«አያገባሽም! ሰው በሰላም ተቀምጦ ቴሌቪዥን ማየት አይችልም? ኡፍ!» ከመቅፅበት አራስ ነብር ሆነችብኝ፡፡

«አትቅበጪ!..»

«ገና ለገና የቤቱ አከራይ ብትሆኚ የምፈራሽ መሰለሽ?»

«ያምሻል?» አለቻት ቲጂ፡፡

«አንቺን የጠራሽ የለም ጥልቅ አትበይ!» ወደ ቲጂ ዞረች፡፡

ቲጂ ተሳደበች፡፡ ማህደር የቲጂን ፀጉር አንቃ መነተት ጀመረች፡፡ ቤቱ በጩኸት በአንድ እግሩ ቆመ፡፡ መቅዲ እና እኔ ታግለን የቲጂን ፀጉር ከመነቀል አዳነው፡፡ ውይ ውይ ሴቶች!

«.... በሆሚት ስጋዬን ቦጭቃችሁ ጨረሳችሁት፡፡ ኤድስ አለባት እያላችሁስ ሳታስወሩብኝስ ትቀራላችሁ!?... የሰው ስጋ በሎች!...» አለች ማዱ እየተውረገረገች፡፡

«ካስወራን እውነታችንን ነው! አለብሽ! አልዋሸንም!» አልኳት ተናድጄ፡፡

«ስራሽ ምን ሆነና?» አለችኝ፡፡

መሰዳደብ ስለማልችል አንድ ጥፊ አቅምሼያት ከፊቷ ዞር አልኩ፡፡ ማዱ በጩኸቷ መደበቅ የምትፈልገው ፋራቻ በጉያዋ እንዳስቀመጠች ስለማውቅ ተናገረችኝ ብዬ ቂም አልያዝኩባትም፡፡ የሁለቱ ጭቅጭ ስላላበቃ ወደ ሳሎን መሄድ አልፈለግኩም፡፡ የጀመርኩትን ልቦለድ ሳነብ ሰዓቱ ሣላውቀው ሄደ፡፡ ማታ ለመፀዳዳት እና እራቴን ለመብላት ብቻ ነበር ከመኝታ ቤቴ የወጣሁት፡፡ ማህደር ሳሎን ተቀምጣ ሲጋራ

ታቦላለች፡፡ እትዬ ትእግስት መኝታ ቤታቸው ናቸው፡፡ ድምፄን አጥፍቼ ወደ ክፍሌ ተመለስኩ፡፡ አልጋዬ ውስጥ ተወትፌ ስለ አብዲ እያሰብኩ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ፡፡

ጠዋት አርፍጄ ነው ከአልጋዬ የወረድኩት፡፡ ማዱ ሳሎን ቁጭ ብላ በውሀ ብርጭቆ የቀዳችውን አረቄ እየተጎነጨች ሲጋራዋን ትምጋለች፡፡ አሳዘነችኝ! ቲጂ ከኔ በኋላ ነው የተነሣችው! መቅደስ ቁርስ አቀራርባ፣ ምሳ ለመስራት ቢላዋና መክተፊያ ታጋጫለች፡፡ «አንቺ ቀስበይ!» ማዱ እንባረቀችባት፤ አህያውን ፈርቶ... «ማዱ! ቁርስ አትበዪም?» አልኳት፡፡ ገላመጠችኝ፡፡ ቲጂ ማርኮ ናፍቀሽኛል ብሎ ስለደወለላት ቁርሷን እየተጣደፈች በልታ ለመለባበስ ተነሳች፡፡ ማዱ አረቄውን እንደውሀ እየጨለጠች በላይ በላይ ሲጋራ ትለኩሣለች፡፡ ቁርሴን በልቼ እንደጨረስኩ የለኮሰችውን ሲጋራ ቀምቻት የአረቄውን ጠርሙስ ከፊቷ አነሳሁት፡፡

«ማዱ አብረን እንውላለን አንውልም?» አልኳት፡፡

«ሼኪው ከደወለስ?» አለችኝ፡፡ አብዲን ነው!

«ስልኬን አጠፋዋለው!»

«ምን ችግር አለው? ይመጣላ!»

«የለችም ትይዋለሻ!»

«ኤሚ በቃ ልሞት'ኮ ነው!» መነፋረቅ ጀመረች፡፡

«የምን ሞት ነው የምታወሪው?»

«ሞት ስተኛ ይዞኝ የሚሄድ እይመስለኝ፣ ቁጭ ብዬ ነው የማድረው፡፡»

ሺህ ዓመት ላይኖር መከራ ተሸክሞ መወለድ፡፡ ኤጭ! ቆይ ሴቶች እንዲህ መከራቸው የበዛው በላይኛው ቤት ለፍርድ አይቀርቡ ይሆን?

«ሞት ከኔ ጋር እንደሆነ አውቃለሁ! ከኔ ጋር ነው! ይሰማኛል! ይሸተኛል! እንዲህ ያደረገኝ የአዳም ዘር ነው፡፡ አመንኩት! ይኸው በመርዙ ተበከልኩ፡፡ መጨረሻዬ ሞት ሆነ!»

«አሁን እሱ ያለበትን ታውቂያለሽ?» አልኳት ማን እንደሆነ ለማወቅ ፈልጌ፡፡ መቼም የሰው ታሪክ ማዳመጥ አይሰለቸኝ፡፡

ማዱ እንባዋን አስቀደማ ትረካዋን ቀጠለች!...

«የ15ተኛው የልደት በዓሌ በተከበረ በ6ተኛው ወር ነበር እናቴ እና አባቴ በመኪና አደጋ የሞቱት፡፡ እህቴ በ5 ዓመት ትበልጠኛለች፡፡ ወላጆቻችን ሲደይሙላት ሰፈር ያሰለቸ ጎረምሳ ቤታችን አስገባች፡፡ ፈላጭ ቆራጩ እሱ ሆነ፡፡ እኔን ገረዳቸው አደረጉኝ፡፡ መረረኝ! አንድ ቀን ተጋድመው ቁርስ አምጪ! ሻዪ አምጪ! እያሉ ፋታ አሳጡኝ፡፡ በተጙበት ዘይት ደፋሁባቸው፡፡ ዘውዱ ተብዬ ጎረቤታችን ካላገባሁሽ እያለ ይለምነኝ ስለነበረ እህቴ ስታባርረኝ ስትት ብዬ ቤቱ ገባሁ፡፡ ለነገሩ እሱ ምን አደረገ? እኔው ነኝ ቤቱ ድረስ የሄድኩለት፡፡» ሳቀች፡፡

«ዘውዱ ቤት ከመግባትሽ በፊት ወሲብ ፈፅመሽ አታውቂም?»

«በፍፁም! ካለኮንዶም የዘውዱን ቆለጥ በነጋ በጠባ ስጎርስ ከረምኩና የወር አበባዬ ሲቀር ጤና ጣቢያ እሄዳለሁ... ጉዴን አበሰሩኝ፡፡ የኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ በደሜ ውስጥ እንደሚንሸራሸር

ነገሩኝ፡፡ ወባ አይደለም! ኤድስ ነው!! ወደ 'ዚች' አልም ለመምጣት ሰባት ወር የሚቀረው ፅንስ በመህፀኔ ውስጥ መጋደሙን ደግሞ ስሰማ አበድኩ!... አበድኩ!... ከዛ ፅንሱም ወጣ፡፡ እኔም ኪኒኔን እንደ እንጀራ መብላት ሥራዬ ሆነ፡፡»

አለቀስኩ!

«እህቴ ባይዋጥላትም ተመልሼ ወደ ቤተሰቦቼ ቤት ገባሁ፡፡ የምበላበት ሰሀን፡ የምጠጣበት ብርጭቆ፡ ተለየልኝ፡፡ እህቴ እንደቆሻሻ ተፀየፈችኝ፡፡ ዘውዱ ቤት ከመግባቱ በፊት ስታስመርረኝ የነበረው ለካ ጥቅሟ እንዳይቀርባት ነበር፡፡» ደነገጥኩ!

«ለምን?»

«ቤቱን ጥዬላት እንድወጣ እና ዘውዱ የሚሰጣትን ጉርሻ ለመቀበል፡፡»

«በሽተኛ መሆኑን ታውቅ ነበር?»

«እሱን አላውቅም! ግን በጣም ተቀይሚያታለሁ፡፡ አሁንም የምጠይቃት ስታየኝ የፈፀመችብኝ በደል ትዝ እያላት እንድታመም ነው፡፡ እንድትታመም!»

ከእያንዳንዱ ወንድ ጥፋት ጀርባ ሴት ትገኛለች!!

«ተመልሰሽ ከቤታችሁ መውጣት አልነበረብሽም!»

«እህቴ እንዴት እንደምትፀየፈኝ ብታውቂ ኖሮ እንዲህ አትይም ነበር፡፡ ሽርሙጥናዬ ደህና! ብርም የበቀል እርካታም አገኝበታለሁ፡፡ እድሜ ለቲጂ!»

«ቲጂ ደግሞ ምን አደረገችልሽ?»

«ቲጂ እኛ ሰፈር ተከራይታ ስትኖር፣ ሸርሙጣ መሆኗን አውቅ ስለነበረ፣ መሸርሞጥ እፈልጋለሁ አልኳት፡፡ እሺ! የቤት ክራይ ለሁለት እንከፍላለን ሰፈር እንቀይር አለችኝ፡፡ በቃ!»

ማህደር በዚህ እድሜዋ ይህ ሁሉ መከራ የታዘዘላት ለምን ይሆን?

«ደሜን የበከለኝ ዛሬ ባለ ሬስቶራንት ሆኗል! ዘውዱ ባርና ሬስቶራንት! አንድ ሴት አታመልጠውም! ሀብቱን አይታ እግሯን ትከፍታለች፡፡ ዋጋዋን ታገኛለች!» አለች ማዱ እየሳቀች፡፡

«ቢሞት ደስ ይልሻል?» አልኳት ስሜቷን ለማንበብ፡፡

«ዘውዱ ዛሬ ቢሞት… ሞት የት ነህ? ብዬ እፈላልጌ ነው ውሰደኝ የምለው…» ጭብጥ ብላ ከቆዘመች በኋላ «ፍለጋ ምን አስኬደኝ? ሞት ከኔ ጋር ነው!» አለች፡፡

«መሞትሽ ለማይቀር ነገር አትጨናነቂ በሞት ላይ ስቀሽበት እና አላግጠሽበትሙቺ፡፡» አልኳት ፍራቻዋ እንዲለቃት ብዬ፡፡

ስልኳ ጮኸ!..

«ዮሴፍ ይባላል! ኢንጅነር ነው፤ ስስት ወር ሙሉ ድምፁን አጥፍቶ ደወለልኝ፣ አገኘሁት፤ ባለፈው ከእሱ ጋር ነበርኩ፡፡ ለብሼው የመጣሁት ሱሪ እና ሸሚዝ የእሱ ነው፡፡ እርግጠኛ ነኝ ቢመረመር በሽታው እንደሚገኝበት፡፡» አለች እየሳቀች፡፡

በምታደርገው የበቀል ዘመቻ እርካታን ታገኛለች፡፡ ግን ደግሞ ሞት መጣሁ እያለ ስለሚያስጨንቃት ደስታ የላትም፡፡ ጥርሷ እየሳቀ ውስጧ ያለቅሳል!!

ጫት ለመግዛት ተያይዘን ወጣን፡፡ የጫት ደንበኞችን በጫት እና በሲጋራ የበለዘ ጥርሱን አስጥቶ ተቀበለን፡፡ ጫቱን ከገዛን በኋላ ወደ ዘወትር የቁጠማ ደንበኞችን አመራን፡፡ የተሸበሸበ ፊታቸውን በግራ እጃቸው እያሻሹ በቀኝ እጃቸው የከበቧቸውን ዝንቦች ያባርራሉ፡፡

«እማማ ገበያ እንዴት ነው?» አልኳቸው፡፡

«መቼም ተመስገን ነው የሚባለው!» አሉ፡፡

«ወጥቶ መግባቱ ራሱ አንድ ነገር ነው!» አለች ማዱ፡፡

«ፀሀይ ላይ ተሰጥቶ ውሀ መጠጫ ሳንቲም ሳይዙ መግባት ጥሩ ከሆነ...እዎ!» አሉ አንገታቸውን ደፍተው፡፡

አንጀት ይበላሉ! ይሔኔ እድሜያቸውን ሙሉ በችግር እለንጋ እየተገረፉ ይሆናል የኖሩት፡፡ ከንፈሬን መጠጥኩ! ሀበሻ ከንፈር ከመምጠጥ ወዲያ ምን ያውቃል? የአራት ብር ቁጠማ የስድስት ብር ምርቃት ገዝተን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

እርቦኝ ስለነበር እጄን ውሀ አስነክቼ የቀረበውን እንጀራ እየተስገበገብኩ ጎረስኩ፡፡ ማዱ አልወርድ ብሏት በውሃ እየገፋች ትንሽ ታግላ ተነሳች፡፡ «ለመኖር መብላት አለብሽ!» አልኳት፡፡ መልስ ሳትሰጠኝ እያንጎራጎረች መፀዳጃ ቤት ገባች፡፡ እወዳታለሁ! ገላዋን ታጥባ እራቁቷን ወጣች፡፡ ማዱ ስጋ ሳይሆን ቆዳ የለበሰ አጥንት ነው ያላት፡፡ ውሀ ያዘሉ ግማሽ

የእግሯን ኮቴዎችን ጥላ ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች፡፡ ቢያንስ በእሱ እንኳ ብትፅናና ብዬ ሔኖክ ተብዬ ቀጭኔ ጓደኛዋ ጋር ደውዬ አብሮን ጫት እንዲቅም ጋበዝኩት፡፡ ግብዣዬን ተቀበለ፡፡ ማህደር እኔ የሰጠኋትን ብርቱካናማ ድሪያ ለብሳ እየደነሠች ስትመጣ ውሀ ያዘለ ኮቴዋ አዳለጠ ወለሉ ላይ ዘረራት፡፡

«ኮቴሽን እያጠፋሽ ካልተራመድሽ… በእራስሽ ኮቴ የጠላትሽ እጅ ውስጥ ትወድቂያለሽ፡፡» አልኳት፡፡

«አንቺ ደግሞ ይሀን እና ያን ምን አንድ አደረገው?» አለች ተናዳ፡፡

«አንድ ነገር፣ የአንድ ነገር፣ ምሣሌ መሆኑን አትዘንጊ፡፡» አብዲ ደወለ!

«ትተሺኝ ብትሄጂ አላናግርሽም!» ማዱ ማስጠንቀቂያ ሰጠችኝ፡፡ ስልኩን አነሳሁ!

«የት አባሽ ሄደሽ ነው? እቤት ስመጣ የለችም አሉ!» አለ፡፡ ስልኩን ለማህደር ሰጠኋት፡፡

«ዛሬ ፕሮግራሟ ከኔ ጋር ነው ስለዚ…» ተናግራ ሳትጨርስ ስልኩን ጆሮዋ ላይ ጠረቀመባት፡፡

«ኤምዬ አትቀየሚኝና አብዲን ለአንድ ቀን እንኳ ቢሆን መቅመስ እፈልጋለሁ!» አለችኝ፡፡ መልስ አልሰጠኋትም!

በእስቴር አወቀ ሙዚቃ መንፈሳችንን እያደስን፣ ከሺሻው እየተቋደስን፣ አረንጓዴ እየበላን፣ ወሬ ስናቦካ፣ በሩ ተንኳኳ፡፡ ማህደር እየሮጠች ከፈተች፡፡ አብዲ መስሏት እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ ሄኖክ ነው!

ተደሰተች፡. ወዲያው በሩ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ማህደር አሁን ብትሮጥ ኖሮ አይኔ ይደፋት ነበር፡፡ መቅደስ በሩን ከፈተች፡፡ አብዲ ነው! እንዴት እንደሚያንኳኳ ስለማውቅ ገና በሩ ሳይከፈት ነው እሱ መሆኑን የማውቀው፡፡ ደጋግሜ ባየሁት ቁጥር ውበቱ አዲስ ይሆንብኛል፡፡ ያምረኛል!

ማዱ አይኗን ተከለችበት፡፡ አብዲ ሁለቱን ሰላም ብሎ ከጐኔ ተቀመጠ፡፡ እንገቴ ስር ሲስመኝ ሳይታወቀኝ ተነፈስኩ፡፡ በጋዜጣ ጠቅልሎ ያመጣውን ጫት ፈቶ አጤሬራ አድርጎ ሰጠኝ፡፡ ማዱ አብዲን እየሰረቀች ስታየው ሁለቴ ያዝኳት፡፡ እንዳታይው አይባል?! በአብዲ ቀልድና ጨዋታ እየተዝናናን ጫቱን አገባደድነው፡፡ ማዱ ሺሻውን ስባ ሲወጣላት፣ ሲጋራ ትለኩሳለች፡ ሲጋራው ሲበቃት፣ ጫቱ ላይ ትዘምታለች፡፡ መጥኔውን ይስጣት!

ሰዓቱ እኛን አስቀምጦ በረረ፡፡ አብዲ ጓደኞቹ ሲደውሉለት ተመልሶ እንደሚመጣ ነግሮኝ ወጥቶ ሄደ፡፡ ማህደር ትንሽ ካደረቀችኝ በኋላ ሄኒን አስከትላ ወጣች፡፡ ብቻዬን እንደተቀመጠኩ፣ ሀሳብ ስገነባ ሣፈርስ ቆየሁና፣ ገላዬን ታጥቤ፣ ቀለል ያለ ልብስ ለብሼ፣ የመኝታ ቤቴን መስኮት ከፍቼ፣ ከተፈረዘ ሁለት ቀን የሆነውን ፀጉሬን ማፍተልተል ጀመርኩ፡፡ አብዲ ቆየብኝ፤ ከመኝታ ቤት ወደ ሳሎን፣ ከሳሎን ወደ መኝታ ቤት ተመላለስኩ፡፡ በሩ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ከፈትኩለት፡፡ ገላምጦኝ አልፎኝ ገባ፡፡

«ለምን ስልክሽን አጠፋሽው?» አፈጠጠብኝ፡፡

«ሲጀመር የት እንዳለ አላውቅም! ብፈልገው አጣሁት፡፡»

«አታስመስይ ለምን አጠፋሽው?»

«አባዲ የእውነት የት እንዳደረኩት አላውቅም!»

«ወላሂ እውቀሽ ነው!»

.... አብዲን ለማሳመን ከመጣር ጥፋቱ እንኳ ባይሆን አምኜ መቀበልን እመርጣለሁ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ላይሳካልኝ ላሳምነው እጥራለሁ፡፡ ተደግፌው የነበረውን ትራስ ሳነሣ ሞባይሌ ከትራሱ ጨርቅ ውስጥ ዱብ አለ፡፡ ሞባይሌ አልጠፋም፡፡ በቴሌ ጥፋት እኔ ይጮህብኛል! አብዲ ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ «ስቆይ አንቺ ልታገኚኝ ከፈለግሽ ለምን አልደወልሽም?» አለኝ በሩን ከፍቶ፡፡ መልስ ሳልሰጠው ቦርሣዬን አንጠልጥዬ ወጣሁ፡፡

መኪናው ውስጥ እንደገባን ሞባይሌን እየነካካሁ ነገር አሰላስላለሁ፡፡ ሞባይሌን መንጭቆ ወደ ኋላው ወረወረው፡፡ አልተናገርኩትም፡፡ መኪናውን ያለቅጥ እያበረረ 'ቤቱ ደረስን፡፡ አሁንም አፌን በዳቦ አልኩ፡፡ የሳሎኑን በር በርግዶ ወደ መኝታ ክፍሉ ወጣ፡፡ በሩን ቆልፌ የሚበላ ነገር ፍለጋ ወደ እቃ ቤት ገባሁ፡፡ የተቀቀለ ፓስታ እና በስጋ የተሠራ ስጎ አገኘሁ፡፡ ስጎውን አሙቄ፣ ጠረጴዛ ላይ ባገኘሁት ዳቦ እያጣበኩ በልቼ ስጨርስ፣ ልብሱን አወልቆ በፓንት ወደ ሣሎን መጣ፡፡ ነገር ሽሽት ወደ መኝታ ክፍሉ ሄድኩ፡፡ መፀዳጃ ቤት ገብቼ ጥርሴን እየቦረሽኩ መጣራት ጀመረ፡፡ ስጨርስ ፒጃማ ለበሼ ወረድኩ፡፡

«ምን እያደረግሽ ነበር?» አለኝ በእጁ የያዘውን ባዶ ብርጭቆ እያገላበጠ፡፡

«ተኝቼ!»

«አቤት?»

«እሺ. ምን ፈለግክ?»

«ቁጭ በይ! እንደ ህፃን ኩርፊያ ቢቀርብሽ ጥሩ ነው፡፡» ብሎኝ ውስኪ ቀድቶ ሠጠኝ፡፡

«አልጠጣም!»

ፀጉሬ ላይ ገለበጠው፡፡ ምንም ሳልናገረው ወደ መኝታ ክፍሉ ሄድኩ፡፡ በውስኪ የራሰ ፒጃማዬን አውልቄ፣ አውልቶ ያስቀመጠውን የቆሸሸ ቲሸርት ለብሼ፣ በፒጃማዬ ፀጉሬን ካደረቅኩ በኋላ መብራቱን አጥፍቼ አልጋ ውስጥ ገባሁ፡፡ መብራቱን አብርቶ በሩን ከቆለፈ በኋላ አልጋ ልብሡን ጉትቶ መሬት ላይ ጣለው፡፡

«አብዲ ለምን የህፃን ሥራ ትሠራለህ?»

«ምን ሆነሽ ነው ያኮረፍሽው?»

«እቦ በቃ ዞር በልልኝ!»

«ቲቢትሽ እንደሚያስገድልሽ ማወቅ አለብሽ፡፡»

ጭኖቼ መሀል ገብቶ ሊስመኝ ወደ አፌ ተጠጋ፡፡ ፊቴን አዞርኩ፡፡ አንገቴ ስር ሳመኝ፡፡ በእጄ ገፋሁት፡፡ እጄን ሣመው፡፡ የለበስኩትን ቲሸርት አውልቆ ወረወረው፡፡ ሰውነቱ ግሏል፡፡ አይኖቹን አይኔ ላይ ተከላቸው፡፡ አይኔን አሸሸሁ፡፡ አደፍርሱ ፓንቱን ቀዶ ሊወጣ ምንም አልቀረውም፡፡ ፓንቱን አውልቆ ሲወረውረው ሳላስበው ተነፈስኩ፡፡ ፓንቴን ለማውለቅ እጆቼ ፈጠኑ፡፡ ድንቅነሽ እና አደፍርስ ተገናኙ፡፡ ይበልጥ ተጣበቅኩበት፡፡

«ለዚህ አቅምሽ አይደል…እ?»

«ይ…ይ ቅርታ እ…ኔ»

ትቶኝ ተነሳ! እርር ይገልፀው ይሆን? ፎጣ አሽርጦ ወደ ሳሎን ሄደ፡፡ የእስራኤል ቅዱስ… ቅጥል አልኩ! የአልጋ ልብሡን ከመሬት አንስቼ ለብሼ ተኛሁ!… አልቻልኩም! አልቻልኩም! እሺ እኔስ ይቅርብኝ ለራሱ ሲል ምናለበት ብንጨርስ? ወደ ሳሎን ወረድኩ፡፡ በ MBC4 የሚተላለፍ ፊልም ላይ አፍጥጧል!

«አባዲ… በእ… በእናትህ!»

«እናት ፊልም እያየሁ ስለሆን አትረብሺኝ፡፡»

«እሺ ይቅርታ!»

«ቤትሽ ላድርስሽ?»

«አዎ አድርሰኝ!» አልኩት የቀልዴን፡፡

እንደተገተርኩ ፒጃማውን ለበሶ፣ ልብሴን እና ቦርሳዬን ይዞልኝ መጣ፡፡ ሊስፈራራኝ ፈልጎ ነው ስል፣ ልብሴን ወለሉ ላይ ወርውሮ፣ ቦርሣዬን አንጠልጥሎ ወደ ውጪ ወጣ፡፡ ማመን አልቻልኩም! እንጀቴ እርር እያለ ቤቴ አደረሰኝ፡፡ መለመኑንም ፈለግኩ ግን ለምን? እችለዋለው! እልህ አስለቀሠኝ፡፡ አብዲን ያገኘሁት ይመስል በሩን ደበደብኩት፡፡

…..ኡምቤርቶ ጋር ደውዬ ካልመጣህ ሞቼ እገኛለሁ አልኩት፡፡ አልጨከነም፡፡ እሱ አብዲን አይደለም! መሆንም አይችልም! አብዲ ብቻውን አብዲ ነው! ኡምቤርቶ በሩን ሲያንኳኳ ልብሴን አወላልቄ በሩን ከፈትኩለት፡፡ በጥርሴ ልዘለዝለው ምንም አልቀረኝም፡፡ አብዲ

የለኮሠው እሣት ጭንቅላቴ ላይ ወጥቷል፡፡ የወሲብ ጥም! እርካታ ፍለጋ ማበድ!... ኡምቤርቶን ሣይሆን አብዲን ነከስኩት፡፡ በኡምቤርቶ ላይ ሣይሆን በአብዲ ላይ ከጋለብኩ በኋላ በረደልኝ፡፡ ኡምቤርቶ ማርኮን እመለሳለሁ ብሎት እንድ የምሽት ክለብ ውስጥ ብቻውን ትቶ እንደመጣ ነገረኝ፡፡ የፈለግኩትን አግኝቻለሁ! አስናበትኩት! መኝታ ክፍሌ ገብቼ አልጋዬ ላይ ወደቅኩ፡፡

የመኝታ ክፍሌ በር ተንኳኳ፡፡ የደቀቀ ሰውነቴን እየጎተትኩ በሩን ከፈትኩ፡፡ ማህደር ናት! ተመልሼ ተኛሁ፡፡ «ቆይ አንቺ ሠባት ሠዓት ካልሆነ አይንጋልሽም?» አለችኝ፡፡ «አሁን አይደለ የተኛሁት ከመቼው ነጋ?» አልኳት፡፡ ለካ ነግቶ ሊመሽ ነው! «አለቃሽ ጋር አላደርሽም እንዴ? ስልክሽ እንቢ ሲለኝኮ ደወልኩለት፡፡ ቁጥሩን ከትጂ ነው የወሰድኩት!» አለችኝ፡፡ ማን አባቷ ሰጪ አደረጋት እስቲ?!..

«እና ምን አለሽ?»

«እሱ ደህና ነገር መልሶ አያውቅ...»

እሰይ! «ስንት ሰዓት ሆኗል?»

«ከቀኑ ሰባት ሰዓት! ለምን እሱ ጋር አላደርሽም?»

መልስ ሳልሰጣት ወደ መፀዳጃ ቤት አመራሁ፡፡ የገላ መታጠቢያ ዳንቴሌን ሳሙና ከቀባሁ በኋላ፣ በቀዝቃዛ ውሀ የተነከረ ገላዬን ሞዥርቅኩት፡፡ ውሀን የፈጠረ የተባረከ ይሁን! ጅናባዬን አራግፌ አጠር ያለች ቀሚስ ውስጥ ገባሁ፡፡ የቀረበልኝን ምግብ ፍርፋሪ እንኳ ሳላስቀር ጥርቅ አድርጌ፣ ትኩስ የጠሰኝ ሻይ ገለበጥኩበት፡፡ ማዱ ከጎኔ ተቀምጣ በአበላሌ እየተደነቀች ሲጋራ እያጨሰች ነበር፡፡

«አንቺ ጉደኛ! ከሔኒ ጋር በምንድነው የምትጠቀሙት?» አልኳት ድንገት ትዝ ብሎኝ፡፡ መቼም እወደዋለሁ እያለች በባዶው እንደማትለኝ ተስፋ እያደረግኩ፡፡

«በባዶ!... ግን የእሱ ምርጫ ነው!»

«ከቫይረሱ ጋር እንደምትኖሪ ያውቃል?»

«አዎ!»

«ዕያወቀ ለምን?»

«እንደኛ ስለሚወደኝ!»

«ሁለተኛ?»

«እቃው በጣም ትንሽዬ ስለሆነች!»

ጆሮዬ ብቻ ሳይሆን አይኔም ይበልጥ ተከፈተ፡፡

«ኮንዶሙን አጥልቆ ገና ወደኔ ሲጠጋ፣ ኮንዶሙ ወልቆ ይወድቃል፡፡ ዋናው ምክንያቱ ግን ስለሚወደኝ ነው፡፡»

«አይመስለኝም! ወንዶች ውሸታሞች ናቸው!»

«አንቺ ደግሞ አንድ ቀን እንኳ እውነት ይናገራሉ አትይም?»

«አይተላለፍበትም! እቃው ጥንጥዬ ከሆነች ምንም አይነት ፍትጊያ አይፈጠርም፡፡ ይሄ ማለት ብልቶቻችሁ የመላጥ አደጋ አይደርስባቸውም፡፡ አለተላጠም ማለት ደግሞ፣ ምንም አይነት የደም ንኪኪ የለም ማለት ነው!»

«ወንዶች ምን አድርገውሽ ነው እንዲህ ጥምድ አድርገሽ የያዝሻቸው?»

«ስራቸውን ነው የነገርኩሽ! ከወደድከኝ አግባኝ በይው፡፡ ከዛ... መውደድ አለመውደዱን ታረጋግጫለሻ!»

«አሁን ደውዬ እጠይቀዋለው!» ብላ ስልኳን አነሳች፡፡

ስልኳን ቀማኋት!

«እፉ ይዋሻል! አይኑ ግን ያጋልጠዋል! በአካል ነው የሚሻልሽ!» አልኳት፡፡

የማዱን ጭንቅላት ለኩሼዋለው፡፡ የሄኒ መልስ ደግሞ ያቀጣጥለዋል!... ከዛ... የሄኒን ማንነት እያወቀ ለመቀበል ያመነታው ልቧ እርግጠኛ ይሆናል፡፡ ማህደር እየተጣደፈች ወጣች፡፡

ለረጅም ሰዓት ዓይኔን ጨፍኜ የልጅነት ትውስታዬን እየደጋገምኩ ከተመለከትኩት በኋላ፡ የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥ አድርጌ ወደ ውጪ ተመለከትኩ፡፡ ሠፈሬ በመብራት አሸብርቃለች፡፡ በጣም አጭር ቀሚሴን ለበስኩ፡፡ ተኳኩዬ፡ ተረከዘ ረጅም ጫማዬን አጥልቄ፣ የእጅ ቦርሣዬን አንጠልጥዬ ወጣሁ፡፡ እንደ እድል ሆኖ የተሣፈርኩበት ባለኮንትራት ታክሲ ሹፌር እያበረረ የምፈልገው ቦታ በምፈልገው ሰዓት አደረሠኝ፡፡ ከተነጋገርንበት ሂሣብ ጨመር አድርጌ ሠጠሁት፡፡ «ልጠብቅሽ?» አለኝ ብሩን እየቆጠረ፡፡ ጥሩ ሀሳብ ነው! ጠቀስኩት፡፡

የዘውዱ ባርና ሬስቶራንት... ሲጋራ፣ ማስቲካ፣ ለውዝ፣ በሚያዞሩ ልጆች ተከቧል፡፡ ስገባ ጆሮ የሚበሳ የሙዚቃ ድምጽ ተቀበለኝ፡፡ በስው ተጥለቅልቋል፡፡ አይኔን ጥግ ይዘው ቢራ እየተጋቱ ወሬያቸውን ወደ ሚሠልቁ ሶስት ወንዶች ላኩት፡፡ በፎቶ የማውቀው ሰው በመሀከላቸው

ይገኛል፡፡ «ብቻዬን ልዝናና መጥቼ ፈራሁ፡፡ ከእናንተ ጋር ብቀመጥ ቅር ይላችኋል?» አልኳቸው እየተቅለሰለስኩ፡፡ ከላይ እስከታች ተመለከቱኝ፡፡ «ቅር ካላችሁ ቦታ መቀየር እችላለሁ፡፡» አልኩ ፈገግታዬን እየረጨሁ፡፡ «ኸረ ችግር የለውም ቁጭ በይ!» አለኝ በፎቶ የማውቀው ሰው፡፡ አንድ ባዶ ወንበር ከጐን ሳብ አደረገልኝ፡፡ ስቀመጥ ቀሚሴ ፓንቴን እጋለጠው፡፡ ለመሸፈን የውሸት ሙከራ አደረኩ፡፡

«ዘውዱ እባላለሁ! እነዚህ ጓደኞቼ ናቸው፡፡ ታደሰ እና ሠራዊት ይባላሉ፡፡» አለኝ በፎቶ የማውቀው ሰው፡፡ ስሜን ተናገርኩ፡፡

«ምን ይምጣልሽ?» አለኝ ዘውዱ፡፡

«ለምን ብላክ ሌብሉን እናወርደውምና አንታጠብበትም? አምጣው!» አልኩ፡፡

ሆስቴም ተያዩ፡፡ አጠገባችን ተገትሮ የነበረው አስተናጋጅ ከምኔው ይዞ እንደመጣ አላውቅም፡፡ ዘውዱ ፈጠን ብሎ ከፍቶ አራቱን ብርጭቆዎች ከበረዶ ጋር ሞላቸው፡፡ ብርጭቆዎቻችንን ከፍ አድርገን እጋጨን፡፡

«ከውጪ የመጣሽ ትመስያለሽ!» አለ ሰራዊት ተብየው፡፡

«በተለይ ሽቶዋና አለባበሷ!» አለ ታደሰ፡፡

«ከአዲስ አበባ ውጪ የማውቀው ሀገር የለም!» አልኩ፡፡

«ግን ለሴት ልጅ ብቻዋን መዝናናት አይከብድም?» ታደሰ ተገርሟል፡፡

«ሚስቶቻቸውን እቤት ትተው እኔን እዚህ ሲያደርቁኝ ያመሻሉ፡፡» አለ ዘውዱ፡፡

«ባለትዳሮች መሆናችንን መናገሩ አያስፈልግም፡፡ ይመችህ!» አለው ስራዊት፡፡

«ሴት ፊት ከተሰጣት አትቻልም ብለን ነው!» ታደሰ ተንጠባረረ፡፡

«ትዳር እንደዚህ ከሆነ ይቅርብኝ!» አስመሰልኩ፡፡

ስራዊት እና ታደሰ እየተንገዳገዱ ክብ ሰርተው ከሚጨፍሩት ወጣቶች ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ዜድ አይኑን ፓንቴ ላይ ተክሎ ይቁነጠነጣል፡፡ ማዱ በእሱ የተነሳ መከራዋን ታያለች፡፡ እሱ ውስኪ እየተጐነጨ የእምሮትን ገላ ይመኛል፡፡ ሲያዩት እንኳን ኤድስ የሚያውቀው ራስ ምታት የጐበኘውም አይመስልም፡፡ የተቀዳልኝን ውስኪ ባላወቀ ጭኔ ላይ ለቀቅኩት፡፡ በእጁ ጠረገልኝ፡፡ ጠቀስኩት!...

«እስተናጋጁ የታል? መሂድ አለብኝ!» አልኩ ቦርሳዬን እየከፈትኩ፡፡ እጄን ያዘው፡፡

«ሌላ ቀን ትከፍያለሽ! ብትጫወቺ ደስ ይለኝ ነበር!.. ልሂድ ካልሽ ቤትሽ እንዳደርስሽ ፍቀጅልኝ፡፡»

«የታክሲ ደንበኛዬ እየጠበቀኝ ስለሆነ አትጨናነቅ፡፡ ብከፍል ደስ ይለኝ ነበር!» አልኩት፡፡ ሞቼ እገኛለሁ አለ፡፡ ድሮስ...?!

ዜድ ወገቤ ላይ እጁን አሳርፎ ወደ ውጪ ወጣን፡፡ ቦርሳዬ ውስጥ የነበረው 200 ብር ብቻ ነበር፡፡ ክፊይ ቢሉኝ ከየት አመጣ ነበር? ግን

መላ አይጠፋም፡፡ ሴት እና ብልሀት...! ትንሽ ከቀበጣጠረልኝ በኋላ ስልክ ቁጥሩን ስልኬ ላይ መዝግቦ ተሰናበተኝ፡፡ የማህደርን ጀግና አየሁላት፡፡ ፈጣኑ የታክሲ ሹፌረ እያበረረ ቤቴ አደረሰኝ፡፡ እቤት ስገባ መብራቱ ጠፍቶ ፀጥ ብሏል፡፡ ኮቴዬን አጥፍቼ መኝታ ክፍሊ ገባሁ፡፡ ብቀምሰው ምን ችግር አለው? ዘውዱ ጋር ደውዬ የቤቱን አቅጣጫ ከወሰድኩ በኋላ፣ ተመልሼ ወጣሁ፡፡

የዘውዱ ግቢ በተከረከመ ዕድ ተከቧል፡፡ ዘበኛው እየተጨናበሰ በሩን ከፈተልኝ፡፡ ማንሽ? ከየት ነሽ? አላለኝም፡፡ እያዛጋ ወደ ማደርያው ሄደ፡፡ ዜድ በለሊት ልብሱ ሶፋው ላይ እግሩን ዘርግቶ፣ ያላበው ቢራ እየተጐነጨ፣ ቴሌቪዥን ያያል፡፡ ሲያየኝ ደንግጦ ከተቀመጠበት ተነሣ፡፡ ልብሴን አወላልቄ ተጠጋሁት፡፡

«ለምን መኝታ ቤት እንሂድም?»

«ሶፋ ላይ ቢሆን ይመቸኛል! ባይሆን ኮንዶም ብታመጣ ደስ ይለኛል፡፡» አልኩት፡፡

ከንፈሬ ላይ ስሞኝ ወደ መኝታ ቤቱ ሄደ፡፡ ያመጣሁትን ወይን እና ብርጭቆ ከቦርሳዬ ውስጥ አውጥቼ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩት፡፡ እጅሬ ሲቆይብኝ፣ ወይኑን በስንት መከራ ከከፈትኩት በኋላ፣ ለሁለታችንም ቀድቼ፣ እየተጎነጨሁ ጠበጥኩት፡፡ ኮንዶሙን አጥልቆ እያለከለከ መጣ፡፡ አደፍርሱ የሚያስመረቅን ባይሆንም ደህና ነው፡፡

«ወይን እኔጋ ነበረ ልሽ'ኮ... ለምን አመጣሽ?»

«እኔም በተራዬ ወይን ልጋብዝህ ብዬ፡፡»

የቀዳሁለትን ወይን ሰጠሁት፡፡ ጭልጥ አድርጎ ጠጥቶ ጭኖቼ መሀል ለመወተፍ ተጣደፈ፤ አልፈቀድኩትም፡፡ እግሩ ስር በርከክ ብዬ፣ አይኔን አይኑ ላይ ተክዬ፣ ኮንዶሙን አወለቅኩለት፡፡ ተክለፈለፈ! ሶፋው ላይ እንዲጋደም ፈቀድኩለት፡፡ ማቃሰት ጀመረ፡፡ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ተሠናብቼው ወጣሁ፡፡

ወደ ቤቴ ያደረሰኝ የታክሲ ሹፌሩ ሰው ሳይሆን የጠጅ ጋን ነበር፡፡ የተኙትን እንዳልረብሽ ኮቴዬን አጥፍቼ ገብቼ ተኛሁ፡፡ እርካታን አግኝቻለሁ! ሰላማዊ እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡

መኝታ ክፍሌ በብርሀን ተሞልቷል! ሠዓቴን ተመለከትኩ!... ከረፋዱ አምስት ሰዓት ሆኗል፡፡ ቀጥታ ወደ እቃ ቤት አመራሁ፡፡ መቅዲ ሽንኩርት ትከትፋለች፡፡ ድስቶቹን ስከፋፍት ቂንጬ አገኘሁ፡፡ ያደረ አፌን በውሀ ካፀዳሁ በኋላ ድስቱን ይዤ ወደ ሣሎን ሄድኩ፡፡ ማህደር እና ትእግስት ፌስታል እንጠልጥለው ከውጪ ገቡ፡፡

«ቡና አፈላለሁ! ፏ ብለን ነው የምንውለው፡፡ መቅደስ ፈጠን በይ! ስጋውን ደግሞ እዳታደቂው፤ ጎረድ ጎረድ አድርገሽ አሪፍ ቀይ እና አልጫ ወጥ ስሪ፤ ደግሞ ቡናውን እጠቢልኝ፤ ቶሎ ቶሎ በይ!...» አለች ቲጂ ቂጠማ እየጎዘጎዘች፡፡ ትዕዛዙን አዥጎደጎደችው!

«እኔ ከስንተ ቦታ ልሁን?» መቅዲ አጉተመተመች፡፡ እውነቷን ነው!

«ቲጂ! እራስሽን ችለሽ ስሪ!» አልኳት፡፡

«ትላንናት ለሊት ወጥተሽ ነበር?» አለችኝ ማዱ፡፡

«ዘውዱ ጋር ሄጄ ነበር!»

«ዘውዱ የኔ?»

«አዎ!»

«ለምን?»

«ኤድስ ምናልባት ከደፈረኝ ልሞክረው ብዬ!»

«ያምሻል?» ቲጂ አፈጠጠችብኝ፡፡

«ኤድስ የያዛቸው ሰዎች በትክክል ምን እንደሚሰማቸው ለማወቅ ካለኝ ጉጉት አንፃር ነው ከዘውዱ ጋር የተጋደምኩት፡፡»

«እንደዚህ አይነት ድፍረት... ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም!» አለች ቲጂ፡፡

«ኤድስ! ማንንም ለመግደል ታጥቆ የተነሳ ደፋር ሰይጣን ነው፡፡ ስለዚህ አስቢበት!» አለችኝ ማዱ፡፡

በእርግጥ ኤድስን መዳፈር ጅልነት ነው!

«ግን ለኔ ሳትነግሪኝ እንዴት ሄድሽ?» ማዱ ምርመራ ጀመረች፡፡

«ተቀየምሽኝ እንዴ?» አልኳት ደንገጥ ብዬ፡፡

«በፍፁም!»

ብረት ድስቱን እቃ ቤት አድርሼ ስመለስ ያሸረጥኩት ፎጣ ወደቀ፡፡ ማህደር ጮኸች፡፡ «እራሱን የቻለ ጫካ! አትላጪውም እንዴ?» አለችኝ ቲጂ፡፡ «ቡዳ! ዝም ብለሽ ስራሽን ስሪ፡፡» አልኳት፡፡ «ስትወለጂም ነበረው እንዴ?» አለችኝ ማዱ፡፡ «በስነስርዓት ሽሩባ ይሰራል'ኮ! አብዲ ለምን አይላጭልሽም?» አለችኝ ቲጂ እየሳቀች፡፡ አሁንስ ይሄ አብዲ ፈረደበት፡፡ በቀን ስንቴ ስቅ ይለው ይሆን? «እኔም አብዲም እንላጭም!» አልኳቸው፡፡ «ለምን?» አሉ ሁለቱም፡፡ «ቅማንቿሮቻችን

የት ይደበቁ?» አልኳቸው፡፡ «እይ!... አያስጠላችሁም?» አለች ቲጂ እየቀፈፋት፡፡ «ጭገር የሌለው አደፍርስ አይመቸኝም!! ድንቅነሽም ብትሆን እራቁቷን የሆነች መስሎ ስለሚሰማኝ አላጫትም!! ሲጀመር የድንቅነሽ እና የአደፍርስ ውበት ጭገር ነው!!» አልኳቸው፡፡ «እኔ ከተፈጠርኩ ጀምሮ በቅሎብኝ አያውቅም፡፡» አለች ቲጂ፡፡ «ፈግፍጊው ምናልባት ይበቅልልሽ ይሆናል፡፡» አልኳት፡፡ «ኧረ እኔ አልፈልግም!» አለች እጇን እያወናጨፈች፡፡ «እኔ ካላጨሁት ደስ አይለኝም!» አለች ማዱ፡፡ ሁሉም ሰው ምርጫ ይለያያል!

«የምስራች ልንገራችሁ! ሄኒ አገባሻለሁ አለኝ!» አለች ማዱ፡፡

«እና ምን ያስደንቃል?» አልኳት፡፡

እውነቴን ነው ምን ያስደንቃል?

«በሽተኛ መሆኔን እያወቀ፣ ትበክለኛለች ብሎ ሳይፈራ፣ አግባኝ ስለው ምንም ሳያቅማማ አገባሻለሁ ማለቱ አያስደንቅሽም?» ማዱ ወገቧን ይዛ እስክስታ የምትወርድ ትመስል ነበረ፡፡

«እዩ ችግር አለባት! እንኳን ደስ አለሽ!» አለቻት ቲጂ፡፡

ማዱ በመልሱ በሽቃለች፡፡ ቲጂ አረንጓዴ ጥለት ያለው ረጅም የሀበሻ ቀሚሷን ለብሳ ቡና መቁላት ጀመረች፡፡ እኔ የነዋይ ደበበን ሙዚቃ ስከፍት ማህደር ያናደደችኝ መስሏት የአስቴር ከበደን ሙዚቃ ከፈተች፡፡ ይነጋል፣ ይመሻል፣ እኛ ግን ሁሌም ተመሳሳይ ነገር ነው የምናደርገው፣ እስከመቼ? ቲጂ ምን ታይቷት እንደሆነ አላውቅም፣

የቡና አፈላሏ ከወትሮው የተለየ ነው፡፡ የምሳ ወጪም የሸፈነችው እሷ ናት፡፡ ምሳ ከበላን በኋላ ማዱ ከእኔ ብር ተቀብላ ጫት ለማምጣት ወጣች፡፡

«መንቃራ!» አለች ቲጂ ማህደርን፡፡

«በእሳህ! ዝም ብለሽ ቡናሽን አፍይ!» አልኳት፡፡

«በእሳህ? አብዲ ገና ከክርስቶስም ጋር ያቆራርጥሻል!»

«እሱ ነው እንዴ ያስተማረኝ?»

«በፊትኮ ወላሂ እያልሽ ትምዪ ነበር፡፡»

«ታድያ ለምን በእሱ ታሳብቢያለሽ?»

«ላናድድሽ ፈልጌ! »

«አባዲን ለቀቀ!»

«እኔ እና ማርኮ መዘጋጃ ቤት ተፈራርመን ስንጨርስ፣ የእወቁልኝ ምሳ አዘጋጅተን፣ ትንሽ ሰው እንጠራለን ብዬ አስቢያለሁ፡፡ ምን ይመስልሻ?»

እንደሚያገባት እርግጠኛ ናት! ማርኮ እና ኡምቤርቶ ገርበብ ያለውን በር ከፍተው ገቡ፡፡ ቡናው የተዘጋጀው ለእነሱ መሆኑ ገባኝ፡፡ ማርኮ የቲጂን ቂጥ እየዳበሰ ከንፈሯን መጠጠው፡፡ ቂጥና ማርኮ! ኡምቤርቶ ከጎኔ ተቀምጦ «በጣም ናፈቅሽኝ!» አለኝ ሰማያዊ አይኖቹን ተክሎብኝ፡፡ ከንፈሩ ላይ በስሱ ሳምኩት፡፡ «እንዴት ነህ ማርኮ?» አልኩ፡፡ ከኡምቤርቶ ወሬ ለመሸሽ ስል እንጂ ደህንነቱ አሳስቦኝ አልነበረም፡፡

«ዴናነይ!» አለኝ በተኮላተፈ አማርኛ፡፡

«አማርኛ መናገር ጀመርክ?» አልኩት ተገርሜ፡፡

«አመረኛ ያውካል ኢኔ!» ደገመልኝ፡፡

«ቲጂ አንቺ ነሽ ያስተማርሽው?»

«ከየት አባቱ እንደለቃቀመው አጠይቂኝ፡፡»

«ቲጂ ጉና ኢተታል ቶሎ ከጂ ይኔ ኮንጆ!» አለ ማርኮ፡፡

«አንተስ?» አልኩት የኔን ደንገ፡፡

«እሱ ብዙ ነገር የሚያስተምሩ ብዙ ሴት ጓደኞች አሉት፡፡»

አለኝ በጆሮዬ፡፡

ነው?... ማዱ ሜቱን ይዛ መጣች፡፡ ለነሙቼ ተብሎ የተከፈተውን የሀምሳሉ ምትኬን ቪሲዲ እያየን ቡናውን ጠጥተን ጨረስን፡፡ ሜታችን በላስቲክ ታፍኖ እየጠበቀን ስለሆነ አምስታችንም ፍራሹ ላይ ተደረደርን። ኡምቤርቶን ሜቱን ቅመሰው ብለው እንቢ አለኝ፡፡ ማርኮ ተብዬ ቀልበ ቢስ ግን ሜቱም ሺሻውም አልቀረበትም፡፡ ነሙቼ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወሬ ሲጀምሩ፡፡ እኛም በቋንቋችን ስለተፈጠረው ስላልተፈጠረው እያወራን ሰዓቱን ገፋነው፡፡ ምርቃና ሲመጣ ነገር ማሠላሠል ልማዴ ነው፡፡ እገነባለሁ፤ እፈርሣለሁ፤ እተክላለሁ፤ እነቅላለሁ፡ ዞሬ ዞሬ ግን አብዲጋ እርፋለሁ፡፡ ምስሉን እያየሁ መደነቅ፣ መጨነቅ፤ መደሠት፤ መናደድ... አሀ... አብዲ!

ሜቱ አልቆ ሦስታችን ተጣጥበን እስክንለባብስ ድረስ የማርኮ እና የኡምቤርቶ ወሬ አልተቋረጠም፡፡ የሚያሙን ስለመሰለኝ፡ ኡምቤርቶን ጥፍር ቀለም ቀባኝ ብዬ፡ እጁን እየጐተትኩ መኝታ ክፍሌ ይዤው

ገባሁ፡፡ የተቀባሁትን ቀይ ጥፍር ቀለም አስለቅቆ ቀይ ቡኒ ጥፍር ቀለም ቀባኝ፡፡

«ይህን ቤት ለመግዛት ብትፈልጊ ስንት የሚሸጡት ይመስልሻል?» አለኝ፡፡

«700,000 ብር! ምነው? »

«እገዛልሻለሁ!»

ጆሮዬን አላመንኩትም፡፡ እገዛልሻለሁ? ለኔ ቤት? እኔ ቤት ሊኖረኝ? ህልም ነው እውን? እንባዬ ከትዕዛዜ ውጪ ፈሰሰ፡፡ ደረቱ ላይ ለጥፎ አባበለኝ፡፡ እሱስ ለእኔ ለምን መልካም ሆነ? ከተረጋጋሁ በኋላ ፊቴን ታጥቤ ሜካፕ በስሡ ተጠቀምኩ፡፡

ማርኮ ማዱን እና ቲጂን ይዞ ወደ ስቶኮልም ባር ቀድሞን ሄደ፡፡ እኔ እና በህይወቴ የመጀመሪያው የዋህ ወንድ ዘግየት ብለን ተከተልናቸው፡፡ ቀኑ ቅዳሜ ስለሆነ ቤቱ በሰው ጢም ብሎ ሞልቷል፡፡ ቦታ ይዘው ስለጠበቁን እንደ ሀውልት ከመገተር ድነናል፡፡ እራት እና መጠጡ እየተነጋጋ ቀረበልን፡፡ በልተን ስንጨርስ እኔ እና ጓደኞቼ ወደ መፀዳጃ ቤት ወረድን፡፡ እጃችንን ታጥበን ስንመለስ አይናችን ያልጠበቅነው ትእይንት ላይ አረፈ፡፡ ሄኖክ ጉንጪ ሊፈነዳ የደረሰ ጉራዳ እየደባበሰ ይሰብካል፡፡ ማዱ ረጋ ብላ ሰላምታ ሰጠቻቸው፡፡ ሄኖክ የማያውቃት ለማስመሰል ሞከረ፡፡ «ከማውቀው ሰው ጋር ተመሳስለህብኝ ነው!» ብላ ማዱ አስቀየሰች፡፡

ወደ ቦታችን ተመልሰን እኔ እና ቲጂ ከአሞራዎቻችን ጋር ስንሸካሸክ ማዱ አይኑን ከጣለባት ጉልማሣ ጋር ስትጠቃቀስ ቆይታ ተነስታ ወደ ቆመበት ሄደች፡፡ ቆመው ከሚጠጡት ወንዶች መሀል አይኔ አንድ ሰው ላይ አረፈ፡፡ ልቤ ግን ስራውን ሊያቆም ሠከንድ ብቻ ቀረው፡፡ አብዲ! የያዝኩት ቢራ የተሞላ ብርጭቆ ሊወድቅ ሲል ኡምቤርቶ እጅ ውስጥ ገባ፡፡ የስከርኩ ስለመሰለው ብርጭቆዬን አርቆ አስቀመጠው፡፡ አይኔን ድጋሚ ወደ አብዲ ላኩት፡፡ ከአይኖቹ ጋር ተጋጨ፡፡ አብዲ የተሰማውን ስሜት አላውቅም ወጥቶ ሄደ፡፡ ቲጂ ጠቀሰችኝ፡፡

አብዲ ሲጋራ እየሳበ ተመልሶ መጣ፡፡ ካልተናደደ በስተቀር ሲጋራ ማጨስ አይመቸውም፡፡ ስለዚህ...?! ቅጣቱን ለመቀበል በላዩ በላዩ የሚታዘዘውን ቢራ እየተጋትኩ፣ አብዲን እየሰረቅኩ አያለሁ፡፡ ኡምቤርቶን ማርኮ በወሬ ስለጠመደው ሁኔታዬን አላስተዋለም፡፡ ሰከርኩ! ስሠክር መማቅ ልማዴ ነውና እየሣቅኩ ቲጂ የምታወራልኝን ወሬ በቢራ አወራርዳለሁ፡፡ መመታቴ አይቀረ!... አብዲ እያየኝ የኡምቤርቶን ከንፈር ምጥጥ እያደረግኩ ፀጉሩን እዳብሣለሁ፡፡ ኡምቤርቶ ግለቱ እየጨመረ ስለመጣ እንሂድ አለኝ፡፡ አራታችንም ወደ አረፋብት ሆቴል ሄድን፡፡

ኡምቤርቶ ስካር ያደከመው ገላዬን፣ እንደ ለሚ እያሸ መጠጠው፡፡ እንደ ወትሮዬ መዝለል አልቻልኩም፡፡ ተጋደሜ ድንቅ ችሎታውን በደከመ እና የደስታ ሲቃ በተሞላው ድምጽ ገለጽኩለት፡፡ በበነገታው ከሠዓት በኋላ ቲጂ እና እኔ ወደ ቤት ተመለስን፡፡ ማህደርን ሳሎን ቁጭ ብላ ሲጋራ ስታጨስ አገኘናት፡፡

«አብዲ መጥቶ ነበረ?» አልኳት፡፡

«አይ!... አልመጣም!»

«የሄኒስ ጉዳይ? ከሰውየው ጋር አደርሽ እንዴ?»

«የቱ ሰውዬ? እ...አዎ አብሬው ነው ያደርኩት!»

ማህደር ከራሷ ጋር አይደለችም፡፡

«እናት!.... በቂጡ ሲያረገኝ እንደ አብድ እያደረገኝ የምይዘውን የምጨብጠውን አጣለሁ፡፡ እንዴት መሰላችሁ የሚጣፍጠው?!...» አለች ቲጂ፡፡

ማህደር እየተጣደፈች ቦርሳዋን አንጠልጥላ ወጥታ ሄደች፡፡

«የኔ ወሬ ደብሯት ነው? ወሬ አለባት! ኤሚዬ ማርኮን በጣም በጣም እየወደድኩት ነው!» ቲጂ ከሚገባው በላይ ተንቀልቅላለች፡፡

«እና ለዛ ነው የወሊድ መከላከያውን አልወጋም ያልሽው?»

«እሱን የሚመስል ልጅ መውለድ ስለፈለግኩ ነው!» ቀበጠች!

ማርኮ ኮንዶም መጠቀም አይወድም፡፡ የትም መልከስከስ ደግሞ ስራው ነው፡፡ ቲጂ ታምነዋለች! ካመነችው ኮንዶም አለመጠቀሙ ደንታ አይሰጣትም፡፡ መጨረሻዋ አሳሰበኝ! በየሦስት ወሩ የወሊድ መከላከያ መርፌ ስስታችንም እንወጋለን፡፡ በተጨማሪም እኔ እና ቲጂ የኤች አይ ቪ ምርመራ እናደርጋለን፡፡ እስካሁን ሁለታችንም ነፃ ነን!

«ሰሊ ወዶ አይደለም ለካ ቂጡን የተበሳው!» አለች ወይዘሮዋ፡፡

«አልገባኝም?» አልኳት ተገርሜ፡፡

«በቂጥ ማድረግ በጣም ነው የሚጣፍጠው!»

«በቃ አፍሽን ዝጊ!»

«ለወንድ ይደብራል! ለሴት ግን ጣጣ የለውም! ኤሚዬ!... ቅመሺውና ትተይዋለሽ!»

«ተቀምሶ የሚተው ነገር ቢሆን ማንም አይቀድመኝም ነበር!»

«አብዲ ጠይቆሽ አያውቅም?»

«ጠይቆኝ ያውቃል! ግን ሊፈትነኝ ነበር፡፡»

«ሲያስመስል ነው ባክሽ! ብትስጪው አይምርሽም! ኤሚ ግን ኡምቤርቶን አግብተሽ ከዚህ አመዳም ሀገር ለምን አትላቀቂም?»

«አባዲ አያሳዝንሽም?» አልኳት ላናድዳት፡፡

«ኃይማኖታችሁ የተለያየ፣ በዛ ላይ ዱላው፣ በዛ ላይ ንቀቱ፣ ምን ይሆን ያስነካሽ?»

አላውቅም!! አልጋዬ ላይ ተጋድመን ወሬ ስናቦካ ዋልን፡፡ መክሰስ ቢጤ ፍለጋ እቃ ቤት ገባን፡፡ ምስጋና ለመቅደስ... ሁለቴ ከመጉረሴ በሩ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ደነገጥን! ቲጂ የእቃ ቤቱን በር ዘግታብኝ ልትከፍት ሄደች፡፡ በሩ ላይ ጆሮዬን ለጠፍኩ፡፡ ኡምቤርቶ ሰላምታ ሲሰጣት ሰማሁ፡፡ «ተመስገን!» እጄን ታጥቤ ወደ ሳሎን ሄድኩ፡፡ ኡምቤርቶ የሚታዘለውን ቦርሣ አንጠልጥሎ ቆሟል፡፡ ሳምኩት! ቦርሣውን ከፍቶ ሰጠኝ፡፡ የመቶ ብር ኖቶች ቦርሳው ውስጥ ታጭቀዋል፡፡

«ምንድነው?» አልኩት ደንግጬ፡፡

«የቤቱ መግዣ!»

«ለእኔ?»

«የእውነት ብር ነው?» አለች ቲጂ ግራ ተጋብታ፡፡

ውስጤ ቀስ በቀስ መረበሽ ጀመረ፣ ጥሩነቱ አመመኝ፡፡ ልቤ በጥላቻ የተሞላ ፍቅር የማይበቅልበት በርሀ ነው፡፡ ኡምቤርቶን ልወደው ባለመቻሌ አዘንኩ፡፡ አለመቻል የሚባል በሽታ ተጠቂ ከሆንኩ ሰንብቻለው፡፡ ማፍቀር መቻል ለተሰጣቸው ነው! እኔ የዚህ ስጦታ ባለቤት አይደለሁም!! እራት ውጪ በልተን ወደ አረፈበት ሆቴል እንድንሄድ ፈልጎ ነበር፡፡ ብሬን ይወስዱብኛል ብዬ ስለፈራሁ እራት ውጪ በልተን ወደ ቤቴ ተመለስን፡፡

አልጋዬ ላይ መርፌ እና ክር ሆንን፡፡ ማርኮ ምን አባቱ ሆኖ እንደ ሆነ አላውቅም፡፡ ደውሎ ወደ ሆቴሉ ተመለስ አለው፡፡ ቅር እያለው ተሰናብቶኝ ወጥቶ ሄደ፡፡ ወንዶች ውሸታሞች ናቸው! ኡምቤርቶ እንደሚያፈቅረኝ በምን እርግጠኛ እሆናለው? ጥሩነት የፍቅር ውጤት ነው! ያፈቅረኛል ማለት ነው? ሲጀመር ፍቅር ምንድነው? እንቅልፌ መጣ፡፡

ጥዋት ከእንቅልፌ እንደነቃሁ ተጣጥቤ ወደ ቤተክርስትያን ሄድኩ፡፡ ቀዝቀዝ ያለ የጥዋት አየር አዲስ አበባን ከቧታል፡፡ የምን በአል እንዳለ ባላውቅም የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በሰውና በመኪና ተጨናንቋል፡፡ የደረስኩት ቅዳሴ ከገቡ በኋላ ስለነበር በር ላይ ተሳልሜ ተመለስኩ፡፡ ሠፈር ስደርስ ቲጂ ወደ እኔ እየሮጠች ስትመጣ አየኋት፡፡ ስስ የሌሊት ልብስ ስለለበሠች መንገደኛው ሁሉ እየገላመጣት ያልፋል፡፡

«ጉድሽ!...ጉድሽ!...» አለችኝ እጇን እያውለበለበች፡፡

ገንዘቤ ትውስ አለኝ! «ሌባ ነው?» አልኳት፡፡

«ገና አልታወቀም! ማርኮ ከሆስፒታል አሁን ገባን ብሎ ነው የደወለልኝ፡፡»

በረጅሙ ተነፈስኩ! ብሬ መስሎኝ ደንግጬ ነበር፡፡

«ኡምቤርቶን ፈነከቱት!»

ሐውልት ሆንኩ!

«አብረን እንሄዳለን እዚሁ ጠብቂኝ፡፡ ልብሴን ቀይሬ ለታክሲ ብር ይገኝ ልምጣ፡፡» ብላኝ እየሮጠች ሄደች፡፡

ቲጂ ተመልሳ እስክትመጣ ተንቆራጠጥኩ፡፡ ብር ይገኝ ቢሆን ኖሮ አልጠብቃትም ነበር፡፡ ልብሷን ቀይራ ብር ይዛ መጣች፡፡ ታክሲ ይዘን ወደ አረፈበት ሆቴል ሄድን፡፡ ሆቴሉ በር ላይ ላለው... ፍተሻ! ወዴት ነሽ? ማንሽ? ጊዜ አልነበረኝም፡፡ እየሮጥኩ ወደ ክፍሉ ገባሁ፡፡

ኡምቤርቶ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ላፕቶፑን ይነካካል፡፡ ለምን እንደሆነ ባላውቅም ሳየው ውስጤ ተረበሸብኝ፡፡ ያ ውብ ፀጉሩ በጉን በኩል ተላጭቶ ፋሻና ፕላስተር ተለጥፎበታል፡፡ አቅፌው አለቀስኩ፡፡ የሚከብድ ቁስል እንዳልሆነ ነግሮ አባበለኝ፡፡ ጭንቅላቱን በጠርሙስ፡ ጀርባው ላይ ደግሞ በዱላ፡ ከሙቱት በኋላ ሰው ሲመጣባቸው ትተውት እንደሄዱ ነገረኝ፡፡ ሌቦች ናቸው እንዳይባል ምንም አይነት እቃ አልወሰዱበትም፡፡ ግን ለምን? ድንገት ጉሮሮዬ ደረቀ፡፡ አብዲ ትዝ አለኝ! ኡምቤርቶ በእኔ ሰበብ ሊሞት ነበር፡፡ ይሄ የአብዲ ስራ ነው! እኔ ቲጂ ማርኮን መኝታ ክፍሉ ሄዳ ስላጣችው ወደ ቤት ተመለሰች፡፡ እኔ

ቀኑን ሙሉ ኡምቤርቶን ሳስታምም ውዬ ማታ ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡ አብዲ ጋር መደወልና መሣደብ ፈልጌ ነበር፡፡ ግን ፈራሁ፡፡ በእኔ ሰበብ ሺዎችን እንደሚያጠፉ ደጋግሞ ነግሮኝ ነበር፡፡ አልሰማሁትም! ይኸው በተግባር አሳየኝ፡፡ እራቴን ሣልበላ ጥቅልል ብዬ ተኛሁ፡፡

ጠዋት የኤች አይ ቪ ምርመራ እኔ እና ቲጂ ካደረግን በኋላ ስስታችንም የወሊድ መከላከያውን መርፌ ተወግተን ወደ ቤት ተመለስን፡፡ ቲጂ ሀሳቧን ቀይራ የወሊድ መከላከያውን መርፌ ለምን እንደወሰደች ፈጣሪ ይወቀው፡፡ መኝታ ክፍሌን ገርበብ አድርጌ ልብሴን አወላልቄ የምለብሰው የቤት ልብስ ሳማርጥ አብዲ ገብቶ በሩን ቆለፈው፡፡ ደነገጥኩ!

«ሸርሙጣ ነሽ!» አለኝ፡፡

«ቄሬ ነው ያወቅከው?»

በጥፊ መታኝ!

«አልሞተም አይደል? ሁለተኛ አንድላይ ልያችሁና እገለዋለሁ! ይህን የምትመኪበትን ገላሽን ደግሞ አይንሽ እያየ ተልትዬ ነው ደምሽን የምመጠው፡፡» አለኝ፡፡

ልብሴን ፈጠን ብዬ ለበስኩ፡፡

«ጓደኛሽን እያገላበጥኩ ስበዳት እንዳደርኩ አልነገረችሽም? ማህደርን በጳጷት!»

«ያለ ነው!» አልኩት ንዴቴን ለመደበቅ እየሞከርኩ፡፡

«ከሀዲ!» ብሎኝ ወጥቶ ሄደ።

«ኤምዬ ስለሰከርኩ ነው በጣም ይቅርታ።» አለችኝ ማህደር እየተርበተበተች። ቲጂ ገፍትራ አስወጥታት በሩን ዘጋችባት።

«ባለጌ ናት! እጋጣሚውን ተጠቅማ አብራው ታድራለች? አይዞሽ በቃ ጥርግ ይበል ኡምቢርቶ አለልሽ!» ቲጂ ያዘነችልኝ መሰለች።

«....ብቻዬን መሆን ስለምፈልግ አንቺም ውጪልኝ!» አልኳት ኮስተር ብዬ። ወጥታ ሄደች።

ማስታወሻዬ ላይ በሚያነባው ብዕሬ ንዴቴን ተወጣሁ። እኔ ድሮውንም ለሴት አዝናለሁ እንጂ ሴት አትሆነኝም። የማላደርግለት ነገር የለም፣ እሷ ግን... አብዲን... አላናግራትም። አይኗን ማየት አልፈልግም። በሬ ተንኳኳ። እሷ መስላኝ ፊቴን ኮሶ አስመስዬ በሩን ከፈትኩት። አዜብ ናት አብዲ ሡቁን ዘግቶ ቁልፉን እንደወሠደባት ነገረችኝ። ደሞዟን ሠጥቼ አሠናበትኳት።

አንድ ሲጋራ በደቂቃ ውስጥ ስቤ ጨረስኩ። ሁለተኛ ደገምኩ። በቅርቡ የለየልኝ አጫሽ እሆናለሁ። ቲጂ ጫት ገዝታ እንቃም ስትለኝ ወደ ሳሎን ሄድኩ። ትንሽ ምግብ ቀማምሰን ወደ ጫቱ ዞርን። ማህደር ከየት አባቷ እንደምትመጣ አላውቅም። እየተመናቀረች ከውጪ ገባች። የያዘችውን ጋዜጣ ለቲጂ ሰጥታት ወደ መኝታ ክፍላቸው ሄደች። የጋዜጣው የመጀመሪያ ገፅ ላይ የዘውዱ ፎቶ ጉብ ብሏል።

የዘውዱ ባርና ሬስቶራንት ባለቤት መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ተገለው ተገኙ፡፡ ገዳያቸው እስካሁን እንዳልተያዘ ፖሊስ አስታውቋል፡፡ ጉዳዩን የያዙት መርማሪ እንደሚናገሩት ከሆነ ወንጀሉ አሰቃቂና፣ እስካሁን ከተፈፀሙት ወንጀል ሁሉ ለየት ያለ ሲሆን፣ ወንጀለኛው አሻራውን ሳይተው፣ ዱካውን አጥፍቶ መሰወሩን ተናግረዋል፡፡ ሟች ከሰው ጋር የማይጋጩ ትሁትና፣ ለሰው አዛኝ እንደነበሩ ቤተሰቦቻቸው ገልፀው፣ ወንጀለኛውን ፖሊስ አድኖ እንዲይዝላቸው ተማፅነዋል፡፡ ወንጀለኛው ሟችን መርዝ አጠጥቶ ከገደላቸው በኋላ፣ ደረታቸው ላይ በስለት በትልቁ የራይት ምልክት አድርጎ፣ ግንባራቸው ላይ "ፍትሕን በራሴ" ብሎ በደማቸው መጻፉ፣ ወንጀሉን ምስጢራዊ አድርጎታል፡፡

ይላል ጋዜጣው!...

«ይህን ጆግና ባገኘው ውስጥ እግሩን እስምለት ነበር፡፡» አለች ማህደር፡፡

ፊት ስለነሳኋት ወደ መኝታ ክፍላቸው ተመለሰች፡፡

«ፍትሕን የተጠማ ሰው መሆን አለበት ይህን የፈፀመው፡፡» አለች ትጂ፡፡

«በምን አወቅሽ?» አልኳት ገርሞኝ፡፡

«ፍትሕን በራሴ! ማለት ምን ማለት ይመስልሃል?»

«የራሱ ጉዳይ አያገባኝም!»

«የኡምቤርቶም እጣ ፋንታ ሞት ነበር፡፡ የአብዲ ስራ እንደሆነ የማላውቅ መሰለሽ? አሁንም በዘውዱ ግድያ አብዲን እጠረጥረዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ከዘውዱ ጋር ተኝተሻል፡፡ የአብዲ አላማ ደግሞ ካንቺ ጋር የታየን የአዳም ዘር ማጥፋት ነው፡፡»

«ቲጂ አፍሽን ዝጊ!» እንባረቅኩባት፡፡ «ስለ ዘውዱ፣ ስለ አብዲ፣ ስለ ኡምቤርቶ አያገባኝም፡፡ አሁን ማሰብ ያለብኝ ስለራሴ ብቻ ነው፡፡» አልኩ አንገቴን ደፍቼ፡፡

«ልክ ነሽ! ከነማርኮ ጋር ባህርዳር ለምን አትሄጂም? ለትንሽ ቀን ከአብዲ አይን ብትርቂ የተሻለ ነው፡፡ እኔም አብሪያቸው ብሄድ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ግን የወር አበባዬ ከነገ ወዲያ ይመጣል፡፡» አለች ቲጂ አጤሬራ ያደረገችውን ሜት እያጎረሰችኝ፡፡

እኔ እና ማህደር መርፌውን ከጀመርን ጀምሮ የወር አበባ አይተን አናውቅም፡፡

«ሕጅሬ እንደሆነ አያማርጥ በጎረቤት ይጠቀማል አትቅሪ፡፡» አልኳት፡፡

«ባክሽ አልሄድም!»

ማርኮ እና ኡምቤርቶ ባህርዳርን ለመጎብኘት በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡ እኔ የቤቱን ጉዳይ መጨረስ ስላለብኝ የጉዞው አካል አለመሆኔን ቀደም ብዬ አሳውቂያለሁ፡፡ ሰዓቱ እንደ'ኛ ስራ ፈት ስላልሆነ እስቀምጠን ወደፊት ገሰገሰ፤ በወሬ ቅመም ያመነኘርግነውን ሜት ተፍተን ስፈራችን

ወደሚገኝ ባርና ሬስቶራንት አመራን፡፡ እራት በልተን፣ ሁለት ሁለት ቢራ ከልብሰን፣ ንፋስ እየተቀበልን፣ ቀስ ብለን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡ ማህደር ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ ሲጋራዋን እየማገች የወሲብ ፊልም ታያለች፡፡ ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁ፡፡ የገንዘቤን ደህንነት አረጋግጬ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ፡፡

አንዳንዴ የተኛሁበት ሰዓት እና የምነሳበት ሰዓት እየተመሳሰለብኝ ግራ እጋባለሁ፡፡ በደንብ ከነቃሁ በኋላ ነው ሁሉን ነገር ማገናዘብ የምችለው፡፡ ዛሬ ያገጠመኝ ይሄ ነው… ከእንቅልፌ የነቃሁት ከጥዋቱ እራት ሰአት ላይ ነው፡፡ የመሰለኝ ግን ከምሽቱ እራት ሰዓት ነበር፡፡ የኔ ነገር እንዲ እና እንዲያ ነው! ኡምቤርቶ ጋር ደውዬ ደህንነቱን ካረጋገጥኩ በኋላ ጀምሬ ያቋረጥኩትን ልብወለድ ሦስት ገፅ አንብቤለት ወደ መፀዳጃ ቤት ገባሁ፡፡ ከመፀዳጃ ቤት ስወጣ የምርትነሽ መዝሙር ተከፍቷል፡፡ እቃ ቤት ስገባ መቅደስ እየዘመረች ምሳ ትሰራለች፡፡

ለቁርሴ ዳቦ ገዝታ እንድትመጣ ልኬያት ቆም ብዬ የምርትነሽን መዝሙር አዳመጥኩት፡፡ በልጅነቴ የሰንበት ተማሪ ነበርኩ፡፡ መዝሙርም በጣም እወድ ነበር!… ነበር ከሆነ ዛሬ ያ ታሪክ የለም ማለት ነው፡፡ የመዝሙሩን ሲዲ አውጥቼ የዘሪቱ ከበደን ሲዲ ከተትኩ፡፡ መዝሙሩን ጠልቼው ሳይሆን፣ መዝሙር ሳዳምጥም ሆነ ስለ እግዚያብሔር ሲሰበክ ስሰማ፣ ሀጥያተኛ መሆኔ ጎልቶ ስለሚታየኝ ነው ከመንፈሳዊ ነገር እራሴን የማገለው፡፡ ቲጂ ድምፅ ጨምራ ከዘሪቱ ጋር መዝፈን ጀመረች፡፡

ለሌላ ሰው ፍቅር ልቤ አይከፈትም
እጎዳለሁ እንጂ ለማንም አልጠቅምም
ሰው ቀርቦ ለማቁሠል ምን አንቀዠቀዠኝ
ፍቅር ለእኔ እሡ ነው እሡም አልወደደኝ...

ቁርሴን በልቼ ሰሌ.ጋ ደወልኩ፡፡ ስልኩ ጥሪ አይቀበልም፡፡ ባል ተገኝቶልሀል የሚል መልዕክት ጽፌ ላኩለት፡፡ «እሱንም እንዳታስገድይው አርፈሽ ተቀመጪ፡፡ ካንቺ ጋር የታየ ወንድ እድሜ አይኖረውም፡፡» አለችኝ ቲጂ፡፡ ከእሷ ለመገላገል ሜት እና የሞባይል ካርድ ልግዛ ብዬ ወጣሁ፡፡

መንገድ ላይ ህፃን ልጅ አቅፋ የምትለምን ግንባሯ ላይ ንቅሳት ያለባት ወጣት አየሁ፡፡ ህፃኑ በጣም ያምራል! አዲስ ምጽዋተኛ መሆኑን በልብሱ ንጽህና አወቅኩ፡፡ በምድር ላይ ካሉ ውብ ነገሮች ሁሉ እንደ ህፃን ልጅ ልቤን የሚገዛው ነገር የለም፡፡ ልቀፈው አልኳት፡፡ ፈቀደችልኝ፡፡ አቅፌ አጫወትኩት፤ ፀጉሬን በትንንሽ እጆቹ ጨምድዶ ያዘው፡፡ እናቱ ቀስ ብላ አስለቀቀችልኝ፡፡ እጆቹን ሣምኳቸው፡፡ ለመከራ ወደዚች ዓለም ለምን እንዳመጣችው ጠየኳት፡፡

«ተቀጥሬ የምሠራበት ሰው ደፍሮኝ፣ እንዳረገዝኩ ሳውቅ፣ ለሚስቱ ለመንገር ፈርቼ፣ ለእሱ ስነግረው፣ ጐረምሳ አስገብታ አልጋችን ላይ ተኝታ አየኋት ብሎ ከቤቱ አባረረኝ፡፡»

የቤት ሰራተኞች ብሶት!

ሴቶች፣ ለሴቶች፣ እያሉ ባዶ ቃል በየሚድያው የሚያስተላልፉት ሰዎች የታሉ? የዘረጋችው ያደፈ የጨርቅ ቁራጭ ላይ ሁለት አስር ብር ጥዬላት ትንሹን አዳም ተሰናበትኩት፡፡ ጫትና የሞባይል ካርድ ገዝቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡

ቀኑ የምግብ ቀን ነው የተባልኩ ይመስል እንደገባሁ ምግብ አስቀርቤ ሆዴ እስኪወጠር ድረስ በላሁ፡፡ ለነገሩ የተሰራው ወጥ በጣም ይጣፍ ነበር፡፡ አብዲ ተብዬ ሰይጣን ደወለ፡፡ ቲጂ አንስታ ስታናግረው ዘጋባት፡፡ ደጋግሞ እየደወለ ሰላም ሲነሳኝ አነሳሁለት፡፡

«ለሰው የምታስነሽው አብዲ መሆኔን ዘንግተሽ ነው? ጥሩ! ለማንኛውም እቤት መጥተሽ ከዘበኛው የሱቁን ቁልፍ ውሰጂ፡፡» አለ፡፡

«ስለ መልካምነትህ ሳላመሰግንህ ማለፍ አልፈልግም፤ ቁልፉን ቀቅለህ ብላው፤ ደሞ ሁለተኛ እየደወልክ አትረብሸኝ፤ በእኔ ሰበብም ሰው ከመጉዳት ተቆጠብ፤ እኔ እና አንተ ከእንግዲህ ምንም የሚያገናኘን ነገር የለም፡፡»

ተናግሬ ሳልጨርስ ጆሮዬ ላይ ጠረቀመው፡፡

«እንቢ ካለ ለፖሊስ አመልክቺ!» የቲጂ ተልካሻ ምክር፡፡

ፖሊስ ጣቢያ የመመላለስ ሱስ የለብኝም!! ልክ ጫቱን ስፈታ ሰለሞን ከተፍ አለ፡፡ ዝንጥ ብሏል፡፡ መለያው የሚቀባው ሽቶ ነው፡፡ እቅፍ አድርጎ ሣመኝ፡፡

«ያ ከንፈራም ወጠጤ ጓደኛህስ?» አለችው ቲጂ፡፡

«ደህና ነው! ሰሞኑን ደብረ ዘይት አብረን ነበርን፡፡»

«በሰላም?» አልኩት፡፡

«ጦርነት ቢኖርማ አታገኙኝም ነበር፡፡»

እውነቱን ነው!

«በነገራችን ላይ አንዱ ፈረንጅ አግብቶ ውጪ ይዞኝ ሊሄድ ነው፡፡ የምናሳድገው ልጅም በጉዲፈቻ መልክ ይዘን እንሄዳለን፡፡ ስለዚህ ያገኘሽልኝን ባል ባለመቀበሌ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡» አለኝ፡፡ ቲጂ አማተበች፡፡

«የት አገኘኸው?» አልኩት፡፡

«የምሽት ክለብ ውስጥ ስደንስ አይቶኝ ተማረከብኝ፡፡ ከዛ አንድ ላይ አደርን፡፡ ከዛ....»

አቋረጥኩት!

«ኢትዮጵያኮ ግብረ ሰዶማውያን ይጋቡ የሚል ህግ አላወጣችም፡፡»

«አይጋቡ የሚል ህግም አላፀደቀችም!» አለ ሰለሞን እጁን እንደሴት እያወናጨፈ፡፡

መቅደስ አከራዬ ውጪ እንደሚጠብቁኝ ስትነግረኝ ፈጠን ብዬ ወጣሁ፡፡ አከራዬ ቤቱን ሽጡልኝ ስላቸው፣ ልጃቸውን ወደ አሜሪካ የሚልኩበት ወቅት በመሆኑ ጥያቄን በደስታ ተቀበሉት፡፡ ካርታውን በእኔ ስም ለማዛወር በተለይ ለእሳቸው በጣም ቀላል ስራ መሆኑን አበሰሩኝ፡፡ ከሰባት መቶ ሺህ ብር በታች ግን የማይደፈር መሆኑን ደጋግመው

ነገሩኝ፡፡ አከራይና ተከራይ ሳይሆን ገገርና ሻጭ ሆነን ተለያየን፡፡ ቲጂ ለባብሳ እየተጣደፈች ወጣች፡፡ እኔ እና ሰሌ ብቻችንን ቀረን፡፡ ሺሻ እየሳብን ከአረንጓዴው የቅጠሎች ንጉስ እየቀነጣጠብን ወደ አፋችን ከማድረግ አልቦዘንም፡፡

«ባሌ ከደወሉልኝ ትቹሽ ስለምሄድ ቅር እንዳትሰኚ!» አለኝ፡፡

«ይመችህ! የት ነው የተዋወቅካቸው?»

«ደግሞ ለሀይላይ እንዳትነግሪው! የሀይላይ አጐት ናቸው፡፡»

«ሀይላይ ጓደኛህ ሆኖ ከአጐቱ ጋር እንደምትወጣ አያውቅም?»

«አያውቅም! ባለስልጣን ስለሆኑ ስማቸው እንዳይጠፋ በድብቅ ነው የምንገናኘው፡፡»

«ትንሽ አይቀፍህም? እሳቸውስ ቢሆኑ?»

«አታካብጂ! እኔ ተመችተውኛል፡፡ ሳንቲም ደግሞ በደንብ ነው የሚያሸሩኝ፡፡»

«ከእኔ ጋር መኖር ትፈልጋለህ?»

«ጓደኞችሽስ?» አለኝ ቀስ ብሎ፡፡

«አስወጣቸዋለው!»

«ከአከራዬ ጭቅጭቅ ገላገልሽኝ!?»

«ማን የባልህን ስም ትነግረኛለህ!»

«..... በህልሜ እንኳ እምልጦኝ ብናገር እስር ቤት እንደሚወረውሩኝ ደጋግመው ነግረውኛል፡፡»

አጅሬ እድሚያቸው ረጅም ነው! ደወሉለት፡፡ ሳይሰናበተኝ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡ የቀረውን ጫት ብቻዬን ወረድኩበት፡፡ ምርቃና

ተቆጣጠረኝ! ንጉሱ ታምራት ያቀነቀነውን ምርጥ የአረመኛ ዘፈን ከፍቼ፣ ሳሎኑን ትርምስምሱን አውጥቼ ካፀዳሁ በኋላ፣ ገላዬን መታጠብ ጀመርኩ፡፡ እጄ መስመሩን እየሳተ የጡቴን ጫፍ እየነካ የሰውነቴን የሙቀት መጠን አዛባው፡፡ ዓይኖቼን ጨፍኜ አብዲን እያየሁ እጄን ጭኖቼ መሀል ወደ ሚገኘው ትኩሳት ላኩት፡፡ ወላፈኑ ተቀበለኝ፡፡ የመፀዳጃ ቤቱ በር ተንኳኳ፡፡ ከእውናዊ ህልሜ ነቃሁ፡፡ በንዴት በሩን በረገድኩት፡፡ ቲጂ ናት! ስልኬን ይዛለች፡፡ «ኡምቤርቶ ነው አናግሪው!» አለችኝ፡፡ በሩን ፊቷ ላይ ጠረቀምኩት፡፡ ገላዬን ለቅለቅ ብዬ ስወጣ ቲጂ ወገቧን ይዛ ትጠብቀኛለች፡፡ ጉንጯን ስሚያት ስልኩን ተቀበልኳት፡፡ ሊገርፈኝ የነበረው ምላሷ ኩምሽሽ አለ።

የመኝታ ቤቴን መስኮት መጋረጃ ሰብስቤ፣ ከመስታወቱ ባሻገር የምትታይኝን ጨረቃ ሰላምታ ሰጥቼ፣ ቀለል ያለ ልብስ ለበስኩ፣ ከንፈሬን ቫዝሊን በስሱ ተቀብቼ፣ ወደ ቶቶት ባህላዊ ምግብ ቤት ሄድኩ፤ ኡምቤርቶ ቀድሞኝ ደርሷል፡፡ የሙንቅላቱን ቁስል በኮፍያ ደብቆታል፡፡ አብዲ በቦታው ተገኝቶ ከሆነ ብዬ በአይኔ ፈለግኩት፡፡ የለም! ኡምቤርቶ ስስት በተላበሰ አስተያየት ተቀበለኝ፡፡ ለእሱ ቀዝቀዝ ያለ ቢራ ለእኔ የተለመደ ምርጫዬን ቀይ ወይን ከእራት ጋር አዘዝኩ፡፡ ማርኮ እና ሰለሞን እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ተቀመጥንበት መጡ፡፡

የት ተገናኙ? ለምን? ሰለሞን ባሌ ደወሉ ብሎ ለምን ዋሸኝ? ማርኮ እና ቲጂ ያላቸውን ግንኙነት ያውቃል ማለት ነው? እራሴን በጥያቄ አጣደፍኩት፡፡ የታዘዘው እራት እስኪመጣ ድረስ ሁለቱ ጠጅ አስመጥተው በአንድ ብርሌ መጠጣት ጀመሩ፡፡ ውስጡ የሚብላላው

ጥያቄ አፈትልኮ እንዳይወጣ ተጠንቅቄ ሞዋታቸውን እያዳመጥኩ የውሸት እገለፍጣለሁ፡፡ እራቱ ቀረበ፡፡ ሰለሞን ፈጠን ብሎ ማርኮን አጉረሰው፡፡ ማርኮም ብድሩን መለሰ፡፡ እጃኢባ! አፍላ ፍቅር ላይ ያሉ ጥንዶች ይመስላሉ፡፡ ድርጊታቸው ስላስጠላኝ እጄን በቆሎ እና በእንጀራ ተከቦ ወደ ቀረበው ክትፎ መስንዘር አስጠላኝ፡፡ በልቼ ነው የመጣሁት በሚል ሰበብ ከገበታው ሳልቋደስ ቀረሁ።

«አግብቶ ሊወስደኝ ነው ያልኩሽ ጉብል እሱ ነው!» ሰለሞን ቀጠለ.... «ነገ ወደ ባህርዳር ሆስታችንም እንሄዳለን፡፡»

ወንድን ያመነች ሴት...! አገባሻለሁ! አገባሀለሁ! የሚባል የጣሊያኖች መስተፋቅር ይኖር ይሆን? ቲጂ ብነግራት ታብዳለች፡፡ ስለዚህ በራሷ ጊዜ ትወቅ፡፡ ከሁለት ሰዓት በላይ ከተቀመጥን በኋላ ማርኮ የስሌን እጅ እየጎተተ ወጥቶ ሄደ፡፡ እኛም ትንሽ ቆይተን ወደ ቤቴ ተመለስን፡፡

እኔ እና ኡምቤርቶ የመኝታ ክፍሊን የተቆለፈ በር መክፈቻ ጊዜ አልነበረንም፡፡ ልብሱን እስኪያወልቅ ድረስ መጠበቅ አልቻልኩም፡፡ እሱም እንደዛው! ዚፑ የተከፈተ ሱሪ እና የተገለበ ቀሚስ ይዘን አንድ ሆንን፡፡ ...ግን አብዲ ጋር እንደነበርኩ አስታውሳለሁ!... አልጋው ላይ የምናደርጋቸው ትግሎች፣ ንክሻው፣ ቁጣው፣ ዱላው፣ እንደ ህልም ቁልጭ ብሎ ታየኝ፡፡ ኡምቤርቶ በሀይል ሲያቃስት ነበር ወደ እሱ የተመለስኩት፡፡

«የምበዳሽ እኔ! አንቺ የምትጠሪው አብዲን!» አለኝ፡፡

«ማነው አብዲ? ስለምን እንደምታወራ አላውቅም!» ተኮሳተርኩ፡፡

«ልክ ነሽ! ነገ መንገደኛ ስለሆንኩ መሄድ አለብኝ፡፡» ብሎ ወጥቶ ሄደ፡፡

አብዲ የሚባል ስም ከአፌ ወጣ? ወጣ? እኔ አላምንም! መኝታ ክፍሌን ከመከፈቴ ማህደር ገብ:ታ አልጋዬ ላይ ተጋደመች፡፡

«ውጪልኝ!» ጮሁኩባት፡፡

«ከአብዲ ጋር ስለተፈጠረው ነገር ይቅርታ! ያቺን ቀን መሠረዝ ብችል እሠርዝልሽ ነበር፤ ደግሞ ኡምቤርቶ እየጋለበሽ አብዲን መጥራትሽን አቁሚ፡፡» አለችኝ ረጋ ብላ፡፡

«ደሞ በር ላይ ተለጥፈሽ ማዳመጥ ጀመርሽ?»

«እንቅልፍ እንቢ አለኝ ከዛ...»

«አብዲጋ ሂጂ...!»

«እሱ የሆን ሴትን የሚስብ ማግኔት የተገጠመለት አባላች ፍጡር ነው! ስለዚህ...»

እውነት ነው! አብዲ ሴትን ለማንበርከክ የተፈጠረ ሰይጣናዊ ሰው ነው፡፡ በሩን ቆልፌ ጀርባዬን ሰጥቻት ተኛሁ፡፡ «በኮንዶም ያወጣኝ በሽተኛ መሆኔን ነግረሽው ነው?» አለችኝ፡፡ ዝምታ ወርቅ ነው! «ሄኖክ ምን እንዳለኝ ታውቂያለሽ? እወድሻለሁ ስልሽ በማመንሽ በጣም ስቄያለሁ፡፡ ምክንያቱም ሴትን የሚወድ ልብ አልፈጠረልኝም፡፡ እኔም እንዳንቺው የኤድስ በሽተኛ ነኝ አለኝና አረፈው፡፡ ታዲያ ወንድ ምኑ ይታመናል? እኔንኮ ሁለቴ ነው የገደሉኝ፡፡ እምላኬን ምን በድዬው ይሆን?» ማልቀስ ጀመረች፡፡

ብዙ ሴቶች ወንድ ሲበድላቸው የሚበሳጬት ወንድ እውነተኛ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ማህደር ፈጣሪዋን ስታማርር ከቆየች በኋላ እንቅልፍ ወሰዳት፡፡ እኔም ተከተሏት፡፡

ከለሊቱ አስር ሰዓት ላይ ከእንቅልፌ ባንኜ ተነሳሁ፡፡ ከዛ በኋላ እንቅልፍ የሚባል በአይኔ አልዞር አለኝ፡፡ መብራቱን አብርቼ የጀመርኩትን ልብወለድ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ በምንም አይነት መንገድ ሊገናኙ የማይችሉ ሰዎች ተፋቅረው አሳራቸውን ሲበሉ የሚያሳይ የፍቅር ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ አንብቤ ጨረስኩ፡፡ እየተፋቀሩ እሷ የሌላ ሆነች፡፡ እሱም የሌላ ሆነ፡፡ ይሄ ታዲያ ፍቅር ነው? ለነገሩ ፍቅር የሚባለው ነገር ያለው ክርስቶስ ጋር እንጂ ሰው ጋር አይደለም!

# ክፍል ሶስት

## ሴት ለሴት

ብርሀን ጨለማን ድል መንሳቱን በምሮች ዝማሬ ገለጸ፡፡ ቲጂና ማዱ ይለፈልፉሉ፡፡ ተሸፋፍኜ ተኛሁ፡፡ ማሀደር የአልጋ ልብሱን ጎትታ ወሰደችብኝ፡፡ ቲጂ ውሀ ይዛ ቆማለች፡፡ እየተነጫነጭኩ ተነሳሁ፡፡ ማዱ በቅመም ከተፈላ ወተት ጋር አሪፍ ቁርስ አዘጋጅታለች፡፡ መፀዳጃ ቤት ገብቼ እስከመጣ አጋምሰውት ጠበቁኝ፡፡ እኔም በተራዬ ቶሎ ቶሎ እየጎረስኩ አናደድኳቸው፡፡

«ዛሬ ፍል ውሀ መሄድ አምሮኛል!» አለች ቲጂ፡፡

«እኔ ደግሞ ረጅም ሰማያዊ ቀሚስ ለብሼ ብቻዬን በባዶ እግሬ ሀይቅ ዳር መጓዝ!...» አልኩ፡፡

«እኔ ግን የሀበሻ ቀሚስ ለብሼ ቡና ማፍላት ነው ያማረኝ፡፡» የማዱ ምኞት ፀደቀ!

ግሪክ በምትሰጣቸው የጡረታ ሳንቲም ኢትዮጲያ ውስጥ ዘና ብለው የሚኖሩ ግሪካዊ ሽማግሌ ቲጂን በጣም ነው የሚወዷት፤ እሷ ግን በመንገድ እንኳ ሲያልፉ ብታያቸው ትናደዳለች፡፡ ማርኮ ትቷት ቢሄድ በእሳቸው ትፅናናለች ብዬ ደውይላቸውና ያዳብሩን አልኳት፡፡ ፍቅር ከማርኮ ሌላ ሰው እንዳታይ ብሎኛል አለች፡፡ በትርፍ የሚንቀሳቀስ ነጋዴ አይከስርም! እንዴትስ ብዬ ስለማርኮ እና ሰለሞን ልንገራት?

የማዱ ቡና እስኪደርስ አልጋዬ ላይ የከረመውን እንሶላ ቀይሬ መኝታ ክፍሌን አፀዳሁ፡፡ ለብሼው ያደርኩትን ፒጃማ ወርውሬ የዓዳምን ዘር

የሚያማምል የሰውነት ቅርፄን በመስታወት እያየሁ ፈጣሪን አደንቃለሁ፡፡ መስታወቱ ሌላ ተጨማሪ ሰው አሳየኝ፡፡ አብዲ!... እራቃኔን ስሆን ሹክ የሚለው ሰይጣን አለ መሰለኝ ከየት እንደሚመጣ አላውቅም!... የወረወርኩትን ፒጃማ መልሼ ለበስኩ፡፡

«አሁንም ቢሆን እራቁትሽን ነሽ!... ሌላ ልብስ ብትለብሺ አይሻልሽም?» አለኝ ስሜትን በሚቀሰቅስ አስተያየት እያየኝ፡፡

«አይገባህም!»

«እርቃንሽን ካየሁሽ እንደምቀየር ስለምታውቂ ብዬ ነው፡፡»

ሌላ ቀሚስ ደረብኩበት!

«ፓንት አለማድረግሽን ግን አውቃለሁ! ስለዚህ....»

ዘልዬ ከንፈሩን ብጎርሰው ደስ ይለኝ ነበር! ግን...

«ምን ፍለጋ መጣህ?» ለመኮሳተር ሞከርኩ፡፡

«መልካም ልደት እንድትይኝ!»

ሥራው ከሀሣን አይሻልም፡፡ የሱቁን ቁልፍ አልጋው ላይ ወርውሮልኝ ወጥቶ ሄደ፡፡ ምን ባደርግ፡ እኔ እሱን፣ እሱ እኔን፡ ይተወኛል? ተመልሶ መጣ፡፡ ቆራጥ ባልሆንም መምሰል አለብኝ፡፡

«እኔ እና አንተ ከእንግዲህ...» መጨረስ አቃተኝ፡፡

«ጨርሺው!» አለኝ እጄን ይዞ፡፡

«ምንም አይነት ግንኙነት የለንም!» አምልጦኝ ነው፡፡

«ልደቴን በማስመልከት ማታ ቤቴ ውስጥ ዝግጅት አለ! ከጓደኞችሽ ጋር ተጋብዘሻል፡፡ ንፁህ እህቴ ነሽ!» ብሎኝ ወጥቶ ሄደ፡፡

ተንቆራጠጥኩ! አየር ለመሳብ ታገልኩ! ንፁህ እህቴ? እኔ ሳላውቅ ነው ምንም አይነት ግንኙነት የለንም ያልኩት! የቀልዴን ነው! አንዳንዴ የምናገረውን እንደማላውቅ እሱም ያውቃል! ቲጂ በሩ ላይ ተገትራ ከታዘበችኝ በኋላ አልጋዬ ላይ አስቀመጠችኝ፡፡

«ትወጂዋለሽ!... እም... ይወድሻል!...»

«ውጪልኝ!» አፈጠጥኩባት፡፡

«የማትወጂው ከሆነ ማታ ቤቱ እንሂዳለን!»

«አልሄድም!»

«ትወጅዋለሽ ማለት ነዋ!»

«እሄዳለሁ!»

ማህደር የሄለን በርሄን ዘፈን መዝፈን ጀመረች...

*ከማይህ ሲጨንቅህ ከማይህ ከማይህ ይቀረ የለ ወይ*
*ከማይህ አንተ የኔ ሠማይ ሠማይ ከፍቶህ እንዳላይ*
*ሠማይ ቅርብ እየመሠለኝ ሠማይ ልብህን ልነካ*
*ሠማይ እንደ ራሴው ጥላ ስጠጋ ትርቃለህ ለካ...*

ማህደር እኔን ለመንካት ወይም ለራሷ ነው የዘፈነችው፡፡ ምን አገባኝ? ቡናችንን አንቃረን እንደጨረስን ወደ ፀጉር ቤት ሄድን፡፡ ወረፋችን ሲደርስ የቆመ ፀጉራችን በነውያ ተለብልቦ አማረበት፡፡ የማዱን እና የእኔን ሂሳብ ከፈልኩ፡፡ ቲጂ የእራሷን ከፍላ ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡ መተጣጠብ መኳኳል ተጀመረ፡፡ ሠዓቱ አልሄድ አለኝ፡፡ አንዱን ስለከ ሳወልቅ ከቆየሁ በኋላ ከማህደር የገዛሁትን ቀሚስ ለበስኩ፡፡ ተረከዙ በጣም ረጅም የሆነ ቀይ ጫማ አጠለኩ፡፡ አብዱን ማሻፈድ መቻል

አለብኝ! የተቀባሁት ቀይ ሊፕስቲክ ደመቅ እንዲል ደግሜ ተቀባሁ። ያለኝን የሽቶ አይነት ልብሴ ላይ አርከፈከፍኩት። ቁምሳጥኔ ውስጥ የከረመ የወንድ ሽቶ አውጥቼ በእጄ ከያዝኩ በኋላ ጓደኞቼን አስከትዬ ከቤቴ ወጣሁ።

ሰማዩ ቢጠቁርም እድሜ ለጨረቃ ብርሀን ነግሶበታል። የአብዲ ግቢ በጓደኞቹ መኪና ተከቧል። የእሸር ዘፈን ከውጪ ተቀበለን። ሣሎኑ በጥንዶች እና በግሩፕ እየጠጡ በሚንሾካሾኩ ወጣቶች ተሞልቷል። አብዲን በአይኔ ፈለግኩት... የለም! መጠጥ ወደ ተደረደረበት ጠረጴዛ አመራን። ቲጂ እና ማዱ ውስኪ ቀዱ። እኔ ማቀዝቀዣው ውስጥ ቀዝቃዛ ቢራ አገኘሁ። አብዲን ከሆነች ቆንጆዬ ወጣት ጋር ከፎቅ ሲወርድ አየሁት። ከመኝታ ቤት መሆኑ ነው። ፊቴ በንዴት ተለዋወጠ።

«ተረጋጊ!» አለችኝ ቲጂ።

«የማስመሰል ጥበብሽ ተጠቀሚ!...» አለች ማዱ።

«ሰላም አመሻችሁ? ጓደኛዬ ናት ተዋወቋት። ሊዲያ ትባላለች። ሊዲያዬ ይቺ የሀገሬ ልጅ ናት ኤሚ ትባላለች። እናቴ ባትወልዳትም እህቴ ናት። እነዚህ ደግሞ ቲጂ እና ማዱ ይባላሉ ጓደኞቿ ናቸው።» አብዲ አነበነበ።

የውሸት ፈገግታ እያሳየሁ ሽቶውን ሠጠሁት።

«ሚኪ በቅርቡ ልደቱን ስለሚያከብር አበረክትለታለሁ።» አለ።

«የኔ ፍቅር መልስላትና እሷ ለሌላ ባለልደት ታበረክተው።» አለችው ሊዲያ ተብዬዋ።

ዮናስ በአይኑ ሲፈልገኝ አየሁት፡፡ ፈጠን ብዬ አጠገቡ ሄጄ ተጠመጠምኩበት፡፡ ጀርባዬን እያሻሸ አንገቴ ስር ሣመኝ፡፡ አይኔን ወደ አብዲ ወረወርኩ፡፡ እያየን ነው! ከማቀዝቀዣው ቀዝቃዛ ቢራ አውጥቼ ለዮናስ ሠጠሁት፡፡ ግርግዳው ላይ ደገፍ ብሎ፣ የግራ እግሩን ትንሿ ጠረጴዛ ላይ ሠቅሎ፣ መጠጣት ጀመረ፡፡ ቢራዬን ይዤ እግሩ መሀል ገብቼ ደረቱ ላይ ተለጠፍኩ፡፡ አብዲ ወደ እኛ መጣ፡፡

«ዮኒ እሱ ነው ባለልደቱ አብዲ ይባላል!» አልኩት፡፡

«ዮናስ እባላለው! መልካም ልደት!» አለ ዮኒ አንገቱን እየደበሰ፡፡

አብዲ በተራው ንዴት እያስተናገደ ነው፡፡ ሊዲያ የያዘችው መጠጥ ውስጥ ጣቷን ነክራ አብዲ አፍ ውስጥ ወተፈችው፡፡ ጣቷን መጠጠው፡፡ የማናት ፈጣጣ! አልኩ በሆዴ፡፡ በጥሬ ብላት እንዴት ደስ ይለኝ ነበር!!

«እንግዶች አስቀምጠን እልጋ ላይ እንውጣ?» አላት፡፡

«አሁን አይደል ከአልጋ የወረድነው እንደርስበታለን!» አለችው እየተቅበጠበጠች፡፡

«አብዲ ባልሳሳት የሙስሊም ስም ነው!» ዮኒ ጨዋታ ጀመረ፡፡

«አልተሳሳትክም!» አብዲ ኮራ አለ፡፡

«በጣም ብዙ ሙስሊም ጓደኞች አሉኝ፡፡ ከሙሀና ከወተት ውጪ ፈላሽ ነገር ብዙም አይሞክሩም፡፡ አንተ ስምህ እንጂ ሁኔታህ የሙስሊም አይደለም፡፡»

እኔ እና ሊዲያ አድማጮች ነን፡፡

«ክርስትና መጠጥ ይፈቅዳል እንዴ?» አብዲ ጠየቀ፡፡

«አይፈቅድም! ግን ሙስሊሞች ያከራሉ ብዬ ነው፡፡ በእኛም የሚያከሩ አሉ፡፡ በዛው ልክ ደግሞ ጠጥቶ ካልሰከረ ሠማይ የሚደፋበት የሚመስለው ደግሞ አይጠፋም፡፡» ዮኒ እስካሁን ደህና ነው!

«ችግሩ ከኃይማኖቱ ሳይሆን ከሰውየው ላይ ነው! በተለይ የሴት ስጋ የለበስ ሰይጣን ካጋጠመህ፣ ከኃይማኖትህም፣ ከራስህም፣ ሳትሆን ወድቀህ ትቀራለህ፡፡ ተጫወቱ!» ብሎ አብዲ ወደ ውጪ ወጣ፡፡

ሊዲያ ሚካኤል እና ጓደኞቹ ወደ ተሰበሰቡበት ሄደች፡፡ እኔ እና ዮኒ አብዲን ፍለጋ ወደ ውጪ ወጣን፡፡ አብዲ አይኑን ሰማዩ ላይ ተክሎ ተገትሯል፡፡ ንዴት ፊቱ ላይ ቤቱን ሰርቷል፡፡ በረንዳው ላይ የተሰበረ ብርጭቆ አየሁ፡፡ የአብዲ ስራ ነው! እኔን አያሳበረኝ እንጂ...

«እንግዳ አስቀምጠህ ውጪ መገተሩ አስፈለገ ነው?» አለው ዮኒ ትከሻውን ያዝ አድርጎ፡፡

«ትንሽ አየር ልውሰድ ብዬ ነው!» አብዶ ረጋ ብሎ መለሰ፡፡

«ሌላ የተጠራንበት ቦታ ስላለ እንሂድ!... ጓደኞችሽን ጠርቻቸው ልምጣ፡፡» ብሎ ዮናስ ወደ ውስጥ ገባ፡፡

አብዲ እንቅ አድርጎ ከንፈሬ ላይ ሳመኝ፡፡ መሸነፍ ካልፈለግኩ አልሸነፍም! ገፍትሬው ከግቢው ወጣሁ፡፡ ቲጂና ማዱ ስከረው ስለነበረ ዮኒ ደግፎ ይዟቸው መጣ፡፡ ዮኒ እኛን ቤት አድርሶን ተመለሰ፡፡

«እናንተ!... ያ ኢንጅነር ካላገኘሁሽ ሞቼ እገኛለሁ!... እያለኝ ነው፡፡ ላግኘው?» አለች ማ ዲር፡፡

«ባታገኚው ይሻላል! ወንዶች ተንኮል ሲያስቡ ነው ከጠፉ በኋላ የሚመጡት፡፡» አልኳት፡፡

«የአብዲን ከሌሎች ወንዶች ጋር ለምን ታያይዥዋለሽ?» አለች ቲጂ ሲጋራ እየለኮሰች፡፡

ውይ ምላሷ! ትንሽ ከቆየን ደግሞ ስለአብዲ እና ስለሊዲያ እያነሳች ታበሽቀኛለች፡፡ የለኮሰችውን ሲጋራ ተቀብያት መኝታ ክፍሊ ገባሁ፡፡ በሲጋራው ጭስ ተሳፍሬ አብዲ ጋር ሄድኩ፡፡ በእሱ ቤት እኔን ማስቀናቱ ነው? እኔማ ሰራሁለት! ወንድ እንደሆነ ሞልቷል! ሰውነቴን መጠጥ ደቁሶታል፡፡ ሲጋራዬም አለቀች፡፡ በሞባይሊ የትእግስት ፋንታሁንን ሙዚቃ ከፍቼ፣ ለማስታወሻዬ፣ አብዲ በልደት እሳቦ በቅናት ሲቆላኝ እንዳመሸ አጫወትኩት፣ ለነገሩ እኔም ብድሬን መልሻለሁ፡፡

ሂድ ብዬ ነበር ቆርጦልኛል ብዬ
አልቻልኩም ተመለስ ተረታሁ ሸግዬ
ሂድ ሲል እንደበቱ ቆይ ይላል አንጀቱ
ሂድ ሲል እንደበቱ ቆይ ይላል አንጀቱ
አልተስማሙልኝም ዳኙልኝ በሞቴ...

ትዕግስት ፋንታሁንን እወዳታለሁ፡፡ ግን ይህ ዘፈኗ ወስዶ አብዲ ጉያ ውስጥ ወሸቀኝ፡፡ ስለዚህ ሞባይሊ መጥፋት አለበት፡፡ በትራሴ ተደበቅኩ፡፡ ሰይጣን ስለሆነ አይኔንም ጨፍኜ ነብስ ዘርቶ ከጐኔ ተኝቶ እየዋለሁ፡፡ በሬ ተንኳኳ፡፡ ቀስ ብዬ ከፈትኩት፡፡ ማዱ ነች፡፡

«መጨረሻችን ምንድነው?» አለች አልጋዬ ወስጥ እየገባች፡፡

«መቃም፣ ማጨስ፣ መጨስ፣ መጠጣት፣ መስከር፣ መበዳት፣ መሞት!» አልኳት፡፡

«ቆይ ለምን አይወስደኝም? ቦርሣዬ ውስጥ ያለችው 50 ብር ብቻ ናት፡፡ ሁሌ ካንቺ እየወሰድኩስ እስከ መቼ?»

«ዝም በይና ተኚ!»

«ኡምቤርቶ ከአብዲ ጋር ያለሽን ግንኙነት ያውቃል፡፡ አብዲ እንዳስደበደበውም በደንብ ተነግሮታል፡፡ ቲጂ ለማርኮ ትተርክለታለች፡፡ ማርኮ ደግሞ ለኡምቤርቶ ያነበንብለታል፡፡»

የማህደር ድንገተኛ ወሬ ድንገተኛ በሽታ ለቀቀብኝ!

«ስለሚያፈቅርሽ ካንቺ መራቅ አይችልም! እሱ ተጉድቶ አንቺን ማስደሰት ነው የሚፈልገው፡፡ ይህንንም ለራሷ ለትእግስት ነግሯታል፡፡»

የሰው ማንነት እንዴት ነው የሚታወቀው? ሰው ለምን ይሆን በሰው እንቅልፍ የሚቀናው? ሰው ካለሰው መኖር ካልቻለ ለምን ጠላቱ ሆነ? ሴት ለሴት!... እንቅልፌ መጣና ነገር ከማብሰልሰል ተገላገልኩ፡፡

የዛሬው ጭጋጋማ ቀን ድብርት ለቆብኛል፡፡ ሠማዩ በደመና ተሸፍኖ ሠዓቱን ለመገመት ያስቸግራል፡፡ ከእንቅልፌ የነቃሁት ሞባይሌ ካልዋሸ ከጥዋቱ 2፡00 ሠዓት አናትዋ ላይ ነው፡፡ ቁርስ ከማታ የተረፈ የድስት ጥራጊ ነው ያገኘሁት፡፡ እኔ ገዛዘቼ ካልገባሁ፣ ቲጂ ካለ ትገለብጣለች፤ ከሌለ ወጣ ብላ ተልከስክሳ ትመጣለች፤ መጨቃጨቅ ስላልፈለግኩ ገዛዘቼ ልምጣ ብዬ ወጣሁ፡፡

ወደ ሱቁ ጐራ ብዬ ያለውን ብር ኪሴ ከትቼ የአዜብን ዘመድ እቃውን የሚረከበኝ ሰው እንድታፈላልግልኝ ነገርኳት። በዛውም አዜብ ከባሏ ጋር ታርቃ መኖር መጀመሯን ሰማሁ። አልደነቀኝም! «ልጄ ካለአባት እንዳያድግ ብዬ...» የሚል ፈሊጥ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን ያጠቃልና! ወደ አትክልት መሸጫው ጐራ ብዬ የተለያዩ አትክልቶችን ገዛዝቼ ወደ ቤቴ ስመለስ ማዱን ቆማ ታክሲ ስትጠብቅ አገኘኋት።

«የት ለመሄድ ነው?» አልኳት ቆጣ ብዬ። ምክንያቱም አብረን እንውላለን ብላኝ ነበር።

«ኢንጅነሩ ጨቅጭቆ ሊገለኝ ነው።»

«ማዱ አትሂጂ! በኋላ...»

አልሰማችኝም! ከኪሴ መቶ ብር አውጥቼ ሰጠኋት። ዓይኖቿ እምባ አቀረሩ። ትቻት መንገድ ጀመርኩ። እቤት ስገባ ቲጂ ሶፋው ላይ ተጋድማ ስልክ ታወራለች። የያዝኩትን እቃ ለመቅደስ ሰጥቼ፣ ቁምሳጥኔን ውስጥ ወደ ተቆለፈበት ገንዘብ ሄድኩ፤ ከቦታው አልተነቃነቀም። ከሱቅ ለቃቅሜ ያመጣሁትን ብር ቦርሣዬ ውስጥ ከትቼ፣ ዮናስጋ ደወልኩ፤ አከራዬ እዳና እገዳ እንደሌለባቸው ማጣራቱን ነገረኝ። ቀጣይ የሚሆነው ወደ ሚመለከተው አካል ሄዶ ካርታውን ወደ እምሮት ካንትይገኝ ማስቀየር ነው። ዮናስ ወደኔ እየመጣ ስለሆነ ፈጠን ብዬ ልብሴን ቀይሬ ቁምሳጥኔን ሲያሞቅ የከረመውን ገንዘብ ይዤ ከቤት ወጣሁ።

በአጠገቤ ያለፈ ሁሉ ሊባ እየመሰለኝ ስበረግግ ዮናስ መኪናውን ይዞ ከተፍ አለ። ከአከራዬ ጋር የተቀጣጠርንበት ቦታ ስንደርስ አከራዬ

ቀድመው በቦታው ተገኝተዋል፡፡ ከሳምንት በላይ ጊዜ የሚወስደውን ጉዳይ በሰላሳ ደቂቃ ውስጥ ጨረስን፡፡ ካርታው በኔ ስም ሆነ፡፡ ይሄ ሁሉ የሆነው የአከራዩ ጓደኛ ሀላፊ ሆነው መስሪቤቱን በማስተዳደራቸው ነው፡፡ የቤት ባለቤት ሆንኩ፡፡ ልቤ ኡምቤርቶጋ ሄደብኝ፡፡ ልቧ በጥላቻ የተሞላን ሴት አፍቅሮ በእሷ ደስታ የሚፅናና ሰው! ልዩ ሰው ነው! ከዮናስ ጋር ከሰው እይን ራቀ ያለ ሆቴል ገብተን ስንጠጣ ዋልን፡፡ የደስደስ መሆኑ ነው! ጨለምለም ሲል ቤቴ አድርሶኝ ተመለሰ፡፡

ቲጂ ቁጭ ብላ ሺሻ ትስባለች፡፡ እይኗን ማየት አስጠልቶኛል ሰላምታ ሳልሰጣት ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሌ አመራሁ፡፡ ልብሴን የቆምኩበት አወላልቄ ጠረኔን የምትናፍቀው አልጋዩ ውስጥ ገባሁ፡፡ እንቅልፍ ወዲያው ወሠደኝ፡፡

ማስታወሻዩ ይህን እንዴት መግለፅ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡ ጥዋት ከሰላማዊ እንቅልፌ ለይ የተለየሁት በተረገመ የስልክ ጥሪ ነው፡፡ የማላውቀው ቁጥር ስለሆነ ማንሳት አልፈለግኩም ነበር፡፡ ተደጋግሞ ሲደወል እንስቼ ጆሬዩ ላይ ለጠፍኩት፡፡ «ይቅርታ! ዶክተር ገበየሁ እባላለሁ! ማህደር የምትባል ታካሚ ናት ስልክሽን የሰጠችኝ፡፡» ሲለኝ ከተጋደምኩበት ተስፈንጥሬ ተነሳሁ፡፡ «ምኒሊክ ሆስፒታል ፈጠን ብለሽ ብትደርሺ መልካም ነው፡፡» ስልኩን ዘጋው፡፡ የምይዘው የምጨብጠው ጠፋኝ፡፡ ቲጂን ቀሰቀስኳት፡፡ «ስክራ ቱቦ ውስጥ ወድቃ ይሆናላ! ወይ ደግሞ መኪና ገጭቷት! ወይ ደግሞ... አላውቅም!» ብዙ ቀበጣጠርኩ፡፡ በኮንትራት ታክሲ እየበረርን ሚኒሊክ ሆስፒታል ደረስን፡፡ ወደ ዶክተር ገበየሁ ቢሮ ቀጠን ያለች ነርስ ይዛን ገባች፡፡

«ወዴት እያመራን እንደሆን አላውቅም! ማህደር አራተኛ ሴት ናት! ግን የእሷ በጣም የከፋ እና አሡቃቂ ነው፡፡» አለ ዶክተሩ፡፡

«አማጥረው!» አለችው ቲጂ፡፡

የእኔን አፍ የለጎመውን.... ፈጣሪ ይወቀው!

«አሲድ ተደፍቶባ...»

ዶክተሩ ተናግሮ ሳይጨርስ ቲጂ ጮኸች፡፡ የሆነ ነገር ከአካሌ ላይ ተቆርጦ የተወሰደብኝ መሰለኝ፡፡ ዶክተሩ ማዶ ወደ ተኛችበት ክፍል ይዞን ሄደ፡፡ ቲጂ የለቅሶ ውድድር ያለባት ትመስላለች፡፡ እኔ እንባ የሚባል ነገር ጠብ አላደረኩም፡፡ ማህደር ከወገቧ በላይ በፋሻ ተጠቅልላ ተጋድማለች፡፡ የአፍንጫዋ ቀዳዶች እና አፏ በፋሻ ከመጠቅለል ድነዋል፡፡ አይኖቿ ማረፊያ አጥተው ይቅበዘበዛሉ፡፡ ዶክተሩ ጩንቆት ወጥቶ ሄደ፡፡

«ኤሚ ተቃ... ጠልኩ... ልሽ! ተቃጠል..ኩ!... አቃጠለኝ!.. ኡፍ! እናቴ እህ... እህ!...» ትላለች አቅም ባነሰው ድምፅ፡፡

ስቃይ!

«ማዱዬ አይዞሽ!» አለቻት ቲጂ፡፡

«አሁንኮ ተሽ... ተሽሎኛል!»

«ማነው የደፋብሽ?» ቲጂ መልሷን ለመስማት የቋመጠች ትመስላለች፡፡

«አቃጠለኝ!... ተቃ...ጠልኩ... እ...እ... ተቃ... ተ... ቃጠ... የሆነ ቦታ እንሂድ ብሎ... ጭር... ጭር ያለ ቦታ ይዞኝ ሄ... ሄዶ ደ..ፋ..ብኝ! ኤሚ...ዬ ምነው ዘጋ.... ኡፈይ!»»

ደንዝዣለሁ! ማረፊያ ያጡ የማህደር አይኖች ጣራው ላይ ተተክለዋል፡፡ ማዱ እያየኋት ሞተች! ቲጂ ጮኸች!... ዶክተሩ ከሁለት ፖሊሶች ጋራ ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ፖሊሶቹ እየጎተቱ ውጪ በገተሯት የፖሊስ መኪና ጭነው ፖሊስ ጣቢያ አደረሱን፡፡ የጣቢያው ሀላፊ በጥያቄ አጣደፉን፡፡

«የተጣላችው ሰው አለ?»

«እንዴት ልናውቅ እንችላለን?»

«ጓደኛችሁ ስለሆነች!»

«ሚስጥሯን ለእኛ አትናገርም!»

«አስፈላጊ ከሆነ በድጋሚ ትመጣላችሁ!»

ቤታችን እስክንደርስ ድረስ እኔ እና ቲጂ አልተነጋገርንም፡፡ የሰው ልጅ ፈጣሪው የፃፈለትን መኖር ግዴታው ነው! ሴት ደግሞ አዳም የፃፈላትን የመኖር ተጨማሪ ግዴታ አለባት!

«አሲድ ነው የማስደፋበት!» ቲጂ ጥርሷን ነከሰች፡፡

«እሱ መሆኑ መች ተረጋገጠ?»

«እሱ ነው! ትእግስት አይደለሁም እንደ ሴት ካላስለቀስኩት፡፡»

ከቀኑ አስር ሠዓት ላይ ገላዬን ለቅለቅ ብዬ፣ ለባብሼና ተኳኩዬ ወጣሁ፡፡ የያዝኩት ታክሲ ቀርፋፋ ቢሆንም የፈለግኩት ቦታ ከመድረስ አላገደኝም፡፡ አላፊ አግዳሚውን ለማየት እንዲመቸኝ ፊት ለፊት ወዳለው ካፌ ጎራ ብዬ በረንዳ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ አስተናጋጅ እጁን ወደ ኋላ አጣምሮ ፈገግታውን ቸረኝ፡፡ እሱ ደስ ያለውን ነገር እንዲያመጣልኝ አዘዝኩት፡፡ ቀዝቃዛ ኮካ አመጣልኝ፡፡ አይኔ ፊት

አልከለከለኝም፤ ታክሲ መያዣው ድረስ ሸኘኝ፡፡ ሰፈሬ ስደርስ ሲጋራ ገዝቼ ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ ቲጂ መቃሚያ ፍራሽ ላይ ተጋድማለች፡፡ ቀብሯ ነገ ነው ብላ እህቷ ደውላለች፡፡ አትሄጂም'ንዴ አለችኝ፡፡ እንዳልሰማ ዝም አልኳት፡፡ ትንሽ እንጀራ ላይ ወጥ ጠብ አድርጌ መኝታ ክፍሌ ገባሁ፡፡ እራቴን ከቀመስኩ በኋላ አንድ ሲጋራ አጨስኩ፡፡ የቀረኝ እንቅልፍ ነው፡፡

ጠዋት እንቅልፌን ሳልጠግብ ነው ቲጂ የቀሰቀሰችኝ፡፡ ፊቴን በቀዝቃዛ ውሀ ደጋግሜ ነከርኩት፡፡ ትንሽ ለቀቅ አደረገኝ፡፡ ለለቅሶ ተዘቅዝቆ የሚለበስ ነጠላ ስለሌለኝ ጥቁር ሻርፔን አዘጋጀሁ፡፡ ቲጂ ጥቁር በጥቁር ለብሳ፣ ጠቆረ ያለ ጥለት የለው ነጠላ አዘቅዝቃ፣ ሳሎን ቁጭ ብላ ታለቅሳለች፡፡ መቅዲ ስትገባ ትእግስት የማጹን መሞት አረዳቻት፡፡ እሷም ለቅሶውን ተያያዘችው፡፡ የኔን እንባ የበላው ጅብ አልጮህ አለ፡፡

ሦስታችንም ቀብሯ ላይ ለመገኘት፣ ታክሲ ላይ ስንወጣ ስንወርድ ውለን የቀብር ስነስርአቱ የሚፈፀምበት ቤተክርስትያን ደረስን፡፡ ቆሜ ለመፀለይ ሞከርኩ፡፡ አልቻልኩም! ወደ ውጪ ወጣሁ፡፡ አብዲ መኪናው ውስጥ ቁጭ ብሎ ሞባይሉን ይነካካል፡፡ ቤተክርስቲያን መሰገድ መስሎት ወይስ...? ወደ ውስጥ ተመልሼ የአብዲን መምጣት ለቲጂ ስነግራት፣ ደውላ ማህደር መሞቷን እንዳሳወቀችው ነገረችኝ፡፡ ለቅሶ ከውጪ ተሰማኝ፡፡ ወደ በሩ አፈጠጥኩ፡፡

ማህደርን በሣጥን አሽገው አራት ወንዶች ተሸክመዋታል፡፡ ለቀስተኞች የሰንበት እንባ እየረጩ፥ አጅበዋታል፡፡ ይሄ ሁሉ ሰው በህይወት እያለች

ብላ ስጋዋን ለማንም ሴሰኛ ስትቸረችር ሲጠቃቀስባት የነበረ ሁሉ ዛሬ ደግሞ አፈር ሲበላት ለማየት የአዞ እንባ እያፈሰ እየረጨ መጣ:: እህቷስ ለምን ታለቅሳለች? እሷ መሰለችኝ ለሞት አሳልፋ የሰጠቻት:: አሀ! ገባኝ! ሰው ምን ይለኛል! ብላ ነው::

«ኧረ የሰው ያለ!... ኧረ የሴት ያለ!... ኧረ የነብስ ያለ!... ኧረ የአይን ያለ!... ኧረ የማህደር ያለ!... እህቴ እንደወጣች እንደተራራቅን ቀረን!... ኧይ...ኧይ» እያለች የማህደር እህት ደረቷን ትመታለች::

አብዲ ከለቀስቶኞቹ ጋር ተቀላቅሎ ወደ ግቢው ገብቷል:: ማህደር እስከ ወዲያኛው ተኝታለች! ፍትሀት ሲደረግላት አታይም! አትሰማም! ፍትሁቱ እንዳለቀ ወደ ጓሮ አዘገምን:: ማህደርን አፏን ለከፈተች መሬት ሲያጐርሷት ልቤ ከደረቴ ፈንቅሎ የሚወጣ እስኪመስለኝ ድረስ ምቱ ጨመረ:: እየሮጥኩ ከግቢው ወጣሁ:: ሰፈሬ መድረሴን ያወቅኩት የታክሲው ሹፌር ብር ጨምሪ እያለ ሻርፔን ሲጐትት ነው:: የያዝኩትን ብር እጁ ላይ ዘርግፌ ወደ ቤቴ ገባሁ:: ከረጅም ሰዓት በኋላ ቲጂ መጣች::

«ማዷ ላይ ቂም ይዘሽባታል ማለት ነው?» አፈጠጠችብኝ::

«ምን አድርጋኝ?» ደነገጥኩ!

«አብዲን ስላወጣችው ነዋ!»

ገፍትሬ ከክፍሌ አስወጥቻት፣ በሩን ወርውሬ ዘጋሁት:: አብዲ በሩን ከፈተው:: ኮሜዲኖዬ ላይ ተበላሽቶ የተቀመጠውን የትራስጌ መብራት እንስቼ ወረወርኩበት:: ጐንበስ ባይል ኖሮ ጭንቅላቱን አገኘው ነበር::

«አንተም እድሉን ብታገኝ እኔን ትገለኛለህ! ስለዚህ ለማህደር የዘንክ አታስመስል፡፡» አልኩት፡፡

ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ወጥቶ ሄደ፡፡ አለማልቀሴ ይሁን፣ ማህደር መሞቷ፣ እላዬ ላይ ያለውን ኃኔል ያናደደው ምን እንደሆነ አላውቅም፡፡ ባገኝ የሰው ስጋ በጥርሴ ብዘለዝል ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ልብሴን ቀይሬ እየበረርኩ ዮሴፍ ቤት ደረስኩ፡፡ ቤቱ ቁልፍ ነው፡፡ በሩን ለመክፈት ስታገል ትከሻዬ ላይ እጅ አረፈ፡፡ ዮሴፍ ነው! እቅፍ አድርጌ አንገቱ ስር ሳምኩት፡፡

«....ባለውለታዬ ነው ብድር መመለስ አለብኝ ብዬ ነው እየተጣደፍኩ የመጣሁት፡፡» አልኩት የውሸት ፈገግታ እየረጨሁ፡፡

«ውለታን የማይረሱ እንስቶች ይመቹኛል!» አለኝ ሣቅ ብሎ፡፡

መኝታ ክፍሉ ይዞኝ ገባ፡፡ ማህደር ላይ አሲድ የደፉ እጆች የኔን ልብስ ለማውለቅ ጥድፊያ ላይ ናቸው፡፡ አንገቱ ላይ ባለው የብር ሰንሰለት አንቄ ሲጥ ላደርገው ፈለግኩ፡፡ የሳሎኑ በር ተንኳኳ፡፡ ፊቱ በድንጋጤ አመድ ለበሰ፡፡ መኝታ ክፈሉን ዘግቶብኝ ሄደ፡፡ እኔም ደንግጫለሁ፡፡ አብዲ ቢሆንስ ብዬ በሩን በቀዳዳው ከፈትኩት፡፡ ቲጂ ሳሎኑ ውስጥ ተገትራለች፡፡

«አልፈልግሽም አልኩሽ! አይገባሽም?» አላት፡፡

«ውሻ ነህ!... ማህደር አሲድ ተደፍቶባት ሞተች!»

«አሲድ? ማ…ማ…ማነው የደፋባት?»

«የደፋባትን አንተን ልጠይቅህ?!»

«እ...እኔ በምን አውቃለሁ?»

«አሲድ ነው የምደፋባት ብለህ ስትዝት ውሽትህን መስሎኝ ነበር፡፡ ሴት እህት የለህም? ተቃጠልኩ እያለችኮ ነው የሞተችው፡፡»

እስካሁን ነገሩ ግራ እንደሆነብኝ ተገትሪያለሁ!

«ድምፅሽን ቀንሺ! አብራኝ የምትወጣው ኤድስ ልታስተላልፍብኝ እንደሆን የነገርሽኝ እንድሸልማት ነበር?»

ሴት ለሴት!

«ስንግዲህ እኔም ሴት እያደንኩ ከማህደር የተረከብኩትን የተበከለ ደም አወርሳለሁ!... ሴቶችን እበቀላለሁ!...»

«አንተ አረመኔ ጓደኛዬ ናት እኮ!»

ዮሴፍ ሳቀ! እንዴት አይሳቅ? አሳልፋ ከሰጠቻት በኋላ ጓደኛዬ ስትል እሷስ አታፍርም?

«የመሞቻዋን መንገድ አመቻችተሽ ከአፈር የቀላቀልሻት አንቺ?! አረመኔው እኔ ሳልሆን አንቺ ነሽ! እኔስ በቂሜ ስለገደለችኝ ነው የተበቀልኳት! አንቺን ምን አደረገችሽ? እኔን ስለነጠቀችሽ? እሷ እኮ አይደለችም የነጠቀችሽ! እኔ ነኝ አልፈልግም ያልኩሽ! ከሀዲ!»

ቲጂ ፊቱ ላይ ተፋችበት!

ገፍትሮ አስወጣት!

ምንም እንዳልሰማ ሰው በሞባይሉ ሙዚቃ ከፍቼ ቁጭ አልኩ፡፡ ገብቶ ከጐኔ ተቀመጠ፡፡ ፊቱ የተረበሸ ከተማ መስሏል፡፡ ለረጅም ሰዓት አቀርቅሮ በጫማው መሬቱን ሲደበድብ ቆየ፡፡ ምን እያሰበ ይሆን?

«አሁን የመጣችው የስራ ባልደረባዬ ናት! ሰርቼ ያላስረከብኩት ሥራ ስላለ መሄድ አለብኝ፡፡»

«ችግር የለውም ማታ እመጣለሁ!» አልኩት ፈጠን ብዬ፡፡

ተመልሼ ስመጣ የማዱ እጣ ቢደርሰኝስ? አምላኬ! ታክሲ አሳፍሮኝ ተመለሰ፡፡ ለሴቶች መበደል ሁሌ ወንዶችን እኮንናለሁ! ዛሬ ግን ለአንድ ሴት መጥፋት ተጠያቂው፣ ከወንድ ጀርባ የምትገኘው ሴት መሆኗን አረጋግጫለሁ፡፡

በተፈጥሮዬ አልቃሻ ነኝ፡፡ ችግሩ የሰው ልጅ ስቃዩ እንጂ ሞቱ አስለቀሶኝ አያውቅም፡፡ ሞት እረፍት ነው! ምድራዊ ስቃይ ግን ለሰው ልጅ ትልቁ እልህ አስጨራሽ ፈተና ነውና ያስለቅሰኛል! ማህደር ተቃጠልኩ እያለች ስታቃስት ግን አላለቀስኩም፡፡ ለምን? አላውቅም! እቤት ስገባ ትእግስት የለችም፡፡ መኝታ ክፍላቸው ገባሁ፡፡ ማህደር ምላሷን አውጥታ የተነሳችው ፎቶ የልብስ ማስቀመጫዋ ላይ ጉብ ብሏል፡፡ ደጋግሜ ፎቶዋን ሳምኩት፡፡ ልብሶቿን አሸተትኳቸው!... ተዘበራርቀዋል! አጣጥፌ አስቀመጥኩላት፡፡

ማታ ከበድ ያለ ቀጠሮ ከዮሴፍ ጋር ስላለብኝ መተጣጠብ መኳኳል አለብኝ፡፡ ከማህደር ገዳይ ጋር አሪፍ ምሽት ማሳለፍ እፈልጋለሁ፡፡ አብዲ ቢያየኝ ደግሞ የበለጠ አሪፍ ምሽት ይሆንልኛል፡፡ ለየት ያለ ቀጠሮ ሲኖረኝ የምለብሰውን ልብስ አዘጋጀሁ፡፡ ሠዓቱ እየተንቀራፈፈ የእኔ ልብ ምት ግን እየፈጠነ ነው፡፡ ስንቆራጠጥ አመሸሁ፡፡

ሰው መንገድ ላይ ውርውር የሚልበት ሠዓት አልፏል፡፡ ጨለማ ብርሀን የሆናችው ሰዎች ብቻ አልፎ አልፎ በእግርም በመኪናም ይታያሉ፡፡ ባለታክሲው የነዋይ ደበበን ሙዚቃ ከፍቶ እያንጐራጐረ ዮሴፍ ቤት አደረሰኝ፡፡ ዮሴፍ በረንዳው ላይ ይንቆራጠጣል፡፡ አልፌው ወደ ውስጥ ዘለቅኩ፡፡ እየሮጠ ተከትሎኝ ገባ፡፡

«አይንሽን ለምን ይሆን እንዲ የኳልሽው? ያስፈራል!» አለኝ፡፡

ዝም እንዲል ከንፈሩን ጐረስኩት፡፡ ጭኔ ስር ለመወተፍ ቾኮለ፡፡ ተረጋጋ!... ከቦርሳዬ ውስጥ ትልቁን ወይን መዘዝኩ፡፡ ብርጭቆ ፈጠን ብሎ አቅርቦ ወይኑን ከፈተው፡፡ ወይኑን ከነጠርሙሱ አንስቼ አፌ ውስጥ አንቆረቆርኩት፡፡ ልብሴን አውልቄ ወረወርኩት፡፡

«እርቃንሽ ስትሆኚ ደግሞ የበለጠ....»

«የሚበላ አላዘጋጀህም እንዴ?» አቋረጥኩት፡፡

ወደ እቃ ቤት ሮጠ! የሚጠጣበትን ብርጭቆ ይገፍ ተከተለኩት!

«ቁጭ በይ እኔ አቀራርባለሁ!» አለኝ፡፡

አደፍርሱን ጨበጥኩት፡፡ ምራቁን ዋጠ!

«ምላስህ እንዳይደርቅ ጠጣበት!»

ብርጭቆውን ሰጠሁት፡፡ ጭልጥ አደረገው! እንገቴ ስር ገባሁ!

«እራቱ ይቅር?» አለኝ እየተቅለሰለሰ፡፡

«መጀመርያ ጡቶቼን ጭመቅልኝ!.. አንገቴ ስር ገብተህ ንከሰኝ!... አንገላታኝ! ከዛ... እራት እንበላለን፡፡»

«እስከዛሬ ምን ውስጥ ተደብቀሽ ነው? እሣት እኮ ነሽ!»

«እውነት ነው!»

ወደ ሳሎን ተመለስን፡፡ ሶፋው ላይ በጀርባው ዘርሬው ተቀመጠኩበት፡፡ ሊገለብጠኝ ፈለገ፡፡ አልቻለም! አለመቻሉ ስሜቱን አቀዘቀዘው፡፡ ማዱ ብታየኝ ምን ትለኝ ይሆን? እርካታዬን ካገኘሁ በኋላ ጆሲን ተሰናብቼ ወደ ቤቴ ገሰገስኩ፡፡

......ቤቴ እንደገባሁ ልብሴን አወላልቄ በመስታወት እራሴን ተመለከትኩት፡፡ ጭኖቼን፣ ጡቶቼን፣ ትኩር ብዬ ተመለከትኳቸው፣ ዳበስኳቸው፡፡ ያማሣሉ! ግን የአብዲን እጆች ናፍቀዋል፡፡ «አብዲ ያስፈልገኛል!» እሱ ነው ለገላዬ ተስማሚው ሰው!... ደወልኩለት! አያነሳም! ይበልጥ አስፈለገኝ! ደግሜ ደወልኩለት አያነሳም!

ማስታወሻዬን ከኮሜዲኖዬ ውስጥ አውጥቼ ውሎ እና አዳሬን አንድም ሳላስቀር ፅፌ አስቀመጥኩ፡፡ እፎይታ ተሠማኝ! የሳሎኑ በር በሀይል ተንኳኳ፡፡ ወደ በሩ ሮጥኩ!... አብዲ ነው! ሲጠፋ መከራ፣ ሲመጣ መከራ፣ ተለጠፍኩበት፡፡ መኪናው ውስጥ እንደሚጠብቀኝ ነግሮኝ ሄደ፡፡ ልብስ ቀይሬ ተከተልኩት፡፡ አንድም ቃል ሳንተነፍስ የቴዲ አፍሮን ሙዚቃ እያደመጥን ቤቱ ደረስን፡፡ ልብሱን አወላልቆ አልጋው ላይ ተቀምጦ ላፕቶፑ ላይ አፈጠጠ፡፡

«ጉዳይ አለኝና አይንህን አውሰኝ! ተንሸራትቼ እንዳልወድቅ ከልብህ አስቀምጠኝ!...» አልኩት፡፡

«ዜማውስ?» አለኝ ላፕቶፑ ላይ እንዳቀረቀረ፡፡

«አብዲ! በጣም በጣም አስፈልጎኛል! በጣም!...»

«እኔ ደግሞ! በጣም በጣም.... አላስፈለገኝም! ደክሞኛል!...»

ላፕቶፑን ቀምቼው ራቅ አድርጌ አስቀመጥኩት፡፡ ለረጅም ሰዓት በዝምታ ተመለከተችኝ፡፡ ተጠጋሁት፡፡ ጎትቶ በጀርባዬ ከዘረረኝ በኋላ ጭኖቼ መሀል ገባ፡፡ ይሄን ነው የምፈልገው!

«ያንቺ ስቃይ እንዴት መስለሽ የሚያረካኝ?!»

«አስቃየኝና እርካታን አግኝ! ደስ እንዳለህ አሰቃየኝ!...»

አንገቴ ስር ነከሰኝ፡፡

«ኡምቤርቶን ልገለው ነበር! ትቃረሚያለሽ ብዬ ነው የተውኩት! ዛሬም ህይወቱ በእጅሽ ናት!»

ሰውነቴ ቀዘቀዘ!

«ቢቃሽኝ እስከልሽ ድረስ ከማንም ወንድ ጋር እንዳላይሽ! አይ ካልሽ... ብዙዎች በተለይ ደግሞ ኡምቤርቶ በእጄ ይጠፋል፡፡ እያንዳዷ እርምጃሽ በቁጥጥሬ ስር ናት፡፡ የት እንደምትውዪ ከማን ጋር አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ ተጠንቀቂ!...»

የተረገመ ቀን! ልብሴን ለብሼ ወደ ሳሎን ሄድኩ፡፡ ለረጅም ሰዓት ከተንቆራጠጥኩ በኋላ ወደ መኝታ ቤት ተመለስኩ፡፡ ፊቱን አዙሮ ተኝቷል፡፡ ኮቴዬን አጥፍቼ አልጋው ውስጥ ገባሁ፡፡ እቅፍ ጭምቅ አደረገኝ፡፡ የምገላበጥ መስዬ ከእቅፉ ለመውጣት ሞከርኩ፡፡ አልተሳካልኝም! የጋለ ገላዬን በነገር እቀዝቅዞ እንቅልፉን መለጠጥ ጀመረ፡፡ ጨከነኝ!

ጠዋት አብዷ ከእንቅልፉ ሳይነቃ ነበር ከቤቱ የወጣሁት፡፡ እቤቴ ስገባ የማህደር እህት ግልምጫ ተቀበለኝ፡፡ ትዕግስት በጥዋቱ ቱጭ ብላ ሸኝ ትስባለች፡፡ በሺሻ ጠርሙሱ ነበር ጭንቅላቷን መበርገድ፡፡ ከሀዲ!

«በሰላም የእህቴን ንብረት ልወስድ ነው የመጣሁት፡፡ ትንሽ ላንቲምም አንቺጋ ሳይኖራት አይቀርም፡፡ አይ አልሰጥም ካልሽ በፍርድ ቤት እንጨርሳለን፡፡» አለችኝ የማህደር እህት ወገቧን ይዛ፡፡

«ንብረት እንዳላት አልክድም! ግን ብክድሽ በምን ማስረጃ ለትከሺኝ ነው?» አልኳት ተገርሜ፡፡

«ትእግስት አለችልኝ! እሷ ባትኖርማ የልጅቷን ንብረት ጭጭ ልታደርጊው ነበር፡፡» ብላኝ እርፍ፡፡

የማህደር የሆነን እቃ ባጠቃላይ መቅደስ አውጥታ በረንዳ ላይ እንድታስቀምጥ ትዕዛዝ አስተላለፍኩ፡፡ ትዕግስት ደግሞ በአስቸኳይ ቤቴን ለቃ መውጣት እንዳለባት ነገርኳት፡፡ ነገ እኔንም እንደ ማህደር አሳልፋ ለጠላቴ ትሰጠኛለች፡፡ ትዕግስት የይሁዳ ታናሽ እህት ናት!

ከትእግስት ለመሸሸ የሱቁን ቁልፍ አንጠልጥዬ ወጣሁ፡፡ እንዲጋጣሚ ሆኖ የሱቁን እቃ የሚረከበኝ ሰው ተገኘልኝ፡፡ እቃውን አስረክቤ ብር ተቀበልኩ፡፡ ሱቁን አብዲ ይወስደብኛል፡፡ አይወስድብኝም፡፡ ከሚል ስጋት ነፃ ነኝ፡፡ ወደ ቤት ስመለስ ማተዝተዣው እና ሶፋው የለም፡፡ ያገለገለ እቃ ለሚሸጡ ነጋዴዎች ትእግስት እንደሸጠችው መቅደስ ነገረችኝ፡፡ በሰላም ልትለቅልኝ ነው ብዬ ተደስትኩ፡፡ በጥዋት የቀረበልኝ ቁርስ ነገር ስለነበር፤ የእንጀራ ረሀብ ተቆጣጥሮኛል፡፡ የቀረበልኝን የድርቆሽ ፍርፍር እምሽክ አድርጌ፣ ትኩስ የጠስኝ ሻይ ካለስኩበት፡፡

ሁሌም ቢሆን ውስጤ ሰላም ሲሰማውም ሆነ ሲከፋ በመሞነጫጨር ነው እፎይታን የማገኘው፡፡ ብዕሬን ጨበጥኩ፡፡ ትንትናዬን ከዛሬጋ እያዋዛሁ ብዕሬ በሚተፋው ቀለም ወረቀቴ ላይ አተምኩ፡፡ ዛሬ አልፎ ትላንትናዬ ሆነ እንጂ… ዛሬ የምለው ቀኔ ነበር፡፡ ለነገሩ እኔ ተጠያቂ አልሆንም፡፡ ዛሬን ትላንትና ያደረገው ጎረቤቱ ነገ ነውና! የአብዲን ድምፅ ስለሰማሁ ፈጠን ብዬ ማስታወሻዬን ትራሴ ስር ደብቄ የተኛሁ ለመምሰል ሞከርኩ፡፡

«ቂጥሽን ገልብጠሽ የተኛሽው እኔን ለማሻፈድ ነው?» አለኝ፡፡

«ምን ፍለጋ መጣህ ?» ተኮሳተርኩ፡፡

«አኩርፈሽ ነው በጥዋት ወደ ቤትሽ የተመለሽው?»

ልብሱን ማውለቅ ሲጀምር «ልትክሰኝ ነው?» አልኩት ደስ ብሎኝ፡፡

«አይደለም! እኔ መብዳት ስላማረኝ!» አለኝ፡፡

ምናለበት አዎ ቢለኝ? ጠማማ! በመርዛማ እጁ እየደባበሰ ሲስመኝ ቆይቶ በጥፊ ደረገመብኝ፡፡ ደንግጬ ለረጅም ሰዓት ከተመለከትኩት በኋላ አስር የሾሉ ጥፍሮቼን ወደ ፊቱ ላኩበት፡፡ መዳፉ ወስጥ ገቡ፡፡ አለቀስኩ፡፡ እንደገና አባብሎ በሚያስደስት ህመም ገደለኝ…! እንደገና በፈዋሽ መዳፉ እየጨመቀ ህይወትን ዘራብኝ…! አብዲ የሰይጣንን ጥበብ የሰረቀ ሰዋዊ ሰይጣን ነው፡፡ እየሸሸሁ የምቀርበው፤ ሳልፈልግ የምፈልገው፤ ሰይጣን ነው፡፡ ሁለት ስሜቶችን በአንዴ ማስተናገድ እንዴት ይከብዳል?

«አጃኢብ! በምግብ መልክ እንኳ ቢቀርብልሽ አትጠግቢም እኮ!»

«ምን?» አልኩት ግራ የተጋባሁ መስዬ፡፡

መለስ ሳይሰጠኝ ወደ መፀዳጃ ቤት ሄደ፡፡ ስለምን እንደሚያወራ ገብቶኛል! ገላውን ታጥቦ ያመጣውን ሸርጥ ከለበሰ በኋላ መቃሚያ ፈራሹ ላይ ተሰየመ፡፡ የእኔ ቆንጆ! ሸርጥም፣ ሱሪም፣ ሁሉም ነገር ያምርበታል! መቅደስ ምሳ አቀረበችልን፡፡ ሲለው እያንቋሸሸኝ፣ ደስ ሲለው ደግሞ እየሳመኝ ምሳችንን በላን፡፡ ምን ይሆን መጨረሻችን?

«ያረቢ!... አትበለን እንቢ!... ስሙረኝ ከዚች ሰላቢ!...» ብሎ አጤሬራ ያደረገውን ጫት አጎረሰኝ፡፡

ውስጡን ለምን ይከንክነው? «ሊድያ ማናት?» አልኩት፡፡

«የሚካኤል መደበርያ ናት!»

«ዮናስ ማነው? አትለኝም?»

«የአንትሽ ልጅ ነው! ሌላ ሰው ቢሆን እስከ አሁን በሰላም ቆየ?!»

አብዲ ስለእኔ የማያውቀው ምን አለ?

«ልክ ልኬን እስነገርሽኝ አይደል?! ለነገሩ ባንቺ የተነሳ ማን የማይናገረኝ አለ? አባቴ እንኳ እረግምሀለሁ እያለ እያስፈራራኝ ነው! ከአባቴም፣ ከአላህም፣ የተጣለሁት በአንቺ መሆኑን እንዳትዘነጊ፡፡» ማስጠንቀቂያ ይመስላል!

«ሰላት በመስገጃዬ ሰዓት ከአንቺ ጋር እማግጣለሁ! ከእስልምና ህግ ወጪ ሆኛለሁ! አባቴ በጣም አዝኖብኛል!»

ፊቱ ላይ ፀፀት አነበብኩ!

«የምታደርገው ነገር ስተት ከሆነ ለምን አትተወውም?»

«አልችልማ!»

ይሄ አለመቻል አብዲም ጋር አለ ለካ! እኔም እንደእሱ የሚረግመኝ አባት ባይኖረኝም፣ የፈጣሪን ሕግ መጣሴን አውቃለሁ!... ግን አለመቻል የሚሉት በሽታ ምርኮኛ ነኝ! በመሀላችን ለረጅም ሰዓት ፀጥታ ነገሰ፡፡ ፀጥታውን ለመስበር ስለጓደኛው ማውራት ጀመረ፡፡

«ኢንጅነር ነው! ከሀዲ ስለሆነ አላናግረውም!»

«ከሀዲዎችን ከምድር ላይ ማጥፋት ነው የሚሻለው!»

«ዛሬ ምን ተገኝና አነሳኸው?»

«ቤቱ ውስጥ ተገሎ መገኘቱን ፉአድ ደውሎ ነገረኝ!» ጣቀ፡፡

«ማን ይባላል?»

«ዮሴፍ ይባላል!... ዘውዱ የሚባለው ባለሆቴል ላይ የተፈፀመው አይነት ግድያ እንደተፈፀመበት ጋዜጦች ዕፈዋል፡፡ "ፍትሕን በራሴ" እያለ ነብስ ለቀማ የያዘው ወንጀለኛ ብልህ ነው፡፡ ወደ አንቺ እንዳይዞርና እድሜሽን እንዳያሳጥረው ጠንቀቅ በይ!» አለኝ አብዲ ትከሻዬን መታ መታ እያደረገ፡፡

መሳቅም፣ ማልቀስም፣ አማረኝ፣ ሳቄ ቀድሞ ለቅሶዬ ተከተለ፡፡ ለማዱ ደስታ አለቀስኩ፣ ለማዱ ስቃይ አለቀስኩ፣ ታፍኖ የነበረው እንባ እንደልቡ ፈሰሰ፡፡ አብዲ ደነገጠ!

«.... ውሀ እንደተጠማ ውሻ እያለከለካችሁ ትጋልቡንና በአሲድ ታጥቡናላችሁ፡፡ ያለምንም ርህረሄ አይናችንን ጎልጉላችሁ ታወጡና ስንደናበር ትሳለቁብናላችሁ፡፡»

«መንግስት ተገቢውን ቅጣት እየሰጣቸው ነው'ኮ!»

«የመንግስት ቅጣት የፈሰሰውን አይን ይመልሳል? ወይስ የማህደርን ነብስ? የማህደር ገዳይ ዮሴፍ መሆኑን ታውቃለህ?»

«እና የዮሴፍ መሞት ማህደርን ይመልሳል? አይመልስም! ለማንኛውም እኔ የሚያገባኝ ነገር የለም! እስቲ ዛሬ እንኳ በሰላም እንዋል?!»

እራስ ነብር ሆንኩ!

«አንተስ ብትሆን የእንዷን ነበስ ሳታጠፋ ትቀራለህ? እጅህ በደም የተጨማለቀ መሆኑን የምንግርህ ምንም ጥርጣሬ ውስጤ ሳይኖር ነው፡፡ መንግስት ከመሰረቱ ደህና ቅጣት ቢሰጣችሁ ኖሮ ድጋሚ ሴት ላይ እጃችሁን ባላነሳችሁ ነበር?!»

አብዲ ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ተነሳ!

«አንቺንም አርፈሽ ካልተቀመጥሽ ትሞቻለሽ!»

«እኔ ሞት አልፈራም!»

ሊናገረው የነበረውን ቃል ውጦ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ!

አዎ! አስገድደው ደፈሩ፣ ጡት ቆረጡ፣ አሲድ ደፉ፣ አይን አወጡ፣ ኧረ ስንቱ... ግን ቅጣቱ ያው ነው! ነገ ደግሞ ሌላ አይነት ወንጀል በሴቶች ላይ ይፈፀማል! ነገም ቅጣቱ ያው ከሆነ... ለማን አቤት ይባላል? ፍትሕ እናሰፍናለን የሚሉት የታሉ?... አው!... ሥራ በዝቶባቸዋል!!

# ክፍል አራት

## ክህደት

ጨለማ የዋጠው ሰማይ በከዋክብት አሸብርቋል፡፡ ሥራው ግሩም ነው! ንፋስ ለመቀበል ነበር ከቤቴ የወጣሁት፣ ተላካፊ እና ተሳዳቢ ሲበዛብኝ ወደ ቤቴ መመለስ ጀመርኩ፡፡ አይኔ እና ጆሮዬ መንገድ ላይ ባለው ትእይንት ተገርሟል፡፡ ሴት ተላካፊ ወንዶችን ያሳደገችው ከተማ ወንድ ተላካፊ ወንድ ማምረት የቅርብ ጊዜ ልማዷ ሆኗል፡፡ ጊዜና ትውልድ ተመራመርን እያሉ መጥፊያቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ ሰማይና ምድር ግን የፈጣሪያቸውን ትዕዛዝ እንደጠበቁ ይቀጥላሉ፡፡ እቤት ስገባ ትእግስት ፍራሹ ላይ ቁጭ ብላ ሺሻ ትስባለች፡፡ መቼ ቤቱን እንደምትለቅልኝ አላውቅም፡፡

«የማህደር ጠላት መገደሉን ሰማሽ?» አለችኝ፡፡

«እንደዛትሺው ገደልሽው?» ትንሽ ላስበርግጋት ብዬ ነው፡፡

«ዛትኩ እንጂ አልገደልኩትም!» አለች ዘና ብላ፡፡

«እሱን አንቆ እስር ቤት ለሚወረውርሽ ፖሊስ ትነግሪዋለሽ! ነብሰ ገዳይ! ሥራሽን የማላውቅ መሰለሽ?!»

ፊቷ አመድ ለበሰ! ክህደት ልብን የሚያደማ በሽታ መሆኑን የሚያውቁት የተካዱ ሰዎች ብቻ ናቸው! ገና በሰቀቀን ስጋዋን መጨረስ እፈልጋለሁ፡፡ ጎኔን ለማሳረፍ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ፡፡ እኔን ከሀሰብ ነፃ ለማድረግ ሀይሉን አጠራቅሞ የመጣው እንቅልፍ ተከመረብኝ፡፡

መቼም የሚነጋልኝ የረፋዱ ፀሀይ በመስኮቱ ገብታ ስትበጠብጠኝ ነው፡፡ ትዕግስት ያልታጠበ ፊቷን ይዛ አጠገቤ ተቀመጠች፡፡

«ዮሴፍን እንዲደበድቡልኝ ጎረምሶች አስከትዬ ወደ ቤቱ ስሄድ... ተገሎ አገኘሁት! ጎረምሶቹ እኔ የገደልኩት መሰላቸው፡፡ ፖሊስ ይጠቁሙብኛል ብዬ ስለፈራሁ አፋቸውን ለመዝጋት ያለኝን ገንዘብ በሙሉ ሰጠኋቸው፡፡ ስለዚህ ገንዘብ እስካገኝ ታገሺኝና ቤቱን አለቅልሻሁ፡፡» አለች እያለቀሰች፡፡

እሷን ማመን የዋህነት ሳይሆን ቂልነት ነው! ትእግስት ራስወዳድ ናት! ግን እኔ እንደእሷ አይደለሁምና «ግሪካዊውን ሽማግሌ ጠበቅ አድርገሽ ያዢ፡፡» አልኳት፡፡

«ማርኮ አልፈልጋትም ብሎሻል? ንገሪኝ!»

«አላውቅም!»

«ማርኮ እናቱን እና ልጇን...»

ልጇ? ትእግስት ልጅ አላት? አዲስ ወሬ ይዛ ብቅ አለች!

«.... ልጅ እንዳለኝ መደበቅ ፈልጌ ሳይሆን ልጁ የመጣበትን መንገድ ማስታወስና መናገር ስለሚያመኝ ነው፡፡» አለች፡፡ አላመንኳትም! ቀጠለች....

«አባቴ በልጅነቴ ነው የሞተው፤ ርሀብ ቆንጥጦ ነው ያሳደገኝ፤ እናቴ በየሰዉ ቤት እየዞረች እሻሮ በመቁላት በምታገኛት ሳንቲም ነበር እስከ አራተኛ ክፍል የተማርኩት፡፡ ግን ውዷ እናቴ የጠቀመችኝ

መስሏት አዲስ አበባ ለሚኖረው ወንድሟ እንዲያስተመረኝ አሳልፋ ሰጠችኝ፡፡ የአጎቴ ሚስት ገረዷ አደረገችኝ፡፡ ደብተሬን ዞር ብዬ አይቼው ስለማላውቅ ውጤቴ በጣም ዝቅተኛ ሆነ፡፡ ጓደኞቼ «ደደቧ!» የሚል ቅፅል ስም አወጡልኝ፡፡ የአጎቴ ልጅ ከቤት ውስጥ ገንዘብ በሰረቀ ቁጥር ሌባ ተብዬ የምገረፈው እኔ ነበርኩ፡፡ የኔ መከራ በዚህ ቢያበቃ ጥሩ ነበር!» አለቀሰች፡፡ ተረበሽኩ!

«ገረ..ምጎው የአጎቴ ልጅ… እናት አባቱ እራት ተጠርተው ወደ ጎረቤት ሲሄዱለት ትንሿ አልጋዬ ላይ ጋደም ብሎ ጠራኝ፡፡ ከጎኑ ቁጭ አልኩ፡፡ አፉ በመጠጥ ሽታ ከረፍቷል፡፡ ለሊት ተነስቼ እንጀራ ስለምጋግር መተኛት አለብኝና ከክፍሌ እንዲወጣ ተማፀንኩት፡፡ እሱ ግን ከእኔ ጋር ማደር አማረው፡፡ አልጋዋ እንኳን ለሁለት ሰው ለእኔም አትብቃኝም ነበር፡፡ መሬት ላይ አንጥፌ የምተኛበት አሮጌ ብርድልብስ ፍለጋ ሻንጣ ስከፋፍት ውዱ የአጎቴ ልጅ ሳላስበው ከንፈሬ ላይ ግጥም አድርጎ ሳመኝ፡፡ ደነገጥኩ! ይባስ ብሎ አፌን ግጥም አድርጎ ይዞ፣ ቀጫጭን እግሮቼን በርግዶ፣ ካለእድሜው በተሽከመው ቆለጥ ክብረ ንፅህናዬን ወሰደው፡፡ ከማልቀስ ውጪ ምን አደርጋለሁ? ምንም!» ትእግስት የዚህ ሁሉ መከራ ውጤት ናት ለካ!

«ሁሉም ነገር አስጠላኝ፡፡ ትምህርቱን ተውኩት፡፡ ቀናቶች በገፉ ቁጥር የእኔ የወር አበባ መምጫ ጊዜ ናፈቀኝ፡፡ እንጀራ ይሁን ውሀ ተጠራቅሞበት አላውቅም!... ሆዴ እያበጠ መላ ቅጡ ጠፍቶኝ እንቅልፍ አጥቼ ስንቆራጠጥ ቃመምኩና አልጋ ላይ ወደቅኩ፡፡ እንዳልሞት ፈርተው ሀኪም ቤት ወሰዱኝ፡፡ አንድ የተረገመች ዶክተር እርግዝና

እና ጭንቀት እንደደቆሡኝ አረዳችኝ፡፡ ልጃችሁ ነው! አልኩ፡፡ ስም በማጥፋት ወንጀል ባልና ሚስቱ ዱላ ፈረዱብኝ፡፡ ቅጣቴን ከጨረስኩ በኋላ የፈረደባት እናቴ ጋር ናዝሬት ተጣልኩ፡፡ የሰባ ሰባቱ ድርቅ የመታት ሆዷ የተቆዘረ አፅም ሆንኩ፡፡ ተወለደ ያለው እርጉም ፍጡር ተወለደ፡፡ እግዚአብሔር ደግ ነው! ከማንም ጐረምሣ ጋር ስትዘል የተባልኩት ሴትዮ የአትቴን ልጅ ድጋሚ ወለድኩት፡፡ አንቄ መግደል ፈልጌ ነበር... ግን አንጀቴ ተመቀኘኝ፡፡ እናቴ ተበድራና በእሣት እየተጠበሰች በምታመጣው ገንዘብ የበቆሎ ገንፎ በዘይት እያበላች አረሠችኝ፡፡ ጡቴ ወተት ስለሌለው ለዲቃላዬ ወተት ተከራየችለት፡፡ እናቴን ግን በሽታ እየመዘመዘብኝ ነበር፡፡ ልጁ ጠንክር ሲል የምጠላውን የወንድ ገላ እያሞቅኩ ገንዘብ ማምጣት ጀመርኩ፡፡»

ትእግስት አሳዘነች!

«ኤሚዬ!... ያገባ፣ የፈታ፣ ወጣት፣ ሽማግሌ፣ የሚቀረኝ የአዳም ዘር አልነበረም፡፡ እናቴም ሳትወድ በግዷ የማመጣውን ገንዘብ እየቀፈፋት ትቀበለኛለች፡፡ ከዛ ወዲህ ከፉ እና ራስወዳድ መሆን ተማርኩ፡፡ አዋጪም ነው! ማርኮ ያስፈልገኛል፡፡ አይደለም ቂጤን ሆዴን ቢበላው አልከፋም፡፡ የእኔ አላማ ገንዘብ አግኝቶ እናት እና ዲቃላዬን መርዳት ነው፡፡ ደግሞም ማርኮን እወደዋለሁ!..»

ወይ እወደዋለሁ?!... መውደድ እና ጥቅምኮ የማይጣጣሙ ነገሮች ናቸው! ከትላንቱ ይልቅ ነገ ይበልጥ እንዳይጐዳት ሰጋሁ፡፡ ትላንትና ትዝታ ሆኖ ቢያምም አልፏል፡፡ ነገ ግን ገና ያልታወቀ መከራ ተሸክሞ ነው የሚመጣው፡፡ ነገን ማን ይሆን የሚያውቀው? ነገን ለመዋጋት ማን

ይሆን ቀድሞ የታጠቀ? የትእግስት ነገ ባይታወቅም ጠረኑ አፍንጫዬ ስር እየተንከራተተ ነው፡፡ መቼም ትልቅ ችግር አለብኝ ያደረገችውን ሁሉ ወደ ኋላዬ ጥዬ ምሣ ልጋብዛት ለባብሰን ወደ ቦሌ ሄድን፡፡

……ቦሌ ድልድይ ስር ቆመጣቸውን እንጠልጥለው ወሬያቸውን የሚሰልቁትን ሁለት ፖሊሶች ሰራዊት እና ታደሰ ወደ እኛ ሲጠቁሟቸው አየሁ፡፡ ትእግስትም አይታቸው ደንግጣ በእኔ ተሸሸገች፡፡ ከመቅስፈት ስምንት እግሮች እየተክለፈለፉ አጠገባችን ደረሱ፡፡

«የሙት እምላክ ነው ዛሬ ያስያዛት!» አለ ሰራዊት፡፡

«ነብስ ገዳይ ናት!» አለ ታደሰ፡፡

ቅል አውራጁ ፖሊስ እጇን ጥርቅም አድርጎ ይዞ «ነገሩ ከበረደ በኋላ ከተወሸቅሽበት ጉሬ ተረስቷል ብለሽ ብቅ አልሽ፡፡ ግን ከፖሊስ የሚያመልጥ የለም፡፡ ቀጥይ!» አለኝ፡፡

አፈላልጎ የያዘኝ አይመስልም?

«መጥሪያ ስጠኝና ወደ ጣቢያ እሄዳለሁ! ፌስታል እይደለሁም ባንተ እጅ ተንጠልጥዬ በማላውቀው ነገር ጣቢያ የምሄደው፡፡» አልኩት ኮስተር ብዬ፡፡

«ቲቢኛ!» ታደሰ ሊበላኝ ደረሰ፡፡

«እናቱ በሰላም አብረን ወደ ጣቢያ ብንሄድ ለሁላችንም መልካም የሚሆን ይመስለኛል ስለዚህ ተባበሪን፡፡» አለኝ ሁለተኛው ፖሊስ፡፡

«የምን መለማመጥ ነው? ቀጥይ!» ብሎ እያ ቁመቴ ገፈተረኝ!

መንግስት ህግን አስከብርበት ብሎ የሰጠውን የደንብ ልብስ ጉልበት መሳያ የሚያደርግ የፖሊስ አባል በሀገሪቱ ማየት የተለመደ ነው፡፡ «እናቱ ተባበሪና!» ከተሜው ፖሊስ ጠቀሠኝ፡፡ የከበቡን ሰዎች የአፈር ያስበላሽ አስተያየት አመመኝ፡፡ «መቼስ ማልጎደኒ!» አለ የሀገሬ ሰው፡፡ በፖሊስ ታጅቤ ፖሊስ ጣቢያ ደረስኩ፡፡

የጣቢያው አዛዥ ቢሮ ነው ብለው ስለከ ጆሮው ላይ ደቅኖ የሚንሾካሾክ ፖሊስ ፊት ለፊት ጎልተውኝ ወጡ፡፡ የስልኩ ውይይት ከሌላ ጣቢያ አዛዥ ጋር ነው፡፡ ስለ አንድ ሀብታም እስረኛ መፍቻ ዘዴ እየተወያዩ ነው፡፡ ሲጠየቅ ምን መመለስ እንዳለበት እንዲነግረው እኔ ፊት የተጎለተው ለዛኛው ምክር ይለግሳል፡፡ ምን አድርጎ ይሆን የታሠረው? ምንም ያድርግ! ዋናው መፈታቱ ነው፡፡ ብሩ ደህና! ኧረ እነ እያ ጅቦም ደህና ይሁኑለት፡፡ በሠራው ወንጀል መቅጣት ሲገባቸው... እንዴት ከወንጀሉ ራሱን ነፃ ማውጣት እንደሚችል ተጨንቀው ይወያያሉ፡፡ ወንጀለኛውን ነፃ ለማውጣት ግዴት ንፁሁን ባልሰራው ስራ ወንጀለው ወህኒ ከወረወሩ በኋላ... በድሀ እንባ ታጥበው የሀብታም ኪስ ይቦጭቃሉ!... ማን ይሆን እነዚህን ተመቾች የሚያጠፋልን? የስልኩ ውይይት በአካል እንደሚቀጥል ተነጋግረው ስልኩ ተዘጋ፡፡

«ምን ልርዳሽ?» አለኝ ፈገግ ብሎ አዛዥ ተብዬው፡፡ ከንፈሩ እና ጥርሱ ሜት እና ሲጋራን ያሰድባሉ፡፡ የመጣሁበትን ምክንያት ተናገርኩ፡፡ «ሲያዩሽ እንኳን ሰው... ዝንብ!... አይም ትክብድሻለች!... ቁጫጭ መግደል የምትችይ አይመስለኝም፡፡» አለ እየገለፈጠ፡፡

«ለምን?»

«ሴት ስለሆንሽ ነዋ!»

ይህ ቃል ያመኛል!

«ለሺህ ወንድ ጉልበት የአንድ ሴት ብልሃት በቂ እንደሆነ ስነግርህ በኩራት ነው፡፡» አልኩት ፡፡

አልተዋጠለትም! ጭራሽ ፊቱን ኮሶ አስመስሎ ወንጀሉን ወደ ሚከታተለው መርማሪ ክፍል ይዞኝ ሄደ፡፡ መርማሪ ተብዬው ቁጭ ብሎ በሞባይሉ ሙዚቃ ያዳምጣል፡፡ አዛዡ ድንገት ስለመጣበት ደንግጦ ሞባይሉን አጥፍቶ ሰላምታ ሰጠ፡፡ አዛዡ እየተጀነነ «አምሮት ማለት እሷ ናት! » ብሎት ወጥቶ ሄደ፡፡

«እስኪ ፍትሕን በራሴ ብለሽ ፃፊልኝ!» ብሎ መርማሪው ወረቀት እና ብዕር ሰጠኝ፡፡

«ግንባር ላይ እና ወረቀት ላይ አንድ ይሆናል ብለህ ነው? ደግሞ እኮ ስለት በተፋው ደም የተጻፈ እንጂ....» ተናግሬ ሳልጨርስ አፈጠጠ፡፡ «አይዞህ ከጋዜጣ ላይ እንብበ ነው!» አልኩት፡፡

ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ደውል ተጫኑው፡፡ አንድ ፖሊስ በሩን ከፍቶ ገባ፡፡ «ዘበኛውን አምጣው!» አለው ኮስተር ብሎ፡፡ ፖሊስ ትዕዛዙን ተቀብሎ ወጥቶ ሄደ፡፡

«ዘውዱን ገድለሻል ተብለሽ ቢፈረድብሽ ምን ይሰማሻል?» አለኝ በፈገግታ፡፡

ፈገግታው የምርመራ ስልቱ ይሆን? ሚርቶኛ!

«ይህን ጥያቄ ከተፈረደብኝ በኋላ ጠይቀኝ!» አልኩት፡፡

የዘውዱ ዘበኛ ከፖሊሱ ጋር ገባ፡፡ የዘውዱን ገዳይ ዱካ ይጠቁሙናል ብለው በቁጥጥራቸው ስር እንዳዋሉት ገባኝ፡፡ ደስ የሚለው ነገር ግን ዘበኛው ጭራሽ አይቶኝ እንደማያውቅ ተናገረ፡፡ ፖሊሱ እየገፈተረ ወደ ማረፊያ ቤት ይዞት ሄደ፡፡ መርማሪ ተብዬው ሙሉ አድራሻዬን ወረቀት ላይ ካስፈረ በኋላ የጥያቄ መዓት ደረደረብኝ፡፡ የማውቀውን ተናገርኩ! ወዲያው የሞባይል ስልኩ መዝፈን ጀመረ፡፡ ስልኩን አንስቶ ካናገረ በኋላ ከተፈለግኩ ደውሎ እንደሚጠራኝ ነግሮኝ እንድሄድ ፈቀደልኝ፡፡ የገደለችው ሴት ነች ብለው ለምን እንዳሰቡ ጠየቅኩት፡፡ ጧች ከሴት ስር ስለማይጠፋ! መሆኑን ነገረኝ፡፡ ከሴት ጀርባ ወንድ ቢኖርስ?

«ወንጀለኛው በዘውዱ ነብስ ማጥፋት ብቻ አይደለም እየተፈለገ ያለው... በኢንጅነር ዮሴፍ ሞትም ተጠያቂ ነው!» አለኝ እያዛጋ፡፡ ...ቡና ወይስ እንቅልፍ?

ቲጂ ከመርማሪው ቢሮ ስወጣ ዘሳ ተጠመጠመችብኝ፡፡ ልብዋ በፍርሃት ይዘላል፡፡ ፖሊስ ጣቢያው አካባቢ ወደሚገኝ ሬስቶራንት ገብተን ምሳ በላን፡፡ የሚጃቹ አስከሬን ላይ ምንም አይነት አሻራ ስላላገኙ ወንጀለኛውን ለማግኘት እድላቸው ጠባብ ነው፡፡ ለዛም ይመስለኛል የለቀቁኝ! ግን ካለዋስ እንዴት ለቀቁኝ?

እቤቱ እንደገባሁ የመጀመሪያ ስራዬ የሆነው ገላዬን በቀዝቃዛ ውሀ መታጠብ ነበር፡፡ ቀዝቃዛ ውሀ ዘና ያደርገኛል፡፡ ማርኮ እና ኡምቤርቶ እንደሚመጡ ሳይናገሩ ድንገት ቤቱ ውስጥ ተገኝተዋል፡፡ ትእግስት ማርኮ ላይ ተጣብቃ አለቀሰች፡፡ በለቅሶም ከተሳካላት ተመስገን ነው! እኔ እና ኡምቤርቶ መኝታ ክፍሌ ገባን፡፡

«የኔ ፀሀይ! ምን ያህል እንደናፍቀሽኝ በምን ቋንቋ ልግለፅልሽ?» አለኝ ስማያዊ ዐይኑን ዐይኔ ላይ ተክሎ፡፡

«ዐይንህ ስለገፀልኝ አትጨናነቅ፡፡» አልኩት ፈገግ ብዬ፡፡

«ፈገግታሽ ምግቤ መሆኑንስ ዐይኔ አልነገረሽም?»

«እሱን አልነገረኝም!»

«ሁለመናሽ በሰውነቴ ላይ ሙቀትን እንደሚፈጥርስ ያንቺ ዐይን አልነገረሽም?»

«ለየት አልክብኝ!...»

«ናፍቆት ነው እንዲህ የሚያቅበጠብጠኝ!»

ናፍቆት እኔም ጋር ነበር! ግን አልነገርኩትም፡፡ ወደ እገሩ ለመሄድ 10 ቀን ብቻ ነው የቀረው፡፡ መንትያ ወንድሙ አልቤርቶ ቶሎ እንዲመለስ እየደወለ ይጨቀጭቀዋል፡፡ ኡምቤርቶ ግን እኔን ይዞ ካልሄደ መሄድ እንደማይፈልግ ደጋግሞ ነግሮኛል፡፡ ወደ እገሩ ካልሄደ ደግሞ በእሱ እና በወንድሙ ላይ ትልቅ ችግር እንደሚፈጠር አጫውቶኛል፡፡ የሚፈጠረው ችግር ምን እንደሆነ ግልፅ አድርጎ ባይነግረኝም ዘራቸው መረገሙን እና ከዘራቸው የተረፉት መንትያ ወንድሙ እና ያሳደገቻቸው አክስታቸው ብቻ እንደሆኑ አልደበቀኝም፡፡ ወደ እገሩ

ከተመለሰ ግን እርግማኑን ከወንድሙ ጋራ ሆነው መስበር እንደሚችሉ ሲነግረኝ ወደ አገሩ እንዲመለስ ተማፀንኩት፡፡

«አንቺን ካጣሁ መኖሬ ትርጉም አልባ ስለሆነ ልቤን አዳምጬ ዐይን ዐይንሽን እያየሁ መሞትን መርጫለሁ፡፡» ነበር መልሱ፡፡

አላመንኩትም! ልቡ ውስጥ ያለውን እውነት ማወቅ ይከብደኛል፡፡ ሰው የብዙ ጥበብ ባለቤት ነው፡፡ ልብን መመርመር ለሰይጣን እንኳ የተነፈገው ትልቅ ክህሎት ነው፡፡ እኔን ለማሳመን የፈጠረው ታሪክ ነው ብዬ አሰብኩት፡፡

ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ምግብ ስለሌለ ወደ ማታ ወጣ ብለን የአትክልት ሳንዱች ቀምሰን ወደ ቤት እንደተመለስን የምን እርግማን ቤተሰባቸውን እንደሚያምስ ደጋግሜ ብጠይቀው ሊነግረኝ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ይልቅ ስለወንድሙ ባህሪ አወራልኝ፡፡ አልቤርቶ ተብዬ መንትያ ወንድሙ ያመነበትን ነገር ከማድረግ ወደኋላ የማይል ቆራጥ እና ኩሩ ሰው መሆኑን አወቅኩ፡፡ አንድ ቀን አብሯው የተኛችን ሴት ደግሞ ማየት እንደማይፈልግ ኡምቤርቶ ሲነግረኝ መንትያ ወንድሙን ለማየት ጓጓሁ፡፡ በስንት ልመና የሚመጣው እንቅልፌ ዛሬ ሳልፈልገው ከች አለ፡፡

በኡምቤርቶ ታቅፎ ያደረው ገላዬ ላይ በተከፈተው መስኮት የሾለከው ብርሃን ሲያርፍበት አይኔን እያሸሁ ቀና አልኩ፡፡ ደስ የሚል የምግብ ሽታ ወደ አፍንጫዬ ዘለቀ፡፡ ገላዬን ለቅለቅ ብዬ ሳሎን ተቀመጥኩ፡፡

እ·ምቢርቶ በመረቅ የታጀበ የስጋ ጥብስ አቀረበልኝ፡፡ ስጋው ግንትሮበታል ግን ይጣፍጣል፡፡ ቁርሳችንን እየተጎራረስን በላን፡፡ ሽንኩርት አቃጥሎት፣ እያለቀስ፣ በለቅሶው እየተዝናናሁ፣ ምግቡን ለሁለት አዘጋጀን፡፡ ቲጂ ከማርኮ ጋር እንደወጣች አልተመለሰችም፡፡

እ·ምቤርቶ አብሮኝ ስለዋለ ተደስቻለሁ! ሳገኘው ነፃነት ይሰማኛል! የአገሬ የቡና አፈላላ ደስ ስለሚለው ላፍላለት ብዬ የቡና እቃ እንዲያቀራርብ አዝዤው ቡናውን ማጠብ ጀመርኩ፡፡ የታዘዘውን ትቶ ከጀርባዬ ቆሞ አንገቴ ስር ይስመኛል፡፡ እጁ ጡቴ ላይ አርፏል፡፡ ቡናውን የሚያሹት እጆቼ ስራቸውን አቆሙ! በወሲብ ባህር ለመዋኘት ልብሳችንን በጥድፊያ አወላልቀን ከባህሩ ገባን፡፡ ዋና ተጀመረ...

ስቃያዊ ደስታ!... ስቃዩን ወድጄዋለው!... ጭኖቼ መሀል ያለውን ህመም ይበልጥ ፈለግኩት፡፡ ወደ ኋላ ከመሸሽ ይልቅ ይበልጥ ደረቱ ላይ ተጣበኩ፡፡ የምሆነውን የማደርገውን አላውቅም!... ግን እፎይታን አገኘቻለሁ፡፡

«እባክሽ!... እባክሽ የኔ ፍቅር! የአብዲን ስም አትጥሪ፡፡ አውቃለሁ እንደምታፈቅሪው ግን ሞት እስኪለየን ድረስ አብጄን እርሺው!... ማለቴ ስሙን መስማት አልፈልግም!... እባክሽ!...» አለኝ፡፡

ደርቄ ቀረሁ! የአብዲን ስም ጠርቼ ነበር? በፍፁም አልጠራሁትም! አለመጥራቴንም አላስታውስም! ሳልፈልግ እ·ምቤርቶን እያስቀየምኩት ነው፡፡ ዐይኖቼ ያዘኑ ዐይኖቹን ማየት አልቻሉም፡፡ እንደተዘጋጋን የቆላሁትን ቡና ውቢ ወግጩ ስመለስ እ·ምቤርቶ ወለሉ ላይ

ተዘርሯል፡፡ ደነገጥኩ! ውሀ ደረቱ ላይ እያፈሰስኩ ብጠራው መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ ግራ ገባኝ!... ተጨንቄ እያገላበጥኩት፡፡ «ሰቀለድ ነው!» አለኝ እየሳቀ፡፡ በጆጉ ውስጥ ያለውን ውሀ ፊቱ ላይ ገለበጥኩት፡፡

«ትወጅኛለሽ? ውስጤ ልብዋ ውስጥ ትንሽ ቦታ አግኝተሀል ይለኛል!... ለዛም ነው ተስፋ የማልቆርጠው! ለነገሩ እውነተኛ አፍቃሪ ተስፋ አይቆርጥም!... ፍቅር 'ራሱ ተስፋ ነው!!» አለኝ፡፡

እውነት ልቤ ውስጥ ትንሽ ቦታ አግኝቶ ይሆን? አይ... አይ... የምን ቦታ? ሆ! የምን መዘባረቅ ነው? ታድያ ለምን አልተወውምና ወደ አብዲ አልሄድም? ገንዘቡስ? ውለታውስ? ቀጠን ያለ ቡና አንዳንድ ስኒ ጠጣን፡፡

እትዬ ትእግስት የሳሎኑን በር በረግዳ ገባች፡፡ በእንባ የታጠበው ፊቷ ጥቁር ብሏል፡፡ ማርኮ አሳገባሽም እንዳላት ገባኝ፡፡ የኔው በግ እንባዋን እየጠረገላት ሌላ ማግባት እንደምትችል ነገራት፡፡ ቤት ልጅ በቂዋ የሚበዳትን ወንድ ለመለየት በጣም ይከብዳታል የሚባል ወሬ አለ!.. ይኸው ጓደኛዬ የቂጧን ህግ የወሰደውን ሰው አፍቅራ እያለቀሰች ነው፡፡ ሽማግሌውን ጠበቅ ብታደርጋቸው ኑሮዋን መምራት የምትችል ይመስልኛል! እሳቸውንም ካላገቡ ወይ ካልሞቱ ነው የምታገኛቸው፡፡

«ኡምቤርቶ! እባክህ ንገረው አፈቅረዋለሁ!» አለች ቲጂ፡፡
«እነግረዋለሁ!... ግን ውሳኔውን ማስቀየር አልችልም!» አላት፡፡
«የምርሽን ነው ፍቅር ምናምን የምትይው?» አልኳት አባቅቼ፡፡
«የምርሽን ነው ፍቅር ምንም ምን የምትይው?» አልኳት አባቅቼ፡፡
«ያልቆሠለ ስለቁስል ቢያወሩለት መች ይገባዋል?!...»

ትእግስት እና ኡምቤርቶ ፍቅር እንዴት እንደሚያደርግ እየተቀባበሉ ማውራት ሲጀምሩ ትቻቸው ወደ ውጪ ወጣሁ፡፡ ትንሽ ቆይቼ ወደ ውስጥ ስገባ ኡምቤርቶ አልጋዬ ላይ ጋደም ብሎ ማስታወሻዬን ያገላብጣል፡፡ ቀምቼው ኮሜድኖዬ ውስጥ ቆለፍኩበት፡፡ አማርኛ ማንበብ እንደማይችል እያወቅኩ ምን እንዳስደነገጠኝ አላውቅም፡፡ ከጀርባው ተቀምጬ፣ ጣቶቼን ውብ ፀጉሩ ውስጥ ሽጉጬ፣ ማርመስመስ ጀመርኩ፣ የተፈነከተበት ቦታ ጠባሳ ሆኗል፡፡ የኔ ውጤት ነው! አብዲ የሚባል ሰይጣን ድጋሚ ይተናኮለዋል ብዬ ፈራሁ፡፡

«ምን እያሰብሽ ነው?» አለ እንጋጦ እየተመለከተኝ፡፡

«ስለ አንተ!»

«ስለ እኔ ምን?»

«ስለ አንተ… ስለ አንተ… መልካምነት!»

«ኦ! እኔ መልካም ሰው አይደለሁም!»

«መልካምነትህን በበጎ ነገር መመለስ ባለመቻሌ ደግሞ ወስጤ ታሟል!»

«በማደርገው ነገር ደስተኛ ነኝ! ካንቺም ምንም ነገር አልጠብቅም!» ግንባሬን ሳመኝ፡፡

ቲጂ ከማበዷ በፊት ማርኮን ደውሎ እንዲጠራላት ለመንኩት፡፡ ኡምቤርቶ መልስ ሳይሰጠኝ ስልኩን ይዞ ወደ ውጪ ወጣ፡፡ ቲጂ ያግባኝ ያፍቅረኝን ትታ እስኪሄድ ድረስ ብትጠቀምበት ጥሩ ነበር፡፡ እሷ ግን… እራት ከማርኮ ጋር መሆናችንን ኡምቤርቶ ሲናገር ቲጂ በደስታ ሰከረች፡፡ በናፍቆት እቃጠላታለሁ እንጂ በአማላጅ

አላደርገውም፡፡ ቀለል ያለ የእራት ልብስ ከለበስኩ በኋላ በመስኮት የሚታየኝ ጥቁሩ መከደኛ ላይ ተራርቀው የሰፈሩትን ከዋክብት መመልከት ጀመርኩ፡፡ ምን ሀሳብ አለባቸው? በእነሱ ዐለም ሞት የለ! መቀበር የለ! አላቸው እንዴ? ሳይንስ ብዙ ስለሚቀባጥር እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይከብዳል፡፡

ቲጂ አለባበሷ ያምር ነበር የሜካፕ ነገር ግን... ሳታስለቅቀው መናገሩ አፍ ማድከም ነው፡፡ ኡምቤርቶም ሜካፕዋን አልወደደላትም፡፡ በኮንትራት ታክሲ ታጉረን ወደ ሜክሲኮ ሄድን፡፡ ወደ ተቀጣጠርንበት ሬስቶራንት ስንገባ ማርኮ እጁን አውለበለበ፡፡ ቲጂ እላዩ ላይ ለመውጣት ምንም አልቀራትም፡፡ ከእሱም ብሶ ጭራሽ ፊት ነሣት፡፡ እሱ ባይሆን እሷ አናደደችኝ፡፡

«ማርኮ አፈቅርሀለሁ!» አለችው እጁን እየሳመች፡፡

«ሜካፑ አስቀያሚ አድርጎሻል!» አላት፡፡

አያናድድም? እጅሪት ታምሪያለሽ ያላት መስሏት ነው መሰለኝ አንገቱ ስር ሳመችው፡፡ ሴት አሰዳቢ! ማርኮ ጭራሽ መጣሁ ብሎ ወጥቶ ሄደ፡፡ ቲጂ አይኗን በሩ ላይ እንደተከለች ቀረች፡፡ እራቱ ፊት ለፊታችን ተደረደረ፡፡ እኔ እና ኡምቤርቶ ጥስቅ አድርገን በላን፡፡ ተናፋቂው ማርኮ ለኡምቤርቶ ደውሎ እንደማይመጣ ነገረው፡፡ ቲጂ ባልበላ አንጀቷ እንባዋን አወረደችው፡፡ ውይ ሴቶች! ወይስ? ውይ ወንዶች! ከሬስቶራንቱ ወጥተን ወደ ሌላ መዝናኛ ቦታ ሄድን፡፡

የገባንበት የምሽት ክለብ የመንሀሪያ መልክ ስለሌለው ወድጄዋለሁ፡፡ ቲጂ የቀረበላት መጠጥ ከልክፍቷ የሚያድናት ፀበል መስሏት ነው መሰለኝ እየደጋገመች ትጨልጠዋለች፡፡ እንድ ጎልማሳ ቲጂ ላይ አይኑን ተክሎ በእጁ የያዘውን መጠጥ የተሞላ ብርጭቆ እየደጋገመ ወደ አፉ ይልካል፡፡ ቲጂን ወደ ጎልማሳው ጠቆምኳት፡፡ እጅሬ መጠጥ ጭንቅላቷ ላይ ስለወጣ ያለምንም ፍርሀት ወደ ጎልማሳው ሄዳ እጁን እየጎተተች ይዛው መጣች፡፡ የህግ ባለሞያ ነው፡፡ ህግ አውጪ እንጂ ፈፃሚ አካል ኢትዮጲያ ውስጥ ማግኘት ከባድ መሆኑን ስነግረው፣ ፊቱ ተለዋወጠ፡፡ ይውጣለት ብዬ ፍትሕ የለም አልኩት፡፡ የምጠይቀውን ጥያቄ አለማወቅ አደጋ እንዳለው ነግሮኝ የቲጂን እጅ እየጎተተ ሄደ፡፡ ዲሞክራሲ እስክትሰጠኝ ድረስ የፈለግኩትን ጥያቄ ባነሳ ለምን አደጋ ይኖረዋል? ዲሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው?

አዲስ ሀሳብ መጣልኝ፡፡ ኡምቤርቶ እስኪሄድ ድረስ እኔ ቤት እንዲኖር ማድረግ፡፡ ፍቅር አይደለም! የበለጠ ባቀረብኩት ቁጥር ኪሱ ኪስ ይሆናል፡፡ ከጎኔ ሲሆን ደስታ ስለሚሰማኝ ወደ አገሩ እስኪመለስ ድረስ ከእኔ ጋር እንዲኖር እንደምፈልግ ነገርኩት፡፡ ኡምቤርቶ እውነቱን መስሎት ተደሰተ! ትንሽ ከጠጣን በኋላ ሞቅ ሲለን ቲጂን ትተናት ወደ ቤት ሄድን፡፡ ስለደከመኝ ወሲብ ትዝ አላለኝም፡፡ እሱም አላስቸገረኝም!

ቀና ቀን ያድርገውና ረፋዱ ላይ ነው ከአልጋችን የወረድነው፡፡ ለሁለት የሠራነውን ቁርስ እየበላን የቲጂ መኝታ ክፍል ተከፍቶ የህግ ባለሞያ ተብዬው ብቅ አለ፡፡ ሰላምታ ሳይሰጠን አንገቱን ደፍቶ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡

«እንጀራ አረስ ሞፈር ተሸክሞ ስራ ዜሮ!» አለች ቲጂ፡፡

«ስራ ላይ ማን እንደ ድሬው ልጅ!» አልኳት፡፡

«አጠገብሽ ያለውስ?»

«አሪፍ ነው! የድሬው ሚጥሚጣ ሳይኖረው አይቀርም!»

«የነፉቱ ስኳር በዛበት? የድሬውን ስለምትወጂው ነው ባክሽ!...»

ቲጂ ያልተፃፈ ማንበብ ትወዳለች፡፡ ኡምቤርቶ ኮተቱን ለማምጣት ወደረፈበት ሆቴል ሲሄድ ሁለታችን ሻይ ቡና ለማለት ወደ ካፌ ገደን፡፡ ትዕግስት ባላወቀችው መንገድ ፍቅር የሚባል ሙጫ ውስጥ ተጣብቃለች፡፡ ፍቅር የሚይዘውን ሰው ለምን እንደማይመርጥ አላውቅም፡፡ ስለኑሮ ወይስ ስለፍቅር ታስብ? እኔ የፍቅር ሰው አይደለሁም! ሲጀመር መች አውቀውና! እሱስ ያውቀኝ ይሆን?

ከካፌው እንደወጣን ሜት እና ሙአሠል ገዝተን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡ ቲጂ ቡና እስክታቀራርብ ድረስ ትንሽ ሽሮ እንደከደኩ፡፡ ወቅዲ ፈተና ስላለባት መጥታ አታውቅም፡፡ ስለዚህ የሰሞኑ ምግባችን እነ ሽሮ እና ፍርፍር ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ሴቶች የጋገሩት እንጀራ ተገዝቶ ቀረበ፡፡ ቀምሰን ተነሳን፡፡

ድሪያ ለብሼ የመቃሚያ ፍራሹ ላይ ተሰየምኩ፡፡ ስራ ፈት ሰዓቱን የሚገፋው ጫት በማመንገግ ስለሆነ አይፈረድብኝም፡፡ ቤታችን በቡናው እና በእጣኑ ጭስ ሞቅ ብላለች፡፡ ቲጂ የቆላችውን ቡና ለመውቀጥ ወደ ውጪ ስትወጣ ኡምቤርቶ ሻንጣውን እየገፋተተ ገባ፡፡ አብዲ ካሁቀ ምን ሊከሰት እንደሚችል ለሰይጣን መተው ነው፡፡

ጣሊያናዊው ጉብል ላፕቶፑን ይዞ አጠገቤ ተቀመጠ፡፡ የተቀባው ኬክ ደስ ስላለኝ እንገቱ ስር ሳምኩት፡፡ አሁንም ደስ አለኝና ደገምኩት፡፡ በድርጊቱ መደሰቱን አይኖቹ አሳበቁበት፡፡ የቲጂ ቡና ሲደርስ እንደጀ ሲኒ ከጠጣንለት በኋላ ጫቱን በስመ መቃም ብዬ ባረኩት፡፡ ኡምቤርቶ ላፕቶፑ ላይ አይኖቹን ተክሎ ጭንቅላቱን ይነቀንቃል፡፡

«የተፈጠረ ችግር አለ?» አልኩት፡፡

«ወንድሜ የፃፈልኝ...» ብሎ ዝም አለ፡፡

«የቤተሠብ ጉዳይ ነው!» አለኝ መልሶ፡፡

...... ስለ እሱ ቤተሰብ ምን አገባኝ? ስለ እሱ ከተጨነቅኩ ይበቃኛል ከተጨነቅኩ?... ማለቴ ጥሩ ሰው ስለሆነ ክፉ ነገር እንዲገጥመው አልፈልግም! እኔኮ ለወንዶች የማልጨነቅ ሰው ነኝ! እዎ! ነገር ግን ኡምቤርቶ ለእኔ ጥሩ ሰው ነው! ስለዚህ... ሳስበው ወንዶች የማይበግሩት እኔነቴ እየተንገዳገደ ሳይሆን አይቀርም! ኧረ በፍፁም እኔን ማንም ወንድ አይበግረኝም!

ቲጂ ድንገት ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች፡፡ ላባብላት አልፈለግኩም፡፡ ማልቀስ ጥሩ ነገር ነው፡፡ እንባ የውስጥን ቆሻሻ ጠራርጎ የሚያወጣ የእፎይታ ባህር ነው ብዬ አምናለሁና! ወዲያው ከት ብላ ሣቀች፡፡

«ፍቅር ያዘኝ!... ለባውም ከማርኩ!... እንዴት ደስ ይላል?!...» አለችው ለኡምቤርቶ፡፡

«እኔም ከኤሚ ፍቅር ይዞኛል!... ስለያዘኝም ደስ ብሎኛል፡፡ የሚሰማኝን ስሜት እወደዋለሁ፡፡ ስለፍቅር ለመናገር ቃላት ያጥረኛል ፍቅር...» ቃላት አጠረው እና ዝም አለ፡፡

«ግን ለፍቅራችን ምላሽ አላገኘንም!... ያ ደግሞ ያማል!...» ቲጂ እንባቿን ደፋች፡፡

«...የኮነው ደስ የሚለው!... የማይወድሽን ሰው መውደድ!... የማይፈልግሽን ሰው መፈለግ!...» አላት፡፡

ይኼ ቂልነት ነው!

«ስቃዩስ?» አለች ቲጂ ልቧን ደግፋ፡፡

«...ስቃዩኮ ነው ዋናው ደስታ! ከእሱ ምንም አትጠብቂ!... እንቺ ያለሽን ግን አትንፈጊው!... ሲጠላሽ እንደገና እንደገና ውደጂው!... ይሄ ነው የፍቅር ትርጉም!...» አለ ኡምቤርቶ፡፡

ለማላውቀው ነገር ስለሚያወሩ አልተሳተፍኩም!

ሰዓቱ ሮጧል! ፀሀይ ወደ ጉሬዋ ገብታለች፡፡ ጨለማ ነግሶ በሰው ሰራሽ ብርሀን ደብዝዟል፡፡ ጠጥቶ መስከር ደግሞ በጣም ያማረኝ ነገር ነው፡፡ ረዘም ያለ ቀሚስ ለበስኩ፡፡ ፓንት ማድረግ አልፈለግኩም፡፡ ኡምቤርቶ ፓንት አለማድረጌን ያውቃል፡፡ ያኔ ድንቅነሽ እራቁቷን መሆኗን ያለማቋረጥ እያሰበ ይቁነጠነጣል፡፡ ፊቱ ፍም ይመስልና ከንፈሩን እየደጋገመ ይነክሰዋል፡፡ ይሄ ለእኔ ደስታን ይፈጥርልኛል!

ቲጂ አብራን መውጣት አልፈለገችም፡፡ ብቻዋን ሆና ስለማርኮ ማሰብ እንደምትፈልግ ነገረችኝ፡፡ ዕናቱን ይስጣት! የተሳፈርንበት ታክሲ ሹፌር የቀመርን ምርጥ አሮምኛ ዘፈን ከፍቶ እያንጎራጎረ ይሾፍራል፡፡ ጓደኛው የጓደኛዬን ህይወት እንዳበላሸ ለኡምቤርቶ ምርር ብዬ ስነግረው፡፡ የሚያበሳጭ መልስ ነበር የሰጠኝ፡፡

«ፍቅር በትእዛዝ የሰው ልብ ወስጥ የሚቀመጥ እቃ አይደለም»

«ይሄ ነው መልስህ?»

«እኔ እንቺን በማፍቀሬ ተጠያቂዋ አንቺነሽ ማለት ነው?»

«የኔ እና ያንተን ከእነሱ ጋር ምን አንድ አደረገው?... ሲጀመር አንተ ስለፍቅር አታውቅም!...» አፈጠጥኩበት!

መልስ አልሰጠኝም!

«ፍቅር አንድ ነው! ስሜቱን አትጉጂው! ባታፈቅሪውም ፍቅሩን አክብሪለት!... ጓደኛሽ ማፍቀር በመቻሏ እድለኛ ናት!... ስለዚህ ያፈቀረችውን ሰው አትኮንኚው!...» አለኝ የታክሲው ሹፌር ከታክሲው ስንወርድ፡፡

የውሸት ፈገግታ ለገስኩት!

ወደ ምግብ አዳራሹ ስንዘልቅ አብዲ በቦታው ከተገኘ ብዬ አይኖቼን አንከራተትኩ፡፡ የለም! ሁለት ቀዝቃዛ ቢራ አዘዝን፡፡ ኡምቤርቶ የመጣለትን ቢራ ሣይጨርስ እኔ ሁለተኛ አዘዝኩ፡፡

«ኡምቤርቶ ጥሩ ሰው ነህ!... የኔን ማንነት እያወቅክ ልሸሸኝ አልፈለግክም፡፡ ያ ደግሞ እኔን እየተጫኑኝ ነው፡፡ እውነቱን ልንገርህ? እኔ ወንዶችን የምፈልጋቸው ለወሲብ እና ለገንዘብ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ...»

ተናግሬ ሳልጨርስ እቅፍ አድርጎ ግንባሬን ሳመኝ፡፡ ታዲያ ይሄ አያናድድም? ምን አባቱ እንደማደርገው አላውቅም!

«ብዙ ጊዜ ፓንት የማታደርጊው ለምንድነው?» አለኝ፡፡

እስካሁን ፓንት አለማድረጌን እያሰበ ነው ማለት ነው!

«ቂጤ ትልቅ እንዲሆን!»

«ፓንት አለማድረግ ቂጥ ትልቅ ያደርጋል?... ሰምቼ አላውቅም!»

ፒያኖ ማታ ላይ ነበር፡፡ የሚመግቡ ... (ማርኮ) ...

ኡምቤርቶ እንደ ሀበሻ፡ ክትፎ ጥርግ አድርጎ መብላት ለምዷል፡፡ በእንጀራ አቆራረሱ ግን እስካሁን አልተስተካከለም፡፡ ያዘዝነው እራት ከመቅረቡ ማርኮ የሰሌን እጅ እየጐተተ ወደ እኛ ሲመጣ አየሁት፡፡ ኡምቤርቶ ላይ አፈጠጥኩ፡፡ ቲጂ ከሌለች የእነሱ መምጣት ችግር እንደማይፈጥር ረጋ ብሎ አስረዳኝ፡፡ ማርኮን ፊት ነሳሁት፡፡ እንደ ጠርሙስ ጠጅ! ከአንደ ብርሌ ጋር አዘዙ፡፡ የቀረበውን ምግብ ቀምሼ ተውኩት፡፡ ኡምቤርቶም በማርኮ ወሬ ስለተጠመደ ብዙ አልበላም፡፡

«መምጣታችን የደበረሽ መሰለኝ!» አለኝ ሰሌ፡፡

«በጣም!» አልኩት ማርኩን በክፉ አይን እየገረፍኩት፡፡

ማርኮ አየት አድርጎኝ ወደ ኡምቤርቶ ዞረ፡፡

«ከቲጂ ጋር ስለነበራቸው አጭር ጊዜ አጫውቶኛል! አሁን እኔን ነው የፈለገው!... ነገ ደግሞ ሌላ ሰው ሊያምረው ይችላል!.. ይሄ የነጮች ባህሪ ነው!... እኔም ብሆን ካልፈለገኝ ከእሱ ጋር መጭጭ አልልም፡፡»

ቲጂ መጭጭ አለችብኝ ብሎት ይሆን? መፀዳጃ ቤት ደርሼ ስመለስ ቲጂ ከማርኮ ጎን ቁጭ ብላለች፡፡ ደነገጥኩ! ማርኮ እራቱ ላይ እንደሚገኝ ለምን እንዳልነገርኳት ጠየቀችኝ፡፡ ድንገት እንደመጣ ስነግራት አላመነችኝም፡፡ የስሊ መገኘት አልተዋጠላትምና እየሰረቀች ታየዋለች፡፡ ስሊ በእሷ እና በማርኮ መካከል በተፈጠረው ችግር ማዘኑን ገለፀላት፡፡ ህይወት ወረተኛ መሆኗንም አስረዳት፡፡ ቲጂ ስለምን እያወራ እንደሆነ የገባት አይመስለኝም፡፡ ግን አስተያየቷ አላማረኝም፡፡ ቲጂ የቀረበላትን ቢራ ነገር እያብሰለሰለች ጠጥታ ከጨረሰች በኋላ ከተቀመጠችበት ተነሳች፡፡ የአራታችንም አይኖች እሷ ላይ ተተከሉ፡፡

«ምን አይነት ሴራ እየሸረብሽልኝ ነው?» አለችኝ፡፡

«ምን ሆንሽ? ቁጭ በይ!» አልኳት፡፡

«አፍሽን ዝጊ! የሆነ ነገር እንዳለማ ውስጤ ነግሮኛል!»

«አዲስ ነገር አልተፈጠረም!... አንቺን ትቶ ወደኔ መጣ!... ነገ ደግሞ ወደ ሌላው ወይም ሌላዋ ይሄዳል፡፡» አላት ስሊ፡፡

ትዕግስት ሁላችንንም በየተራ ከተመለከተችን በኋላ እንደመሳቅም እንደማልቀስም አደረጋት፡፡ ሰለሞን ላይ የሌባ ጣቷን ቀስራ፣ ግብረ ሰዶማዊ መሆኑን ተናገረች፡፡ በምግብ አዳራሹ ወስጥ ያለው የተኳለና ያልተኳለ ዐይን ባጠቃላይ ሰለሞን ላይ ተተከለ፡፡ ማርኮ እና ኡምቤርቶ

ግራ ገብቷቸው ይተያያሉ፡፡ ሰለሞን አፍሮ ፊቱን ለመሸፈን ጥረት ያደርጋል፡፡ ቲጂ ሰለሞንን ለመፈንከት የቢራ ጠርሙስ አነሳች፡፡ መንጭቄ ተቀበልኳት፡፡ ማርኮ ከተቀመጠበት ተነስቶ ቲጂን መሳደብ ጀምረ፡፡ ሴት ይመስል ለመሳደብ አፉን ያሾላል? በጥፊ ደረገምኩበት፡፡ ኡምቤርቶ ማንን መናገር እንዳለበት ግራ ገብቶት እያፈራረቀ የየናል፡፡ ብቻ በጣም የሚገርም ምሽት ነው፡፡

ቲጂን ወንዶች አስተናጋጆች እየጐተቱ ከምግብ አዳራሹ አስወጧት፡፡ ኡምቤርቶም በተራው እኔን እየጐተተ ይዞኝ ወጣ፡፡ ሰለሞን እና ማርኮ ፈጠን ብለው ታክሲ ውስጥ ገብተው ተፈተለኩ፡፡ ቲጂ ታክሲው ከዐይኗ እስኪሰወር ድረስ ተንበርክካ እየጮኸች አለቀሰች፡፡ እውነት አሳዘነችኝ! ኡምቤርቶ አባብሏት ወደ ቤት ይዘናት ተመለስን፡፡

ሁለት ሴቶች፣ በአንድ ወንድ ፍቅር ተጣሉ፣ ሲባል መስማት የለመደ ጆሮ፣ ወንድ እና ሴት፣ በአንድ ወንድ ፍቅር ተጣሉ፣ ሲባል መስማት እንግዳ ሆኖበታል፡፡ ቀናቶች እሽቅድድሞሽ ያለባቸው ይመስል ፀሀይ ብቅ ጥልቅ ባለች ቁጥር ፍጥነታቸውን ይጨምራሉ፡፡ ቀብራራው አብዲ ድምፁን ያጠፋበትን ምክንያት ባላውቅም፤ መጥፋቱን እየወደድኩ ጠልቼዋለሁ፡፡ እውነት ለመናገር ንፍቅ ብሎኛል፡፡ የዋሁ ኡምቤርቶ አንድ ቀን የእሱ እንደምሆን ተስፋ እያደረገ ከጎኔ አልተለየም፡፡ ግን እኔ የማንም መሆን አልችልም፡፡ ትዕግስት ማርኮ ባደረሰባት በደል ተጠያቂ ያደረገችው እኔን ነው፡፡ ቂጥ አፍቃሪው ማርኮ እና ሰለሞንም ድምፃቸውን አጥፍተዋል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ እና የህይወት የቁማር ጭዋታ ይቀጥላል...

# ክፍል አምስት

## ፍቅር እና ቅናት

ቀኑ ማን እንደሆነ አላስታውስም፡፡ እጄ ላይ የተጠመጠመው ሰዓት ከጥዋቱ 4፡15 ይላል፡፡ ቤተክርስትያን ለምን አልሄድም ብዬ ከአልጋዬ ወረድኩ፡፡ ኡምቤርቶን ምን እንደሰለበው አላውቅም ቤት ውስጥ የለም፡፡ መቅደስ በፊተና አባባ ከጠፉች በኋላ ድንገት ተገኝታለች፡፡

አረብ አገር የነበረችው እህቷ ታማ መጥታ እዟን ስታስታምም መክረሟን ስትነግረኝ፣ ሳትናገር በመቅረቷ ልቆጣ የነበርኩት ሴትዮ መልሼ ዝም አልኩ፡፡ መቅደስ እንደነገረችኝ ከሆነ እህቷ ሁለት አመት ሙሉ የሰራችበት ደሞዝ ሳይከፈላት በሽታ ተሸክማ እንደተመለሰች እናትዬው ሲያውቁ ተበድረው ነውና የላኳት ብሩን ከየት አምጥ እከፍላለሁ በሚል ጭንቀት አልጋ ላይ ወድቀዋል፡፡ ባለመኪና ባለቤት ሲሆኑ አይተው ሰው ቤት እየሰሩ እየመሰላቸው ተበድረው ይሄዳሉ ከዛ ለቤተሰብ እዳ ይሆናሉ፡፡ ሰው ቤት ተጠግሮሮ እንኳን መኪና እና ቤት ባጃጅ መግዛት እንኳ አይቻልም፡፡

ወግ ደርሶኝ ባልፀልይም ተሳልሜ ልምጣ ብዬ ነጠላዬን ተከናንቤ ወደ ቤተክርስትያን ለመሄድ ስዘጋጅ፣ መቅደስ ገርሟት የሰኔ ፆም መጀሬን ጠየቀችኝ፡፡ ቀኑ ራሱ ማን እንደሆነ በቅጡ አላስታውስም፣ እንኳን ልፆም?! ቀኑ ማክሰኞ፣ ወሩ ሰኔ፣ መሆኑን አስረዳችኝ፡፡ ቅዳሴ ሳይገባ ለመድረስ እንደሚጣደፍ ክርስትያን ራመድ ራመድ እያለኩ ማርያም

ቤተክርስቲያን ደረስኩ፡፡ በረድፍ የተደረደሩት ነዳያን የእማልክተን ስም እየጠሩ እጃቸውን ዘረጉ፡፡ የያዝኳትን አምስት ብር ሽምግል ያሉ አባት የዘረጉት እጅ ላይ አስቀመጥኩ፡፡ ወደ አደፌ ብልኳቸው ሽጉጠው የምርቃት መዓት አወረዱብኝ፡፡ አስር አስር ሳንቲም ለአስር ነዳያን ከመወርወር አንድ ብር ለአንድ ነዳያን መጣል የተሻለ ነው፡፡

ልብን ለእግዚአብሔር ክፍቶ መስጠት ከቀረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ስጋዬ ለሰይጣን ተገዢ ቢሆንም ነብሴ ግን አምላኳን ትሻዋለች... ዐይኔን ጨፍኜ አምላኬን ፈለግኩት! እኔ ልብ ውስጥ ያለው ክፋት እና በቀል ነውና ላየው አልቻልኩም፡፡ ዐይኖቼ እንባ አመነጩ፡፡ ውስጤ ተረበሸ፡፡ ሳልፈልግ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ፡፡ ምናልባት ነብሴ ትሆን ያለቀሰችው? ግቢውን ቃኘሁት፡፡ ጥቁር ቀሚስ አጥልቀው፡ ያደፈ ነጠላ አዘቅዝቀው፡ የሌባ ጣታቸውን ወደ ሠማይ ቀስረው የሚያነበንቡ እናት አየሁ፡፡ እያስጠነቀቁት ወይስ እየለመኑት?.... እኔ ጣቴን ልቀስርበት ይቅርና ቀና ብዬ የማይባት አቅም እንኳ የለኝም፡፡ ፈጣሪ የጠየቅኩትን ሁሉ አልነፈገኝም፡፡ እኔ ግን በሰጠኝ ውበት እና ጥበብ ሐጥያት እየሰራሁበት ነው፡፡ በሚማርክ ያሬዳዊ ዜማ ቄሶች ቅዳሴያቸውን ሲጀመሩ ቀጥ ብዬ ከግቢው ወጣሁ፡፡

ሆዴ ምግብ ስለጠየቀኝ እየተጣደፍኩ ቤቴ ደረስኩ፡፡ የቤቴን ቁልፍ ስላልያዝኩ በሩን አንኳኳሁ፡፡ ኡምቤርቶ በሩን በቀጮት ከፍቶ ወደ ውጪ ወጣ፡፡ በጥዋት የት ሄዶ እንደነበረ ስጠይቀው መልስ ሳይሰጠኝ! ፊጢን ብሎ ነጠላዬን አይኔ ላይ ካሰረው በኋላ ወደ ውስጥ ይዞኝ ገባ፡፡ "the power of love" የሚለው የሴሊን ዲዮን ሙዚቃ ይሰማኛል፡፡

በጣም የምወደው ሙዚቃ ነው፤ ከየት እንዳገኘው ኡምቤርቶን ስጠይቀው፤ የምወዳቸውን ነገሮች አድኖ ማቅረብ ስራው እንደሆነ ነገሮኝ መኝታ ክፍሌ አስገብቶ በሩን ቆለፈብኝ፡፡ ዐይኔ ላይ የታሳረውን ነጠላ ፈትቼ አልጋዬ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ ወዲያው መቅደስ በሩን በቀጭኑ ከፍታ ምግብ ይዛልኝ ገባች፡፡ ኡምቤርቶ በሩን መልሶ ቆለፈው፡፡ ርሀቤን ካስታገስኩ በኋላ ሳሎን ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ መቅደስን ጠየኳት፡፡

ስለእናቷ እና እህቷ መተረክ ጀመረች፡፡ የጠየቅኳት ሌላ መልሷ ሌላ፡፡ ትረካዋን ስትጨርስ ጥያቄዬን ደገምኩላት፡፡ ግርግዳው ላይ ወጥ ተደፍቶ ኡምቤርቶ እያፀዳ መሆኑን ነገረችኝ፡፡ ግርግዳ ላይ ወጥ? ጆሮዬን በሩ ላይ ለጠፍኩ፤ ምንም ነገር ሊሰማኝ አልቻለም፡፡ በሩን መደብደብ ጀመርኩ፡፡ ኡምቤርቶ ቆየት ብሎ ከፈተልኝ፡፡ ሳሎኑን በአይኔ ከቃኘሁት በኋላ ወደ መኝታ ክፍሌ ገብቼ በሩን ወርውሬ ዘጋሁት፡፡ የኔ በግ በሩን ቀስ ብሎ ከፍቶ ገባ፡፡

«ለምን ይህን አደረክ?» ጮሁኩበት፡፡

«ስለማፈቅርሽ!»

«አይደለም!... እኔን ለመጉዳት ነው!...» እንባረቅኩበት፡፡

«በፍፁም!... ስለማፈቅርሽ እንደገናም ስለማፈ...»

«አውቃለሁ!... ግን እኔን አመመኝ! እባክህ ለኔ ጥሩ አትሁን፡፡»

እንባዬ ሳልፈቅድለት ፈሰሰ፡፡ ውብ ቀይ የአበባ ምንጣፍ ላይ ግርማ ሞገስ ያለው ሶፋ፤ ቴሌቪዥንን እስከ ማስቀመጫው፤ ማቀዝቀዣ፤ የሚያምር የምግብ ጠረጴዛ እስከ ወንበሮቹ፤ የኩሽና እቃዎች... ሳሎኑን

ወረውታል፡፡ በርግጥ ለጥቅሜ ስል ነው ኡምቤርቶን ከእኔ ጋር እንዲኖር የፈቀድኩለት፤ ግን አሁን ውስጤ በስራዬ እየወቀሰኝ ነው፡፡ አይኖቹን ትኩር ብዬ ተመለከትኳቸው ልብ ውስጥ የሚገባ እሳት ይረጫሉ፡፡ ከንፈሩን ጉረስኩት፡፡ አቀፈኝ፡፡ ከዛ በኋላ የተፈጠረውን ነገር ማስታወስ ወይም መግለፅ ይከብደኛል፡፡ ግን እርቃናችንን ነበርን!

የተገዙልኝን የቤት እቃዎች በደንብ ለመጎብኘት ወደ ሳሎን ስሄድ መቅዲ አብዲ መጥቶ እንደነበረ አረዳችኝ፡፡ ምራቄ ደረቀ፡፡ የተገዛልኝን እቃ እንደምወደው እርግጠኛ መሆኑን እንድትነግረኝ ለመቅደስ አደራ ብሏት ነው የሄደው፡፡ አብዲ ዐይኑን ከኡምቤርቶ ላይ አላነሳም፡፡ የሳሎኑ በር መቆለፉን አረጋግጬ ተቀመጥኩ፡፡ አብዲን ደበልጥ ፈራሁት፡፡ ኡምቤርቶ ያለ ሀጥያቱ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዲደርስበት አልፈልግም፡፡ አብዲን ማቆም የኔ ፋንታ ነው! እንዴት?

ኡምቤርቶ ላፕቶፑን ይዞ አጠገቤ ሲቀመጥ ተነስቼ ወደ አልጋዬ ሄድኩ፡፡ አብዲጋ ለመደወል ስልኬን አነሳሁ፡፡ ግን ወኔ አልነበረኝም! አብዲ አደርገዋለሁ ያለውን ነገር ከማድረግ የሚያግደው ነገር ቢኖር... ሞት ብቻ ነው፡፡ ምን ይሻለኛል? ኡምቤርቶን መራቁም ሆነ መቅረቤ ጉዳቱ ለራሱ ለኡምቤርቶ ነው፡፡ ብርቀው የእኔ እጦት ያመዋል!... ብቀርበው አብዲ የሚባል ሠይጣን እሱን ለማጥፋት ታጥቆ ይነሳል!... አብዲ እንደሆነ ብረቀውም ብቀርበውም መድኃኒት የሌለው ደዌ ነው፡፡ የኡምቤርቶን ደህንነት ግን ነብሴ ትሻዋለች፡፡

ማስታወሻዬ ላይ ትንሽ ሞነጫጨርኩ፡፡ ትንሽ ስለ አብዲ፣ ትንሽ ስለ ኡምቤርቶ፣ ብዙ ስለኔ!... ኡምቤርቶን ባገባው ምን ይጎልብኛል? ታማኝ ጓደኛዬ ማስታወሻዬ ሆይ!... ህይወት ቁማሩን ለመብላት የምታቀርበው ጉርሻ ቢኖር... በተለይ ለሴቶች ትዳር እና ልጅ እንዲሁም ፍቀር የሚሉትን እብድት ነው!... ይሄ ሁሉ ህይወት ቁማሩን እንድታሸንፍ ይረዳታል፡፡ እኔ ደግሞ የእነዚህ ነገሮች አድናቂ አይደለሁም! ሽንፈት አልወድማ! ባላሸንፍም መፍጨርጨርን፣ ቆሚ ባልሄድም ዳዴ ማለትን፣ ማንም አይነፍገኝም!... ሁሉም ነገር በምርጫ ይወሰናል!!

አመሻሹ ላይ ከኡምቤርቶ ጋር ንፋስ ለመቀበል ከቤት ወጣን፡፡ ትንሽ ከተንዝን በኋላ፣ አብዲ ቢያያችሁስ? አለኝ ጭንቅላቴ፡፡ ወገቤን አመመኝ ብዬ ወደ ቤት ተመለስን፡፡ በኔ ውሸት አሳሩን የበላ ምስኪን ሰው ቢኖር ኡምቤርቶ ብቻ ነው፡፡ ምን አይነት ሀጢያት ሰርቶ ይሆን እኔ ላይ የጣለው? ወደ ቤታችን ስንገባ፣ አይገርምም?... ቤትችን እልኩ እኮ! ትዕግስት የመቃሚያ ፍራሹ ላይ ቁጭ ብላ ሺሻ እየሳበች ቴሌቪዥንን ታያለች፡፡

«እንዴት አድርገሽ እንደምትሰጪያቸው ብትነግሪኝኮ እኔም የቤት እና የውድ እቃ ባለቤት እሆን ነበር፡፡ አብዲ ኡምቤርቶ እዚህ መኖሩን ቢሰማ ሁለትሽንም ሲጥ እንደሚያደርጋችሁ አትጠራጠሪ! ስለዚህ አስቢበት!... አሳይቶ እንዳይነሳሽ!...» አለችኝ፡፡

«ሰጪማ አንቺ ነበርሽ!... ምን ያደርጋል ነፈገሽ እንጂ...» አልኳት ይውጣላት ብዬ፡፡

ቅናት ቢጤ እንደተሰማት ገባኝ፡፡ ለእራት የተሰራውን ምግብ አሙቄ አቀረብኩ፡፡ እራት ብዬ ስላት እየተለጠጠች አልበላም አለች፡፡ ነገር እንደጠማት ስላወቅኩ ዝምታን መረጥኩ፡፡ ኡምቤርቶ የአገራችንን ጣቢያ ቀይሮ፣ CNN ላይ የሚተላለፈውን ወሬ እየተከታተለ እራቱን ይበላል፡፡ ትእግስት ስትፈልግ ታንጐራጉራለች ሲላት ቁና ቁና እየተነፈሠች ፈጣሪዋን ታማርራለች፡፡

«ዜና እየተከታተለ ስለሆነ ዝም በይ!....» አልኳት፡፡

«ከኔ እሱ በለጠብሽ?»

«ራስሽን ከእሱ ጋር ታወዳድሪያለሽ?» እውነቴን ነው!

«ለነገሩ ሰው ያለውን እንጂ...»

«ብቃ አፍሽን ዝጊ!»

«ምቀኛ! ሊያገባኝ የወሰነውን ሰው ሀሳብ ያስቀየርሽ ሰይጣን ነሽ፡፡ ሰው መሳይ.....»

ተወርውሬ አጠገቧ ደረስኩ፡፡

«ሌላ ነገር ሳይከተልሽ ውጪ ከቤቴ!»

«ባልወጣ ምን ታመጫለሽ?» አፈጠጠችብኝ፡፡

«የተፈጠረ ችግር አለ?» አለ ኡምቤርቶ፡፡

ንቀቷ የሰው ደም ያፈላል! ሰይጣኔ ሀይሉን አሰባስቦ ተነሳ፡፡ እጇን ይዤ መሬት ለመሬት መጐተት ጀመርኩ፡፡ ኡምቤርቶ ለመገላገል ሞከረ፡፡ ገፈተርኩት፡፡ ከምግብ ጠረጴዛው ጋር ተጋጨ፡፡ እሷን ጎትቼ ከቤት አስወጣኋት፡፡ ስድቧን የሰሙ ጐረቤቶቼ በራቸውን እየከፈቱ ጭንቅላታቸውን ብቅ ብቅ አደረጉ፡፡ የሺሻ እቃዋን እንስቼ ከሮቅ ወደ

ምድር ለቀቅኩት፡፡ ፀጉሬ እጆቿ ውስጥ ገባ፡፡ ኡምቤርቶ በግድ ታግሎ ፀጉሬን ከመንቀል አዳነው፡፡ እየጎተተ ወደ ቤት አስገብቶ ቆለፈብኝ፡፡ የትእግስት ስድብ ግን አልቆመም፡፡ ቤት የሚወለወልበትን ማስታጠቢያ ውሀ ሞላሁት! በርበሬ ብጨምርበት ደግሞ የተሻለ ስለሚሆን በርበሬ ከጨመርኩበት በኋላ በሩን ከፍቼ ፊቷ ላይ ለቅቄባት በሩን ቆለፍኩ፡፡ በሬቱሁት ስፈሩን አደባለቀችው፡፡

«እብድ ነሽ?» አለኝ ኡምቤርቶ፡፡

«አንተም ተከትለሀት መሄድ ትችላለህ! አሁኑኑ!.....»

«ከእብዷ ጋር እንደፈለገሽ ለመሆን... እም!... መሄድ አለብኝ!... ራስወዳድ!... የምትናገሪውን እንኳ አታውቂም?»

በጥፊ መታሁት፡፡ እጄን ከጠመዘዘኝ በኋላ ለቀኝ ጀርባውን ሰጠኝ፡፡ አድርጎት አያውቅም!... ግን አደረገው!... እማቱን የለኮሰችው ሠይጣን ፖሊስ ይዛ ትመጣለች ብዬ ስጠብቅ ቀረች፡፡ እኔ እና ኡምቤርቶ እንደተኳረፍን አልጋ ውስጥ ገባን፡፡ አላስቻለውምና ይቅርታ ጠይቆኝ ተቃቅፈን ተኛን፡፡ እኔም በልቤ ይቅርታ ጠየኩት፡፡ ጭንቅላቱ በሀሳብ ስለተወጠረ እንቅልፌ ሊነጋጋ ሲል ነው የመጣው፡፡

የዛሬው ቀን እንዴት እንደሚያልፍ አላውቅም፡፡ ምክንያቱም እትዬ ትእግስት እቃቸውን ለመውሰድ ሲመጡ መርዛማ ምላሳቸውን ማወናጨፋቸው አይቀርም፡፡ በጥዋት የተነጀሰ ቀን ደግሞ እዚማም ሆኖ ነው የሚውለው፡፡ ቁርስ በልተን እንደጨረስን የሳሎኑ በር በብዙ መዳፍ መደብደብ ጀመረ፡፡ መቅደስ እየሮጠች ከፈተች፡፡ ትእግስት ከሁለት

ወዘ ቢስ ሴቶች ጋር ዘው ብላ ገባች፡፡ ልብሳቸው ያደፈ፣ ዐይናቸው በበርበሬ የተለወሰ የሚመስል፣ ሁለት ጐረምሶች ከተል ብለው ገቡ፡፡ ኡምቤርቶን ወደ መኝታ ክፍሌ እንዲገባ በምልክት አዘዝኩት፡፡ አላንገራገረም!

«እራስሽን የቆለልሽ አይመስልሽም?» አለችኝ የሴት ቅርፅ ያልፈጠረባት ጓደኛዋ፡፡ ሁለተኛዋ ድብልብል ቀጠለች፡፡ «ያን ቋጠ ቀዳዳ ባገኘው እንጨት ነበር የምከትብት፡፡» አለች፡፡ «ኧረ አንቱ ነበር የምገለው!» አለ አንደኛው ጐረምሳ አፍንጫው ላይ ያለውን ውሀ መሳይ ንፍጥ ባደፈ ሸሚዙ እየጠረገ፡፡ ሁለተኛው ምራቁን ምንጣፌ ላይ ለድፎ «ወንድ አሠዳቢ!» አለ፡፡

«የት ያላችሁ መሰላችሁ? ውጡ!» አልኳቸው፡፡

«እንወጣም! ምን ታመጫለሽ?» አለ ንፍጣሙ፡፡

«ይቺን ክፍታፋ እርቧትና ኑ አልጋውን ፍቱልኝ፡፡» አለች

ትእግስት ሻንጣዋን እየጐተተች፡፡

«... የወሰድሽባትን ብር ፈጠን ብለሽ ስጫት!... እንቢ ካልሽ

ሆድሽን በማንጃ ነው የምዘከዝከው፡፡» አለኝ ንፍጣሙ፡፡

የቡድኑ መሪ ነው መሰለኝ፤ እሱ ብቻ ነው ተናጋሪው፡፡

«መቅደስ ቶሎ በይ ዘቦቹን ጥሪልኝ እና ፖሊስ ይዘሽ ነይ፡፡ ወንበዴዎች ዘረፋ እያካሄዱ እንደሆነ መንገርሽን እንዳትረሺ፡፡» ከማለቴ....

«እናትዬ የቀልዴን ነው! እኛ በሰላም ነው ከዚህ ቤት መውጣት የምንፈልገው፡፡» አለ እያ ንፍጡ እየተርበተበተ፡፡

ፖሊስ የሚፈራው ሌባ ነው!... ይባላል፡፡ እኔም ላስፈራራቸው እንጂ ፖሊስ የመጥራት አላማ ኖሮኝ አይደለም፡፡ እየተጣደፉ ኮልኮሊያቸውን በረንዳ ላይ ደርድረው ጨረሱ፡፡

«ጉድሽን ለአብዲ ዝክዝክ አድርጌ እነግርልሻለሁ!» ቲጂ አስፈራራችኝ፡፡

«.... የዮሴፍ ገዳይ መሆንሽን ለፖሊሶች አስታውቃለሁ!.... በተጨማሪም፣ ማዱ ላይ አሲድ ለመድፋት ሲዘጋጅ፣ እያወቅሽ፣ ለፖሊስ አላመለከትሽም፡፡ በሁለት ወንጀል ፍርድ ቤት ትገተሪያለሽ ማለት ነው፡፡» እኔስ ማነኝ?!

አፏን እንደከፈተች ተገትራ ቀረች፡፡ በሩን ወርውሬ ዘጋሁባት፡፡ ትንሽ ካስቦካኋት በቂ ነው፣ እርፉ ቁቀመጣለች፡፡ ወደ መኝታ ቤት ስገባ ኡምቤርቶ ልብሱን ለባብሶ፣ ውብ ፀጉሩን በመስታወት እየተመለከተ፣ በአለንጋ ጣቶቹ ያስተካክላል፡፡ የተቀባው ሽቶ ልብን ይሰርቃል፡፡ ማርኮ ጋር ደርሶ እንደሚመጣ ነግሮኝ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡

ሰው ቤቱ ውስጥ ከሌለ ማስታወሻዬ እና እኔ ነፃነት ይኖረናል፡፡ ሰው ካለ ግን ያነቡብኛል ብዬ ስለምፈራ እየተሳቀቅኩ ነው ማስታወሻዬን አውጥቼ የምፅፈው፡፡ ከማስታወሻዬ የምደብቀው ምሥጢር የለኝም፣ እያንዳንዷን ድርጊቴን በውስጡ እሰፍራለሁ፡፡ እኔ የረሳኋቸውን ታሪኮቼን ለማስታወስ ማስታወሻዬን መግለጥ ብቻ ነው የሚጠበቅብኝ፡፡ ማስታወሻዬ ከማንም በላይ ታማኝ ጓደኛዬ ነው!! ሳሎን ቁጭ ብዬ ጠዋት ያጋጠመኝን ድራማ ከፃፍኩ በኋላ ኡምቤርቶን ትንሽ እራት ሰርቼ ልጠብቀው ብዬ ሽርጉድ ማለት ጀመርኩ፡፡ የፈረንጅ ምግብ

ለመስራት መፅሐፍ ማገላበጥ ነበረብኝ፡፡ ይጣፍጠዋል ብዬ ያሰብኩትን የምግብ አይነት በመፅሐፉ እየታገዝኩ መስራት ጀመርኩ፡፡ ሦስት አይነት ምግብ ሰርቶ ለመጨረስ ዓመት ፈጀብኝ፡፡ ያውም ከመቅደስ ጋር፡፡

ሰዓቱ ሄዷል ሳይሆን በሯል ነው የሚባለው፡፡ ሁሉ በመስኮት ብቅ ብዬ የምሳለማቸው ከዋክብት እልፎ እልፎ ይታያሉ፡፡ ኡምቤርቶ ቆየብኝ፡፡ ደወልኩለት ስልኩ ጥሪ አይቀበልም፡፡ ትንሿ ልቤ ምቷን ጨመረች፡፡ ማርኮ ጋ ደወልኩ አያነሰውም፡፡ አብዲ እና ኡምቤርቶ ተገናኝተዋል! አብዲ ጋ ደወልኩ አያነሣውም፡፡ ደግሜ ደወልኩ ዘጋብኝ፡፡ ኡምቤርቶ አብዲ መዳፍ ውስጥ ገብቷል! ተንቆራጠጥኩ፡፡ በሩ ተንኳኳ፡፡ እየፈራሁ ቀስ ብዬ ከፈትኩት፡፡ ኡምቤርቶ ነው!...

«የኔ ውድ ምን ሆነሽ ነው የምታለቅሺው?» አለኝ ደንግጦ፡፡

አልቅሼ ነበር?

«ፀይኔ ውስጥ የሆነ ነገር ገብቶብኝ ነው፡፡»

«እስቲ አሳይኝ!»

«እንዳትነካኝ! እራት ሳቀርብ ነው፡፡» ሸሸሁት!

እራስ ነብር ያደረገኝን ነገር ባውቀው ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ጠረጴዛው ላይ የተሰየመውን ወይን ከፍቶ ለሁለታችንም ቀድቶ ተቀመጠ፡፡ እራቱን አቀራርቤ ከጎኑ ተቀመጥኩ፡፡ ከሦስቱም አይነት ምግብ ቀምሶ ግንባሬን ሣመኝ፡፡ ስልኩ ባትሪው ደከምበት እንደተዘጋ ሲነግረኝ እውነም እንዳልሰማ ዝም አልኩት፡፡ ስላመሸ ይቅርታ ጠየቀኝ፡፡ እሁንም

እንዳልሰማ ዝም አልኩ፡፡ ስለዘጋሁት ጨነቀው፡፡ እራታችንን በልተን ስንጨረስ ብርጭቆዎቻችንን በወይን ሞልተን ሶፋው ላይ ተቀምጠን፡፡ እየተሰራረቅን ስንተያይ ዐይኖቻችን እየተጋጩ እስቸገሩን፡፡ የሁለታችንም ብርጭቆዎች ባዶ ሲሆኑ የወይኑን ጠርሙስ ለማምጣት ተነሣሁ፡፡ እጄን ያዘኝ! እጄ ኤሌክትሪክ ላይ የተሠካ ይመስል ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ነዘረኝ፡፡ ከተቀመጠበት ተነስቶ ፀጉሬን እየዳበሰ ስማያዊ ዐይኖቹን አቅም ያነሣቸው ዐይኖቼ ላይ ተከለ፡፡

«ትወጅኛለሽ? ውስጤ ትወድሀለች ይለኛል!» አለኝ፡፡

ዐይኔን አሸሽሁ!

«ካለህ ለምን ትጠይቀኛለህ?»

«ፍቅርን የሚገልፅ ቋንቋ ይኖር ይሆን? ላንቺ ያለኝን ፍቅር ለመግለፅ እቸገራለሁ፡፡ አልችልም! አለመቻል የፍቅር ቋንቋ ይሆን? ወይስ አለመቻሌ ፍቅር ያደከመው እኔነቴ ነው? ከማንም፣ ከምንም፣ ከምንም በላይ አፈቅርሻለሁ! ከምንም በላይ!.. ውስጤ ምን እየሰራሽ እንደሆነ ልነግርሽ እፈልግና ቃላት ያጥረኛል! አንቺ አትውደጂኝ! እኔ ብቻዬን እንድወድሽ ብቻ ፍቀጂልኝ!»

.....ስለ ፍቅር ምንነት ለማይገባው ሰው የፍቅርን አላማ መስበክ ምን መፍትሄ አለው?... ጥሩነቱ እንዳከብረው አስገድዶኛል!... የእሱ የአፈቅርሻለሁ ዝማሬ ግን ድንጋይ ላይ ውሀ እንደማፍሰስ ይቆጠራል።

«አግቢኝ!»

«ለምን ታስጨንቀኛለህ?»

«ለምን አትረጂኝም?»

«እሺ እኔ ምን ላድርግ?»

«ምንም!.... እንጠጣ!... እንስከር!... በቃ!....» ከወይኑ ተጎነጨ፡፡

«ፍቅር ለኔ ተራ የፊደል ጥርቅም ነው! ስለዚህ...»

አቋረጠኝ፡፡

«ፍቅር ፈልገሽው የምታገኚው ነገር አይደለም! ፍቅር በእራሱ ዓለም፤ በእራሱ ሀይል የሚኖር፣ በመረጣቸው ሰዎች ልብ ገብቶ የሚያብረከርክ፤ በሀይል የተሞላ፣ በሀይል የተገነባ ንጉስ ነው፡፡ ፍቅር በዐይን አይታይም፡፡ ልብሽ ውስጥ የገባ ቀን ግን ታጣጥሚዋለሽ፡፡ እኔ ልብ ውስጥ ስላለ ባላየውም እያጣመጥኩት ነው፡፡ በፍቅር መንግስት ውስጥ ዐይን ያለው እና የሌለው እኩል ነው፡፡ የፍቅር ዕርስት ዐይን ሳይሆን ልብ ነውና!! ሰዎች የማንረዳውን ነገር ፍቅር እያስተማረን ነው፡፡ የምናየው በዐይናችን እየመሰለን እንሸወዳለን፡፡ ማነው ልቡ የወደደውን ትቶ አይኑ ያየውን የመረጠ? ዐይንሽ ሳይሆን ልብሽ ካየኝ መቼም ቢሆን አንቺ የእኔ እና የእኔ ብቻ ነሽ፡፡»

ከውስጡ የወጣ ወይስ ከመፅሐፍ ያነበበው? ባልቀበለውም ጥሩ እንጋገር እንደሆነ ስነግረው ተናደደ፡፡ መልሴ ያናድድ ነበር? ስልኩን ቻርጀሩ ላይ ከመሰካቱ ወንድሙ ደወለ፡፡ በቋንቋቸው ስለሚያወሩ ለማዳመጥ አልጓጓም፡፡ የቀዳሁትን ወይን ጨልጬ ሶፋው ላይ ጋደም አልኩ፡፡

ጠዋት እራሴን ያገኘሁት አልጋዬ ውስጥ ነው፡፡ ኡምቤርቶ ጀርባውን ሰጥቶኝ ተኝቷል፡፡ ቀስ ብዬ ከአልጋዬ ወርጄ ፎጣ አሸርጬ ወደ መፀዳጃ ቤት ሄድኩ፡፡ ገና ከመግባቴ የመፀዳጃ ቤቱ በር በሀይል ተንኳኳ፡፡ ማነው ተንኳኳ፡፡ ጆሮዬን ተጠራጠርኩት፡፡ ድጋሚ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ማነው

ማለት አይጠበቅብኝም። በር በሀይል የሚያንኳኳው አብዲ ነው፤ አምላኬ! እየተንቀጠቀጥኩ በሩን ከፈትኩት። ኡምቤርቶ እርቃኑን ቆሟል። በጥፊ ብለው ደስ ይለኝ ነበር።

«አስደነገጥከኝ!... ሁለተኛ እንደዚህ እንዳታንኳኳ!....»

«አብዲ መስሎሽ ነበር?» አለኝ ፈገግ ብሎ።

«ምን?»

«ስለ አብዲ ትእግስት በደንብ አጫውታኛለች!»

«እሱ የሚያደርገውን ነገር ማድረግ እኔን ያበሳጨኛል።» ይበልጥ ተጠጋኝ።

«ምን ፈለክ?» አልኩት ለመኮሳተር እየሞከርኩ።

«አሁን ብገልሽ ማን ይደርስልሻል?» አለኝ የተገተረ አደፍርሱን ጨብጦ።

«አንተ!» ሻፈድኩ።

«እኔማ ገዳይሽ ነኝ!»

«ገደለኝና የሚደርስልኝ ማን እንደሆነ እንይ!» አልኩት ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ።

«እሺ!» አለኝ እሱም በጆሮዬ።

የሚወርደው ውሀ ስር ቆምኩ። ኡምቤርቶ ከከንፈሬ ጀምሮ እየሣመኝ ወረደ። እግሬ መሀል ሲደርስ ሎሚ ሲቆረጥ ያየሁ ይመስል ምራቄን ዋጥኩ። ኡምቤርቶ እንዳለው ሊገለኝ ፈልጓል መሠለኝ፤ ንጉስ ናቡከደነፆር እንዳነደደው እሣት ካነደደኝ በኋላ፣ በመዳፉ መውደቄን አምኜ አለቀልኝ ስል፣ አቀዝቅዞ መለሰኝ። ገድሎ አዳነኝ!

ተጣጥበን እኔ ፎጣዬን አሸርጬ እሱ እርቃኑን ከመፀዳጃ ቤት ስ ወጣ አብዲ እጁን ኪሱ ውስጥ ከቶ ቆሟል፡፡ በንዴት የጋለ አይኖቹን የማየት አቅም አልነበረኝም፡፡ ምን ሊሰራ እንደመጣ ኡምቢርቶ ጠየቀው፡፡ አብዲ ተጠጋኝ! ወደኋላ ለማፈግፈግ የሚችሉ እግሮች የሉኝም፡፡ ግጥም አድርጎ ከንፈሬን ሳመኝ፡፡ ኡምቤርቶ ሊመታው እጁን ሠነዘረ፡፡ መሀላቸው ገባሁ፡፡ አብዲ ገፍቶ ከመሀል ካወጣኝ በኋላ፣ ኡምቤርቶን በቴስታ መቶት ወጥቶ ሄደ፡፡

«ምንድነው ፍላጎትሽ?.... » አለኝ ኡምቤርቶ እንደመተት እየናጠኝ፡፡

«ምንም!...» አልኩት ደንግጬ፡፡

«እንደማትጣጣሙ ካንቺ በላይ የሚያውቅ ሰው አለ?»

«የለም!»

«እደል ስጪኝና ፍቅሬን በቃል ሳይሆን በተግባር ላሳይሽ!»

ስንቴ ላስረዳው... ፍቅር እንደማላውቅ?! ቁርስ በልተዋል ለመባል ብቻ የቀረበውን ምግብ ቀምሰን ተነሳን፡፡ እሱ ቴሌቭዥኑን ከፍቶ ጣቢያ መቀያየር ሲጀመረ እኔ መኝታ ክፍሊ ገብቼ ገላዬን አልጋዬ ላይ አሳርፌ ልቤን አብዲጋ ላኩት፡፡ ሳይፈልጉ ስላልፈለጉት ሰው ማሰብ ምን የሚሉት በሽታ ይሆን? መዳኃኒትስ ይኖረው ይሆን? ሳሎኑ ውስጥ የሰለሞን እና የማርኮ ድምፅ ይሰማኛል፡፡ ጆሮዬ መስማቱን ይሰማል የሚያደምጠው ልቤ ግን አብዲጋ ሄዷል፡፡ ልቤ በእኔ ሰውነት እየኖረ እንዴት የራሱ ብቻ ዓለም ሊኖረው ቻለ? እግር ሳይኖረውስ መንገደኛ እንዴት ሊሆን ቻለ?

ስለሞን የመኝታ ቤቱን በር ሲያንኳኳ ከሀሳቤ ባነንኩ፡፡ ደህንነቱን ስጠይቀው፣ የዋህ ምን ይሆናል? አለኝ፡፡ የዋህ ፊደል እንጂ የዋህ ሰው የለም! መቆዘም ተገቢ አለመሆኑን ነግሮኝ ወደ ሳሎን ሄደ፡፡ እውነቱን ነው! ተከተልኩት፡፡ ማርኮ ሰላምታ ሲሰጠኝ አፀፋውን አልመለስኩም፡፡ ምክንያቱም ጓደኛዬን አገባሻለሁ ብሎ መዋሸት አልነበረበትም፡፡ ስለሞን እንዳስረዳኝ ከሆነ ማርኮ ሴት የማግባት አላማ የለውም፡፡ ምክንያቱም ማርኮ አድራጊም ተደራጊም ነው፡፡ እንደገባኝ ከሆነ ማርኮ የእሱ ቢጤ ቂጠ ቀዳዳ ወንድ ሲያገኝ ቲጂን ፈነገላት፡፡ ሰለሞንን ባያገኝም አያገባትም ነበር ማለት ነው!...

የማርኮ አመጣጥ ነገ ወደ አገራቸው ስለሚመለሱ የመጨረሻ ምሳ ሊጋብዘን ነበር፡፡ አቶ ኡምቤርቶ ግን ኢትዮጲያን እና አምሮትን ትቼ ከምሄድ ሞቴን እመርጣለሁ አለ፡፡ ማርኮ ፊቱ ፍም መስሎ ቁና ቁና መተንፈስ ጀመረ፡፡ እኔ እና ሰለሞን ግራ ተጋብተን መቁለጭለጭ ጀመርን፡፡ ኡምቤርቶ የምሳ ግብዣውን ስለተቀበለ ልብሱን ለመቀየር ወደ መኝታ ቤት ገባ፡፡

«ኤሚ! አብሮኝ ካልሄደ ወንድሙ ይገለኛል!» አለ ማርኮ፡፡

«ህፃን ልጅ ነው እንተ እየጐተትክ የምትወስደለት?» አለው ሰለሞን፡፡

«እኔ የኡምቤርቶ ጠባቂ እንጂ ጓደኛው አይደለሁም! ወንድሙ ለደቂቃ እንኳ ከእሱ ብለይ ሟች መሆኔን ነግሮኛል፡፡»

«ኤሚ!... ወንድሙ የታወቀ ነብሰ ገዳይ ሳይሆን አይቀርም፡፡» አለኝ ሰለሞን፡፡

ኡምቤርቶ ጥቁር በጥቁር ለብሶ ብቅ አለ፡፡ ማርኮ አቀረቀረ፡፡ እስከዛሬ እኛ የምናውቀው ማርኮ ጓደኛው መሆኑን እንጂ ጠባቂው መሆኑን አልነበረም፡፡ ኡምቤርቶ ማነው? ዘራቸውስ ለምን ተረገመ? እርግማኑንስ እንዴት ነው የሚሰብሩት? ከዚህ ሰው ጆሮባ የሆነ የሚከብድ ነገር ሳይኖር አይቀርም፡፡ ልብሴን ቀይሬ አራታችንም ተያይዘን ምሳ ልንበላ ወጣን፡፡ አብዲ ድንገት ካየን የሚፈጠረው ነገር ጥሩ ስለማይሆን የምሳው ግብዣ እንዳለቀ ቶሎ ወደ ቤት ተመለስን፡፡

ማርኮ እና ኡምቤርቶ ጭቅጭቅ ጀመሩ፡፡ ጣልቃ እንዳልገባ ምን ሰምቼ?... በአገራቸው ቋንቋ መናቆር ስለያዙ እንደዘፈን ቆጥሬው ከሰለሞን ጋር ወሬ ያዝኩ!... ግን ጭቅጭቃቸው እየከረረ ሲመጣ ባልሰማቸውም ትኩረቴን ወደ እነሱ አደረግኩ፡፡ ማርኮ ተናዶ በሩን በርግዶ ውጪ ቆመ፡፡ ኡምቤርቶን ምን እንደሆነ ችግራቸው ስጠይቀው፣ ባሪያ የአለቃውን ትዕዛዝ ከመፈፀም ውጪ የመከራከር መብት እንደሌለው ኮስተር ብሎ ነገረኝ፡፡ ገላምጬው ወደ ማርኮ ሄድኩ፡፡ ኡምቤርቶ የጣሊያን ምግብ ለእራት ማዘጋጀት ስለፈለገ ማርኮን ወደ ውስጥ እንዲገባ አዘዘው፡፡ እኔ ከማርኮ ጋር እንዳላወራ የተጠቀመበት ዘዴ መሆኑ ገባኝ፡፡

የአልጀዚራ የቴሌቭዥኑን ጣቢያ... የፍልስጤምን ድንጋይ ውርወራ፣ የእስራኤልን አትንኩኝ ባይነት፣ የኢራንን የነገር ጥንስስ ከኒውክሌርዋ፣ ያሣያል፡፡ ኡምቤርቶ እና ማርኮ ጭቅጭቃቸውን ረስተው በቋንቋቸው እያወሩ ይስቃሉ፡፡ እስራኤል እና ፍልስጤም ሁሉን ረስተው እንደ አገራችን ጥሩ ጐረቤታሞች በና ተጠራርተው

ይጠጡ ይሆን? እንዴት ሆኖ? እስራኤል እና ፍልስጤም ያነደዱትን እሳት ለመሞቅ የኋኳችው ኢራን ያከማቸችውን ጭድ እሳቱ ውስጥ ለመጨመር አሠፍስፋ ቆማለች፡፡ ባለ ውሀስ ይገኝ ይሆን?

ጊዜ ፈጣኑ ለአራት ሠዓት አድርሶን የጣሊያን ምግቦች በጣሊያናዊያን ቀረበልን፡፡ የሚጣፍጥ ምግብ ነው፡፡ ሁለቴ እንደጎረስኩ በሩ በሀይል ተንኳኳ፡፡ ሦስቱም አይኖቻቸውን እኔ ላይ ተከሉ!... ኡምቤርቶ ለመክፈት ተነሳ!... እንዲቀመጥ አዘዝኩት! ድጋሚ ተንኳኳ! ከፍቼ ወጣሁ፡፡ አብዲ ነው! አብዲ ለረጅም ሠዓት በዝምታ ተመለከተኝ፡፡ አይኔ ማረፊያ አጥቶ ተንከራተተ፡፡

«ይህን ነጭ ውሻ እደፋዋለሁ!» አለኝ፡፡

«ይህን ልትነግረኝ ነው የመጣኸው?» አልኩት ረጋ ብዬ፡፡

«ልነግርሽ የመጣሁት ሌላ ነገር ነበር፡፡ ግን በእሱ ጉያ ተሸጉጠሽ እንደምታድሪ ማስበው...»

«አብዲ እኔ እና አንተ እኮ መስማማት አልቻልንም፡፡ ስለዚህ....»

«እነዚህ ነጮች ትላንት አገራችን ለመውረር መጡ፡፡ ግን አልቻሉም! ዛሬ ሴራቸውን ቀይረው፤ በገንዘብ እያታለሉ እየገዙን ነው፡፡ አይገባሽም?»

ሳቄ መጣ፡፡

«ጠጥተሀል?»

«ጠጥቻለሁ! ግን የምናገረውን አውቃለሁ፡፡» ብሎኝ ሄደ፡፡

በስቀተን ስጋዬ ከሚያልቅ መወሰን አለብኝ! ኡምቤርቶን ወደ አገርህ መመለስ አለብህ አልኩት፡፡ አልሰማኝም፡፡ ጭራሽ እሱም እያለ ከአብዷ ጋር መሆን እንደምችል ዘና ብሎ ነገረኝ፡፡ ለእሱ ደህንነት ብዬ መከራዬን እንደማይ ቢያውቅ ኖሮ እንደዚህ አይነት መልስ ባልሰጠኝ ነበር፡፡ የቀረበው እራት ተነካክቶ ተነሳ፡፡ ሰለሞን እና ማርኮ ወጥተው ሄዱ፡፡ ኡምቤርቶን ደግሜ ደግሜ ወደ አገሩ በሰላም እንዲሄድልኝ ተማፀንኩት፡፡ እኔ የጠየኩትን ሁሉ ማድረግ ያስደስተዋል፡፡ ግን ይህን ጥያቄ መቀበል አልቻለም፡፡ ከእኔ መለየት ለእሱ የቁም ሞት ነውና!

«ከዚህ በፊት አፍቅረህ ታውቃለህ?» አልኩት ቢጨንቀኝ፡፡

«አላውቅም! ግን ጓደኛ ነበረችኝ!»

«ለምን ተውካት?»

«ስለማልወዳት! እሷ ግን ከነብሷ በላይ ትወደኝ ነበር፡፡ ዛሬ ፍቅር በእኔ ሲደርስ ምን ያህል እንደጎዳኋት ተረዳሁ፡፡»

ወዳጄ የእሷ እንባ ነዋ እኔ ላይ የጣለህ! ኡምቤርቶ ስለፍቅር ማውራት አይሰለችም፡፡ ፍቅር የስቃይ እና የደስታ ንጉስ ነው! እያለ አሞካሸው፡፡ እውነት ፍቅር ተብዬው እንዲህ የሚያደርግ ከሆነ ሀያል መባል ......... እንቅልፍ ወሬያችንን አቋረጠን፡፡

ጥዋት 2፡03 ሲሆን እንቅልፌ ተሰናበተኝ፡፡ ኡምቤርቶ አጠገቤ የለም፡፡ ስገላበጥ ግማሽ ሰዓት አልጋው ላይ ካሳለፍኩ በኋላ ሳሎን ሄድኩ፡፡ ስልኩን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ የለም፡፡ መፀዳጃ ቤት ገባሁ የለም፡፡ መቅዲን ስጠይቃት አላየሁትም አለችኝ፡፡ እሷ ከመምጣቷ በፊት ነው

የወጣው፡፡ በጥዋት የት ሄዶ ነው? በረንዳ ላይ ስንቆራጠጥ ከልፍለፉ ማርኮ መጣ፡፡ ለወንድሙ የሚሰጥ እቃ አስቀምጦለት እንደሄደ እንግዳ ተቀባይዋ ስትነግረው አብሮት እንዲሄድ ሊለምነው ነበር የመጣው፡፡ የሚለመነው እኮ ሰውየው ሲገኝ ነው፡፡ ማርኮ ግራ ገብቶት ማላዘን ሲጀምር ትቼው ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁ፡፡ ተከተለኝ፡፡

«ኤሚ አግቢው እና ፍቺ ትጠይቂዋለሽ! በዛ ላይ ንብረቱን እኩል የመካፈል እድል ይኖርሻል፡፡ አብሮኝ እንዲሄድ ካደረግሽ ደግሞ ጠቀም ያለ ጉርሻ እሰጥሻለሁ፡፡» አለኝ ማርኮ፡፡

ኡምቤርቶ ከየት እንደመጣ አላውቅም ዘሎ የማርኮን አንገት አነቀው፡፡ ደርቄ ቀረሁ፡፡ ማርኮ በቋንቋቸው ተበጣጥሮ ካሳመነው በኋላ የኡምቤርቶን እጅ ከአንገቱ ላይ አስለቀቀ፡፡ ኡምቤርቶ ትንሽ ከተረጋጋ በኋላ ማርኮን ከቤቱ ባስቸኳይ እንዲወጣ አዘዘው፡፡ ማርኮ እንባ እየተናነቀው ተሰናብቶት ወጥቶ ሄደ፡፡ ሁለተኛ ሳይነግረኝ ከቤት ቢወጣ ከእኔ ጋር እንደሚጣላ ነግሬው ወደ ሳሎን ልሄድ ስል ትቶቶ አልጋው ላይ ጣለኝ፡፡ ሊስመኝ ሞከረ፤ አልፈቀድኩለትም፡፡ ልብሴን ለማውለቅ ትግል ሲጀምር ገፍትሬው ከአልጋው ወረድኩ፡፡ እየተነጫነጨ ወጥቶ ሄደ፡፡

የማንነቱ ጥያቄ ስለረበሸኝ በሩን ቆልፌ ሻንጣውን መበርበር ጀመርኩ፡፡ ግን የእሱን እና የወንድሙ ማንነት የሚጠቁመኝ ምንም አይነት ነገር አላገኘሁም፡፡ ማስታወሻ ደብተሩን አገላበጥኩት፡፡ ያስገረመኝ ነገር በቀይ እስኪርቢቶ ብቻ መፃፉ ነው፡፡ አንድም በእንግሊዘኛ የተፃፈ

አሪፍት ነገር የለም፡፡ በጣሊያንኛ ብቻ የተፃፈ ነው፡፡ እነሱ ያለ ጥቁር ቦርሣ አገኘሁና ከፈትኩት፡፡ ሁለት ፎቶግራፍ እና ትልቅ የወርቅ ሀብል አለበት፡፡ ሀብሉ ላይ ያለው ማጫወቻ ክብ ነው፡፡ ምኑን ነክቼው እንደሆነ አላውቅም ክቡ ማጫወቻ ተከፈተ፡፡ ሁለት የሚመሳሰሉ ህፃናት ፎቶግራፍ ውስጡ አለ፡፡ ኡምቤርቶ እና ወንድሙ ይሆናሉ ብዬ ገመትኩ፡፡ ሀብሉን ቦታው መለስኩና ወደ ፎቶዎቹ ዞርኩ፡፡

አንደኛው ፎቶግራፍ ላይ ሁለት ህፃናት ያቀፈች ሴት አለችበት፡፡ የድሮ ፎቶግራፍ ነው፡፡ አክስቱ ከወንድሙ ጋር በህፃንነታቸው አቅፋቸው የተነሱት ነው ስል አሰብኩ፡፡ ምክንያቱም እናቱ እነሱን ከወለደች በኋላ ሕይወቷ እንዳለፈ አጫውቶኛል፡፡ ሁለተኛው ፎቶግራፍ ደግሞ የኡምቤርቶ እና የወንድሙ ለመሆን እርግጠኛ ነኝ፡፡ በቅርቡ የተነሱት ፎቶ ስለሆነ ለመለየት አልከበደኝም፡፡ ሁለንተናቸው ይመሳሰላል!.. የትኛው ኡምቤርቶ እንደሆነ መለየት አልቻልኩም! እናታቸው እንኳ የምትለያቸው አይመስለኝም!

ከአብዲ ተንኮል ኡምቤርቶን መጠበቅ በግ ከተኩላ ለማስጣል መሞከር እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ለዛውም እንደኔ አይነት እረኛ ያለው በግ፡፡ ቀኑን ሙሉ ስገባና ስወጣ ዋልኩ፡፡ ሰከንድ ደቂቃን እያስከተለ፣ ሰዓት ሰዓታትን ወለደ፡፡ ኡምቤርቶ የውሀ ሽታ ሆኖ ቀረ፡፡ የት ተብሎስ ይፈለጋል? የአብዲ ስልክ ጥሪ አለመቀበል ደግሞ ፍርሀቱን አጠናከረልኝ፡፡ ውጪ መቀመጥ ሲሰለቸኝ፣ ወደ ውስጥ ገባሁ፣ የባሎኑን በር በርግጄ፣ በሩ ላይ ዐይኔን እንደተከልኩ፣ ብርሃን በጨለማ ተሸንፎ ቀዝቃዛ አየር ወደ ቤቴ መግባት ጀመረ፡፡

..... ኡምቤርቶ ከሠማይ ዱብ ያለ ይመስል በር ላይ ተገትሮ ሳየው ተወርውሬ በጥፊ ደረገምኩበት፡፡ እልፎኝ ወደ መኝታ ቤት ገባ፡፡ ስለመታሁት ተፀፀትኩ፡፡ ለረጅም ሰዓት ሳንነጋገር ቆየን፡፡ አላስችል ስላለኝ አጠገቡ ተቀምጬ የት እንደዋለ ጠየቅኩት፡፡ የእሱ መጥፋት ሊያስጨንቀኝ እንደማይገባ አስረግጦ ነገረኝ፡፡

«ታዲያ እዛው ብታድር አይሻልህም ነበር?» አልኩት ተናድጄ፡፡

«ስለናፈቅሽኝ ነው የመጣሁት!»

«ራስወዳድ መሆንህን ማወቅ አለብህ!...»

«አውቃለሁ! ለምወዳት ሴት ስል፣ ህይወቴን አሣልፌ የምሠጥ ራስወዳድ፣ አንድ ወንድሜን ትቼ፣ በማላውቀው አገር፣ በብቸኝነት ባህር እንደዋኘሁ የምሞት ራስወዳድ፣...» አለቀሰ፡፡

«ቀኑን ሙሉ ስትጠፋ የማልጨነቅ ይመስልሀል?»

«ይህን ሁሉ የማደርገው ስለማፈቅርሽ ብቻ ነው!»

«በቃ ይቅርታ! አታልቅስ!.... ይቅርታ!» ግንባሩን ሳምኩት፡፡

«ለምን ይቅርታ ጠየቅሽኝ?»

«በጥፊ ስለመታሁህ! ስለተቆጣሁ!....»

«እጅሽ ሲነካኝ ልቤ በደስታ ይመታል! የተቆጡ አይኖችሽ በጨለማ የተከበበው ህይወቴን በብርሀን ይሞሉ-ታል፡፡ ቁጣሽ ስቃዩ ደስታዬ ነው!»

እሺ እኔ ምን ላድርገው? እኔ ፍርሀቴን እሱም ጭንቀቱን ረስቶ ገላችንን አብረን ታጥበን እራት ከበላን በኋላ አልጋ ውስጥ ገባን፡፡ ቀስ በቀስ የወሲብ ዛር ጓዙን ጠቅልሎ መጣ!... ባለጌ መሆኔን ዘንግቼ ከሀ

አላውቅም!... ግን እንደዛሬ ባልጌ የማውቅ አይመስለኝም!... መስሎኝ ሊሆንም ይችላል!... ግን ምን ነካኝ? በሰዓቱ እራሴን ያስረሣኝ ወሲብ ነበር፟... ተቃቅፈን ወደ ሁለተኛው ሞት ሄድን፣፣ እንቅልፍ!

ዱካክ እያገላበጠ ሲጫወትብኝ ስላረፈደ ተጫጭኖኛል፣፣ እርቃኔን መሆኔ ደግሞ ይበልጥ አስደንግጦኛል፣፣ ማታ ፒጃማ ለብሼ ነው የተኛሁት፡፡ ወይስ?... ?... እራሴን ጠየኩት ላስታውስ አልቻልኩም!... ኡምቤርቶን ለመጠየቅ ወደ እሱ ዞርኩ፣፣ ኡምቤርቶ የለም! ትራሱ ላይ ብጫቂ ወረቀት ተቀምጧል፣፣ «ሁሌም አፈቅርሻለሁ!» የሚል ፅሁፍ በእንግሊዘኛ ሰፍሮበታል፣፣ ወደ ሳሎን ስሄድ አብዲ ሶፋው ላይ ተቀምጦ የኡምቤርቶን ስልክ ያገላብጣል፣፣ ደነገጥኩ፣፣

«ፈረንጁ ባልሽ ቦሌ መዳኃኒያለም ቤተክርስቲያን ምን ሊያደርግ እንደሄደ ካልነገርሽኝ ከዚህ ቤት አልወጣም!» አለኝ፣፣

የእሱ ቤተክርስትያን መሄድ አስጨንቆት ሳይሆን እየተከታተለው እንደሆነ እንዲገባኝ ፈልጎ ነው፣፣ በማያገባው ነገር ስራ እየፈታ መሆኑን አስረዳሁት፡፡ ፀጉሬን ጨምድዶ «ራስወዳድ ሸርሙጣ ነሽ!» አለኝ፡፡ አልከፋኝም! በኡምቤርቶ ፍቅር መነደፌ ራስወዳድ እንዳደረገኝ አረዳሁት፣፣ ሁለተኛ ዞር ብሎ እንደማያየኝ ቃል ገብቶ ወጥቶ ሄደ፣፣ የተናነቀኝን እንባ ዋጥ አድርጌ ቦርሣዬን አንጠልጥዬ ወደ ቦሌ መዳኃኒያለም ቤተክርስቲያን ሄድኩ፣፣

ቀኑ እሁድ መሆኑ ትዝ ያለኝ ግቢው በመኪና እና በሰው መጨናነቁን ላይ ነው፡፡ ምናልባትም ቀኑ 27 ሊሆን ይችላል፡፡ ኡምቤርቶን በአይኖቼ ፈለግኩት ላገኘው ግን አልቻልኩም፡፡ ቅዳሴው ሲያበቃ ሰዉ ቀስ በቀስ ግቢውን እየለቀቀ ወጣ፡፡ ኡምቤርቶ የለም! ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡ ውሎዬን ለመግለፅ እቸገራለሁ፡፡ ኡምቤርቶ ቀኑን ሙሉ ተደብቆ ጅብ ከጉሬው ሲወጣ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ ገላውን ታጥቦ እራት ከበላን በኋላ የዋለበትን ጠየኩት፡፡ ከትእግስት እና ከጓደኞቿ ጋር ሓት ሲቅም እንደዋለ አረዳኝ፡፡

«ቤቷን እንዴት አወቅከው?» ነበር የመጀመርያ ጥያቄዬ፡፡

«እቃዋን ይዛ የወጣች ቀን ደወለችልኝ!»

«ስልክህን ለምን ሰጠሀት?»

«ካማርኮ ስልክ ውስጥ ነው የወሰደችው!»

«ብዳሀት?»

«ብፍፁም!»

«አላምንህም!»

«አላዋሽሁሽም! ግን... ጠብታልኛለች!»

ግን ለምን? ማለቴ ካልወደድኩት ለምን ተናደድኩ? ማልቀስ ሁሉ አምሮኝ ነበር፡፡ ድንገት ራሱን ይዞ ተንሠቅሥቆ ማልቀስ ጀመረ፡፡ ስለተናደድኩ ዝም አልኩት፡፡ «ሰዓቱ ደረሰ!... ደረሰ!» አለ፡፡ እንዳልሰማ ዝም!... «ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ነው!...» አለ፡፡ ምን አቅምሰውት ነው ብዬ ተጨነቅኩ! ሀኪም ቤት እንሂድ ስለው እምቢ አለኝ፡፡ ድንገት ቤቱን በጩኸት አደባለቀው፡፡ ጭንቅላቱን ከግርግዳ

እያጋጨ በጣሊያንኛ ከቀባጠር በኋላ ጉሮሮዬን አንቆ ግርግዳው ላይ ለጠፈኝ፡፡

«እገልሻለሁ!... አብረን እንሞታለን!...»

«እባክ... ል.ቀ.ቀ.ኝ!»

ለቀቀኝ!

«ምንድነው? ጐዳሁሽ?» አለ በስስት እየተመለከተኝ፡፡

«አንተ እብድ ነህ! ወደ አገርህ ወይም ትእግስትጋ መሄድ አለብህ!» ፈራሁት!

«ይቅርታ የኔ ፍቅር! ምን ሆኜ እንደሆነ አላውቅም! የሆነ...»

«እሱ ያንተ ችግር ነው! ልትገለኝ ነበር እኮ...እብድ!»

ከሰንቴ ጋር ተናንቄ እችለዋለሁ? መብራቱን አጥፍቶ ጀርባዬን ሰጥቼው ተኛሁ፡፡ የኡምቤርቶ ነገር እንቆቅልሽ ሆኖብኛል! የአእምሮ በሽተኛ ይሆን? ስል እራሴን ጠየኩት፡፡ ባይሆንማ ጠባቂ ባልታዘዘለት ነበር፡፡ ቀስ ብዬ መብራቱን አበራሁ፡፡ እንቅልፍ ወስዶታል፡፡ ለረጅም ሰዓት በዝምታ ተመለከትኩት፡፡

ፍቅር በሚለት ውበቱ ሁሊም በሰራው እጅ እንድደነቅ ያደርገኛል፡፡ ውበቱ ከአባዴ እንደሚበልጥ በሽታ የተለከፈ አማባኝ ፍጡር ነው፡፡ ውበት የማይገባኝ ውበት አለው፡፡ አውቃለሁ፡፡ አባዲ ግን የሆነ የማላውቀው የማይገባኝ ውበት አለው፡፡ የሆነ ሊዳሠስም ሊጨበጥም የማይቻል፣ ለመግለፅም ሆነ ለመረዳት የሚከብድ ማንነት፣ መጥፎነቱን እያወቁ ጥሩ ነው እያሉ የሚያጣጥሙት ጠዓም ባለቤት ነው፡፡ ወይስ ወሲብ ላይ አፍርሶ ስለሚሰራኝ እና ስለተመቸኝ? አላውቅም!

ለምን ይሆን እነዚህን ሁለት ሰዎች የማወዳድረው? ለምንስ ስለ እነሱ አስባለሁ? ከወንዶች ጋር የሚያገናኙኝ የወሲብ እና የገንዘብ ፍላጎት ብቻ ነው! ስለዚህ ፍላጎቴን ከሚሟላት ውጪ መጨነቁ... «እብደት ነው!» ኡምቤርቶም ሆነ አብዲ ጠዓሙ እንዳለቀለት ማስቲካ ለመተፋት ጊዜያቸውን የሚጠብቁ የአዳም ዘሮች ናቸው፡፡ አሁን አሁን እራሴን እየተጠራጠርኩት ነው፡፡ ምክንያቱም የማስበውና የማደርገው ለየቅል እየሆነብኝ ነው፡፡ የመሆን ህልምን እንጂ መሆንን ማግኘት አልቻልኩም! ለምን ይሆን? ማስታወሻዬን ትራሴ ስር ሸጉጬ መብራቱን አጠፋሁ፡፡ ዛሬ ነገ እስኪሆን ድረስ በእንቅልፍ ማሳለፉ የተሻለ ነው፡፡

ማስታወሻዬ ሆይ... አፈር ቅጠል ሆነ ሲሉኝ ተቀበልኩ፡፡ ቅጠል አፈር ሆነ ሲሉኝም አልተቃወምኩም፡፡ በዚህም አሳበቱም ጭቃ ስጋ ሆነ ብለው ሰው ከአፈር መገንባቱን ተረኩልኝ፡፡ ኡምቤርቶ ከአፈር ነው የተሰራው? አይኖቼ ተተክለው እንዲቀኑበት የሚያደርግ ውበት ያለው ሰው ከአፈር ነው የተሰራው ሲሉኝ እንዴት አልጠራጠር?

አሁን እኔን የጨነቀኝ የኡምቤርቶ መጥፋት ነው! የዛሬውን ደግሞ ለየት የሚያደርገው እሱ እና ወንድሙ በልጅነታቸው የተነሱት ፎቶ ያለበትን የወርቅ ሀብል ከእንቅልፌ ስነቃ አንገቴ ላይ ማግኘቴ ነው፡፡ የእገሬ ስራእጥ በመስረቅ ስለሚተደደር የሰው ሀብል ከአንገቴ ላይ በጥሶ እንዳይወስድብኝ ኮሜዲኖዬ ውስጥ ቆለፊኩበት፡፡ መስረቅ ራሱ ሥራ ነው ተብሎ የለ! መስረቅ ራሱ ሥራ ነው ካለ.... ሰው ሁሉ ሌባ ቢሆን ምን ይደንቃል? ስራእጥ ማለትም አይጠበቅብኝም!

ኡምቤርቶ እንደለመደው ሲጨልም ወደ ቤት ይመለሳል ብዬ ስላሰብኩ ውስጡ ያለውን ፍርሀት በውሸት ወኔ ሸፈንኩት፡፡ ፈጣሪ ደግ ነው! ስሌ ሜት ገዝቶ ከምሳ ሰዓት በኋላ ከች አለ፡፡ ብቸኝነት ተሠምቶኝ ስለነበር በመምጣቱ ተደስቻለሁ፡፡ የመቃሚያ ፍራሹ ላይ ተሠይመን አፌር ነው ያሉትን ቅጠል እየቀነጠብን ወደ አፋችን መከተት ጀመርን፡፡ አፌር አፌርን እንዴት ይበላል? እራሡን በራሡ ነጠፋ እንዴት መንግስቱ ትፀናለች? ነው አፌር መንግስት የለውም?

ስሌ ማርኮ እገሩ ከገባ በኋላ ባለመደወሉ ተጨንቋል፡፡ ማርኮ እንደፈራው አልቤርቶ ገድሎት ቢሆንስ የሚል ፍራቻ ውስጡ አድሯል፡፡ እኔ ደግሞ አብረያቸው እንድሄድ የፈጠሩት ድራማ ነው ባይ ነኝ፡፡ ሥራቸው ሁሉ ግራ ስለሆነ የእነሱን ነገር መርሳት ነው የሚሻለው፡፡ ብቸኝነት እኔ እና ስሌ ጋር አለ፡፡ እሱ እኔ ጋር መኖር ቢጀምር የሁለታችንም ብቸኝነት መፍትሔ አገኘ ማለት ነው፡፡ ስሌን እኔ ጋር እንዲኖር ስጠይቀው ያለምንም ማንገራገር መስማማቱን ገለፀልኝ፡፡ ደስ አለኝ! ሰው እስከነክፋቱ አስፈላጊ ነው! ስሌ ሲያሜውተኝ ውሎ ስልኩ ሲጮህ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡

ሲጋራ ለኩሼ የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥ አደረኩት! ሰማዩ ባኮረፈ ደመና ተሸፍኗል!... ቀስ በቀስ ኩርፊያው ወደ ለቅሶ ተቀየረ!... የክረምት ነገር ማላዘን ነው!... ኡምቤርቶ የሚመጣበት ሠዓት ደርሷል!... የለኮስኩትን ሲጋራ ምኜ ከጨረስኩ በኋላ፣ እራት አቅርቤ ረጅም ነጭ ስስ ፒጃማዬን ለበስኩ፡፡ ሽቶ አንገቴ ስር ረጨሁ! ፀጉሬን ወደኋላ ሙጥጥ አድርጌ

አስያዝኩት!... አላማረኝም! ለቀቅኩት!... መብራት ጠፋ! ሻማ ደግሞ በቤቱ የለም!

ስማዩ እንባውን ወደ ምድር መልቀቁን አላቋረጠም፡፡ ሆንጥላዬን ዘርግቼ ወደ ሱቅ ሄድኩ፡፡ ብርዱ ስስ ፒጃማዬን አሸንፎ ገላዬን አኮራመተው፡፡ ሻማውን ገዝቼ ወደ ቤት እንደተመለስኩ በጭቃ የተጨማለቀ ጫማዬን እቃ ቤቱ ውስጥ ወርውሬ ሻማውን ለኩሼ በባዶ እግሬ ወጥቼ በረንዳ ላይ ተገተርኩ፡፡ ኡምቤርቶ በጣም ቆየ፡፡ ስደውልለት ስልኩን አያነሳም፡፡ ወዲያው ትእግስት ደወለችልኝ፡፡ ከእሷ ጋራ አለሙን እየቀጨ መሆኑን እንዳውቅ ፈልጋ መሆኑ ስለገባኝ ዘጋሁባት፡፡ እራቴን ሳልበላ ሻማውን አጥፍቼ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ፡፡ የተሸነፍኩ መስሎ ስለተሰማኝ በጣም ተናድጃለሁ፡፡ ቀርፋፋው ለሊት ዐይኔ እንዳፈጠጠ ነጋ፡፡

ጥዋት ባልበላ አንጀቴ የራስ ምታት ኪኒን ወሠድኩ፡፡ በላዩ ላይ ሁለት ሲጋራ ማብኩበት፡፡ እውነት ለመናገር ተቃጥያለሁ! የኡምቤርቶን ሽንገላ ሳሎን አስቀምጬ መምጣቴን እየተጠባበቅኩ ነበር፡፡ ግን ትእግስት ናት የመጣችው፡፡ ቃድያ ይሄ አያናደድም? ሽንጣዬን እምጨልኝ ብለ ላከሽ? አልኳት አይኔን አጉረጥርጬ፡፡ እሷ ግን ተረጋግቼ እንዳዳምጣት ተማፀነችኝ፡፡

«መጠጥ አሳስቷችሁ አብራችሁ እንዳደራችሁ ወይስ የተበሣ ቂጥሽ ስለተመቸው አንቺን እንደመረጠ፡፡»

«አንቺ እንደምታስቢው ሳይሆን ኡምቤርቶ...»

«ልትዋሺኝ ባትሞክሪ ጥሩ ነው!»

«ይህን ሦስት ቀን ከእኔ ጋር ነበር የሚውለው… ከዛ ሲመሽ ወደ ቤት እንደሚመለስ ነው የማውቀው!… ከትላንት ምሽት በስተቀር!…»

«አዳርስ ለምን ይቅርባችሁ?»

«እኔ አብሬው ማደር ፈልጌ ነበር!… አንቺን ለመበቀል!… ግን ድንገት ራሱን ስቶ ወደቀ፡፡»

ጥሩ ማስተባበያ ነው! ቀጠለች….

«አልጋ ይዘን ልብሳችንን ካወላለቅን በኋላ ወንድሙ ጋር ደውሎ እያለቀሰ በጣሊያንኛ ሲያወራ ቆይቶ ጭንቅላቱን ይዞ መጮህ ጀመረ፡፡ የሆቴሉ አስተናጋጆች በሩን በርግደው ገቡ፡፡ እኔ ፈርቼ የሚሆነውን ከማየት ውጪ የረዳሁት ነገር አልነበረም፡፡»

ትዕግስት የውሸት ሊቅ ናት!

«እራሱን ስቶ ከወደቀ በኋላ አረፋ በአፉ እየደፈቀ መውጣት ጀመረ፡፡ ሀኪም ቤት እስኪደርስ ድረስ ህይወቱ እንዳልወጣች እርግጠኞች ነን፡፡ ሀኪም ቤት ከደረሰ በኋላ ሀኪሞች መሞቱን ነግረውን ወደ ተኛበት ክፍል ስንገባ አጣነው፡፡» አለች እጇን እያፍተለተለች፡፡ ሳቄ መጣ!…ማለቴ ያስቃል!

«መንፈስ ሆነ ለማለት ፈልገሽ ነው?» አልኳት አልቆም ያለኝን ሳቅ እየታገልኩ፡፡

«እያሾፍኩ አይደለም! ሰማያዊ አይኖቹ በቀይ ተለውጠው ነበር… ሰውነቱ አመድ መስሎ…»

«ሰውየው ሲጀመር አመድ ነው!... ስለዚህ ልታሳምኚኝ አትሞክሪ!»

«ኤሚ ማርያምን የነገርኩሽ ሁሉ እውነት ነው!»

«ሞተ ብለው ሀኪሞች ከነገሯችሁ የት ሄደ?»

«እሱ ነው የጨነቀኝ! ሀኪም ቤቱ ታሰሰ አልተገኘም!»

የሞተና የደከመ መለየት የማይችል ሰው እንዴት ሀኪም ይሆናል? ለነገሩ ትእግስትን ማመን ከባድ ነው:: የነገረችኝ ሁሉ አዋጪ ቲያትር መሆኑን ነግሪያት ከቤቴ እንድትወጣልኝ በሩን ከፈትኩላት:: እየተመናቀረች ወጥታ ሄደች:: ከሀኪም ቤት ከጠፋ በኋላ ለምን ወደ እኔ አልመጣም? ትእግስት ውሸታም ናት! ለምን አምናታለሁ? ለሁለት የፈጠሩት ድራማ ነው! የምፈልገውን ነገር አድርጎልኛል!... ከበቂ በላይ!... ከአሁን በኋላ አልፈልገውም!!

ሁሉን ለመርሳት እና የከዳኝን እንቅልፍ ለማግኘት... ሁለት ስኒ አረቄ ጠጥቼ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ:: ግን ኡምቤርቶ ጋር ነበርኩ!... ለገንዘቡ ብቻ የምፈልገው ከሆነ ለምን ቀናሁ? መናደድ፣ መቅናት ላይሆን ይችላል!... አረቄው ሰውነቴን ገደለብኝ፣ ዓይኖቼ ክፍት ክድን ሲሉ ቆይተው ተከደኑ:: ሰለሞን የመኝታ ክፍሌን በር ከፍቶ ሲገባ ሰመመን ውስጥ ነኝ:: ሠራተኛሽ እቃህን ይዘህ አትግባም ብላኝ ነው! ያለኝ መሰለኝ:: በምልክት የሆነ የማላስታውሰውን ነገር አልኩትና ወደ ረፋዱ እንቅልፌ ተመለስኩ::

*.....ኡምቤርቶ በውሀ የተከበበ በጣም ትልቅ ተራራ ላይ ቆሞ ያለቅሣል፡፡ ሁለት አሞራዎች እየጮሁ እንዣበቡበት፡፡ ኡምቤርቶ ፈርቶ ከተራራው ለመውረድ ሲታገል ውሀው ውስጥ ወደቀ፡፡ እኔ ላድነው ልብሴን አውልቄ እራሴን ወደ ውሀው ልወረውር ስል አሞራዎቹ ሰውነቴን ከላይ እስከታች እየነከሱ ጣሉኝ!...*

ከአልጋዬ ተስፈንጥሬ ተነሳሁ፡፡ መኝታ ቤቴ ውስጥ ነኝ፡፡ ቅዠት ነው!... ቀን የማስበው ነው!... የቀን ህልም ይሰራል እንዴ? አይሰራም!... ወደ ሳሎን ሄድኩ፡፡ ሰለሞን ቁጭ ብሎ ስልኩን ይነካካል፡፡ ግርግዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት ላይ አፈጠጥኩ፡፡ ገና ከቀኑ 7:00 ሰዓት ነው፡፡ ግን ብዙ አንቀላፍቼ ነበር፡፡ ኡምቤርቶን በህልሜ እንዳየሁት ለሰሌ ነገርኩት፡፡ ቀን የማስበውን በቅዠት መልክ እያስተናገድኩ እንጂ ህልም አለመሆኑን አስረዳኝ፡፡ ትንሽ ተፅናናሁ! ሰለሞን ዞር ዞር ብዬ ልምጣ ብሎኝ ወጥቶ ሄደ፡፡

እቃውን እንዴት እንዳስቀመጠው ለማየት ብዬ ክፍሉ ስገባ፤ ግርግዳው በአሜሪካ ራፐሮች ፎቶግራፍ ተወሯል፤ አልጋው ባማረ የአልጋ ልብስ ተሸፍኗል፤ የቁምሳጥኑ በር ላይ የድንግል ማርያም ስዕል ተለጥፏል፤ የመጽሐፍ መደርደርያም አለው፤ የተለያዩ የትርጉም መጽሐፎች እና መጽሐፍ ቅዱስ ተቀምጠበታል፤ መጽሐፍ ቅዱስ እና የድንግል ማርያምን ስዕል በማየቴ ተደንቂያለሁ፡፡ የሽቶ አይነት አልጋው ጎን ካስቀመጣት አነስ ያለች ጠረጴዛ ላይ አየሁ፡፡ ሁሉንም እያነሳሁ ተመለከትኩ፤ የሴት ሽቶዎች ናቸው፡፡ ቆይ ቂጡ ተበሳ ማለት ፆታው ተቀየረ ማለት ነው እንዴ? ቀሚስ ለብሶ፤ ሊፕስቲክ መቀባት ብቻ

ነው'ኮ የቀረው፤ ሴታሴትነቱን እንደሆነ ተከናታል፡፡

....እድሜ ለክረምት መከረኛው ዝናብ መውረድ ጀመረ፡፡ ሞባይሌ ጮኸ! የውጪ ስልክ ነው! ማርኮ ይሆናል ብዬ ፈጠን ብዬ አነሳሁት፡፡ «ኡምቤርቶ ሞተ?» አለኝ በስልኩ ውስጥ ያለው ሰው፡፡ የማርኮ ድምፅ አይደለም፡፡ «ከሞተ አንቺም ሟች ነሽ!» ስልኩ ተዘጋ፡፡ ደዋዩ ጥርት ያለ እንግሊዘኛ ስለተናገረ ገብቶኛል፡፡ ኡምቤርቶ እሞታለሁ ሲለኝ የነበረው እውነቱን ነበር ማለት ነው? ወይኔ! ኡምቤርቶ ሞቷል! ከሀኪም ቤት ወጥቶ ወደ እኔ ሲመጣ ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ቱቦ ውስጥ ገብቶ ሞቶ ነው፡፡ ምርር ብዬ አለቀስኩ፡፡ ከሀኪም ቤት ሲወጣ አብዲ አግኝቶት ገሎትም ሊሆን ይችላል፡፡ አብዲጋ ደውልኩ፡፡ ስልኩን ሴት አነሣችው፡፡

«ስልኩን ለባለቤቱ ስጪው!» ጮህኩባት፡፡

«ምን ላድርግሽ?» አለኝ አብዲ፡፡

«አብዲ ኡምቤርቶን የገደልከው አንተ ነህ?»

«አዎ! ለምን? እንዳትዪኝ!...»

«አብዲ እባክህ ውሸቴን ነው በለኝ፡፡»

«እኔ ነኝ የገደልኩት! ፖሊስ ጣቢያ አመልክቺ፡፡»

«ገድለህ የት ጣልከው?»

«ኡው!... አታገኚውም!» ስልኩን ጆሮዬ ላይ ጠረቀመው፡፡

ለማን አቤት ይባላል? ምንስ ማስረጃ አለኝና? የሀገራችን ፖሊሶች ማስረጃ ካልቀረበላቸው በስተቀር ጉዳዩን ተከታትሎ ወንጀላኛን መቅጣት አይሆንላቸውም!! ማስረጃ ቢኖረኝስ? አብዲ ገንዘቡን

ይጭነቀው ጠዋት ታስሮ ከሠዓት ይፈታል! ገንዘብ ሀያሉ ያለው… አለምን ይገዛል!

የሀሳብ መዓት በጭንቅላቴ ውስጥ ይራወጣል፡፡ አዙሪት እንደያዘው ሰው ለረጅም ሰዓት ሳሎን ውስጥ ስሽከረከር ከቆየሁ በኋላ ሲጋራ ፍለጋ የቦርሳዬን እቃ አልጋዬ ላይ ዘረገፍኩት፡፡ የለም! ሰዐቱ ደግሞ የብርሀን ሳይሆን የጨለማ ነው፡፡ ግን ማጨስ አለብኝ፡፡ አረንጓዴ ብር ጨብጬ ወጣሁ፡፡ ሰዓቱ ስለገፋ ሱቆች ተጠርቅመዋል፡፡ ወደ አንዱ ግሮሰሪ አመራሁ፡፡ አንድ ቢራ እና ፓኮ ሲጋራ አዘዝኩ፡፡ ቂጧ ላይ የተጣበቀ በጣም አጭር ጉርድ የለበሰች ወጣት አስተናጋጅ፣ ማስቲካዋን እያላመጠች ያዘዝኩትን አመጣችልኝ፡፡ መቶ ብሩን ሰጥቻት ቢራውን እና ሲጋራውን ይዤ ወጣሁ፡፡

ቢራውን በጥርሴ ከፍቼ እየጠጣሁ ወደ ቤቴ ሳዘግም አንድ ሰካራም ፊት ለፊቴ ተገተረ፡፡ አልፌው ልሄድ ስል እጄን ያዘኝ፡፡ «ሴት መሆንሽን የዘነጋሽ አይመስልሽም? ለዛውም ቆንጆ!» አለኝ፡፡ ግራ ቀኜን ተመለከትኩ፡፡ ማንም የለም! ስለዚህ ለእራሴ ያለሁት እኔው እራሴ ነኝ! የቢራ ጠርሙሴን በደንብ ጨበጥኩት፡፡ «መልሽልኛ!» አለኝ ወደ አፌ እየተጠጋ፡፡ «አደፍርስ ባስፈለገኝ ሰዓት በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል፡፡» አልኩት፡፡ የምስመው መስዬ ወደ አፉ ይበልጥ ተጠጋሁ፡፡ አቀፈኝ! የያዝኩትን የቢራ ጠርሙሱ ለመብዳት የቋመጠ ቆለጡ ላይ በደንብ አድርጌ ወሸቅኩለት፡፡ አፉን እንደከፈተ አጐነበሰ፡፡ ሴት መሆኔን አልዘነጋም!

እቤቴ ገብቼ ሲጋራዬን ለኮስኩ፡፡ ሱሰኛ ሆኛለሁ! ጠምቶኝ ስለነበረ በረጅሙ እየሣብኩ በምለቀው ጪስ ውስጥ አብዲን አያለሁ፡፡ እንቅልፍ የሚባል ነገር የማይታሠብ ስለሆነ ሲጋራዬን እየሣብኩ እስኪነጋ መጠበቅ አለብኝ፡፡

ሰዓት ሰዓታት እየሆነ ሄደ!. የጨለማ ሀይል በብርሃን ተሸንፎ ወፎች መንጫጫት ጀመሩ፡፡ እንቅልፍ የሚባል ነገር ያላየው ዐይኔ ፈዟል፡፡ ጥቁር ጡት መያዥያ እና ፓንት ፍለጋ መሳቢያው ውስጥ ያለውን ጡት መያዣና ፓንት መሬት ላይ ዘረገፍኩት፡፡ በካኪ ወረቀት የተጠቀለለ ነገር አብሮ ዱብ አለ፡፡ አገላበጥኩት፡፡ የኡምቤርቶ ስም ካኪው ላይ ተቀምጧል! ከፈትኩት! ውስጡ ገንዘብ አለ! እያለቀስኩ ገንዘቡን ከነካኪው ደብቄ፤ ልብሴን ቀይሬ፤ ከቤቴ ወጣሁ፡፡

አብዲ ማነውና በኔ ህይወት ያዛል?... ከራሴጋ እየተጨቃጨኩ አብዲ ቤት ደረስኩ፡፡ ዘበኛው በር ላይ ቆመው ስልክ ያናግራሉ፡፡ ሲያዩኝ ስልኩን ኪሣቸው ውስጥ ከተው ሰላምታ ሰጡኝ፡፡ አልፌያቸው ወደ ግቢው ልገባ ስል አብዲ ድሬዳዋ መሄዱን አረዱኝ፡፡ እውነትም የኡምቤርቶ ገዳይ አብዲ ነው! ድንገት ፖሊስ ገዳዩ እሱ መሆኑን ካወቀ፤ ይይዘኛል ብሎ ፈርቶ ነው ወደ ድሬዳዋ የሸሸው፤ አልኩ ለራሴ!

ኡምቤርቶ በመሞቱ ውስጤን ከፍቶታል! አለቀስኩ! እኔ እኮ የሰው ልጅ ስቃዩ እንጂ ሞቱ አስለቅሶኝ አያውቅም፡፡ ታድያ ለምን አለቀስኩ? በሽታውን የማያውቅ ሰው መድኃኒት ከየት ያገኛል? በትራሴ ተደብቄ ከራሴ ጥያቄ ለማምለጥ ሞከርኩ፡፡ መልስም ማምለጥም የለም!

# ክፍል ስድስት

## *ሰዶም በኢትዮጵያ*

ሰው በመረጠው መንገድ እሄዳለሁ ብሎ ጉዞ ይጀምራል፡፡ ግን ደግሞ እግሩ ወይ ልቡ ወደ ማያውቀው መንገድ ይመራዋል፡፡ ያኔ መመለሻው ይጠፋውና ልቡን ወይ እግሩን እያዳመጠ ይኖራል፡፡ ጥፋቱ መጀመርያ ለሁለቱ እድል መስጠቱ ላይ ነው፡፡ ሰለሞን በጥዋት ፀጉሩን እየነጨ እና እያለቀሰ እንደገባ መቅደስ ስትነግረኝ ወደ ክፍሉ ሄድኩ፡፡ ለቅሶው አላባራም፡፡ ምን እንደሆነ ስጠይቀው ጭራሽ ባሰበት፡፡

«ተይኝ!... ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቼ ነው!...»

«ለምን?»

«ግደለኝ እያልኩ ስለምነው፣ እንቢ አለኝ፡፡»

«አንተ ምን ትሰራለህ?»

«ታነቅኩ! ዳንኩ! መርዝ ጠጣሁ! ይኸው እተነፍሳለሁ! ሌላው ይቅር! ሞት እንኳ እከለከላለሁ?» አለ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ፡፡

«ምንድነው እንዲህ ያስከፋህ? ንገረኝና መፍትሄ እንፈልግለት!» አልኩት፡፡ ጠንቋይ ለራሱ አያውቅ...

«ቆይ አንቺ ማነሽ? እኔን የሚፀየፈኝ እንጂ የሚቀርበኝ ሰው የለም! አንቺ ግን...»

«ውስጥህ ተጋድሞ የሚያስለቅስህን ሀዘን መንቅሬ አወጣና ገብቼ ጋደም እላለሁ፡፡ አይዞህ አልካበድም!... ትስማማለህ?» አልኩት፡፡

ጭንቅላቱን በመነቅነቅ መስማማቱን ገለፆልኝ፡፡ ከትናንሽ አይኖቹ የሚወርደውን እንባ ጠረግኩለት፡፡
ሰለሞን ትረካውን ጀመረ....

«ሀይላይ ሁለት ወር ሙሉ ከዘጋኝ በኋላ... ቀኑ ቅዳሜ መሆኑን አስታውሳለሁ፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ደውሎ በጣም ችግር ላይ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ የእናቴን ልመና ችላ ብዬ እየበረርኩ ያለበት ቦታ ድረስ ሄድኩ፡፡ ባለስልጣኖች በድብቅ የሚዝናኑበት ቦታ በመሆኑ እንደፈለገ ማንም መግባት አይችልም፡፡ ውጪ ሆኜ ለሀይላይ ስደውልለት፤ በር ላይ የተገተሩት ጠብደሎች እንዲያስገቡኝ ከውስጥ ሰው ላከ፡፡ ገባሁ፡፡ ሀይላይ ከአንድ ባለስልጣን ጋር ቁጭ ብሎ ይቀመቅማል፡፡ ናፍቄው ሊያየኝ ፈልጐ የፈጠረው ዘዴ እንደሆነ ሲነግረኝ ተረጋጋሁ፡፡ አጠገቡ የተቀመጡት ባለስልጣን አጐቱ እንደሆኑና ሊያስታርቁን እንደተገኙ ትከሻዬን መታ መታ እያደረጉ ገለጹልኝ፡፡ በአካል አላውቃቸውም እንጂ በቴሌቭዥን መስኮት አይቻቸው አውቃለሁ፡፡» ሰሌ በረጅሙ ተንፍሶ ትረካውን ቀጠለ....

«ባለስልጣኑ ውስኪውን ወተት ያገኘ ድመት ይመስል እየተስገበገቡ ነው የሚጨልጡት፡፡ ጨዋታ ይችሉበታል! እኔ እና ውስኪ በስም እንጂ በአካል አንተዋወቅም ነበር፡፡ የቅዳሜዋ ምሽት ከብዙ ነገር ጋ አስተዋወቀችኝ፡፡ እራሴን እስክስት ድረስ ጠጣሁ፡፡ ከዛ...» ጉሮሮውን ተናነቀውና ትንሽ ዝም ብሎ ቀጠለ!....

«እሁድ ጠዋት እራሴን ያገኘሁት አነስ ባለች ክፍል ውስጥ በተነጠፈች ስስ ፍራሽ ላይ ነበር፡፡ ወይኔ!... እራቁቴን ነኝ! ለመነሣት

ሞከርኩ!... መቀመጫዬ መሀል ህመም ተሰማኝ! እየፈራሁ ጣቴን ላኩት!... ደም ይዞ መጣ፡፡» አቋረጥኩት!

«ተደፍረህ ነው እንዴ ሰሌ?» አልኩት፡፡

«አዎ! እንደምንም ብዬ ቤቴ ደረስኩ፡፡ ክፍሌ ገብቼ የሆንኩት ነገር ለማስታወስ ታገልኩ፡፡ ግን አልቻልኩም! ብርሀን ወጾም ሆነ ሳይወድ በጨለማ ተተካ፡፡ ሀይላይ ደውሎ አጐቱ ሊጋብዙኝ እንደሚፈልጉ ነገረኝ፡፡ እኔም የቅዳሜ ምሽት ምን ጠንስሳልኝ እንደነበር ለማወቅ መዝናኛ ቦታቸው ተገኘሁ፡፡ ጭራሽ አብሮኝ የነበረው ማን እንደሆነ ጠየቁኝ! ግራ ገባኝ! ተሰናብቻቸው ከሆነ ፈርጣማ ጎረምሳ ጋር እንደወጣሁ ሲነግሩኝ ጎረምሳውን ለማስታወስ ከጭንቅላቴጋ ትግል ጀመርኩ፡፡ አልተሳካልኝም! የሰው ግብዣ አይናቅም ስባል እንደ ጅብ የቀረበልኝን ወደ አፌ መላክ ጀመርኩ፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት እራሴን ስሷ ፍራሽ ላይ አገኘሁት!» ሰሌ አለቀሰ፡፡

«የሆንኩት ሳይሆን የሆንኩትን አለማወቄ አስለቀሰኝ፡፡ ወደ ቤት ሄጄ ተኝቼ ሳለቅስ ዋልኩ፡፡ ሲመሽ አስታራቂው የጓደኛዬ አጐት ደውለው የሆንከውን እነግርሀለሁ ብለው የተለመደው ቦታ ቀጠሩኝ፡፡ በነገራችን ላይ እዛ ቦታ ለመግባት ባለስልጣኖቹ ስምሽን በር ላይ ለሚገተሩት ጠብደሎች ማሳወቅ ግዴታቸው ነው፡፡ ያንን ካላደረጉ ማንም አያስገባሽም፡፡ የኔ ስም ጠብደሎቹጋ ስላለ አልተጨናነቅኩም፡፡» አንጀቴ ተላወሰ!... ሰሌ እያማጠ ትረካውን ቀጠለ፡፡

«ጉዴን ለመስማት ጆሮዬን አቆምኩ! መጀመሪያ ቀን ይዞኝ የሄደውን ጎረምሳ ሲጠይቁት... ሚስቴ ነው! አንተ ማነህ? ብሎ እንዳፈጠጠባቸው ሲነግሩኝ አፌን እንደከፈትኩ ቀረሁ፡፡ ወንድ ባለሚስት እንጂ ባለባል እንዴት ይሆናል? እኔ ባለ ባል? ስል 'ራሴን በጥያቄ አፋጠጥኩት፡፡ አልመለሰልኝም! በመጠጡ ውስጥ ጎረምሳውን ማግኘት የምችል ይመስል በቃህ ስባል አሻፈረኝ እያልኩ ይህን መጠጥ ተጋትኩ፡፡ ጠዋት እራሴን ያማረ እና ጠረኑ የሚጣፍጥ ክፍል ውስጥ ሳገኘው፣ ያለፉትን ሁለት ቀናት ቅዥት፣ የዚህኛውን ቀን ደግሞ ህልም አድርጌ፣ ከአልጋው ወርጄ ልብሴን ለበስኩ፡፡ ኮሜዲኖው ላይ በዛ ያሉ የመቶ ብር ኖቶች ተቀምጠዋል፡፡ አንስቼ ኪሴ ከተትኳቸው፡፡ የሆንኩትን ለእናቴ ለመናገር ነበር ወደ ቤት የሄድኩት፡፡ ግን እንዴት ብዬ? በምን ቋንቋ?» ስሌ አሳዘነኝ!

«ቀናቶች ነጐዱ! መቀመጫዬ መሀል የሚገኘው ቀዳዳ ውስጥ ነብስ ያለው ነገር የሚተራመስ ይመስለኛል፡፡ ይበላኛል! ጣቴን ከትቼ አልረካ ስል... ጠርሙስ መክተት ጀመርኩ፡፡ ህመም እንጂ እርካታን አልሰጠኝም፡፡ ከመኝታ ክፍሌ የምወጣው ለመመገብና ለመፀዳዳት ብቻ ሆነ፡፡ አባቴ ትምህርቴን ትቼ እንደ አራስ መቀለቤን ካልተውኩ ቤቱን ለቅቄለት እንድወጣ መናገር የዘወትር ስራው አደረገው፡፡ ህመሜን የሚረዳልኝ ሰው አልነበረም፡፡» መድኃኒቱ ያልታወቀለትን በሽታ ማስተናገድ ስቃዩ ከባድ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ የስሌ ደፋሪ ናፈቀኝ!

«.... ከጎኔ ያልተለዩ ሰው ቢኖሩ የጓደኛዬ አጐት ብቻ ናቸው! አንድ ቀን ምሽት አፍ አውጥተው ሚስት እንድሆናቸው ጠየቁኝ፡፡

አልደነገጥኩም! አልተገረምኩም! ከአፌ አፈትልኮ የወጣው ቃል... እሺ! ነበር፡፡ ለምን? ባል ያስፈልገኛል!...»

አቋረጥኩት፡፡

«ቆይ! የደፈሩህ እሳቸው ናቸው ማለት ነው?»

«የደፈረኝንማ በሀሰት ወንጅለው ወህኒ እንደወረወሩት ነገሩኝ፡፡»

«ላንተ አዝነው?»

«ለኔ ብለው የደፈረኝን ወህኒ ወረወሩት! ለኔ ብለው ባል ሆኑኝ!»

ሰለሞን ለረጅም ሠዓት በዝምታ ተውጦ ሲንጐራደድ ቆይቶ ተንበርክኮ አለቀሰ፡፡ ወንድ ልጅ ለቅሶ አያምርበትም ለካ! «የደፈረኝ ባለስልጣኑ፣ ያስደፈረኝ ሀይላይ፣ መሆኑን ያወቅኩት፣ ከቀበሩኝ በኋላ ትላንትና ነው!» አለ ሰሌ፡፡ ቆሌዬ ግፍፍ አለ!

የካምፓስ ትምህርታቸውን ከማቋረጣቸው በፊት ሀይላይ የሚያፈቅራት ስዕል የምትመስል ወጣት ነበረች፡፡ እሷ ደግሞ በሰሌ ፍቅር ታውራ ነበር፡፡ ሰለሞን ግን የውበቷ አድናቂ ጓደኛዋ ነው፡፡ ሀይላይ በቆንጆዋ ባለመፈቀሩ ሰለሞንን ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ ቅናት ቤቱን ሰርቶበት በቀልን እንዲያቆጠቁጥ ይረዳዋል፡፡ ጊዜ ነገሮችን አመቻችቶ ሰሌ ሀይላይ መዳፍ ላይ ይወድቃል፡፡ ሀይላይ በአምስት መቶ ብር ሰለሞንን ለባለስልጣኑ ሸጠው፡፡ ባለስልጣኑ የገዙትን ድንግል በውስኪ አጥበው የሰዶም እሳት ውስጥ ጨመሩት፡፡ በአምስት መቶ ብር ነብስ መሸጥ ተጀምሯል፡፡ ሀይላይ ሰለሞንን ብቻ አይደለም ያስበላው፣ ሌሎች ህፃናትን እና ወጣቶችንም እየተከፈለው አስበስቷል! ስራ ፈጠራ ነው?

ስሌ ሌላ ከባድ ነገር እንደሚያስጨንቀው ሹክ አለኝ፡፡ ባለስልጣኑ ወደ ታላቋ አሜሪካ በራሪ ናቸው፡፡ እሱ ደግሞ የሳቸው ነገር አይሆንለትም፡፡ ምክንያቱም ገንዘብ እና እርካታ ከእሣቸው የሚያገኛቸው ውድ ነገሮች ናቸው፡፡ ሲቀጥል ደግሞ ባለስልጣኑ ቢያንበረክኩትም ለስማቸው ሲሉ ገመናውን ይሸፍኑለታል፡፡ ሌሎች ግን የሚያስፈነድዱት መጠቋቆሚያ እና መሳለቂያ ሊያደርጉት ነው፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ባለስልጣኑ ባለትዳር መሆናቸው ነው፡፡ ከሚስታቸው የተነፈጉትን ከሰለሞን ወይም ከብዙ ህጻናት ያገኛሉ፡፡ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ህፃናት ለውትድርና ሲመለመሉ ጉድ ብለን ስናወራ ነበር፡፡ እኛ አገር ደግሞ ህፃናት ለሴሰኞች እየተመለመሉ ወደ ሰዶም እሣት እየተጣሉ ነው፡፡ የእኛን ደግሞ ማን ያውራልን?

ግብረ ሰዶማዊያንን የሚረዳቸው ሰው ስለሌለ ተገለው በብቸኝነት አለንጋ ይገረፋሉ፡፡ ሁለት ስቃይ፣ ሁለት ፍላጎት፣ ሁለት አለመፈለግ ያስተናግዳሉ! ከዚህ ህይወት ለመውጣት ያለመቻላቸው ዋናው ምክንያት... መገለላቸው ነው!!

የሰው ልጅ መጥፊያውን ይቆፍራል! ሰለሞን ፊንጢጣው ውስጥ ስፐርምየሚመገብ ነብስ ያለው ፍጡር አለ ብሎ ያምናል፡፡ ምክንያቱም ፊንጢጣው ስፐርምሳያገኝ ከዋለ በጣም ስለሚበላው፡፡ ከዚህ ህይወት መውጣት በትክክል ይፈልጋል! ክብር፣ ፍቅር፣ ሰው፣ ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ያጣበት ህይወት ስለሆነ፤ ሰለሞን ከዚህ ህይወት መውጣት ይፈልጋል፡፡ ግን "አለመቻል" የሚባል ቡዳ በልቶታል፡፡ ህይወት እንዴት ከባድ ናት? እንዲህ እየተሰቃየንም ለመኖር እንጓጓለን! ሞትስ ሲገኝ አይደል?

«ባለስልጣኑ ወይም ባልህ ለምንድነው አሜሪካ የሚሄዱት?» አልኩት፡፡

«ካዝናቸውን የሞላው የሙስና ብር ፀረ ሙስናዎች ዐይን ውስጥ ገብቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ሙስና ጨለማ ውስጥ የሚያስወረውር ከባድ ወንጀል ነው፡፡ ስለዚህ በግዜ ላሽ ሊሉ ነው፡፡» አለ ሰሌ፡፡

«አስር ሙሰኞች ወህኒ ቢወረወሩ ሀያ ዲቃሎቻቸውን ትተው ነው፡፡ ታጥቦ ጭቃ! ሙስና ካልጠፋ ደግሞ ፍትሕ ይኖራል ማለት ዘበት ነው፡፡ ታዲያ ለምን ይዘውህ አይሄዱም?»

«አልጠየኳቸውም!»

«አሜሪካ በነፃነት ከፈለጉት ወጣት ጋራ በአደባባይ የፈለጉትን ማድረግ ስለሚችል አታስፈልጋቸውም፡፡» አልኩት ጥላቻን ለመዝራት፡፡

«ፈጣሪ አለኝ!»

«ፈጣሪ የዚህ ህይወት ተባባሪ አይደለም! እንደተመጠጠ ሸንኮራ አገዳ ተተፋህ! ምንድነው መጨረሻህ?....»

«የምኖረው ህይወት ለኔ ተመችቶኛል!....» አለ ንዴቱን ለመደበቅ እየሞከረ፡፡

«እያየን?!»

መልሴ አበሳጨው፡፡ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡ ስልኩን ጠረጴዛ ላይ ትቶልኝ በመሄዱ ሊመሰገን ይገባዋል፡፡ ራስወዳዱ ባለስልጣን፣ ንፍጥ የሞላበት ጭንቅላት እንዳለው ለመንገር፤ ስልክ ቁጥሩን ከሰለሞን ሞባይል ማግኘት ቻልኩ፡፡ ጊዜ ለእኔ ዳይመንድ ነው! ወርቅማ ፒያሳ ሞልቷል፡፡ ወዲያው ደወልኩለት፡፡

«መንግስት ሙሰኞች ላይ ጨክኗል የሚባል ወሬ ሰማሁ፡፡ ጭካኔውን አንተ ላይ እንዲተገበር ከማይፈልጉ ሰዎች መሀል በመሆኔ ደግሞ ደስታ ይሰማኛል፡፡» ቆጣ ያለ ድምፅ እንዳቋርጥ ትዕዛዝ ሰጠኝ፡፡ እኔ ግን ቀጠልኩ፡፡

«መግባባት ብንችል የተሻለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡»

«ባንግባባስ?» ነበር የባለስልጣኑ መልስ፡፡ ባለጊዜ እንኳን ሰውን ፈጣሪውንም አይፈራም፡፡

«አሜሪካ ሳይሆን ፍርድ ቤት እንገናኝ፡፡» አልኩት ኮራ ብዬ፡፡

«ምናባሽ ነው የምትፈልጊው?»

«ወሲብ!»

«ወሲብ?» ሳቀ፡፡

«በጣም አስፈልጎኛል!... አንተ ደግሞ እርካታን በመስጠት የተካንክ እንደሆንክ አውቃለሁ፡፡ ቀዳዳዎቼን ባጠቃላይ መጠቀም ትችላለህ፡፡ እሺ ወይስ...»

«እሺ! የት ነው መገናኘት የምንችለው?» አለኝ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ምርጫዬ ተራ ሆቴል ነበር፡፡

«ተንኮል አስበሽ ከመጣሽ ትሞቻለሽ፡፡»

«ገዳይ ወንድ ደስ ይለኛል!» ስልኬን ዘጋሁት፡፡

ለድሌ አንድ ሲጋራ ለኮስኩ! የቁም ሳጥኔ መስታወት ውስጥ ለማያት እኔን መሳይ ሲጋራ አጫሽ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አማከርኳት፡፡ አሪፍ ሀሳብ ያለችውን አቀረበች፡፡ ተስማማሁ፡፡ የመጀመሪያ ሥራዬ ገላዬን መታጠብ፡፡ ከዛ ፀጉር ቤት መሄድ፡፡ ሌላው ቀላል ነው፡፡ ገላዬን

ለቅለቅ ካልኩ በኋላ ወደ ፀጉር ቤት ሄድኩ፡፡ አንዷ ቆንጆ ቀለም እየተቀባች ደረስኩ፡፡ እኔስ ለምን ይቅርብኝ? እጄን ይባርከውና ፀጉር ሰሪው ምርጫዬ የሆነውን የቀለም አይነት ቀብቶ፣ አሳምሮ ወደ ቤቴ ላከኝ፡፡

ብርሀን በጨለማ የሚተካበት ሰዓት እየደረሰ ነው፡፡ ውስጤ በደስታ እየፈነደቀ ነው፡፡ ከሰዓታት በኋላ የናፈቅኩት ጨለማ ብርሀንን አሽንፎ ሠማዩ ላይ ተዘረጋ፡፡ ከዋክብት ከምሽጋቸው ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ ጨረቃ ዘግየት ብላ ትመጣለች ብዬ እራሴን አፅናናሁ፡፡ ጨረቃን እና ከዋክብትን የማገኛቸው በጨለማ ስለሆነ ጨለማን እወደዋለው፡፡ ጨለማ በብርሃን ለታገቱ ከዋክብት፣ በፀሀይ ለተሸፈነችው ጨረቃ፣ ለእንደኔ አይነቱ እድል ጠማማ፣ ጨለማ ጉልበት ነው! ጨለማ ለወዳጆቹ ብርሃን ነው!!

የሰለሞን ባል የያዘውን የቤርጎ ቁጥር ደውሎ ነገረኝ፡፡ እኔ ቀድሜ ከጐን ካለው ክፍል ተጋድሜ እየጠበኩት ነበር፡፡ ከክፍሌ ወጥቼ አፍንጫዬን ከፈትኩ፡፡ ሰላማዊ ጠረን ሸተተኝ፡፡ ወደ ባለስልጣኑ ክፍል ሰተት ብዬ ገባሁ፡፡ ባለስልጣን ተብዬው ከአልጋው ላይ ተስፈንጥሮ በጐኑ የሻጠውን ሽጉጥ መዘዘ፡፡ አልደነገጥኩም! በሩን ረጋ ብዬ ከዘጋሁ በኋላ ልብሴን ማውለቅ ጀመርኩ፡፡

«ወኔህ ሽጉጥ ነው እንዴ?» አልኩት፡፡

«የምን ፓርቲ አባል ነሽ?» አለኝ፡፡ አያስቅም?

«የወሲብ!»

«እውነቱን ተናገሪ! አለበለዚያ....»

«ፖለቲካ አልወድም! ስለዚህ የፓርቲ አባልም ሆነ ደጋፊ አይደለሁም! »

እርቃኔን እግሬን ከፍቼ ቆምኩ፡፡

«ግንባርሽን ሳልበትነው ማንነትሽን ንገሪኝ!» አንባረቀብኝ፡፡

እርቃኗን የቆመች ሴት የሚገድል ወንድ ካለ አይነ ስውር ነው!!

«ሰለሞን እየከነፈ ሲመጣ እርካታን ሰጥተህ እንደምትልከው ሹክ አለኝ፡፡ ባሌ የወጣሁበትን ቀዳዳ እንጂ ጉረቤቱን አልደፍርም ሲለኝ፤ ያለኝ አማራጭ አንተን ማግኘት ነው፡፡ የወሲብ ጥም ሊደፋኝ ስለሆነ እባክህን ሰው ሰራሹን ሽጉጥ ጣልና፤ ተፈጥሮ የለገሰችህን ሽጉጥ ምዘዝ፡፡» አልኩት ቅንዝር የተሞላበት አይኔን አይኖቹ ላይ ተክዬ፡፡

«አፍሽን ዝጊ!» አለኝ፡፡

መሬት የጣልኩትን ቦርሳ ለማንሳት አፈነደድኩ፡፡ እጄን እንድሰበስብ ማስጠንቀቂያ ሰጠኝ፡፡ አልሰማሁትም! ቦርሣዬን ከፈትኩት፡፡ ልተኩስ ነው አለኝ፡፡ ግን አልተኮሰም፡፡ ትልቁን ወይን ከሁለት ብርጭቆ ጋር ከቦርሣዬ ውስጥ አወጣሁ፡፡ «ወንድ አይደለህ ምን ያንበጫብጭሀል?...» አልኩት፡፡ ለወንዶች ወኔ የሚሰጥ ቃል!... «ወንድማ ነኝ!» አለ ኮራ ብሎ፡፡ ወይኑን እስከመከፈቻው ሰጠሁት፡፡ ሽጉጡን አልጋው ላይ አስቀምጦ ወይኑን ለመክፈት መታገል ጀመረ፡፡

«ሽጉጥ የፈሪዎች ድፍረት ነው ይባላል!» አልኩት፡፡

«ስለዚህ…»

«ፈሪ ነህ!»

«ምላሳም ነሽ!»

ወይኑን ከፍቶ ሰጠኝ፡፡

«በምላስ አገር ማስተዳደር እንደሚቻል አታውቅም እንዴ?....»

ወይኑን ቀድቼ ሰጠሁት፡፡ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው፡፡

«ፍራቻ ጥም ለቀቀብህ እንዴ?»

«ጋዜጠኛ ነሽ?... እሺ! ፀረ ሙስና ውስጥ ምንድነው ስራሽ?»

«ሙሰኞችን ማበረታታት! የኔ ወንድም እኔ ወሲብ ያሠከረኝ ቅንዝረኛ ነኝ! እመነኝ!...»

ከንፈሩን ሳምኩት፡፡ ገፈተረኝ፡፡ ጥያቄ የሚያበዛ ወንድ ያስጠላኛል፡፡ ልብሱን ማውለቅ ጀመረ፡፡ ለኔ የቀዳሁትን ወይን አጠጣሁት፡፡ ወይኑን ከነ ጠርሙሱ አንስቶ ጋተኝ፡፡ ደነገጥኩ! አስክሮ ሲጫወትብኝ ሊያድር ወይም ከሰከርኩ በኋላ በመኪናው ጭኖ ወስዶ ሊገለኝ ነው አልኩ ለራሴ፡፡ ሽጉጡን ትራሡ ስር ወሽቆ የውስጥ ሱሪውን ካወለቀ በኋላ በጀርባው ተጋደመ፡፡

«አደፍርሴን ከመጥባት ጀምሪ!» አለኝ፡፡

ቅሌታም ሽማግሌ!

«ከከንፈርህ ጀምሬ ብወርድ ይሻላል! አይመስልህም?....»

«አይሆንም!» አለኝ፡፡

አደፍርስ ላይ እንደ እሣት የምቀጣጠለው ሴትዮ በረዶ ሆንኩና ተገትሬ ያለ የሌለውን መቀበጣጠር ጀመርኩ፡፡ ሰውየው ቀፈፈኝ! አይደለም ቆለጡን መጥባት ሰውነቱን እንኳ ለመንካት ተፀየፍኩ፡፡ ትዕዛዙን ካልፈፀምኩ ደግሞ አይለቀኝም፡፡ ሰዓቱ ደግሞ እየበረረ ነው፡፡ መቼም

ሲፈጥረኝ ጥበበኛ አድርጎ ነው! እንደምንም ብዬ በሰላም ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡

እቤቴ እንደገባሁ ጥርሴን ቦርሼ ከተኛሁ በኋላ ገላዬን ያ ሽማግሌ እንደነካው ሳስታውስ ቀፈፈኝ፡፡ እርቃኔን እየሮጥኩ መፀዳጃ ቤት ገባሁ፡፡ በክረምት በቅዝቃዛ ውሀ መታጠብ ማለት ደግሞ…! ከውሀው ድምፅ ሌላ የሚንኳኳ በር ድምፅ ሰማሁ፡፡ ትንጧ ልቤ በትልቁ መደለቅ ጀመረች፡፡ ቀስ ብዬ ወደ በሩ ተጠጋሁ፡፡ ባለስልጣኑ ሠራልኝ! አልኩ በሆዴ፡፡

«አንቺ አትከፍቺም?» አለ አብዲ፡፡

ኡፍ!… ተመስገን!… ከፈትኩለት!

«ስማ!… ገድለህ የት እንደቀበርከው ልትነግረኝ ትችላለህ?…» አልኩት ወገቤን ይዤ፡፡

«ማንን?»

«ከኡምቤርቶ ሌላ ማንን ገድለህል?»

«ካንቺ ጋር የታየ ሁሉ ሟች መሆኑን አታውቂም?»

«እሺ! ኡምቤርቶን ገድለህ የት ነው የጣልከው?»

«የቀበና ወንዝ ወስዶታል!» አለኝ ኮራ ብሎ፡፡

በዐይኔ የታዘለው እንባ ተንሸራቶ ወረደ፡፡ እንባዬን ጠረገልኝ! ሸሸሁት፡፡ ስለሌሎች ሞት የሚያገባኝ ነገር የለም፡፡ ኡምቤርቶ ግን መሞት አልነበረበትም፡፡ ሰለሞን እያንጎራጎረ ሲገባ አብዲ ከላይ እስከታች ተመለከተው፡፡ የሌሎች እጣ እንዳይደርሰው ሰግቼ ቶሎ ብዬ ግብረ ሰዶማዊ መሆኑን ተናገርኩ፡፡ ሰለሞን ከአብዲ ፊት ዞር ከማለት ይልቅ

መቅለስለስ ጀመረ። አብዲ በንቀት ከተመለከተው በኋላ፣ አንድ ቦክስ አሳርፎበት ወጥቶ ሄደ።

አብዲ ኡምቤርቶን ገደለው! እኔ ደግሞ እጄን አጣጥፌ ቁጭ ብያለሁ። ምንስ ማድረግ እችላለሁ? መንግስት ባለበት አገር ሰው ተገድሎ አቤት ማለት ካልተቻለ፤ መንግስት ባለበት አገር እንደ አብዲ ያሉ ቲቢተኞች እንዳሻቸው ሲፈነጩ ዝም ከተባለ፤ ምኑን ኖርነው? አብዲ እንዳላጠፋ በደንብ አውቃለሁ። ጥፋተኛዋ እኔ ነኝ! ምክንያቱም አብዲን መበቀል አልፈለግኩም። አለመፈለግ ሳይሆን፤ ያለመቻል ጉዳይ ነው። ለሊቱን ከራሴ ጋር ስጣላ አሳለፍኩት። ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ አሸነፈኝ።

ጨለማዬን የነጠቀኝ ብርሃን፣ በዘመዱ ፀሀይ ደምቆ፣ እንደሌባ በመስኮቴ ገብቶ፣ እንቅልፌን ነጠቀኝ። ሰዓቴን ተመለከትኩ፤ 6:30 ሆኗል! ምግብ ፍለጋ ወደ እቃ ቤት ሄድኩ፤ ሰለሞን በሰው ተደግፎ መግባቱን መቅዲ ነገረችኝ። ሰለሞን ፊቱ አባብጦ ኩርምት ብሎ ተኝቷል። ደነገጥኩ!

«ማታ አንቺ በርሽን ስትቆልፊ፤ ከኔ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለሽ ላስረዳው፤ ተከተልኩት!» አለ ሰሌ ፈገግ ብሎ።

«ያምሀል?» ጮህኩበት።

«ከዛ ካልጋበዝኩህ ብሎ ይዞኝ ሄደ። ቦሌ ጫፍ ስንደርስ ቅጥረኞቹ ናቸው መሰለኝ ደውሎ ጠራቸውና ይዛችሁት ሂዱ ግን ተመላሽ ነው አላቸው።»

«እና እንዲህ ሲል ከመኪናው ወርደህ አታመልጥም ነበር?»

«ምን ያደርጉኛል ብዬ ልጠርጥር?»

«እኔ የት ሄጄ ልደበቅ?»

«አንቺ ምን አጠፋሽ?»

«ከእኔ ጋር ባትታይ ኖሮ ይሄ ሁሉ አይደርስብህም ነበር፡፡» ቆይ ምን አባቴ ላድርግ?

«ልብሴን አውልቀው በኤሌክትሪክ ገመድ ከገረፉኝ በኋላ ወዝ ያለው ቦክስ አቀመሱኝ፡፡ ስደክምባቸው በውሀ ነክረው ካርቶን ላይ አጋደሙኝ፡፡ ሲነጋ ደግፈው አልጋዬ ላይ አስተኝተውኝ ሄዱ፡፡» አለ ሰለሞን ያበጠ ፊቱን እየዳበሰ፡፡

«በቃ! ከቤት እንዳትወጣ!»

«ወንድሜ ሊያገኘኝ ይፈልጋል! ምናልባት ቤተሰባችን ላይ የተፈጠረ ችግር ሊኖር ስለሚችል የግዴታ ዛሬ ወጥቼ እሱን ማግኘት አለብኝ፡፡ እዚህ ደግሞ አይመጣም፡፡ ይደፍረኛል ብሎ ስለሚፈራ ካፌ ውስጥ ካልሆነ እኔን ማግኘት አይፈልግም፡፡»

ጭንቅላቴ የሆነ ነገር ሹክ አለኝ፡፡ ፈጠን ብዬ በወረቀት ላይ ካሰፈርኩት በኋላ፤ ለመቅዲ ሰጥቼ ወደ ሱቅ ላኳት፡፡ ከሰሌ ጋር ሳሎን ቁጭ ብዬ ወሬ ሳቦካ፤ አብዲ እየደጋገመ ይደውላል፤ አልመለስኩለትም! አጅሬ ለካ በረንዳ ላይ ቆሞ ነበር የሚደውለው፤ በሩን በርግዶ ገባ፡፡ ሰለሞን ደንግጦ ከተቀመጠበት ተነሳ፡፡ አብዲ እኔን እየጐተተ መኝታ ክፍሌ ይዞኝ ገባ፡፡

«ቆይ አትወጂኝም?... ንገሪኝ!...» አለኝ እጄን አጣምሮ፡፡

«ኡምቤርቶን ነው የምወደው!... በዙሪያዬ ያሉትን ወንዶች ተዋቸውና፤ ወንድነትህን እኔን በመግደል አሣየኝ እስቲ፡፡»

በጥፊ መታኝ!

«ባንቺ ሰበብ እጁ በደም ታጥቦ ሰላም እንደሚነሳኝ ብታውቂ ኖሮ በተረዳሽኝ ነበር፡፡ »

አይኖቹን አይኖቹ ላይ ተከላቸው፡፡ አልቻልኩምና ፊቴን አዞርኩ፡፡ ወጥቶ ሄደ፡፡ ትንሽ ለመረጋጋት የተደረደረውን ሽቶና የቅባት አይነት መሬት ላየ በተንኩት፡፡ አብዲ ጠላቴ ነው! ግን ለምን ጨክኜ እንደማልበቀለው አላውቅም!! ሳየው ሰውነቴ ይግላል! ድንቅነሼ ትረጥባለች! ልቤ ምቱን ይጨምራል! የማደርገውን አላውቅም! ብቻ እኔ.... እኔ ደደብ ነኝ!!

መቅደስ ወረቀት ላይ የፃፍኩላትን እቃ ገዛዝታ አመጣችልኝ፡፡ እራሴን ወቀሳ ትቼ ወደ እቃ ቤት ሄድኩ፡፡ □መጣችልኝን የተዘጋጀ የአቮካዶ ጭማቂ በኩባያ ከቀነስኩ በኋላ ቀሪው ላይ ሁለት እሽግ የእንግሊዝ ጨው ጨምሬ በደንብ አዋሀድኩት፡፡ ስቀምሰው የጨውና የስኳር ግጭት ጠዓም ነው ያለው፡፡ ሰለሞን በቴሌቪዥን መስኮት ውስጥ የሚያየው የስፖርት ዜና ላይ አፍጥጧል፡፡ አንዱን ብርጭቆ ሰጠሁት፡፡

ልቡ ዜናው ላይ ስለነበረ አንድ ሁለቴ ከቀመሰው በኋላ አጣጣመው፡፡ ጨው ጨው የሚለው ለምን እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡ ስኳር መስሎኝ ጨው ጨመርኩበት ብዬ ዋሸሁት፡፡ መቼም ገንዘብ ወጥቶበታል ብሎ ነው መሰለኝ፤ እያንገሸገሸው ጠጥቶ ጨረሰ፡፡ ለነገሩ ልቡ የአርሴናል እና የቼልሲ ዜና ላይ ስለነበረ፤ ምን ያህል እንደጠጣ እንኳ የሚያስታውስ አይመስለኝም፡፡

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሰለሞን ቂጡን እየደገፈ መፀዳጃ ቤት መመላለስ ጀመረ:: እኔም የታመምኩ ለመምሰል፣ እሱ ሲወጣ፣ እየሮጥኩ ገብቼ መስታወት እያየሁ ሆዴን ደግፌ እወጣለሁ:: ሰለሞን መመላለስ ሲደክመው መፀዳጃ ቤቱ አጠገብ ቁጭ አለ:: ፋታ አይሰጤ እንደሆነ እንኳን ቀለበቱ ለለቀቀ ፊንጢጣ ለደህናውም አይበገር! ማን ያውቃል?! ስም የሌሾቹ ፍጡራን ከቀጭኑ ወንዝ ጋር አብረው ይወጡ ይሆናል! ሰለሞን ቀኑን ሙሉ መፀዳጃ ቤት ሲመላለስ ዋለ:: እኔ መመላለሱ ሲደክመኝ አርፌ ቁጭ አልኩ:: የተበላሸ አቮካዶ አጠጥቼ ጉድ ሰራሁህ! አልኩት:: እኔን እንዴት ወዲያው ሊተወኝ እንደቻለ ጠየቀኝ:: ሚጥሚጣ በጥብጬ ጠጥቼ ነው ብዬ ዋሸሁ:: ከቤት እንዳይወጣ ብዬ፣ የእንግሊዝ ጨው በአቮካዶ፣ እንዳጠጣሁት ቢያውቅ፣ ምን ይል ይሆን?

ሽሽቼ የማላመልጠውን ሰው እያሰብኩ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ:: ቃሌን አሳጥፎ ወላዋይ ያደረገኝን ሰው ለመበቀል ሳስብ አለመቻል የሚባል በሽታ በርህራሄ ተደብቆ አንጀቴ ውስጥ ገብቶ ይዘፈዝፋል:: አምሮት ልፍስፍስ ሴት አይደለችም! ግን ሴሰኝነቷ ለሽንፈት ዳረጋት! አብዲ በወሲብ ገመድ ተብትቦ እግሩ ስር አንበረከካት:: እንቅልፍ ወዳጄ ሆይ ሀሳቤን አሸንፈህ ናልኝ:: እንቅልፌ ብዙ ከተለመነ በኋላ መጣ::

.....የዛሬዋን ቀን ቅድስት ብዬ ብሰይማት እወድ ነበር:: በርግጥ ጠዋት ላይ አማርሪያት ነበር:: ሰለሞን ለሊቱን ሙሉ መፀዳጃ ቤት ሲመላለስ ስላደረ አቅም የሚባል ነገር አልነበረውም:: ስለእውነት ደንግጬ ነበር! ምግብ ከሰጠሁት በኋላ ትንሽ ጉልበት አገኘ:: ተረጋጋሁ! አልጋው ላይ

ስቶ ስለነበር የቤቱ ጠረን ለአፍንጫ ተስማሚ አልነበረም፡፡ መቅደስ እየተነጫነጨች አንሶላውን አጥባ ክፍሉን አፀዳችለት፡፡ ከሰዓት በኋላ የጥዋቱ ተረስቶ ሰለሞን ቀልደ ጣል ሲያደርግ እኔ እና መቅደስ እየገለፈጥን ቡና ጠጣን፡፡ ሰሌ ከስንት ልመና በኋላ ከወንድ ጋር ያለውን የወሲብ ግንኙነት እንደሚቀንስ ቃል ገባልኝ፡፡ ተመስገን!

«ወንድ የሚመኝ ጭንቅላትህን፣ ሴትንም መመኘት እንደሚችል ንገረው፤ የማይቀበልበት ምንም ምክንያት እንደሌለ ማወቅ አለብህ፡፡» አልኩት፡፡

«እግዚያብሔር ለእኔ ይሆን የፈጠረሽ?» አለኝ፡፡

«ይህን ቃል መስማት የምፈልገው ተቀይረህ ሳይ ነው፡፡»

የማይቻል ነገር የለም! ቀኑ እሁድ በመሆኑ መቅዲ የአገራችንን የቴሌቭዥን ጣቢያ ከፍታ ታያለች፡፡ ከሰለሞን ጋር የነበረኝን ወሬ ገታ አድርጌ ወደ ቴሌቭዥኑ ዞርኩ፡፡ አዲስ ነጠላ ዜማ ብለው የደቡብ ዘፈን ማሳየት ጀመሩ፡፡ ዘፈኑ ሲያልቅ ደግሞ፣ ጋዜጠኞቹ፣ ትንሽ ፈገግ የሚያስብል ወሬ ጣል ካደረጉ በኋላ፣ የሰለሞንን ህይወት ያበላሸውን ባለስልጣን ፎቶግራፍ፣ ገጭ አደርገው፣ የቀብር ስነስራዓቱን፣ ማሳየት ጀመሩ፤ ዐይኖቼን ከፍቼ ጆሮዬን አቆምኩ፡፡ ሰለሞን ወደ ቴሌቪዥኑ ተጠጋ፡፡ ጋዜጠኛው የህይወት ታሪኩን በጥቂቱ ከተረከ በኋላ "ፍትሕን በራሴ" የሚል መፈክር ባነገበው ነብሰ ገዳይ፣ ቤርጐ ውስጥ ተገድሎ መገኘቱን ተናገረ፡፡ ወንጀለኛውን ለመያዝ፣ ፖሊስ እያነፈነፈ መሆኑን ካሰመረበት በኋላ፤ ለቤተሰባቸው መፅናናትን ተመኝቶ… ማስታወቂያ ማስተላለፍ ጀመሩ፡፡

«አንድ የታወቀ ነጋዴ ጓደኛ ነበራቸው፡፡ ካለ ቀረጥ ያስገባው ኮንቴነር ሙሉ እቃ በጉምርኮች ተይዞበት አስለቅቅልሀለው ብለው ብር እንደተቀበሉት አውቃለሁ፡፡ ጉምርኮች ግን እቃውን ለመንግስት ገቢ አደረጉ፡፡ ነጋዴው እገልሀለሁ ብሎ እንደዛተው ይኸው ገደላቸው፡፡» አለ ሰለሞን፡፡

«በል አፍህን ጥረግ!» አልኩት፡፡

«ኧረ ለማንም አልተነፍስም!»

«ታዲያ አታለቅስም እንዴ?»

«ምን እንደተሰማኝ ታውቂያለሽ? እፎይታ!»

«ትፈራቸው ነበር እንዴ?»

«አንድ ወቅት ላይ ግንኙነታችንን ማቋረጥ ፈልጌ ነበር፡፡ የተቆጣች እጃቸውን በቤተሠቦቼ ላይ እንደሚሰነዝሩ ሲነግሩኝ ግን ሀሳቤን ቀይሬ እየለመድኳቸው እና እየፈረኳቸው መጣሁ፡፡ የወደድኳቸውም ይመስለኝ ነበር፡፡ ግን ዛሬ....»

ሰለሞን ጊዜ ይፈጀል እንጂ ይቀየራል ብዩ አስባለሁ! የዛሬዋ ቀን ቅድስት እንደሆነች ዋለች፡፡ ምሽት ላይ ከሰሌ ጋር አልጋዩ ላይ ቁጭ ብለን ካርታ እየተጫወትን፣ ስለ ኡምቤርቶ እና ስለ ማርኮ እያወራን፣ የኡምቤርቶን መጥፋት ለፖሊስ ማሳወቅ አለብን የሚል ሀሳብ ሰሌ አመጣ፡፡ አልተዋጠልኝም፡፡ መጥፋቱን እንጂ መሞቱን ስለማያውቅ ነው ለፖሊስ አመልከቺ የሚለኝ፡፡ በእኔ ሰበብ መሞቱን ቢያውቅ ኖሮ......

«አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ? ኡምቢርቶን አላገባም ያልሽበትን ምክንያት ታውቂዋለሽ?» ሰለሞን መልሴን በጉጉት መጠበቅ ጀመረ፡፡

«ማግባት ስለማልፈልግ!...» አጭር መልስ ሰጠሁት፡፡

«አብዲን ስለማፈቅረው በሚል ይስተካከል፡፡» አለኝ ካርታውን እየበተነ፡፡ አውቆ ሞቷል!

«ይልቅ የቅድሙን ውሳኔህን አልወደድኩትም!» ወሬ ቀየርኩ፡፡

«ወሬ አትቀይሪና ስለአብዲ የሚሰማሽን ንገሪኝ፡፡»

«እባክህ! ሌላ ወሬ አምጣ!....»

«እሺ! የቅድሙን ውሳኔዬን ለምን ጠላሽው? ለዚህ ሁሉ የዳረገኝ ሀይላይ መሆኑን አትዘንጊ!...» አለ ሰለሞን ብስጭት ብሎ፡፡

ሀይላይ አሰደፈረኝ ብሎ መልሶ እሱን ማስደፈር በቀል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይሄ ሰው ተደፈርኩ ብሎ አርፎ አይቀመጥም፡፡ ብዙዎቹን በመድፈር ሊረካ ይችላል! ከወሲብም ጋር ያለው ቁርኝት እየጠነከረ ይመጣል፡፡ በቀሉን እና ደስታውን በወሲብ ያገኛል! ለዚህ ሰው የሚገባው ቅጣት... ከወሲብ ዓለም መገለል ነው! ሴት የላከው ሞት አይፈራምና «ያፈሰስኩትን እንባ ከአይኖቹ እቀዳዋለሁ!» አለ ሰለሞን፡፡

ብቻዬን ስተኛ የሚያስቸግረኝ መንፈስ እንዳለ ለሰሌ ነገርኩት፡፡ ሰው አማኙ ሰለሞን ልብሱን አወላልቆ አልጋዬ ውስጥ ገባ፡፡ የውስጥ ሱሪውን አላወለቀም፡፡ እህቱ መሆኔን አልረሳም! እኔ ግን እርቃኔን አቅፌው ተኛሁ፡፡ ምንም አልመሰለውም፡፡ የሴት ጠረን የእሱን አፍንጫ አይስበውም፡፡ በእኔ ቤት መፈተኔ ነበር፤ ጭራሽ «ራቁትሽን ስትተኚ አይበርድሽም?» አለኝ፡፡ እንቅልፍ እንደወሰደው ሰው ዝም አልኩት፡፡

ዕለተ ሰኞ ጠዋት ሁለት ሠዓት ላይ እኔ እና ሰለሞን ፖሊስ ጣቢያ ደርሰናል፡፡ የመጣሁበትን ጉዳይ በር ላይ ላገኘሁት ፖሊስ ነገርኩት፡፡ ሀላፊው እስኪመጣ ቁጭ በይና ጠብቂ፡፡ ብሎኝ ሄደ፡፡ ሀላፊው ሦስት ሠዓት ላይ ነው የደረሰው፡፡ የስራ ሰዓት ለምን አሳለፍክ? የሚለው ደፋር ማን ነው? ሀላፊ ነዋ! ማዘዝ እንጂ መሥራት የሚያውቅ ሀላፊ ኢትዮጲያ ውስጥ ማግኘት ከባድ ነው፡፡

ጋሼ ሀላፊ ከዚህ በፊት ቃሌን ወደ ሰጠሁበት ክፍል ይዞኝ ገባ፡፡ ቁንጥንጡ መርማሪ የለም፡፡ በምትኩ ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራ ፀይም ወጣት ቁጭ ብሏል፡፡ ሀላፊው በጆሮው ሹክ ብሎት ወጠቶ ሄደ፡፡ አዲሱ መርማሪ መኖሬን ረስቶታል መሰለኝ ፊት ለፊቱ የተቀመጠው ፋይል ላይ አፍጥጦ ቀረ፡፡ ከዚህ ልጀምር፤ ከዛ ይሻላል፤ እያልኩ ከራሴ ጋር ስታገል ከቆየሁ በኋላ፤ «የመጣሁበትን ጉዳይ አልጠየከኝም!» አልኩት፡፡

«አውቀዋለሁ!» አለኝ እንዳቀረቀረ፡፡

«ታውቀዋለህ?» አልኩት ገርሞኝ፡፡

ትኩር ብሎ ተመለከተኝ፡፡ ዐይኖቹ ውስጤን ያነበቡብኝ መሰለኝ፡፡

«ሰው በመግደል ወንጀል ተጠርጥረሽ የሰጠሻቸውን ቃሎች ደጋግሜ አንብቢያቸዋለሁ፡፡ በሚገርም ሁኔታ ወንጀሉ ከትላንትና ወዲያ በአንድ ባለስልጣን ላይ ተደግሟል፡፡ ተጠርጣሪ ሆነሽ ደግሞ አለመታሰርሽ ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው፡፡» አለኝ፡፡

ሆ! ከየት ብቅ አልክ ወዳጄ? አልኩ ለራሴ፡፡ መርማሪው ቀጠለ...

«ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትሕ የለም ከሚሉት ውስጥ ነሽ?» አለኝ መርማሪ አይኑን አይኔ ላይ ተክሎ፡፡

«ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና አለ የለም?» አልኩት፡፡

«አለ!» አለኝ በፈገግታ፡፡

«ታዲያ ሙስና ካለ እንዴት ፍትሕ ይኖራል?»

«ጥሩ ጭንቅላት አለሽ! ምንድነው ስራሽ?»

«ሽርሙጣና!»

«የምትሰሪበት ቡና ቤት?»

«ለመሸርሞጥ ግዴታ ቡና ቤት አያስፈልግም!»

የቡና ቤት ሴቶችስ ስራ ብለው ስለያዙት ተገደው ነው፡፡ ሽርሙጥና በቤት ልጆች እና በባለትዳሮች እንደባሰ ማን በነገረው...?! ተጠርጣሪ ስለሆንሽ ዋስ እስክታመጪ ድረስ እኛ ጋር ትቆያለሽ ብሎ፤ በአንድ አጠር ባለ ፖሊስ ማረፊያ ቤት አስወረወረኝ፡፡ የእስር ማዘዣ ሳያወጡ ለምን አሰሩኝ?... ምን ታመጣለች ብለው ነዋ!... ደግሞ ዋስ ማንን ብመርጥ ጥሩ ነው? አብዲን! ለነገሩ ማን አለኝና ዋስ አማርጣለሁ? እምቢ ቢልስ ምን ማድረግ እችላለሁ? ጨነቀኝ!

ማረፊያ ቤቱ ውስጥ የታጐሩት ሴቶች ወሬያቸውን ገታ አድርገው ተመለከቱኝ፡፡ ፈንጠር ብዬ አቧራ የደበቀው ወለል ላይ ተቀመጥኩ፡፡ በገጠመኝ ነገር ተገርሚያለሁ!... ሰው ባሠበው ሣይሆን በታሰበለት ሲውል እንዴት አያስገርምም? ሰዓቱ እኔን ጐልቶ ከነፈ፡፡ ምሳ የመጣላቸውን እስረኞች ጉርሻ አልተቀበልኩም፡፡ የአዲሡን መርማሪ ፊት እየደጋገምኩ አይኔ ላይ ኳልኩት፡፡ የማይፈታ ፊቱ፣ ውብ አይኖቹ፣ ግርማ ሞገሱ፣ በዛ ላይ ዝምታው!... የምሣ ሰዓት ካለፈ በኋላ ኩሩሩው ፖሊስ ክንዴን ጨምድዶ መርማሪው ቢሮ ጎልቶኝ ወጣ፡፡

«አምሮት ደስ የሚል ስም ነው!... በነገራችን ላይ የእኔ ስም ኃይማኖት ነው፡፡ መንገድ ላይ ራቅ ብዬ ብታዪኝ እንኳ ለመጥራት እንዲያመችሽ በደንብ አጥኚው፡፡» አለኝ መርማሪ ተብዬው በመስኮት ወደ ውጪ እየተመለከተ፡፡

«.....የተጠረጠርኩበትን ምክንያት ልትነግረኝ ትችላለህ?» ፊት ለፊቴ ተቀመጠ፡፡

«ውብ ስለሆንሽ! ቆንጆ ሴት ደግሞ ሰይጣን ናት! ሰይጣን ደግሞ አሳሳች ነው! ከተሳሳትሽ ደግሞ.... ልቀጥል?...»

«ትንኮሣ አይመስልህም?»

«ሥራዬን እየሠራሁ መስሎኝ ነበር!...»

«ሹፌት ነው የያዝከው?»

«ብዙ ጥያቄ መልስ ያስገኛል ብዬ አላስብም! ስለዚህ መሄድ ትችያለሽ፡፡ አብዲ እና ሰለሞን ውጪ ይጠብቁሻል! እራስሽን ጠብቂ!»

ፖሊስ ጣቢያ የመጣሁበትን ቀን እየረገምኩ ከመርማሪው ቢሮ ወጣሁ፡፡ በመስኮቱ እኔን እያየ እንደሆነ ጀርባዬ ነገረኝ፡፡ ለማረጋገጥ ዞርኩ፡፡ እያየኝ ነው! ስደናበር እንቅፋት አሰግዶ መለሰኝ፡፡ አፍሬ እና አርሬ ከግቢው ወጣሁ፡፡ ሰለሞን የአብዲን መኪና ተደግፎ ቆሟል፡፡ አብዲ መኪናው ውስጥ ተቀምጦ የቴዲ አፍሮን ሙዚቃ እያዳመጠ ያንጎራጉራል፡፡ ጋቢና ገብቼ ተቀመጥኩ፡፡ ሰለሞን ፈራ ተባ እያለ ገብቶ ተቀመጠ፡፡ ጉዞ ጀመርን፡፡

«አሁን እንዳንቺ አይነቷ ሰው አይደለም ዝንብ ትገላለች?» አብዲ መቀባጠሩን "ሀ" አለ፡፡ ሰለሞን ቀጠለ...

«ከዝንብ እና ከሰው የቱን መግደል እንደሚከብድ ታውቃለህ?»

«ዝንብ ልትለኝ እንዳይሆን?» አለው አብዲ፡፡

«ዝንብን ተኩሶ የገደለ ጀግና ጥራልኝ!» አለው ሰለሞን፡፡

አፋቸውን እንዲዘጉልኝ ተማፀንኳቸው፤ ሁለቱም ዝም አሉ፡፡ ቴዲዩን ይቅርታ ጠይቄ ሙዚቃውን ዘጋሁት፡፡ ምንም አይነት ድምፅ መስማት አልፈለግም፡፡ ሠማዩ እያጉረመረመ ነው! እንዳጉረመረመውም አልቀረ ማልቀስ ጀመረ፡፡ አብዲ እቤት አድርሶን ተመለሰ፡፡

ሰለሞን እንደነገረኝ ከሆነ፤ መርማሪው እሱን እና አብዲን በጥያቄ አጣድፏቸዋል፡፡ እኔንም በቀላሉ እንደማይተወኝ ተናግሯል፡፡ ወንጀለኞችን እያፋጠጡ ወሀኒ መወርወር የመርማሪዎች ተግባር በመሆኑ፤ ኃይማኖት ተብዬው መርማሪ ጥፋተኛ ነው ማለት አልችልም፡፡ ግን እኔ ወንጀለኛ አይደለሁም፡፡ ሞቱ የተባሉት ሰዎች ግን ወንጀለኞች ናቸው፡፡ ሰለሞን ለአብዲ እንዳልናገር ቃል አስገብቶ አንድ ምሥጢር ነገረኝ፡፡

«የፖሊስ ጣቢያው ሀላፊ እና አብዲ በደንብ ይተዋወቃሉ፡፡ ከዚህ በፊት ተጠርጥረሽ በቀረብሽ ጊዜ ለአብዲ ተብሎ ነው ያልታሰርሽው፡፡»

«አብዲ እኔ ለጥያቄ መቅረቤን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?.... » አልኩት ገርሞኝ፡፡

«ቲጂ ደውላ ነግራው! እሷ ባትነግረው እንኳ እንቺን እየተከታተሉ ወሬ የሚያቀብሉት ሰዎች እንዳሉ ታውቂያለሽ፡፡»

«ታዲያ ዛሬ ምን ተገኘና አሰሩኝ?»

«ቆንጆዬው መርማሪ! ለዚህ ወንጀል ተብሎ ከፌደራል የመጣ ስለሆነ ሀላፊው እጁን አላስገባም ብሎት ነው አብዲ በአካል ቀርቦ ዋስ የሆነሽ፡፡»

«ታድያ አንድ ቀን እንኳ ሳላድር ለምን ለቀቀኝ?»

«መርማሪው... እስር ቤት ከተቀመጠች እውነተኛዋን አምሮት ማግኘት እቸገራለሁ፤ ስለዚህ ትለቀቅ እና ኮቴዋን እየተከተልኩ ሚስጥሯ ውስጥ እገባና፤ ማንቁርቷን አንቄ ወህኒ እወረውራታለሁ፡፡ ብሎ ለሀላፊው ይነግረዋል፡፡ ከዛ በዋስ እንድትለቀቂ ተወሰነ፡፡ ስለዚህ ጀርባሽን እያጠናሽ ተንቀሳቀሺ፡፡ ማለቴ ለደህንነትሽ ስትዪ....»

ብልጥ መርማሪ ነው! ብልጠቱን በምሥጢር ስላሊያዘው ደግሞ ሞኝም ነው፡፡ ኃይማኖት ምናልባት የፍትሕ ሰው ቢሆን እና ወንጀለኞችን አድኖ ቢይዝ እንኳ መጨረሻው ሽንፈት ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም ሀላፊው በሙስና የደለበ ጅብ ነው፡፡ የፈረደበት በር ተንኳኩቶ ስለሞን ለመክፈት ተነሳ፡፡ አብዲ መሆኑን ስላወቅኩ የለችም በለው ብዬ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ተደበቅኩ፡፡ ማን ያዘዋል በሩን በርግዶ ገባ፡፡ አብዲ...

«የቀበና ወንዝ የወሰደውን ነጭ እንዲያፈላልጉልሽ ልታመለክቺ ሂደሽ እስርቤት ተወረወርሽ፡፡ እኔ ደግሞ ዋስ ሆኜ አስፈታሁሽ፡፡ ከፈለግኩ ደግሞ እስከለተ ሞትሽ ኑሮሽን እስርቤት ማድረግ እችላለሁ፡፡ ይሄ ማለት አንቺ በእኔ መዳፍ ውስጥ ነሽ ማለት ነው፡፡ ተግባባን?» አለኝ መርዛማ እጁን ፀጉሬ ውስጥ እያንሸራሸረ፡፡ የተናገረው ነገር ይሁን፣ ፀጉሬ ውስጥ የገባው እጁ፣ አላውቅም የትኛው እንዳደነዘዘኝ፤ ብቻ ደንዝዣለሁ፡፡

«አሁን በዝናብ የመጣሁት እንድንታረቅ ነው፡፡» አለኝ ልብሱን እያወለቀ፡፡

«አባዲ አላ...ደ...ርገ...» መናገር አቃተኝ፡፡

«እርግጠኛ ነኝ ውስጥሽ የኔን ገላ እየተመኘ እንደሆን፡፡»

«ውስጤ ስለኔ አያገባውም!»

እርቃኑን ፊት ለፊቴ ቆመ፡፡ አይኔን ከአብዲ ሰውነት ላይ መነቀል አልቻልኩም፡፡ ጭኖቼ መሀል ሙቀት ተሰማኝ፡፡ ይበልጥ በተጠጋኝ ቁጥር ስሸሸው ግርግዳው ላይ ተጣበቅኩ፡፡ ሳልፈልግ ተሸነፍኩ!... ልብሴን አውልቆ ጣለው፡፡ አልፈልገውም! በተመሣሣይ ሠዓት ግን እፈልገዋለሁ! ቃላት ቢደረደሩ በሰዓቱ የሆነውን አይገልፁትም፡፡ አበድን ብዬ ላሣጥረው!... አበድን!! እንዳይተወኝ የማደርገው እኔው እራሴ መሆኔን ነግሮኝ፤ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡

ኡምቤርቶ ታወሠኝ! መቃብሩ ላይ ቆሜ የጨፈርኩ መሰሎ ታየኝ፡፡ ባደረግኩት ነገር ተፀፀትኩ፡፡ እንባዬ በደሌን ያጥብልኝ ይመስል አነባሁ፡፡ አንድ ሰው ለሁለት ነገር መገዛት እንዴት ይቻለዋል? መንገድ የማይመርጥ እግር ተሸክሜ የረገጥኩትን አሜከላ ለማምለጥ ከገደል ጫፍ ቆሜያለሁ!... የኡምቤርቶን ሻንጣ ከፍቼ ልብሱን አሸተትኩት!... እሱን ያገኘሁት መሰሎ ተሰማኝ! የእሱን እና የመንትያ ወንድሙን ፎቶ አውጥቼ አልጋዬ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ መልካቸው አንድ ነው! ኡምቤርቶ የትኛው እንደሆነ ስላላወቅኩ ሁለቱንም ሳምኳቸው፡፡ ቤቱ እና እቃው ኡምቤርቶን ያስታውሰኛል፡፡ ኡምቤርቶም ብሸሸው የማላመልጠው ሁለተኛው ሰው ነው!

የገነባሁት የማይፀናልኝ ሰነፍ ግንበኛ ነኝ!... ወድጄ አላውቅም! ጥላቻ ከኔ የሚፈልቅ የደም ጎርፍ ነው!... ጨረቃና ፀሀይ በተፈራረቁ ቁጥር ያልጠበኳቸው ትእይንቶቹ እየተከሰቱ ነው፡፡ ሰሌ ሀይላይን ከወንድሞቹ ጋር ተባብሮ አደፍርሱን እንዳኮላሸለት ሲነግረኝ ፍጥነቱን አደነቅኩለት፡፡ ከወንድሞቹ ጋር መቀራረቡ ደግሞ አስደሳች ዜና ነው፡፡

ቀኑ ማን እንደሆነ አላስታውስም፡፡ ከሰለሞን ጋር ቁጭ ብለን ጫት እየቃምን እስር ቤት የወረወረኝ መርማሪ ከች አለ፡፡ ከእኛ ጋር ጫት ሲቅም ውሎ አመሻሹ ላይ ሳይሰናበተን ወጥቶ ሄደ፡፡ ሰለሞን ቤቴን ለመርማሪው በማሳየቱ ተቆጣሁት፡፡

«አሳይቼው አይደለም! ስልኬን ወስዶ ስለነበር ደውሎልኝ ከጋበዝኝ በኋላ እዚህ ድረስ ሸኘኝ፡፡ ደግሞ እንዴት ጥሩ ሰው መሰለሽ፡፡ የውበቱን ነገር ላንቺ አልነግርሽም፡፡ ብቸኛም ስለሆንኩ....» ሰሌ ተቅለሰለሰ፡፡

«... አንተ የተፈጠርከው ለሴት እንጂ ለወንድ አይደለም!» አልኩት ንዴቴን ለመቆጣጠር እየታገልኩ፡፡

«ኤሚ!.... ከዚህ ህይወት መውጣት እፈልጋለሁ! መቻል እና መፈለግ ግን የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተረጂኝ!....»

ሰሌ እውነቱን ነው! መቻል እና መፈለግ በጣም ይለያያሉ፡፡ ማጹ ከሞተች በኋላ የወሲብ ፊልም አይቼ አላውቅም በሚል ሰበብ ሰለሞንን የወሲብ ፊልም ተከራይቶ እንዲያመጣ ላኩት፡፡ ተከራይቶ እስኪመጣ ተጣጥቤ ስስ ፒጃማ ከለበስኩ በኋላ እራት አቅርቤ ጠበኩት፡፡ ሰሌ ፊልሙን ይዞ ሲመጣ በስስ ፒጃማ የተደበቀው ገላዬ ላይ አይኑን

ማሳረፉ አልቀረም፡፡ እራታችንን በልተን እንደጨረስን ኡምቤርቶ የገዛውን ውስኪ ከሁለት ብርጭቆጋ አቅርቤ ፊልሙን ከፈትኩ፡፡ ሰለሞን ውስኪውን ቀድቶ ሠጠኝ፡፡ ለድላችን! አጋጭተን ፉት ካልን በኋላ ሲጋራ ለኩሼ ሰጠሁት፡፡ ስቦ መለሠልኝ፡፡ የከፈትነው ፊልም ላይ ስድስት ወንዶች የከበቧት አንድ ሴት እርቃኗን ትደንሳለች፡፡ ወንዶቹ ልብሳቸውን እያወላለቁ ወረሯት፡፡

«የወንዶቹ እቃ ያስመረቅናል!» አለኝ ሰሌ፡፡

«ሴት ቀምሰህ ታውቃለህ?» አልኩት፡፡

«አዎ! ከተደፈርኩ በኋላ ግን ሴት አስጠላኝ፡፡»

«ተበድለህል!... ምን አይነት አደፍርስ ነው የሚመችህ?»

«ባለጌ! ብልት ነው የሚባለው፡፡ መሀፀኔን ስለሚያመኝ ብዙም ትልቅ አይመቸኝም፡፡»

«መሀፀኔን?» ሳቄ አመለጠኝ፡፡ ቀስ ብሎ'ኮ የወር አበባም አያለሁ ሊለኝ ነው፡፡ ወዴት እያመራን ነው?

«.... የዓለም ህዝብ በዝቶ የመጠጥ ችግር እና የምግብ ችግር እንዳይፈጠር አምላክ ምን እንዳደረገ ታውቂያለሽ?... ግብረ ሰዶማውያንን ፈጠረ! ሰዶማውያን አይወልዱም! ሌዝቢያኖችም እንደዛው! ይሄ ማለት ጥጋብ እና ደስታ ብቻ በምድር ላይ ይታያል ማለት ነው፡፡»

«አሁን ጤነኛ አለመሆንህን አረጋገጥኩ፡፡ በሽተኛ ነህ!»

«ማርኮ የነገረኝን ነው የነገርኩሽ!» አለኝ እየሳቀ፡፡

«ማርኮ ሰይጣን ነው! ወደፊት የራሴን ኃይማኖት እፈጥራለሁ ብሎ ሲጠረት ሰምተኸው አታውቅም?» አልኩት ተናድጄ፡፡

«አልነገርኩሽም ለካ! ኡምቤርቶ እና ወንድሙ በእግዚ.ያብሔር አያምኑም፡፡ የሆነ ሰይጣናዊ አምልኮ አላቸው፡፡ ማርኮ ነው አምልጦት የነገረኝ፡፡»

«ውሸቱን ነው! ይልቅስ ፊልሙን እንይ፡፡»

ስድስት ወንዶችን ያሰለፈችው ሴት አልበርድ ብላ የመዋኛ ገንዳ ውስጥ እየደፈቁ ያወጧታል፡፡ ሴሠኛ ናት! ሰለሞን መቁነጥነጥ ሲጀምር ጉዱን ለማየት መተኛት አለብኝ ብዬው መኝታ ክፍሌን ቀልፌ ተቀመጥኩ፡፡ እስከ ሀያ ቆጥሬ በሩን ቀስ ብዬ ከፍቼ ጭንቅላቴን ብቅ አደረኩ፡፡ ሰሌ ሱሪውን አውልቆ ሴጋ ይመታል፡፡ የግራ እጁን ወደ መቀመጫው ላከ፡፡ አሣዘነኝ! የታለበው አደፍርስ ማልቀስ ጀመረ፡፡ ሰለሞን ውስኪ የጠጣሁበት ብርጭቆ ላይ ደቀነው፡፡

«ምን ልታደርግ ነው?» አልኩት፡፡

በጣም ደነገጠ!

«ምን አስደነገጠህ? ሁሉም ስሜቱን ለማብረድ በየጓዳው የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡»

«ስ...ስፐርሚን... መሀፀኔ ውስጥ ልጨምር ፈልጌ ነው! ይህን ካላደረኩ በሰላም ማደር አልችልም፡፡» አለ አንገቱን ደፍቶ፡፡

«በግድ ሴት ነኝ! ወንድ መሀፀን የለውም! ፊንጢጣህ ውስጥ ከሆነ እኔ ልጨምርልህ!» ብዬ ብርጭቆውን ነጠኩት፡፡

እያፈረ ተንበረከከ፡፡ ስፐርሙን በጣቴ እያወጣሁ የፊንጢጣውን በር ቀባሁት፡፡ ጣቴን ወደ ውስጥ እንዳስገባለት ተማፀነኝ፡፡ እኔ እራሴ ምን

እያደረግኩ እንደሆነ ግራ ሲገባኝ ብርጭቆውን ይገፔ ተገተርኩ። ሰለሞን ስፐርሙን ካገኘ ሰላም ያለው እንቅልፍ እንደሚወስደው ሲያጫውተኝ ይኸን መኝታ ቤት ሄድኩ። ሰለሞን ደጋግሞ ይናገራል። የኔ ጭንቅላት ግን ውሸት ነው ይላል። ብርጭቆው ውስጥ ያለውን ስፐርም ለመድፋት ወደ መፀዳጃ ቤት ሄድኩ። ሰለሞን ከምኔው አጠገቤ እንደደረሰ አላውቅም ብርጭቆውን ቀምቶኝ መኝታ ክፍሉ ይዞት ገባ።

ሴት አምጣ የወለደች እናት በባሏ መመስገኛዋ ዘመን መጣ! ወንድ የተወለደልህ አባት አመድ በላይህ ላይ ነስንሰህ አልቅስ! እናት ሆይ ሴት ልጅሽ ዲቃላዋን ስታመጣልሽ በእልልታ ተቀበያት! ወንዱ ልጅሽ ተደፍሮ የመጣ ቀን ግን ሱባዔ ገብተሽ ወደ አምላክሽ አልቅሺ! የማይወለድ መከራ አርግዞልሻልና!!

አዲስ ቀን ምን ይዞ እንደሚመጣ ማንም አያውቅም። ሰለሞንን ይረዳዋል ብዬ ላሰብኩት ሁለተኛ ዘዴ መሣሪያ የዳረግኳት መቅደስን ነው። ፃድቃኔ ማርያም ፈውሷ ፈጣን ነው ሲባል እሠማለሁ። የመቅደስን እናት ደግሞ በሽታ አልጋ ላይ ጥሏቸዋል። ስለዚህ መቅደስ እናቷን ይዛ ወደ ፃድቃኔ ማርያም መሄድ አለባት። የእርዳታ እጅ ደግሞ ሰለሞንን መጠየቅ ግዴታዋ ነው። በገንዘብ በኩል እኔ አለሁ። አሪፍ ዘዴ ነው! መቅደስን ከሞላኋት በኋላ ቁርስ እየበላን እጇን እያፍተለተለች ስለ እናቷ በሽታ መቀባጠር ጀመረች።

«ፀበል ውሰጃቸዋ!» አልኳት።

«ገንዘቡስ ከየት ይመጣል? እራሷን ችላ መጠመቅ ስለማትችል ደግሞ የግዴታ ሰው ያስፈልጋታል። እኔ ብቻዬን አልችላትም።»

«በገንዘብ በኩል አታስቢ፣ የሚረዳሽ ሰው ግን ከየት ታገኛለሽ?»

አልኩ ያዘንኩ መስዬ፡፡

«የት ልትወስጃቸው ነው?» አለ ሰለሞን፡፡

«የድቃኔ ማርያም! ወንድም ቢኖረኝ እናቴ የአልጋ ቁራኛ ሆና አትቀርም ነበር፡፡» አለች መቅዲ እያለቀሰች፡፡

መቅደስ አሪፍ ተዋናይ መሆኗን ያወቅኩት ዘግይቼ ነው፡፡

«አይዞሽ!... እኔ አብሬሽ እሄዳለሁ!... ስንት ቀን ነው የምንቆየው?» አለ ሰሌ፡፡

በመላ በሰበብ በዘዴ አማህኝተሽ...

«ሰሌ ፀበል ምናምን ይመችሀል እንዴ?» አልኩት መልሱ እየናፈቀኝ፡፡

«እኔኮ አልጠመቅም! መቅዲን ልርዳት ብዬ ነው እንጂ... »

ከሄደ መጠመቁ አይቀርም! ሴት መሆኔን የምወደው ብልህተኛ መሆኔን ስለማውቅ ነው፡፡ ድራማው ካለቀ በኋላ ሰለሞን ለባብሶ ሸቶውን ለአፍንጫዬ ትቶ ወጥቶ ሄደ፡፡ ቀኑን ሙሉ ሳይመጣ ዋለ፡፡ ሀሳቡን ቀይሮ ይሆን? እያልኩ ስጨነቅ፤ ማታ ሰክሮ እየተንገዳገደ መጣ፡፡

«እርግጠኛ ነኝ ከወንድ ጋር ነበርክ፡፡» አልኩት፡፡

«እና ምን ትጠብቂ ያለሽ?» አለኝ እያለቀሰ፡፡

«ይህን ህይወት ትፈልገዋለህ ማለት ነው?»

«ባልፈልገውስ?»

«ትቶጠብ ነበራ!»

«ስሚ!... ግብረ ሰዶማዊ መሆኔን እያወቅሽ ነው ያስጠጋሽኝ አይደል? ታዲያ አሁን ማንነቴን ለምን ጠላሽው? እኔ ለምኖረው ህይወት አንቺ ምቀኛ ለምን ትሆኛለሽ? ይህ ነው ህይወቴ! አልተመቸሽም? ቤቴን ልቀቅ ማለት ብቻ ነው የሚጠበቅብሽ! በቃ! »

የሚናገረው ከብቅል ጋር ስለሆነ መልስ አልሰጠሁትም:: አልቅሶ ሲወጣለት ይቅርታ ጠየቀኝ:: በጨቅላ እውነትን ለመደበቅ መሞከር የሰው ልጅ ባህሪ ስለሆነ አልተቀየምኩትም:: ለጉዞ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ወጣ ብለን ገዛዝተን ከተመለስን በኋላ፣ ካርታ ስንጫወት አምሽተን እንቅልፌ ሲመጣ ትቼው ወደ አልጋዬ አመራሁ:: የመቅደስ እናት በሰሌ ሰበብ ፃድቃኔ ማርያም ለመጠመቅ እድሉን አገኙ:: ፈጣሪ የሚያስፈልገንን ቀድሞ ያዘጋጃል ማለት እንደዚህ ነው!!

አስራ አምስቱን ቀን ካለ መቅደስ እና ካለ ሰሌ ብቻዬን አሳለፍኩት:: ቤተክርስቲያን መሄድ የዘወትር ስራዬ ነበር፣ ግን ፀሎት ሳላደርግ ነበር ወደ ቤቴ የምመለሰው፤ አብዲ ድምፁን አጥፍቶብኛል፣ ስለ እሱ ማሠብ ባላቆምም፤ ከእሱ መራቅን ግን ምርጫዬ አድርጌዋለሁ:: ኡምቤርቶን መርሣት የማይቻል ነገር ነው:: ለእኔ የመጀመሪያው መልካሙ አዳም ነውና! ቤቴ ውስጥ ስራ በመስራት እና ሲጋራ በማጨስ ከሀሳቤ ለመሸሽ እጥራለሁ:: ለነገሩ ሁነብ የሚመጣው ጕኔ አልጋ ሲነካ ነው:: ስለ ሰለሞን ደህንነት መቅደስ በየጊዜው እየደወለች ትነግረኛለች:: ጠዋት ማታ ጊዜውን በፀሎት እንደሚያሳልፍ እና እንደሚጠመቅ ስሰማ በጣም ተደስቻለሁ:: እናቷም በጥሩ ጤንነት ላይ እንደሚገኙ ሰማሁ:: ብቸኝነት ግን እንዴት ያስጠላል?

አስራ አምስቱ ቀን ዓመት ሆኖ በግድ አለቀ፡፡ መንገደኞቹ ለምሳ እንደርሳለን ስላሉኝ ሦስት አይነት ወጥ ሰርቼ ቁጭ ብዬ ስጠብቃቸው ዋልኩ፡፡ ለምሣ እንደርሳለን ያሉት ሰዎች ድምፃቸው ጠፋ፡፡ የወጣ ሰው መመለሱ በፈጣሪ እጅ ነውና! አንተ ታውቃለህ እያልኩ እጄን አጣምሬ ቁጭ አልኩ፡፡ ምድር ተጠማሁ ያለች ይመስል ሠማይ እዬዬውን ለለቀቀው፡፡ መንገደኞቹ በዝናብ ተጠምቀው ምሽት ላይ ወደ ቤት መጡ፡፡ የተሳፈሩበት መኪና መንገድ ላይ ተበላሽቶ እስኪሰራ ነበር የቆዩት፡፡ ከበን በአንድ ትሪ እራት ከበላን በኋላ ወተት አፍልቼ ሰጠኋቸው፡፡ ብርድ ያኮማተረው ገላቸው ዘና አለ፡፡ ዝናቡ ሲያባራ መቅደስ እና እናቷ ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ ሰሎ እና እኔ አልጋዬ ውስጥ ገብተን ወሬ ጀመርን፡፡

«መቼም ጉዞህ አስደሳች እንደነበር እርግጠኛ ነኝ፡፡» አልኩት እንድ ባሕታዊ የመደመዱለትን ፀጉሩን እየነካካሁ፡፡

«በቅዱስ እጁ ያበረከተልህን ጥቁር ፀጉር ምን ልሁን ብለህ ነው ወደ ቢጫ የለወጥከው? መቼም የዲያቢሎስን ምክር በመስማትህ ነው የፀጉርህ መልክ ሊቀየር የቻለው፣ እኔ ደግሞ ፀጉር ማሳመር አልችልም እንጂ መጉመድ አያቅተኝም፡፡ አሉኝ እና ፀጉሬን ቆርጠው አቃጠሉት እልሻለሁ፡፡» ፊቱ ላይ ፈገግታ አነበብኩ፡፡

«ሌላስ ምን አዲስ ነገር አለ? ማለቴ....»

«በህልሜ ከተለያዩ ወንዶች ጋር ስቀብጥ ነው የማየው፡፡ ወደ እዚህ ተመልሼ በህልሜ ያየሁትን መተግበር አምሮኝ ነበር፡፡ ግን የመቅደስን በሽተኛ እናት ትቶ መምጣት ሀጢያት መሰሎ ታየኝ፡፡ ጨንቆኝ ምርር ብዬ ሳለቅስ አንድ አባት አዩኝና... ምን እንዳሉኝ

ታውቂያለሽ?... በእግዚአብሔር ፊት የፈሰሰች እንባ ፍሬማ ናት! ለቅሶህ ለመልካም ነውና በለቅሶህ ተደሰት ልጄ!... ብለውኝ ሄዱ፡፡»

«ችግርህን ብትነግራቸው እኮ ይፀልዩልህ ነበር፡፡»

«ችግሬንማ ለአንድ መለኩሴ ተቀድጄ ተፀይፈው ሸሹኝ፡፡»

«የመለኩሴ ልብስ የለበሰ ሰይጣን አጋጥሞህ ይሆናል!»

ድንገት በሀሳብ ጭልጥ አለ፡፡ የሰለሞን አንዱ ራስምታት ከቤሰቦቹ መራቁ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ የቤተሰብ ፍቅር ማጣት ቀልድ አይደለም፡፡ ቤተሰቦቹ ከጎኑ ሆነው ፍቅር ቢለግሱት ኖሮ ሰለሞን ሠዶምን በጊዜ ይሰናበታት ነበር፡፡ ፍቅር ሁሉን ያሸንፋልና! ቤተሰቦቹ ግዙፍ የመኪና እቃ ማከፋፈያ ስላላቸው ሰሌ እንደምንም ብሎ ይቅርታ ጠየቆ ሥራ እንዲጀምር መገፋፋት የኔ ሀላፊነት ነው፡፡ ምክንያቱም ቤተሰቦቹ የባህሪ ለውጥ ማምጣቱን ተገንዝበው ያቀርቡታል፡፡ ከእነሱ ያጣውን ፍቅር ሲያገኝ ደግሞ ሰዶምን ይሸሻታል፡፡ ሰለሞን ሥራ መጀመር እንዳለበት ስነግረው አላቅማማም፡፡ ይቅርታ ይነፍጉኛል ብሎ ስለሰጋ ቤተሰቦቹጋ መሆኑ ግን አለተዋጠለትም፡፡ ግን ይቅርታ የማይነፍግ አንድ ወገን እንዳለው ጠቆምኩት፡፡ እናቱ!!

ህይወት ብዙ መንገዶች አሏት! እየመረጠ መጓዝ ደሞ የሰው ልጅ ግዴታ ነው፡፡ ሰሌ በእናቱ አማካኝነት ከቤተሰቦቹ ጋር ታርቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ አምሽቶ ሲመጣ ግን ከወንድ ጋር ሲዳራ ያመሸ እየመሰለኝ እጨነቃለሁ፡፡ መቅደስ ለእናቷ የሰሌን ምሥጢር ሹክ ብላቸዋለች መሰለኝ፡፡ በየቀኑ ግራዋና ሎሚ ይልኩለታል፡፡ እንደዶሮ እና እንደእንስራ እየተንጨፈጨፈ ቁርሡን በልቶ ወደ ሥራው ይሄዳል፡፡

ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ከርቤ ይላከለታል፡፡ መቅደስ ጥዋትና ማታ የሰለሞንን ክፍል ታጥናለች፡፡ ከፈለገች ደግሞ ሰውየውን እራሱ ሳይወድ በግዱ ጊርጊራውን ፊቱ ላይ ደቅና ታጥነዋለች፡፡ ሰሌም እናትሽ ጠንቋይ ሳይሆኑ አይቀሩም እያለ ያናድታል፡፡ ሠዶምን ሙሉ ለሙሉ ተዋት ብዬ ስደሰት፡፡ ውጪ ማደር ጀመረ፡፡

.....ከቤቴ ለአንዳንድ ጉዳዮች በወጣሁ በገባሁ ቁጥር ኃይማኖት ተብዬውን መርማሪ ማየቴ ሰላም ነስቶኛል፡፡ ሁሉም ነገር በአንዴ ተቀይሯል፡፡ ምናልባትም የእኔ ፀባይ! ሥራ ለመጀመር ፈልጌ ማግኘት አልቻልኩም! የወሲብ ጥምም ሊያሳብደኝ ነው! እራሴን በሥራ መደበቅ ስለፈለግኩ መቅደስን ቅር እያለኝ አሠናበትኳት፡፡ መቅደስ አሰናብቻትም አንዳንዴ እየመጣች ልብስ ታጥብልኛለች፡፡ ቀኑን ሙሉ በረባ ባረባው ጉንበስ ቀና ስል እውላለሁ፡፡ ሲመሽ ሰለሞንን ለመደበቅ ማስታወሻዬ ላይ አቀረቅራለሁ፡፡

እንደ እህት እና ወንድም ተቃቅፎ መተኛት ትዝታ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ከሁሉም የደነቀኝ ግን የአብዲ መጥፋት ነው! ከእሱ ጋር ያሳለፍኩትን ሁሉ ሳስታውስ ሂደሽ ፈልጊው የሚል መንፈስ ያስጨንቀኛል፡፡ ስረጋጋ ደግሞ ለእኔ የሚኖርን መልካም ሰው ገሎብኛልና ልርቀው ይገባል እላለሁ፡፡

# ክፍል ሰባት

## እንቆቅልሽ

እንደ ዛሬዋ ምሽት በህይወቴ ደንግጬ አላውቅም፡፡ መብረቅ የወረደብኝ ነው የመሰለኝ፡፡ መብራት አጥፍቼ ልተኛ ስል የሳሎኑ በር ተንኳኳ፡፡ በሩን ስከፍት ግን... ማስታወሻዬ!... ስሜቴን እንዴት ብዬ መግለፅ እንዳለብኝ አላውቅም!... ልቤ ሥራውን ያቆመ መሠለኝ፡፡ አይኔ እንደፈጠጠ አፌን ከፍቼ ተገትሬ ቀረሁ፡፡ ኧረ መሮጥም እምሮኝ ነበር፡፡ የማይታመን ነገር.... ኡምቤርቶ እና ማርኮ በር ላይ ተገትረዋል፡፡ ለእኔ የሰጠኝን አይነት ሀብል አጥልቋል፡፡ ዐይኔን ጨፍኜ መልሼ ገለጥኩት፡፡ በእውኔ ነው! ኡምቤርቶ በህይወት አለ፡፡ ሁለቴ በጥፊ ደረገምኩበት፡፡

«በጣም ይቅርታ የኔ ፍቅር! አንቺን ለመርግት ብዬ ነው ወደ አገሬ የሄድኩት ግን አልቻልኩም፡፡ እንዴት ነሽ?» አለኝ ኡምቤርቶ፡፡

«ከቤቴ ውጡልኝ!» አንባረቅኩባቸው፡፡

ኡምቤርቶ ተጠጋኝ፡፡ ሸሸሁት! ሸሸሁት!

«ኡምቤ...» እንባዬ ቀደመኝ፡፡

«ስትረጋጊ ብመጣ ይሻላል! ማርኮ እቃዎቼን ያዝና ተከተለኝ፡፡» አለ ፊቱን አዙሮ፡፡

ማርኮ ሰላም እንኳ ሳይለኝ መኝታ ክፍሌ ገብቶ የታዘዘውን ይዞ ወጣ፡፡ ትራሴ ስር ወሽቄ ያስቀመጥኩትን ሀብል አውጥቼ ለኡምቤርቶ ሰጠሁት፡፡ ሁለተኛ አይኑን ማየት እንደማልፈልግ እያለቀስኩ

ነገርኩት፡፡ ሀብሉን እያገላበጠ ከተመለከተው በኋላ ሳመውና አንገቴ ላይ አጥልቆልኝ ወጥቶ ሄደ፡፡ አይገርምም? ኡምቤርቶ ትዕዛዜን አክብሮ ሁለት ሳምንት ሙሉ ሳይመጣ ቀረ፡፡ እኔ ግን ይመጣል ብዬ ጠብቄው ነበር፡፡ ከቀናቶች በአንዱ ጭጋጋማ ደባሪ ቀን የፈረደበትን የእርግዝና መከላከያ መርፌ ተወግቼ ስመጣ ኡምቤርቶን በር ላይ ቆሞ አገኘሁት፡፡ ገላምጬው ወደ ውስጥ ገባሁ፡፡ ተከትሎኝ ገባ፡፡

«ምን ፈልገህ መጣህ?» ጮህኩበት፡፡

«ሀብሉ አንገትሽ ላይ የለም!» አለኝ ረጋ ብሎ፡፡

«ትራሴ ስር አለልህ መውሰድ ትችላለህ፡፡»

«የእኔ ፍቅር...»

«አታስመስል!»

«የአቢሲንያ ቆንጆ! ለምን እንደመጣሁ ታውቂያለሽ?»

«ማወቅ አልፈልግም!»

ፀጉሬን ጨምድዶ አንገቴ ስር ገባ፡፡

«አብዲ እንዲህ ስለሚያደርግሽ አይደል የምትወጂው?» የአንገቴን ጠረን ምጎ ለቀቀኝ፡፡

«ከአገር ከመጣህ በኋላ አስራ አምስት ቀን ሙሉ የት ነበርክ? ትዕግስት ቤት?»

«ብዙ ሥራዎች ስለነበሩብኝ ትዝ አላልሽኝም!»

«ጥሩ ለውጥ ነው! አሁን ከቤቴ ውጣልኝ፡፡»

«የገዛሁት ቤት እስከሆነ ድረስ በፈለግኩት ሰዓት መውጣት መግባት እችላለሁ፡፡ ሳልነግርሽ መሄዴ ጥፋት ነው!... ልቤ አልቻለምና ተመልሼ መጣሁ፡፡ ስለዚህ ይቅር በይኝ!»

ያን ውብ አይን ትኩር ብዬ ተመለከትኩት!...

«አብዲ የገደለህ መስሎኝ በጣም አዘንኩ!... ከእሱም ጋር ተጣላሁ! አንተ'ኮ ባለውለታዬ ነህ!... ጥሩም ሰው ነህ!... ደግሞም ናፍቀኸኝ ነበር፡፡»

ለምን እንደሆነ አላውቅም ከልቤ ሳቅኩ፡፡ ደስታ ይሆን?

«ሳቅሽ ያምራል! ቆንጆም ነሽ! ወንድሜ ከከበረ ሰላምታ ጋር ስጦታ ልኮልሻል፡፡» አለኝ ከኪሱ ቀይ ፈርጥ ያለው ቀለበት አውጥቶ፡፡

«ቀለበት?»

የቀለበቱን ውበት ሳደንቅ ፈጠን ብሎ የጋብቻ ቀለበት የሚጠለቅበት ጣቴ ላይ ሰካው፡፡

«ዳይመንድ ነው! አባቴ ለእናቴ ያበረከተው ውድ ስጦታ ስለሆነ አደራ ከጣትሽ እንዳይወልቅ፡፡»

«የወንድምህ እጮኛ ነኝ!» ጠቀስኩት፡፡

«ትንሽ ቀናሁ!...»

«እኔ ደግሞ ላንተ ስጦታ አለኝ!»

የተነፋፈቁ ከናፍሮቻችንን አገናኘኋቸው፡፡ አልጋዬ ላይ ተናፍቂው ሰላማዊ ጦርነት ተጀመረ፡፡ ኡምቤርቶ ሀይል ጨምሯል! ንክሻው እና ትግሉ እንደ አብዲ ሆነብኝ! የእውነት ኡምቤርቶ ተቀይሯል! ሰላማዊ ትግላችን እንዳበቃ ልብሱን ለባብሶ ዞር ብሎ ሳያየኝ እየተጣደፈ መውጣቱ ደግሞ ይበልጥ አግራሞትን ጭሮብኛል፡፡ እርቃኔን እንደተጋደምኩ ሰለሞን ዘው ብሎ ሲገባ ፈጠን ብዬ በአልጋ ልብሱ ተጠቀለልኩ፡፡ አብረን እንውላለን ብሎ ሥራ ፈቶ ነው የመጣው፡፡

«ኡምቤርቶ ፍፁም ተቀየረብኝ! ወሲብ ላይ ደግሞ አብዲን እራሱን ሆነብኝ፤ እንደ ህፃን ልጅ የአንገት ስር ሽታ፤ ጠረኑ መንፈስን ያድሳል፤ እጁ ሰውነቴ ላይ እግት ጭሮ ሞትኩ ስል እንደገና ሕይወትን ዘራብኝ፤ እንደገና እንደገና.....» ሳልጠየቅ ብዙ ቀባጠርኩ፡፡

«ኧረ... ተረጋጊ!» አለኝ ሰለሞን፡፡

«ወንድሙ የላከልኝን ቀለበት እይ... አያምርም?»

«ቀይ ነገር ያለበት ማንኛውም ነገር ያስጠላኛል!»

«ቀይ እና ሰማያዊ ቀለም ምርጫዬ እንደሆነ አታውቅም?»

«አንዱን ምረጪ!»

«አልችልም!»

«ልክ እንደ አብዲ እና እንደ ኡምቤርቶ ማለትሽ ነው? የጋብቻ ቀለበት የምታደርጊበት ጣትሽ ላይ ማድረግሽ ለምን ይሆን?»

«እኔ 'ንጃ! ሳላስበው አጠለቀልኝ!...»

አብረን እንውላለን ሲል የነበረው ሰውዬ እናቴን ማግኘት እፈልጋለሁ ብሎ ወጥቶ ሄደ፡፡ ቦታ አልሰጠሁትም፡፡ ሻይ ቡና ስፕሪስ ስጠጣ ዘና ስለሚያደርገኝ አቅራቢያዬ ወደሚገኝ ካፌ ሄድኩ፡፡ እስፕሪሱን አዝገቤ አይኔን ለቅልውጥና አሰማራሁት፡፡ ደህና ነገር የለም! ያዘዝኩትን ሻይ ቡና ስፕሪስ ፉት ከማለቴ ኃይማኖት ተብዬው መርማሪ ሳያስፈቅደኝ ፊት ለፊቴ ካለው ወንበር ላይ ቁጭ አለ፡፡ ያለ የሌለውን ሲቀባጥር ቆይቶ ከእኔ መልስ ሲያጣ ዝም አለ፡፡

«እውነቱን ንገረኝ እስቲ... ስታየኝ ወንጀለኛ እመስላለሁ?» አልኩት ቁና ቁና እየተነፈሰ ሰላም ሲነሳኝ፡፡

«ጎሽም!... አያደለሽምም!» አለኝ ዓይኔን እየመረመረ፡፡

«አልገባኝም?»

«ወይም ወንጀለኛው ካንቺ ጀርባ ይኖራል!»

«አሁንም አልገባኝም?»

«አንድ ምሥጢር ልንገርሽ? የሚቾቹ አስክሬን ላይ ምንም ዓይነት አሻራ ባለመገኘቱ ወንጀለኛው ላይ በትክክል መድረስ አልቻልኩም፡፡
ግን አንድ ቀን ወንጀለኛው ቀን ጥሎት እራሱ ወደኔ ይመጣል፡፡»

«አደራ ሙስና እንዳያታልልህ!» ብዬው ሒሳብ ሳልከፍል ወጥቼ ሄድኩ፡፡ በተዘዋዋሪ ኃበዘኝ ማለት ነው፡፡

ቤቴ ስገባ ሰለሞን እቃ ቤቱ ውስጥ ጉድ ጉድ ይላል፡፡ አድርጎት ስለማያውቅ ተገረምኩ፡፡ ቴሊቭዥንን ከፍቼ ሶፋው ላይ ጋደም ካልኩ በኋላ የሠማዩን ጉርምርምታ ስሠማ ውጪ ወጥቼ ቆምኩ፡፡ ንፋሱ ያኮረፈውን ሠማይ ማናደዱ ነው መሰለኝ እያፏጨ ያልፋል:: ሆደባሻው ሠማይ መከፋቱን እንባውን በማውረድ ገለፀ:: ቅዝቃዜው ወደ ሰውነቴ ሲገባ ጃኬት ለመደረብ ወደ ውስጥ ገባሁ፡፡ ሰለሞን የጣደው ድስት አሮበት ተበግሞቶ ብቻውን ያጉተመትማል፡፡ የውጭው ትእይንት ስለማበኝ ጃኬት ደርቤ ተመልሼ ወጣሁ፡፡ ይቺ ሠዓት አብዲን ታስታውሰኛለች፡፡ የሰማይ ለቅሶ ለኔ እና ለአብዲ ደስታ ነበር፡፡ ግን ያለፈ ታሪክ ነው! አብዲ በኔ ጩከኖ ጠፍቷል፡፡ ሰዓቱ መሮጥ ልማዱ ነውና እኔን ገትሮ ነጉዷል፡፡ ሰለሞን እራት አቅርቦ ሻማ ለኩሶ እየጐተተ ወደ ውስጥ አስገባኝ፡፡

« ኡምበርቶ መመለስ አብዱን የበለጠ እንዳስታውሰው አደረገኝ፡፡»

«ኢማ!... አብዱ ስቃይሽን እንጂ ደስታሽን ስለማይፈልግ እርሺው፡፡ ቆይ አንቺ አዲስ ሕይወት፡ አዲስ ማንነት፡ አትፈልጊም?»

ሁሌም፡ አዲስ ማንነት፡ አዲስ ሕይወት፡ እፈልጋለሁ፡ ግን ምኞቴ እንዳሆን ይቀራል፡፡ ምክንያቱም የትላንትናው ማንነቴን አዲስ ነገር አይቀይረውም፡፡ በሩ በሀይል ተንኳኳ!... ጆሮዬን ተጠራጠርኩት!... ተደገመ!... እየሮጥኩ ከፈትኩለት!... እሱ ነው!... አብዱ ጊሙ አድጓል! የጠቆረም መሠለኝ!... ተጠመጠመብኝ!... ሰለሞን መኝታ ቤቴ ገብቶ በሩን ወርውሮ ዘጋው!... ብቻችንን ስለተወን ደስ ብሎኛል፡፡ እናቱን እንዳገኘ ህፃን ተቅበጠበጥኩ!...

«አባዱ!... ይቅርታ አድርገህልኝ ነው የመጣኸው?»

«አንቺ ምን አደረግሽኝ?»

«ያልገደልከውን ሰው ገድለሀል ስላልኩህ ነዋ!... ለምን ገደልኩት አልከኝ?...»

«ፈርተሽ ከሌሎች ወንዶች ጋር ያለሽን ግንኙነት እንድታቆሚ ብዬ! ኡምበርቶ ስለኔ ያነሳልሽ ነገር የለም?»

«የለም! ምን ሆነህ ነው የጠፋኸው?»

«ድሬዳዋ ሂጂ ከአባህ ጋር ለመታረቅ ሰላት ጀመርኩ፡፡ ከእራሴ ለመደበቅ ውሎዬን መስጊድ ውስጥ አደረግኩ፡፡ ቤተሰቦቹ የውስጤን አላወቁ በድርጊቴ ተደሠቱ፡፡ እኔ ግን እየተቃጠልኩ ነበር!... አንቺ ውስጤ ተኝተሽ ታቃጥይኝ ነበር፡፡ መቀበል የማልፈልገው እውነት

ወስጤ ተጋድሞ እየበላኝ ነበር፡፡ ማፍቀሬን በግድ ቀላቻ እየርገጥ ከረምኩ፡፡ ዛሬ ግን ተሸነፍኩ! አፈቅርሻለሁ!!»

አብዲ የኡምቤርቶ ልክፍት ተጋባበት!! እጆቼን ይዞ እየተማፀነኝ ነው!!

«የትም ሲጀርር ቆይቶ የመጣውን ሁሉ እየተቀበልሽ ጊዜሽን አትጨርሺ፡፡ ኡምቤርቶ ሲመጣ ነው ትዝ ያለችህ? በብቸኝነቷ ጊዜ የት ነበርክ? ኤማ!... አይንሽ ግለጪ ድራማ እየሰራብሽ ነው፡፡» አለ ሰለሞን አብዲ ላይ አፍጥጦ፡፡

ሰለሞን ማንን እንደተናገረ የዘነጋው መሰለኝ፡፡ የአብዲ ፊት መለዋወጥ ሲጀምር እየጎተትኩ መኝታ ክፍሌ ይዤው ገባሁ፡፡ አብዲ ለረጅም ሰዓት ጀርባውን ሰጥቶኝ ቆየ፡፡ ከጀርባው ቆሜ ቀስ ብዬ እጄን ወደ ደረቱ ላኩት፡፡ ወደኔ ዞሮ አቀፈኝ፡፡ ለረጅም ሰዓት ሳንነጋገር ተያየን፡፡ ልብሴን አውልቄ እርቃኔን ፊት ለፊቱ ቆምኩ፡፡ ልብሴን ከወለሉ ላይ አንስቶ አለበሰኝ፡፡ ተዓምር ሆነብኝ፡፡

«አፈቅርሻለሁ!» አለኝ እጆቼን ይዞ፡፡

«ወንድ የሚያምን ልብ የለኝም!» ተለጠፍኩበት፡፡

«እንድታምኚኝ መሰቀል ነበረብኝ?»

«በእናትህ አታላዝንብኝ!»

«እመለሳለሁ!» ብሎኝ ወጥቶ ሄደ፡፡

ከመስኮቱ ባሻገር ያለው ሠማይ ላይ አፈጠጥኩ፡፡ ከአብዲ የምፈልገው ወሲብ ወይስ...? የመኝታ ክፍሌ በር የመደፍ ውርጅብኝ ታዘዘበት፡፡ ሰለሞን መስሎኝ ልጮህበት በሩን በረገድኩት፡፡ ኡምቤርቶ ነው!

ለስላምታ ጊዜ አልነበረውም፡፡ የለበስኩትን ልብስ በአስገራሚ ፍጥነት ቀደደው፡፡ ፀጉሬ እስኪነቀል ድረስ እየጐተተ አልጋዬ ላይ ወረወረኝ፡፡ አስገራሚ ፍጥነት!... አስደናቂ ችሎታ!... ኡምቤርቶ ምን እንዳደረገኝና ምን እያደረገ እንደነበረ ማስታወስ ባልችልም... በደስታ መስከሬን ግን አውቃለሁ፡፡ ታድያ ከሰከርኩ እንዴት የሆንኩትን ላስታውስ እችላለሁ? ኡምቤርቶ የምፈልገውን ነገር ያወቀው አሁን ነው! ኡምቤርቶ የድሮው አብዲን ሆኖብኛል! አብዲ ደግሞ የድሮው ኡምቤርቶን!!

«መአዛሽ ከአፍንጫ አይነቀልም፡፡ ጥዓምሽ ከወንድ ልጅ ምላስ አይጠፋም፡፡ እየደጋገመ ቢበላሽ አይጠግብሽም፡፡ ተፈጥሮ የለገሠችሽ ወንድን መግዛት የሚችል ሀይል ያለሽ ይመስለኛል፡፡ ልዩ ፍጡር ነሽ!» አለኝ ኡምቤርቶ በሚመስጥ የአነጋገር ለዛ፡፡

«ፍፁም ተቀይረሀል! አገርህ በልተህ የመጣኸውን ነገር ማወቅ እችላለሁ?» አልኩት ደረቱ ላይ ተለጥፌ፡፡

«ቆንጆ!... አብዲን ሲወጣ አግኝቼው ነበር!...»

«ምንም አላለህም?... ማለቴ... »

«ሰላምታ ሰጥቶኝ ነው የሄደው!»

«አብዲ ሰላምታ ሰጥቶህ ሄደ?» ማመን አልቻልኩም፡፡

«ነገ ምሳ አዘጋጅተሽ ጥሪው! ከዛ የሆነ ምሥጢር እነግርሻለሁ፡፡» አለኝ አለንጋ ጣቶቹን ፀጉሬ ውስጥ እያርመሰመሰ፡፡ ተስማማሁ!

አስደናቂው ኡምቤርቶ ማታ እንደህፃን ተረት እየነገረ ነበር ያስተኛኝ፤ በጥዋት ቀስቅሶ ደግሞ መፀዳጃ ቤት ይዞኝ ገባ፡፡ ወንድሙ ልብስ መቅደድም ሳያስተምረው አልቀረም መሰለኝ፡፡ የለበስኩትን ፒጃማ

ከተደደው በኋላ የሚወርደው ቀዝቃዛ ውሀ ስር ይዞኝ ገባ፡፡ ድንገት ዐይኔ ኡምቤርቶ ጀርባ ላይ ተጣብቆ ቀረ፡፡ አፉን የከፈተ ነብር ከትከሻው ዝቅ ብሎ ተነቅሷል፡፡ ወደ አገሩ ከመመለሱ በፊት ንቅሳት እንዳልነበረው እርግጠኛ ነኝ፡፡ ሰሞኑንስ እንዴት አላየሁትም? እያልኩ ከእራሴ ጋር ሳወራ፣ ድንገት፣ «ንቅሳቱ ያምራል?» ሲለኝ በርግጌ ጀርባውን ለመቀባት የያዝኩትን ሳሙና ጣልኩት፡፡ «ነብሩ በህይወት ያለ ስለሚመስል ያስፈራል እንጂ ያምራል!» አልኩት፡፡ መልስ ሳይሰጠኝ ለቅለቅ ብሎ ከመፀዳጃ ቤቱ ወጥቶ ሄደ፡፡ ገላዬን ታጥቤ ከጨረስኩ በኋላ ከመፀዳጃ ቤት ስወጣ ኡምቤርቶ የለም፡፡ ሰለሞን ቁርስ አዘጋጅቶ እየጠበቀኝ ስለነበረ ፎጣዬን እንዳሸረጥኩ ከጎኑ ተቀመጥኩ፡፡

«እራስሽን እየሸጥሽ አይመስልሽም?» አለኝ ሰለሞን በድፍረት፡፡ ፈገግታ የነገሰበት ፊቴ መኮማተር ጀመረ፡፡

«ለገንዘብ ብለሽ የማንም መፈንጫ ሆነሻል!» ጨመረልኝ፡፡

ትንሽ!... ትንሽ እንኳ እፍረት ቢጤ ፊቱ ላይ አይነበብም፡፡ ተናደድኩ!

«የተናናቅን አይመስልህም?»

«እህቴ መሆንሽን አትዘንጊ!»

እህቴ! የሚለው ቃል ትንሽ ቀዝቀዝ አደረገኝ፡፡

«ባህሪህ ተቀይሯል! የማደርገው ነገር ያበሳጭሀል! ችግርነ ምንድነው?»

«ችግሬንማ ነገርኩሽ! ግን አይገ... አይገባሽም!...»

«ሰለሞን መስማማት ካልቻልን በሰላም መለያየት ያለብን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም እኔ ካንተ ጋር መጣላት አልፈልግም፡፡»

«የምትፈልጊያቸው ወንዶች ሲመጡ አስጠሳሁሽ?»

«እነሱን እና አንተን ምን አገናኛችሁ?»

«እኔም ወንድ ነኝ!»

«ወንድማ አይደለህም!»

ማለት አልነበረብኝም! ግን...ሳናድድ...

አንዱን ክቤ ወደ ሌላው ስሄድ ያኛው ተንዶ ይጠብቀኛል፡፡ አንዱ የሌላውን ባህሪ እየወረሰ የጠበቅኩት ቀርቶ ያልጠበቅኩት ይመጣል፡፡ የስለሞን ግን ከሌሎቹ የተለየ ሆነብኝ፡፡ በማያገባው ነገር ጥልቅ እያለ ይበሳጫል፡፡ መቅዲ ጋር ደውዬ መጥታ ሥራ እንድትጀምር ጠየኳት፡፡ አላሳፈረችኝም! መቅዲን ምሳ ለመሥራት የሚያስፈልጋትን ሁሉ ገዛዝታ እንድትመጣ ገንዘብ ሰጥቼ ከላኳት በኋላ አብዲን ደውዬ ምሳ ጋበዝኩት፡፡ ደስታውን ገለፀልኝ!

እኔን ያጓጓኝ ኡምቤርቶ አብዲን የፈለገበትን ምክንያት ማወቅ ነው፡፡ የሚነግረኝ ምሥጢርስ ምንድነው? መቅደስ ካለች ሥራዬ የሚሆነው አምሮት ቆንጆን ማስዋብ ነው፡፡ ከኡምቤርቶ ጋር የመጀመሪያ እራት የበላሁበትን ቀሚስ ለበስኩ፡፡ ዐይኔን ደመቅ አድርጌ ተኳልኩ፡፡ ከንፈሬ በቀይ ልፒስቲክ ደምቋል፡፡ በመስታወት እራሴን በደንብ ተመለከትኩት፡፡ የወሲብ ፍላጐትን የመቀስቀስ ችሎታ የተካንኩ ሴት በመሆኔን ኮራሁ! የሣሎኑን በር ገርበብ አድርጌ ቁጭ ብዬ ሲጋራ እያጨስኩ እንግዶቼን መጠበቅ ጀመርኩ፡፡

መጀመሪያ የመጣው አብዲ ነበር። ጺሙን ከርክሞታል። ሀበሻዊ ውበቱ እንዳለ ነው። ግንባሬን ስሞ ከጎኔ ተቀመጠ። ሰለሞን የተቋጠረ ፊቱን ይዞ ፊት ለፊታችን ተቀመጠ። የዝምታውን ድባብ ለማባረር የአስቴር አወቀን ለስለስ ያለ ዜማ ከፈትኩ። መቅደስ ምግ አቅርባ ቡና ለማፍላት መጣደፍ ጀመረች። ኡምቤርቶ ወደ ፊቱ እየመጣ የሚያስቸግረውን ውብ ፀጉር በጣቶቹ ወደ ኋላ እየገፋ ገባ። አብዲ ደንግጦ ከተቀመጠበት ተነሳ። አብዲ ለኡምቤርቶ ሲደነግጥ ማየት...?! ኡምቤርቶ ለሰላምታ እጁን ዘረጋ። አብዲ እኔ ላይ አፈጠጠ። ተነስቼ ወደ ምግብ ጠረጴዛው ሄድኩ።

«ይሄ ሰውነት አንድ ቀን እንደሚገድለኝ እርግጠኛ ነኝ።» አለ ኡምቤርቶ እጁን እየጐተተ።

«ይህን ካወቅክ አርፈህ ተቀመጥ።» አለው አብዲ እጁን ከገባበት መዳፍ እያስለቀቀ።

«እንግሊዘኛ በደንብ ትናገራለህ።» አለው ኡምቤርቶ።

«አንተ ግን አማርኛ አትሞክርም!...» አልኩት።

ኡመቤረቶ ጠቀሰኝ። ቀኝ አይኔ በፍጥነት አፀፋውን መለሰ። ሰለሞን ወደ ላይ አንጋጠጠ። መጥኔውን ይስጥሽ!... ማለቱ እንደሆነ ገብቶኛል!

«በጣም ይቅርታ የኔ ፍቅር!» ብሎ ኡምቤርቶ ከንፈሬ ላይ ተጣበቀ!... ተ.ጣ.በ.ቀ...! ይሄ እብደት ነው! እንዴ... አብዲ እኮ... የምር ኡምቤርቶ አብዲን እየተዳፈረው ነው! ቀይ ስተት! «ስገባ ስላልሳምኩሽ ነው!» አለኝ ወንበር ስቦ እያስቀመጠኝ። ቀስ ብዬ ዐይኔን ወደ አብዲ ላኩት! ፊቱ ሲያስፈራ! እግዚኦ! የተቆጣ ነብር መስሏል።

«ሊፕስቲክሽን አላበላሽሁብሽም ዘና በይ!» አለ ኡምቤርቶ፡፡

በምን አወቀ? ማለቴ ሊፕስቲኬ ተበላሽቶ ይሆን እያልኩ እየተሳቀቅኩ ነበር፡፡ ሰለሞን እና አብዲ እየተለጠጡ ወንበር ስበው ተቀመጡ፡፡ በኡምቤርቶ እና በአብዲ መሀል ስለተቀመጥኩ ለቅርጫ የቀረብኩ መሰለኝ ተሰማኝ፡፡ ሰለሞን ፊት ለፊቴ ተቀምጦ በታዘብኩሽ አስተያየት እየተመለከተኝ ነው፡፡ ኡምቤርቶ እና አብዲ ደሞ ለጎሪጥ እየተያዩ ቁና ቁና ይተነፍ ነሉ፡፡

ቡናው በማንከሽከሻ ታቅፎ በእሣት እየተጠበሠ መወቀጡን እያሠበ ይጨሳል፡፡ በሁላችንም ሆድ ወስጥ ነገር ስላለ ምግቡን ነካክተን በየተራ እየተነሳን ሶፋው ላይ ተደረደርን፡፡ አሁንም በአብዲ እና በኡምቤርቶ መሀል መቀመጥ አልቀረልኝም፡፡ ኡምቤርቶ የግራ እጄን ወደ አብዲ ዘርግቶ፤ ያመጣልኝን ቀለበት አሳየው፡፡ አብዲ ጣቴ ላይ አፈጠጠ፡፡

«ትላንት አላየሽውም? ወንድሙ ነው የላከልኝ!» አልኩት፡፡

«አትዋሺ! ወንድሜ አይደለም የላከልሽ!... ኤሚ ከእንግዲህ የኔ እጮኛ ናት፡፡»

«እብድ ነህ? ወንድሜ ነው የላከልሽ አላልከኝም?»

«ስቀልድ ነው! ምን ያህል እንደምወድሽ እንድታውቂ ብዬ ነው የእናቴን ቀለበት ያጠለኩልሽ፡፡»

«አውልቀሽ ወርውሪለት!» አለኝ አብዲ፡፡

«ለምን? ዳይመንድ ነው እኮ! ሁለተኛ ደግሞ ቀለበት ስላሰረላት ሚስቱ ሆነች ማለት አይደለም፡፡ እንደማንኛውም ስጦታ ከቆጠረችው ጣቷ ላይ ቢቀመጥ ምንም ማለት አይደለም፡፡ ነገ የሚመጣውን

አታውቂምና ቀለበቱን ጣትሽ ላይ አቆይው፡፡» አለችኝ መቅደስ፡፡ መቅደስ ብልህ ናት!

«ዝም በይ ገረድ!» አላት አብዲ፡፡

«ባለጌ ነህ! ኤሚ እንዳታወልቂ!» አለ ሰለሞን፡፡

«በእንግሊዘኛ ብታደርጉት ጥሩ ነው! ምክንያቱም እኔ ልሰማችሁ አልቻልኩም፡፡ ለማንኛውም!... ከኔ እና ከአብዲ ማንን ትመርጫለሽ?» ያልጠበቅኩት አስቀያሚ ጥያቄ ከኡምቤርቶ ተወረወረብኝ፡፡

«አብዲን ካልሽ እኔ ልተውሽ፤ እኔን ካልሽ ደግሞ... ከሰላም እና ከጦርነት መምረጥ ያንቺ ፋንታ ነው፡፡» አለኝ ኡምቤርቶ ሰማያዊ ዐይኖቹን ዐይኖቼ ላይ ተክሎ፡፡

መምረጥ ያለብኝ ኡምቤርቶን ነው! ነገር ግን አብዲ እንደዛተው ቢገድለውስ? አብዲን መረጥኩ፡፡ ሁሉም ያልጠበቁት መልስ ስለነበረ ደነገጡ፡፡ አብዲ በደስታ ሰከረ፡፡ ኡምቤርቶ ውጪ ተንትኖ ንፋስ ከወሰደ በኋላ አዲስ ሀሳብ ይዞ ተመለሰ፡፡

«አብዲ አንቺን ለማግኘት የአንድ ሰው ህይወት ሊሰጠኝ ይገባል፡፡» አለ ኡምቤርቶ ወደ አብዲ ጆሮ ተጠግቶ፡፡

«እሰጥሀለሁ!» አለው አብዲ፡፡

«የማንን ህይወት ነው የምትሰጠው?» አልኩት፡፡

«ነብስ ማጥፋት ሥራው ስለሆነ ሀሳብ አይግባሽ!» አለ ሰለሞን፡፡

የሆነ ልክ ያልሆነ ነገር እንዳለ ገባኝ፡፡ የመቅደስ ቡና የሚጠጣው አጥቶ ከነስኒው ቀዝቅዞ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ብሏል፡፡ ኡምቤርቶ

ግንባሬን ስሞኝ ሄደ፡፡ አብዲም ማታ መጥቶ እንደሚወስደኝ ነግሮኝ ወጣ፡፡ ሰለሞን እና እኔ ተፋጠን ቀረን፡፡ እሱም በተራው ነገር ሲያብላስል ቆይቶ ወጥቶ ሄደ፡፡

ቁጭ ብዬ ቴሌቪዥን ስመለከት አመሸሁ፡፡ ብርሀን ተሸንፎ ጨለማ ሲነግስ ከዋክብትን ለማየት ወደ መስኮቴ ሄድኩ፡፡ ክረምት ነውና ሰማዩ በጥቁር ደመና ተሸፍኖ ከዋክብት እና ጨረቃ በቦታው አልተገኙም፡፡ ከፋኝ! ወዲያው ሰማዩ ማልቀስ ጀመረ፡፡ ሰማዩ ቁርጥሽን እወቂ ከዋክብትንም ሆነ ጨረቃን ዛሬ አታገኛቸውም፤ እኔም ከፍቶኝ ነው የማለቅሰው ያለኝ መሰለኝ፡፡ ሞባይሌ ጮኸ፡፡ አብዲ ነው! ውጪ እየጠበቀኝ መሆኑ ስለገባኝ፡፡ ቦርሳ መያዝ አልፈለግኩምና ሞባይሌን ጡቴ ውስጥ ከትቼ፣ በቀኝ እጄ የዘረጋሁትን ዣንጥላ ይዤ፣ ረጅሙ ቀሚሴ ጭቃ እንዳይነካ ደግሞ በግራ እጄ ወደ ላይ ሰብስቤ ወጣሁ፡፡

ኡምቤርቶን ከሆነ ጥቁር መኪና ሲወርድ አየሁት፡፡ ሳያየኝ እየሮጥኩ አብዲ መኪና ውስጥ ገባሁ፡፡ አብዲ እያበረረ ቤቱ ወሠደኝ፡፡ ፊቱ ላይ ጭንቀት ይነበባል፡፡ ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባን፡፡ ልብሴን አወላልቄ እርቃኔን አልጋው ላይ በጀርባዬ ተዘረርኩ፡፡ የፈረደበትን ጨቤቤ እያገላበጠ፡፡ ሀጂ አብደላ የሚባሉ አጎቱን እንደማውቃቸው ጠየቀኝ፡፡ መልሴ አላውቃቸውም ሆነ፡፡ በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ የታወቁ ጠንቋይ ሆነው እንዴት አታውቂያቸውም ብሎ አፈጠጠብኝ፡፡ እንኳን የእሱን ጠንቋይ አጎት የኔንም ደብተራ አጎት አላውቀውም፡፡

«ጠንቋዮች ሁሉን ነገር ያውቃሉ ሲሉኝ ውሸት ነው ብዬ እከራከር ነበር፡፡ በተግባር ሳይ ግን...» ብሎ አብዲ ጭንቅላቱን መነቅነቅ ጀመረ፡፡

ምንም የገባኝ ነገር ስለሌለ ዝምታን መርጫለሁ፡፡

«የሰአዳ ጓደኛ መሆንሽን ጠንቋዩ አንቴ ነገሩኝ፡፡»

በረዶ እላዬ ላይ የተገለበጠብኝ መሠለኝ፡፡ ከመቅስፈት በፊዘቢው ታፋዬን ሸረከተልኝ፡፡ ጮሁኩ!

«የሰአዳን ጡት የቆረጠውን ወንድሜን ፍለጋ እኔን አጠመድሽኝ፤ እሱ ጅዳ እንደሄደ ቀረ፡ ከዛ በቀልሽን በእኔ ልትወጪ ቢላሽን ሳልሽ፡፡ ግን ለምን ዘገየሽ?» አለኝ፡፡

«ስለምን እንደምታወራ አላውቅም! ከእጅህ ለማስገባት ነበር አፈቅርሻለሁ ያልከኝ?» አልኩት እያለቀስኩ፡፡

«በርግጥ አፈቅርሻለሁ! ግን አንቺ ከሀዲ ነሽ!»

«ሰአዳ ለኔ ከማንም በላይ ነበረች!... ወንድምህ ነጠቀኝ!... ስለዚህ ልበቀለው ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ ይሄ ከሀደት አይደለም!...» እንባዬ አልቆም አለኝ፡፡

«እሱጋ መድረሻ መንገድሽ ደግሞ እኔ!... እኔን በፍቅር አጥምደሽ ካንበረከክሽኝ በኋላ ልትገይኝ ቀን መቁጠር ጀመርሽ፡፡»

«የበቀል ዘመቻዬ አንተ ላይ አልሠራ አለኝ፡ በማላውቀው መንገድ ወኔዬን አልፈሰፈሰከው፤ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ርህራሄ የሌለው ወንድምህ ነው፡፡ በጣም የምወዳትን እና የምትወደኝን ጓደኛዬን ነው የገደለብኝ! ሠአዲ ማለት...»

አብዲ አቋረጠኝ!

«ሠአዳ መጀመሪያ ከእኔ ጋር ጓደኝነት ጀመረች፡፡ ወንድሜን ስታይ ግን ልቧ ሸፈተ፡፡ እኔን ትታ ወደ እሱ ተገለበጠች፡፡ ባልወዳትም ትታኝ ስትሄድ እራሴን እንደተናቀ ቆጠርኩት፡፡ በቀል ውስጤ አቆጠቆጠ፡፡ ቤታችንም ውስጥ ወንድሜ እንደመላዕክ ነበር የሚቆጠረው፡፡ አባቴ ለእሱ ያደላል፡፡ ውስጤ ያቆጠቆጠው ቅናት አደገ! ወንድሜ ላይ ግን መጨከን አልቻልኩም፡፡ ግን እሷ ላይ መጨከን እችላለሁ፡፡ የወንድሜን ስልክ አንስቼ ደወልኩላት፡፡ ድምፄን በወንድሜ ድምፅ ቀብቼው ስለነበረ አላወቀችኝም፡፡ ከሰፈራችን ራቅ ወዳለ ሆቴል ቀጠርኳት፡፡ ወንድሜ የቀጠራት ስለመሰላት የተባለችው ቦታ በተባለችው ሠዓት አምራና ተውባ ከች አለች፡፡ የተከናነበች ሴት አድርሳት ስትመለስ....»

«የተከናነበችው ሴት እኔ ነኝ!» አልኩት፡፡

ከታፋዬ የሚፈሰው ደም አንሶላውን በክሎታል፡፡

«ወዳለሁበት ክፍል ስትገባ የጠበቀችው ሰው የለምና መሬሖህ አምሯት ነበር፡፡ ፀጉሯን የሸፈነችበትን ሂጃብ አውልቄ አፏ ውስጥ ጠቀጠቅኩት፡፡ እጇን ወደ ኋላ በገመድ ካሰርኩ በኋላ... ሁለቱንም ጡቶቿን በያዝኩት ሳንጃ ቆርጬ ጣልኩት፡፡»

ጡቶቼ ተቆርጠው የወደቁ መሰለኝ፡፡ እብዷን ይበልጥ ፈራሁት፡፡

«አ..አንተ ነ..ህ የገደ...»

«ዝም በይና አስጨርሽኝ አላልኩሽም?» ተጠጋኝ፡፡

«ብለሽኛል!» ተንቀጠቀጥኩ!

እኔም የሰአዳ ዕጣ እንዳይደርሰኝ የተባልኩትን ማድረግ አለብኝ፡፡ ቢያንስ ሀጥያቱን ተናዞ እስኪጨርስ ድረስ...

«ሁሉም ነገር በፍጥነት ተከናወነ! ደሟን ሳይ ነበር የባነንኩት! ባደረግኩት ስራ ተፀፀትኩ! እየሮጥኩ ለእናቴ ያደረግኩትን ነገርኳት፡፡ እንድትደርስላትም ተማፀንኳት፡፡ ፖሊስ ይይዘዋል ብላ ስለፈራች አልሰማችኝም!... ሹፌራችን ተጠርቶ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመርን፡፡ ያደረግኩት ነገር ሊያሳብደኝ ደረሰ፡፡ በጣም ብዙ ቀን ከታመምኩ በኋላ ዳንኩ፡፡ አባቴ ፈርቶ ወንድሜን በጅቡቲ በኩል ወደ ጅዳ ስለላከው ወንጀሉ በወንድሜ ተላከከ እንጂ ጓደኛሽ በእኔ እጅ ነው የሞተችው፡፡ »

የሰአዳ ገዳይ አብዲ? የጓደኛዬን ገዳይ ነበር አቅፌ ስስም የኖርኩት? ከመሳም አልፎም...! ጓደኛዬን የካድኳት መስሎ ተሰማኝ፡፡ አንተ ነህ የገደልካት? አንተ? አልኩት ማመን ተስኖኝ፡፡ አብዲ ጨቤዉን ፊት ለፊቴ ወርውሮ ጀርባውን ሠጥቶኝ ተቀመጠ፡፡

«እኔንም እንደጓደኛዬ ግደለኝ! እባክህ አብዲ!...» አልኩት፡፡ አብዲ ጩቤውን አንስቶ ተጠጋኝ፡፡ የመኝታ ቤቱ በር ተበርግዶ ፊቱን የሸፈነ ሰው ሽጉጥ ይዞ ገባ፡፡ አብዲ ከመሸሽ ይልቅ ባለሽጉጡን ተጠጋው፡፡ የሽጉጥ ድምፅ ቤቱን አደባለቀው.....

እራሴን የሆስፒታል አልጋ ላይ ነው ያገኘሁት፡፡ እጄ ላይ ግልኮስ ተሠክቷል፡፡ ታፋዬ በፋሻ ተጠቅልሏል፡፡ ዙሪያዬን ቃኘሁ፡፡ ኡምቤርቶ ቁጭ ብሎ መፅሐፍ ያነባል፡፡ «አብዲ የታል?» አልኩት፡፡ «በምን ላውቅ እችላለሁ?» አለኝ፡፡ ግልኮሱን ነቅዬ ከአልጋው ወረድኩ፡፡ የእግሬን ህመም አልቻልኩትም፡፡ ኡምቤርቶ ተሸክሞኝ ከህኪም ቤቱ ወጣን፡፡

እቤቴ ገብቼ የተፈጠረውን ነገር ለማስታወስ ሞከርኩ፡፡ አብዲ ወደቀ ከዛስ? ተገትረው የሚያዩኝን ሶስት ወንዶች ጠየኳቸው፡፡ ኡምቤርቶ እና ማርኮ መልስ ሳይሰጡኝ ወደ ሳሎን ሄዱ፡፡ ሰለሞን እኔን ለማዳን ብሎ እንደገደለው ነገረኝ፡፡ ጆሮዬን ተጠራጠርኩት፡፡ አለቀስኩ!... ለምን አላለቅስም? ምናልባትም ማልቀስ የለብኝም ይሆናል!!

ኃይማኖት ሰተት ብሎ መኝታ ክፍሌ ድረስ ሲመጣ ሰለሞን አንገቱን ደፍቶ ወጣ፡፡ የአብዲ ዘበኛ፣ የሆነ ሰው አፍኗቸው፣ ወደ እኛ እንደገባ እና የቶክስ ድምፅ እንደሰሙ ለጣቢያ አመልክተዋል፤ አብዲም ተሰውሯል፡፡ በቦታው ስለነበርኩ የማውቀው ነገር ካለ እንድነግረው ፈልጎ እንደመጣ ኃይማኖት አስረዳኝ፡፡

«ካለፍቃዴ ቤቴ ገብተህ እየወነጀልከኝ ነው?» አልኩት፡፡

የፍርድ ቤት ማዘዣ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ከወረወረልኝ በኋላ ሶስት የፖሊስ አባላትን ወደ ቤቴ አስገባ፡፡ ዝምታን መረጥኩ! እንፈትሻለን ብለው ቤቱን ትርምስምሱን አወጡት፡፡ ምንም ነገር ስላላገኙ ተናደው ወጥተው ሄዱ፡፡

«ሁሉም ነገር ያልፋል! ፍቅር ግን ለዘላለም ይኖራል!» አለኝ ኡምቤርቶ፡፡

ብቻዬን እንዲተወኝ ተማፀንኩት፡፡ ከፊቴ ዞር አለ፡፡ የተፈጠርኩበትን ቀን ረገምኩ፡፡ ሰው ይህን ሁሉ መከራ ይዞ እንዴት ይወለዳል? አልጋዬ ላይ ተጋድሜ አምላኬን ሳማርር ዋልኩ፡፡ ምግብ ስላልቀመስኩ ከንፈሬ

ኩበት ሆኗል፡፡ ሰለሞን ዐይኑን በጨው አጥቦ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ፡፡

«ሰዎች ተዐይፊው በራቁኝ ግዜ ከእቅፍሽ ከተሽ የእናት ፍቅር ሰጠሽኝ፡፡ ለአንካሳው ልቤ ምርኩዝ ሆነሽ ተስፋን አስተማርሽው፡፡ በጨለማ ተከብቤ ውስጤን ሀዘን ሲደቁሰው ብርሀን ሆነሽ ሀሴትን ለገስሽኝ፡፡ ግን ይሄ ሁሉ አመመኝ! መልካምነትሽ በሽታን ገዛልኝ፡፡ የቅናት ሐረግ ልቤን ተብትቦ አቆሰለው፡፡ ማስታወሻ ደብተርሽን ሳነብ ደግሞ...»

አይኖቼ ተጎልጉለው ወጡ!... እንዴት ያለፍቃዴ ያነብብኛል?...

«ከዛም በተፈጠረልኝ አጋጣሚ ተጠቅሜ አብዲን ገደልኩት! ለአንቺ ወንድ አብዲ ብቻ ነው! ለምን በሌሎች ቁስል እንጨት ትሰጂያለሽ? ንገሪኝ! ለምን?» አለኝ ሰለሞን እየጮኸ፡፡

ወጥተሽ ብረሪ ብረሪ የሚለኝ ነገር መጣ!

«አብዲን የገደልኩት ስለማፈቅርሽ ነው!»

በዚህ ንግግሩ ባልስቅ ኖሮ ይቆጨኝ ነበር!

«አንድ ግብረ ሰዶማዊ በሴት ፍቅር ታውሮ ወንድን ገደለ፡፡ ትንሽ ለጆሮ አይከብድም?»

«ግብረ ሰዶማዊነቴን የነጠቅሽኝ አንቺ ነሽ!»

«ታድያ ምን ችግር አለው ማርከ መጥቶልህ የለ!...»

«ላንቺ ስል ሰዶምን ተውኩ፡፡ አሁንም ላንቺ ስል ወደ ሰዶም እሳት እገባለሁ፡፡»

«መጀመርያም አልወጣህም! አንተ የሰዶም አሻንጉሊት ነህ! አሁን አብዲን ገድለህ የት ነው የቀበርከው? ንገረኝ! አለበለዚያ ለፖሊስ ነው የማሲዝህ፡፡»

«ለኡምቤርቶ ሲመኘው የነበረው ወንዝ ወስጥ!... ደህና ሁኚ!»

ለረጅም ሰዓት በትራስ ተደብቄ ከቆየሁ በኋላ እግሬን እየጎተትኩ ወደ ሳሎን ሄድኩ፡፡ በመቅደስ ልምና ትንሽ እንጀራ ጎረስኩ፡፡ የከረመ አረቄ ስለነበር የጠርሙሱን አንገት አንቄ አፌ ላይ ደቀንኩት፡፡ የገባው አረቄ በደምስሬ ተሰራጨና ሶፋው ላይ እንደተጋደምኩ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ፡፡ አረቄ ጠጥቼ እንደተጋደምኩ ነጋልኝ፡፡ ከሶፋ ላይ አንስቶ አልጋ ላይ ያስተኛኝ ማን እንደሆነ አላውቅም፡፡

እኔን እስር ቤት ለመወርወር ትልቅ ምኞት የነበረው መርማሪ በጥዋት ነበር ጨምድዶ የሚወስድ ፖሊስ የላከልኝ፡፡ መቆያ የሚሆን ምግብ ከወሰድኩ በኋላ በሁለት ፖሊስ ታጅቤ እያነከስኩ ውጪ ወደ ሚጠብቀኝ የፖሊስ መኪና ሄድኩ፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ስደርስ ቀጥታ ወደ ሴቶች እስር ቤት ነው የተጣልኩት፡፡ የውጪው ወሬ የጠማቸው ሴቶች አጠገቤ ተኮልኩለው በጥያቄ አጣደፉኝ፡፡ ሲያስጠሉ!... ፀጥታ እንደተጠማሁ ቢያውቁ ኖሮ አፋቸውን በዘጉልኝ ነበር፡፡

«አዲስ የመጣው መርማሪ እርህራሄ የለውም፡፡ አንዱ እንደ ሌሎቹ መስሎት ገንዘብ ልስጥህና ፋይሉን ቀደህ ጣልልኝ አለው፡፡ አጅሬ ቀጥታ ወስዶ እስር ቤት ነው የጣለው አሉ፡፡ ያስፈርድብሻል!» አለችኝ አንድ ወንዲላ እስረኛ፡፡

ሊላኛዋ ቀጠለች፡፡ «እኔንማ ቃሊቲ ነው የሚያስገባኝ!»

«አንቺስ ይገባሻል! የአምስት ዓመት ህፃን ልጅ ደፍረሽ ደግሞ ምህረት ትፈልጊያለሽ?» አለቻት ወንዲላዋ፡፡

«የትአባሽ አየሽኝ?» ደፋሪ ተብዬዋ አፈጠጠች፡፡

«የአራት ዓመት ህፃን ልጅ ቀሚስ ገልበሽ ጭኖቿ መሀል ተቀብረሽ ተገኘሽ፡፡ ከዛ እዚህ አመጡሽ፡፡ ልትክጂ ነው?»

«አንቺስ ብትሆኚ ፍቅረኛዬን ነጠቅሽኝ ብለሽ አንዱን ቤሌቤሌ ዘክዝከሽ አይደል የታሰርሽው?»

ሁሉም የሁለቱን ጭቅጭቅ አዳማጭ ሆኗል፡፡

«እንዳቺ በየተቀጠርኩበት ቤት ያሉትን ህፃናት አልደፈርኩም፡፡ ስለ ፍቅር ብዬ መጣላቴን አልክድም፡፡ እንደማይፈረደብኝ ደግሞ እርግጠኛ ነኝ፡፡» አለች ወንዲላዋ ኩራ ብላ፡፡

«ሀላፊው ዘመድሽ ቢሆንም ፋይልሽ ያለው ኃይማኖት ጋ መሆኑን አትዘንጊ፤ እሱን ደግሞ ታውቂዋለሽ፡፡ ዝንፍ የለም!» ደፋሪዋ ተውረገረገች፡፡

«ሀርድ ሲቦጨቅበት ልክ ይገባል! ያኔ እኔ በነፃ ወደቤቴ፣ አንቺ ደግሞ ወደ ፍርድ ቤት፡፡»

ወይ ወይዘሪት ኢትዮጲያ!

አንዷ አድማጭ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብላ «ሊዝቢያኖች ናቸው! አሁን ቢጣሉም ማታ ሲተሻሹ ነው የሚያድሩት፡፡ የጥላቸው ምክንያት አንቺ ነሽ፡፡» አለችኝ፡፡

ጉድ ፈላ! እንዴ እንዴን ቀድማ ልትጠብሰኝ መሆኑ ነው፡፡ ሴቱም ብሶበታል ለካ! ኩሩሩው ፖሊስ ካለሁበት አስገራሚ ትዕይንት ነጥሎ ኃይማኖት ቢሮ ነለተኝ፡፡

ኃይማኖት ጭቅጭቁን ጀመረ፡፡ ዝም የማለት መብት አለኝ! መልስ ከመስጠት ተቆጠብኩ፡፡ የጥያቄ መዓት ሲያዥጎደጉድብኝ ቢውልም ዝምታ! መልሶ እስር ቤት ወሸቀኝ፡፡ ሌዝቢያኖቹ በፈገግታ ተቀበሉኝ፡፡ ይህን እንኳ አልሞክረውም! ፊት ነሳኋቸው፡፡ ከሰዓት በኋላ ድጋሚ ወደ መርማሪው ቢሮ ተጠራሁ፡፡

«እንኳን ደስ ያለሽ! የአብዲ ገዳይ እጁን ሰጠ፡፡ ሰለሞን በቅናት ተነሳስቶ ገድሎ ወንዝ ውስጥ እንደጣለው አምኗል! ወደ ቤትሽ መሄድ ትችያለሽ!» አለኝ፡፡

«ሰለሞንን ላናግረው እችላለሁ?» አልኩት፡፡

«ማንንም ማናገር አይፈልግም! በተለይ... አንቺን!»

በተለይ እኔን? ገንዘብ ስላልያዝኩ የታክሲ ፍራንክ በፈጣጣ ጠየኩት፡፡ ብድር ነው! ብሎ መቶ ብር ሰጠኝ፡፡ የያዝኩት ታክሲ ቀርፋፋ ነውና ቤቴ ለመድረስ አመት ፈጀብኝ፡፡ ለነገሩ አንድ ደቂቃ ለኔ አመት የሆነብኝ ግዜ ላይ ነው ያለሁት፡፡ እቤት ስገባ ኡምቤርቶ ሶፋ ላይ ተጋድሞ እየጠበቀኝ ነበር፡፡ ተናደድኩ! መኝታ ክፍሌን ቆልፌ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ፡፡ ፍላጎቴ ብቸኝነት ነው! መፍለቂያውን የማላውቀው የእንባ ጎርፍ ጉንጬን እያጠበ ወረደ፡፡ ውስጤ ታሟል!... ውስጤ... ታሟል! ማን አለኝና ህመሜን ለማን ልተንፍሰው? ብዕሬን ጨበጥኩ፡፡

ማስታወሻዬ ሆይ....

የሰሞነኛ ገጠመኙ ስቃይ የበዛበት ነው፡፡ ለበቀል ያደፈጠው ልቤ በጠላቱ ተጠልፎ ሽንፈትን እያጣጣመ ነው፡፡ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሰው ጠላቱን ያፈቅራል? ፍቅር ማለት ይሄ ነው? ጨካኞችን የዋህ ደፋሮችን ፈሪ፣ ጠንካሮችን ደካማ፣ የሚያደርገው ፍቅር ነው? በፍፁም! እኔን ያሸነፈኝ ፍቅር ሳይሆን የሆነ ሀይል ነው፡፡ የአብዲን ሞት ውስጤ አልተቀበለውም፡፡ ምናልባትም ስላልቀበርኩት ይሆናል፡፡ አብዲ ማለት የጓደኛዬ የሰአዳ ገዳይ ነው፡፡ ታድያ ለምን አስበዋለው? ለምን አልረሳውም? አልችልም! ምስጋና ለሽንፈቴ ምክንያት ለሆነው ሀይል!

አብዲ በሞተ በአምስተኛው ቀን ማታ የሳሎኑ በር በሀይል ተደበደበ፡፡ ኡምቤርቶ ፈጠን ብሎ ከፈተ፡፡ ሰለሞን ነው፡፡ ከተቀመጥኩበት መነሳት አቃተኝ፡፡ እንዴት አመለጥክ? ነበር ከአፌ የወጣው ቃል፡፡ አብዲ እንዳስፈታው ተናገረ፡፡ መቼም ወንዝ የወሰደው አብዲ አይሆንም፡፡ ትንሳኤ ለክርስቶስ እንጂ ለአብዲ ማን ፈቀደ?

«ገድዬ ወንዝ ውስጥ የጣልኩት ሰው በህይወት አለሁ ብሎ ከእስር ሲያስፈታኝ የቅዠት አለም ውስጥ ነኝ ብዬ እራሴን አሳመንኩት፡፡» አለ ሰለሞን፡፡

ጭንቅላቴ መረጮህ ጀመረ!

«ሰለሞን እርግጠኛ ነህ ገለኸዋል?» አልኩት፡፡

«ካላመንሽኝ እሱን ጠይቂው!» አለኝ በአንገቱ ኡምቤርቶን እየጠቆመኝ፡፡

ጉድና ጅራት...

«ሽጉጥ የሰጠኝ እሱ ነው! ከገደልኩትም በኋላ ለሁለት ነው ወንዝ ውስጥ የጣልነው፡፡» ሰለሞን በአማርኛ ስለሆነ የሚያወራው ኡምቤርቶ እየተወነጀለ እንደሆነ አላወቀም፡፡

«አብዲን ለመግደል ስንት ቀን ተመካከራችሁ? ለምን?» አልኩ ኡምቤርቶ ላይ አፍጥጬ፡፡

ኡምቤርቶ ጥፋቱን ለመሸፋፈን ሳይሞክር የሰለሞን ጉንጭ ላይ አሪፍ ቡጢ ካሳረፈ በኋላ «መልሱ አንቺጋ ነው!» አለኝ፡፡

ማነው የሚታመነው? አብዲስ ከሞተ እንዴት በህይወት ተገኘ? እንቆቅልሽ! ቀኑም ገሰገሰ፤ ሞተ ተብሎ በህይወት አለ የተባለውም ሰው አልታየ፤ እኛም እንዲህና እንዲያ እያልን አለን፡፡ ሰለሞን እና ማርኮ ምድሩ አልበቃ ብሏቸዋል፡፡ የትኛው ባል የትኛው ሚስት ሆኖ እንደሚጋቡ ባላውቅም የሰለሞንን ክፍል ጎጇቸው አድረገዋታል፡፡ ኡምቤርቶ ለእኔ ያለው ፍቅር እና እንክብካቤ አልቀነሰም፡፡

በአንድ አስቀያሚ ምሽት ኡምቤርቶ ውጬ እራት ጋብዞን ወደ ቤት ከተመለስን በኋላ ክብ ሰርተን ተቀምጠን ቢራ መጠጣት ጀመርን፡፡ ቀስ በቀስ አራታችንም ሞቅ አለንና ሳቅ ጨዋታው ደራ፡፡

«እስከዛሬ የደበቅኩሽን ነገር ልነግርሽ ነው!» አለኝ ኡምቤርቶ፡፡ ማርኮ በጣሊያንኛ ተናግሮ አቀረቀረ፡፡ ኡምቤርቶ ተንቆራጠጠ፡፡ ሰለሞን ቁና ቁና መተንፈስ ጀመረ፡፡ ኡምቤርቶ ቀጠለ..

«ጥሩ ሴት ነሽ! ቆንጆም ነሽ! ወደ ኢትዮጲያ የመጣሁት አንቺን አንቂ ለመግደል ነበር፡፡ አንቺን ገደልኩ ማለት ደግሞ ወንድሜን በቁሙ ቀበርኩት ማለት ነው፡፡ ለወንድሜ ብዬ ብቻ ሳይሆን ጭካኔዬን የሚያሸንፍ ሀይል ስላለሽ ነው ያልገደልኩሽ፡፡ ጥፋቴ ይቅርታ የሚያስጥ እንዳልሆነ ስለማውቅ ይቅርታ አድርጊሊኝ አልልሽም ግን ተገድጄ እንደዋሸሁሽ እንድታውቂ እፈልጋለሁ፡፡»

እንግሊዘኛው ነው? የሆነ ያልገባኝ ነገር አለ!

«ማር! ከሁለት አንዳችን ሰክረናል! ለማንኛውም የማይጥም ትረካህን እንድትቀጥል ፈቅጄልሀለሁ፡፡» አልኩት፡፡

«ለኡምቤርቶ ስትዪ! አብዲን መቅረብ መቻል አለብሽ!» አለኝ ማርኮ፡፡

ሰለሞን ቀጠል አደረገና «እውነቱን ነው!» አለ፡፡

«ማርኮን ያልገደልኩት አንቺን ለማግኘት ስል ነው፡፡ በቁሙ በእሣት ባቀጥለው ደስ ባለኝ ነበር!...»

«ለምን?»

«ወንድሜን አብዲ ለሚባል አውሬ ስለጣለው፡፡»

«ግልፅ ካላደረጋችሁልኝ አፋችሁን ዝጉ፡፡» አልኳቸው፡፡

«ቀጥታ ወደ እውነቱ ግባ!» አለው ሰለሞን፡፡

«እኔ የማላውቀው ሦስታችሁ የምታውቁት እውነት አለ?»

«አዎ! ወንድሜን ለማግኘት አንቺን መቅረብ ስላለብኝ ነው ካንቺ ጋር የተኛሁት፡፡ አብሬሽ ባልተኛ ኖሮ ደግሞ ትርቂኝ ነበር፡፡ ግን የእውነት ነበር ያቀፍኩሽ፡፡ እስከዛሬ አብረን ያደረግናቸው ነገሮች በሙሉ የእውነት ነበሩ፡፡ ደስም ይላሉ!»

ኡምቤርቶ ስለምን እየቀባጠረ እንደሆነ የሚያውቀው አይመስለኝም፡፡

«ወንድምህ ምን አገባው?» አፈጠጥኩበት!

ስስቱም ተያዩ፡፡

«እኔ ኡምቤርቶ አይደለሁም!»

ሰከረናል?... ወይስ...

«መንትያ ወንድሙ አልቤርቶ ነኝ!»

ምራቄ ደረቀ!... ለመዋጥ እታገላለሁ!... ከደረቀ ደሞ....

«እኔ በህይወት አለሁ ማለት ወንድሜ አልሞተም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ...»

የያዝኩትን የቢራ ጠርሙስ ወረወርኩበት፡፡ ቀልቦ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው፡፡

«ወንድሜን በአስቸኳይ ካላገኘነው ነገሮች አስቸጋሪ ይሆናሉ፡፡»

«ሶስታችሁም ከቤቴ ውጥሉኝ!»

«ወንድሜ እስኪገኝ ድረስ አብረን ነው የምንኖረው፡፡»

ቤቱን ለቅቄላቸው ልወጣ ስል አልቤርቶ እጄን ጠምዝዞ ሶፋው ላይ ወረወረኝ፡፡ ማርኮ እና ሰለሞን ደንግጠው ከተቀመጡበት ተነሱ፡፡ እንዲቀመጡ አዘዛቸው፡፡ ኩርምት ብለው ተቀመጡ፡፡

«ወንድሜ ላንቺ ሲል ነው ሞት አፋፍ ላይ ያለው! ለአብዲ አሳልፋ የሰጠችው ደግሞ ትእግስት መሆኗን ደርሼበታለሁ! ልታድኚው የምትችይው አንቺ ብቻ ነሽ! አብዲን እጅሽ ውስጥ በማስገባት!...»

ትእግስት እንደዛተችው ተበቀለችኝ! አሸነፈችኝ! እሷ ሳትሆን እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ፡፡ ምክንያቱም በጊዜ ሒሳቧን አልሰጠኋትም፡፡

«ካለ እኔ ፍቃድ የትም መሄድ አትቺይም! ሁለታችሁ ደግሞ አደን ትጠብቃላችሁ! ብትጠፉ ትሞታላችሁ!» የሚል ትዕዛዝ አልቤርቶ አስተላለፈ፡፡

«አንተ ማነህ በእኔ ላይ የምታዝው? ያለኸው እኮ አገሬ ውስጥ ነው!....»

«አውቃለሁ! ግን በአገርሽ ውስጥ ማነው ተከብሮ የሚኖረው? እኔ ወይስ አንቺ? እኔ ነኝ!...»

«እውነቱን ነው! የሆነ አገልግሎት ፈልገሽ የትኛውም ቦታ ብትሄጂ ቅድሚያ ለእነሱ ነው! ጉዳት አድርሶብሽ አቤት ብትዪ አንቺን የሚሰማሽ የለም! ስለዚህ አድርጊ የሚልሽን ሳታንገራግሪ ማድረግ አለብሽ!» አለኝ ሰለሞን፡፡

«እና ኤሚ!... ስተት ለመፈፀም አትሞክሪ!... ካለፍቃዴም ከዚህ ቤት ለመውጣት እግርሽን እንዳታነሺ!... እኔ ኡምቤርቶ አይደለሁም! አልራራልሽም! ተግባባን?»

# ክፍል ስምንት

## አምሮት

ወቅቱ የክረምት ነውና ደመና እና ዝናብ በከተማዋ እየፈነጨ ለፀሀይ እድል አልሰጧትም፡፡ የሰጠኸኝን የታክሲ ፍራንክ በእራት ልመልስልህ ብዬ ኃይማኖትን እቤቴ ቀጠርኩት፡፡ ሰለሞን እና ማርኮ ጠባቂዎቼ ስለሆኑ ከጎኔ አይለዩም፡፡ ከኃይማኖት ጋር ዘና ብዬ እንዳወራ በረንዳ ላይ እንዲቀመጡ ለመንኳቸው፡፡ አልጨከኑብኝም፡፡ አልቤርቶ ከሄደበት ሳይመለስ ኃይማኖትን ማግኘት አለብኝ፡፡ ኃይማኖት ዘግየት ብሎ ነው እራቱ ላይ የተገኘው፡፡ የእራቱ ፕሮግራሙ ካበቃ በኋላ፣ ኃይማኖት ቢራውን ሲጎነጭ፣ እኔ በቀኝ እጄ በወይን የተሞላ ብርጭቆዬን፣ በግራ ጣቶቼ ደግሞ ሲጋራዬን ሰክቼ፣ ትረካዬን ጀመርኩ....

ውሻ ቀሚስ ለብሳ ካየ የማያልፈው ሴሰኛው አባቴ ገና የስድስት ወር ህፃን እያለሁ ነበር ከእናቴ ጉያ የነጠለኝ፡፡ በክፉ እንጀራ እናት እየተጠበስኩ አስራ ሶስት ዓመት ሞላኝ፡፡ ጡቴ ሲያጎጠጉጥ መከራን ተሸክሞልኝ መጣ፡፡ እንጀራ እናቴ ወደ ሥራ ስትሄድ አባቴ ከትምህርት ቤት እያስቀረ አብሬው እንድተኛ ያስገድደኝ ነበር፡፡ እንቢ ስለው በኤሌትሪክ ገመድ ይገርፈኛል፡፡ ያንቋሽሸኛል!... የማልረባ መሆኔን እየደጋገመ ይነግረኛል፡፡ በአንድ የተረገመ ቀን አባቴ ክብረ ንፅህናዬን ተረከበኝ፡፡ አልተፀፀተም! የመጀመርያው ጠላቴ አባቴ ሆነ፡፡ አረመኔነቱ ጎልቶ ታየኝ!... አይኑን ለማየት ተፀየፍኩ!... ጠላሁት!!

እናቴ ልብስ እና ጫማ በወንድሟ በኩል ትልክልኝ ስለነበር የእንቴን ስልክ ቁጥር ይገባለሁ። ስደውልለት ድሬዳዋን ለቆ አዲስ አበባ መግባቱን አረዳኝ። የት ልሂድ? ዙሪዬ በሾክ ታጥሮ ጨለማ ከበበኝ። የአባቴን ቤት ትቼ በደላላ አማካኝነት ሰው ቤት ተቀጠርኩ።

አሰሪዎቹ ባልና ሚስት ስለሆኑ፤ የቤቱ ሥራ ብዙም አልከበደኝም። ቀን ሲገፋ ሚስትየው ወደ ስራ ስትሄድ የፖሊስ ጣቢያ አዛዥ የሆነው አባወራ ከስራው እየቀረ የእኔን ቀሚስ መነተት ጀመረ። ምን ጠልቼ ከቤቴ ወጣሁ? በፀባይ ካልወደደልሽ አለና በጉልበት ጭኖቼ መሀል ገባ። መሮኛልና ወደ ሚሰራበት ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ አቤት አልኩ። አልታመንኩም! የተከበረውን ሰው ስም ለማጥፋት የተነሳሳሁ ወንጀለኛ ተደርጌ ተቆጠርኩ። ለምን? ፖሊስ ስለሆነ! ሚስቱ የለመደበት ወስላታ መሆኑን ስለምታውቅ ብር ሰጥታ አሰናበተችኝ። ሁለተኛው ጠላቴ ፖሊስ ሆነ!

የመጨረሻ እድሌ የትመህርት ቤት ጓደኛዬ ሰአዳ ነበረች። የሆንኩትን ሁሉ አጫወትኳት። ከመጠን በላይ አዘነችልኝ! እናቷን አልቅሳ ለምና ቤታቸው እንደ ሙስሊም ሴት ፊቴን ተከናንቤ እንድኖር ተፈቀደልኝ። ቀን ከቤት ሠራተኛቸው ጋር ጉድ ጉድ ስል እውልና ማታ ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ። አመታት ተቆጠሩ። ሰውነቴም ጭንቅላቴም እየዳበረ ሄደ። መከናነቢያዬን የማወልቀው ክፍሌ ስገባ ብቻ ቢሆንም የሰአዳ ወንድም ሳላስበው ወደ ክፍሌ እየገባ በውበቴ መማረክ ጀመረ። ነገር መጣ! ሳልፈልግ አብሬው መተኛት የዘወትር ሥራዬ ሆነ። አስረኛ ክፍልን ለመፈተን ስል ነበር ዝምታዬ... ግን ውጤት አልባ ሆንኩ።

የሰአዳ እናት እንደልጇ ነበር የምታየኝ፡፡ አባቷም ቢሆን በክፉ ዐይን አይቶኝ አያውቅም፡፡ ባጠቃላይ ምንም የጎደለብኝ ነገር አልነበረም፡፡ ሰአዳ ለትምህርቷ ግድ ስላልነበራት ውጤቷ እንደኔ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ከአብዲ ወንድም ፍቅር ይዟት ስለነበረ እሱን አግብታ መኖር ብቻ ነበር የምታልመው፡፡ ግን በአንድ ቀፋፊ ቀን በአብዲ ክፉ እጅ ሁለቱንም ጡቷን አጥታ ሞተች፡፡ ለእኔ የመጀመርያዋ ጥሩ ሴት ነበረች፡፡ ኡምቢርቶም ለኔ የመጀመርያውና የመጨረሻው መልካም ወንድ ነበር፡፡ ሁለቱንም በአንድ ራስወዳድ ወንድ አጣኋቸው፡፡

«ግን ራስወዳዱን አፈቀርሽው!» አለኝ ኃይማኖት ፊታሽ ዐይኑን ተክሎብኝ፡፡

«አላፈቀርኩትም!...»

ኃይማኖት ድርድር ጥርሱን ገለጥ አደረገው፡፡

«አሸነፈኝ!... ማለት ልቤ ተሸነፈለት!»

«ይሄ ፍቅር ካልሆነ ምንድነው?...»

«የሆነ... ሀይል!»

ወደ ትረካዬ ተመለስኩ...

መከራ ጠንካራ አደረገኝ! ሰዎች የነፈጉኝን በእጄ መንጠቅ እንድምችል ለእራሴ ነገርኩት፡፡ ህይወት እየመራችኝ ሳይሆን እኔ እንደምፈልገው መኖር አለብኝ፡፡ ወንዶች ከሴቶች የሚፈልጉትን በጉልበታቸው ይወስዳሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ከወንዶች የሚሹትን በብልሀታቸው ተጠቅመው ማግኘት ይችላሉ! እውነት ነው! ይቻላልም! ወንዶች በጉልበታቸው፣ እኔ በብልሀቴ፣ ጨዋታው ተጀመረ፡፡

የፍትሕን ጠር አንገቢ እና ቀሚሴን ገልቤ በቡቅል ፈረስ እየጋለብኩ ወንዶችን ለመቅበር ወደ አዲስ አበባ መጣሁ:: የበቀል እርካታ እንዴት ደስ ይላል መሰለህ?...! አው! ዋናው አመጣጤ ግን የአብዲን ወንድም ለመበቀል ነበር:: አብዲ እጅ ውስጥ ወደቅኩ እንጂ.

ፍትሕ የለም ብዬ በእራሴ መንገድ በጣም ብዙ ከተጓዝኩ በኋላ አንተን አገኘሁህ:: የተቀመጥክበትን ወንበር ሳታቆሽሽ በንፅህና ህዝቡን ለማገልገል ቆርጠህ የተነሳህ መሆንህን ለማወቅ ብዙ ደከምኩ:: ለፍትሕ የቆምክ መኮንን እንጂ ሌባ አለመሆንህን ደረስኩበት:: ታዲያ በእሾክ መሀል የበቀልክ ወይን መሆንህን አትዘንጋ! ሀረግህን በእሾኩ መሀል እያሾለክ እንደምታልፍ እተማመንብሀለው:: ግንድህ ሲጠነክር ደግሞ የእሾኩን ውሀ ምጥጥ አድርገህ አድርቀው:: ሲደርቅ እራሱ ስለሚረግፍ አትጨናነቅ::

ፍትሕን በራሴ እያለች ወንዶችን ስትለቅም የነበረቸው ወንጀለኛ ፊት ተቀምጠህ ትረካዋን እየሰማህ እንደሆን ገብቶህል ብዬ አስባለሁ:: ኃይማኖት አቋረጠኝ::

«ጠርጥሬ ነበር!.. ለፍትሕ የቆሙ ሰዎች እንዳሉ ግን እንካድ::»

«የሉም መች ወጣኝ? አለ!... ታግለው ለመውጣት ግን አልቻሉም!... ምክንያቱም ሊቦቹ ከላይ ስለተቀመጡ!...»

አልቤርቶ በሩን ከፊቱ እያለ በሩን በእርግጫ እና በቡጢ እየነረተው ነው:: ትረካዬን ሳልጨርስ ግን ካልሰበረው በስተቀር መግባት አይችልም:: ኃይማኖት ከተቀመጠበት ተነስቶ ተንቆራጠጠ::

«እጅሽን ለመንግስት መስጠት አለብሽ!»

«ለመንግስት ሳይሆን፣ ላንተ ነው መስጠት ያለብኝ!»

«ሰዎች እንዳንቺ እንዳይሳሳቱ እንቅፋት ላለመሆን እጥራለሁ!» አለ ኃይማኖት የያዝኩትን ባዶ ብርጭቆ እየተቀበለኝ፡፡

«ግን እንዴት እያደረግሽ ነበር የምትገያቸው?» አለኝ በከፋ አይን እያየኝ፡፡

«የተለያዩ የሚሰኩ የሴት ፀጉሮች አሉኝ፡፡ አይኔን በጣም አድምቄ በጥቁር ኩል እኩለዋለሁ፡፡ ከንፈሬን በቀይ ሊፕስቲክ አድምቄ፣ የወንድን ልብ የሚያንበረክክ ገላዬን በሽቶ አጥቤ እቀርባቸዋለሁ፡፡ ከዛ መርዙን በምቀዳላቸው ወይን ውስጥ ሳያዩኝ እየጨመርኩ እግታቸዋለሁ፡፡ የሴትን እራቁት ገላ ያየ ወንድ ልብ ስለሌለው መርዙን እያየ እንኳ ብጨምረው አያስተውልም፡፡ አሻራዬን ላለመተው እጄ ላይ በማጠልቀው ጥቁር ጓንት ነበር የምጠቀመው፡፡ ስልክ ቁጥሬን ከሞባይላቸው ውስጥ አጠፋለሁ፡፡ የተጠቀምንባቸውን ብርጭቆዎች እና የወይን ጠርሙስ መንገድ ላይ እወረውረዋለሁ፡፡ በቃ! ጥንቁቅ መሆኔ ከወንጀሉ ነፃ አድርጎኝ ነበር፡፡»

«የራይት ምልክቱ መልእክት አለው?» ኃይማኖት ተንቆራጠጠ፡፡

«በሚገባ! የቤት ሥራውን የሰራ ተማሪ አስተማሪው የራይት ምልክት ደፍተሩ ላይ ሲያደርግለት ደስ ይለዋል፡፡ አስተማሪውም ጎበዝ ተማሪ ስላፈራ በስራው ይኮራል፡፡ እኔም ልክ ነኝና ራይት ያሥፈልገኛል! እራሴ ባደረግኩት ራይት እደሰታለሁ፡፡ ሟቹም መሞቱ ልክ ነው እያለ ደረቱ ላይ ባለው የራይት ምልክት ይናገራል፡፡ የወይኑ

መክፈቻ ወይኑን ከመክፈት በተጨማሪ ራይት በማድረግ ያገለግለኝ ነበር፡፡»

«ከዛ... ከደረታቸው በሚወርደው ደም.... ፍትሕን በራሴ!... እያልሽ ትፅፊያለሽ፡፡»

አዲስ ሲጋራ ለኩሼ ከሳብኩ በኋላ ጭሱን ወደ ላይ ለቀቅኩት፡፡ ኃይማኖት እያየኝ ሳይሆን እየተመለከተኝ ነው፡፡

«ደስ የሚለው ደግሞ በሚቾቹ ሌባ ጣት መፃፉ ነው! ዘውዱ እና አብዮት በኔ ላይ ያደረሱት ጉዳት አልነበረም፡፡ ግን የበደሏቸውን ሰዎች ቁስል አውቀዋለሁ፡፡ በሌሎች ራስወዳድ ወንዶች የቆሰለ ልብ እኔም አለኝ! ዮሴፍ ደግሞ የምወዳትን ጓደኛዬን ነጠቀኝ፡፡ ደስ እያለኝ ሶስቱንም ገደልኳቸው!»

«...ሶስቱን ሰዎች በመግደልሽ አልተፀፀትሽም?»

«በፍፁም! አብዲን ባለመግደሌ ግን በጣም ተፀፅቻለሁ!»

«አባትሽንስ ለምን አልተበቀልሽውም?»

«.... ድርጊቱን ሳስበው ውስጤ እንዴት እንደሚቃጠል እኔ ነኝ የማውቀው! ግን ሞት ቀድሞ ጨለፈውና እጄ እሱን በመግደል ከመቆሸሽ ዳነ! ስለእሱ ሰውዬ ባታነሳብኝ ደስ ይለኛል! ስሙ ሲነሳ እታመማለሁ!!»

ፊቴ መቀያየር ሲጀምር ኃይማኖት ርዕስ ቀየረ፡፡

«አብዲ ምኑ ያስደስትሻል?»

«ወሲብ ላይ ያለው ክህሎት!»

«ኡምቤርቶስ?»

«ያከብረኛል፡ በጣም ይወደኛል፡ ያለውን ሁሉ ሲሰጠኝ ከኔ ምንም አይጠብቅም፡፡ ባለውለታዬ ነው!»

«አብዲ በወሲብ ለክፎሻል! ኡምቤርቶ ደግሞ የሴትን ልብ በሚገዛ ነገር አስሮሻል፡፡»

ብርጭቆዬን በወይን ሞልቶ ሰጠኝ፡፡ ተቀብዬ ተጎነጨሁ!

«ግን አብዲን ከጭንቅላቴ ማውጣት አልቻልኩም!»

«አብዲ የሴሰኝነትሽ ፊውስ ነው! ለበቀል የምትፈልጊው እና እንደሰይጣን የምትፈሪውም ሰው ነው፡፡ ለዛም ነው ከጭንቅላትሽ ማውጣት ያቃተሽ፡፡ ኡምቤርቶ ግን እያፈቀርሽው የምትሸሺው መላዕክሽ ነው፡፡ ኡምቤርቶን ታፈቅሪዋለሽ! ከአብዲ የምትፈሊጊው ወሲብ ነው! እንደ አራስ ነብር እያደረገ የአብዲን ገላ የሚያዘለዝልሽ በአብዲ ውስጥ የምታያቸው የደፈሩሽ ወንዶች እንጂ የአብዲ የወሲብ ክህሎት አይደለም፡፡ አንቺ ከወሲብ ጋር የተዋወቅሽው በስቃይ ነው፡፡ ለዛ ነው አብዲ እያሰቃየ ሲጋልብሽ የምትደሰቺው፡፡ አልፎተርፎም በፍቅሩ የተነደፍሽ መሰለሽና ለኡምቤርቶ ጀርባሽን ሰጠሽው ግን… ልብሽ ውስጥ ያለው ሰው ኡምቤርቶ መሆኑን አንቺ ሳትሆኚ ልብሽ ያውቀዋል፡፡ እውነቱ ይሄ ነው!»

እውነቱ ያለው እኔ ልብ ውስጥ ነው! ላወጣው አልፈልግም፡፡ ማንን? ለምን?… ልቤ ውስጥ ይቀመጥ! አልቤርቶ በሩን ገንጥሎ ገባ፡፡

«ምን እየሰራህ እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ?»

አልቤርቶ ኃይማኖት ላይ አፈጠጠ፡፡

«ፖሊስ ነው! መረጃ እየሰጠሁት ነው!… ስለ አብዲ!» ዘባረቅኩ፡፡

ማርኮ እና ሰለሞን እኔን ለኃይማኖት ትተው በረንዳ ላይ በመቀመጣቸው ቦክስ ቀምሰዋል መሰለኝ እንገታቸውን ደፍተው በር ላይ ተገትረዋል:: «ኡምቤርቶን ካገኛችሁት እንደማከብረው ንገሩልኝ!» ብዬ መነፋረቅ ጀመርኩ:: ሁሉም ግራ ተጋብተው ተያዩ:: አልቤርቶ ትእግስትን አሰቃይቶ እንዲገልልኝ ቃል አስገባሁት:: በሩ ስለተገነጠለ ብርድ ወደ ቤት እየገባ በመሆኑ ወፈር ያለ ጃኬት ለመደረብ ወደ መኝታ ክፍሊ ገባሁ::

ማስታወሻዬን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አገላብጬ ተመለከትኩት:: እንጥፍጣፊ ቀለም የቀረው ብዕሬን ጨበጥኩ:: የሚስጥሬ ተካፋይ ውዱ ማስታወሻዬ ሆይ... ውስጤ ተጎድቷል! እኔ እንደፈለግኩት ጀመርኩና ህይወት እንደፈለገችው ጨረስኩ:: ይሄ ለእኔ ሽንፈት ነው! ጥቂት ከቆየሁ ደግሞ ቁማሩን መበላቴን አምንና ስፀፀት እኖራለሁ! ፍትሕን በእጄ አግኝቻለሁ...! ሞትንም እንደዛው....! የብዕሬ ቀለም እየተቆራረጠ ነው:: የሰው ልጅ የመኖር ተስፋውም እንደዚሁ ነው! ለመሞት መወሰን እንዴት ይከብዳል?!... ምስገና ለሽንፈቴ ምክንያት ለሆነው ህይል!!

# ክፍል ዘጠኝ

## ምሥጢር

አብዲ ኡምቤርቶን እና ትእግስትን ለአልቤርቶ በሰላም ካስረከበ በኋላ አብዲ እና አልቤርቶ ጥሩ ጓደኛሞች ሆነዋል፡፡ አብዲ ተቀይሮ ውሀ ሲሆን፤ ኡምቤርቶ ደግሞ የለየለት እሣት ሆኗል፡፡ መቼም ትእንግርት ነው! አብዲ ባገባ በሳምንቱ ትእግስት እና ማርኮ ነገ በመዘጋጃ ቤት ይፈራረማሉ፡፡ ትእግስት እንደተመኘችው ማርኮን ስታገባ እኔ ሚዜ ልሆን ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ሥራ የአልቤርቶ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ አልቤርቶ ያዛል፤ ማርኮ ያለምንም ማንገራገር ይፈፅማል፡፡ እናም በአልቤርቶ ትእዛዝ ትእግስት ማርኮን የግሏ ልታደርገው ነው፡፡

በነገራችን ላይ፣ ኡምቤርቶ እና ወንድሙ፣ ኢትዮጲያ ውስጥ ወላጅ አልባ ለሆኑ ህፃናት ማሳደጊያ ማዕከል አቋቁመዋል፡፡ መልካም ነው! መኖሪያ ቤታቸውን ግን ሰው እንዲያውቀው አለመፈለጋቸው እስካሁን ለእኔ ምሥጢር ነው፡፡ ማርኮም ካልተጠራ በስተቀር ድርሽ ማለት አይፈቀድለትም፡፡ እነዚህ ሰዎች ስራቸው ሁሉ እንቆቅልሽ ነው! ለነገሩ በአሁን ሰዓት ሁሉም ነገር ለእኔ እንቆቅልሽ ነው!

ትእግስት ማርኮን ከነጠቀችኝ በኋላ፤ እራሴን መመርመር ጀምሪያለሁ፡፡ ማነኝ? ማን መሆን ነበረብኝ? ለማን ስል? ሁሉም ጥያቄ የየራሳቸውን መልስ ይፈልጋሉ፡፡ ኤሚ ለመኖር ስትፍጨረጨር፣ የጠፋውን ለማልማት ስትውተረተር፣ የፍትሕ ጥያቄ ጭንቅላቷን ሲያደማው፣ እንዲሁ እንደባተለች፣ መርዝ ጠጥታ ነው የሞተችው፡፡ እኔም እንደእሷ

ለጥያቄዬ መልስ ሳላገኝ የምሞት እየመሰለኝ እጨነቃለሁ፡፡ ኤሚ ከሞተች በኋላ ነገሮች ፍፁም ተቀይረዋል፡፡ ትእግስት እና ማርኮ የኤሚን ክፍል ወርሰዋል፡፡ እኔ ደግሞ ማስታወሻ ደብተሯን የግሌ አድርጌ እንደ ዳዊት እደግመዋለሁ፡፡

ኡምቤርቶን ከሰው ወደ አውሬነት የቀየረው የእምሮት እጦት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ሁሌም ከአፉ አይለያትም! አሁንም ቢሆን እንደሚያፈቅራት ነው የሚናገረው፡፡ ፍቅር አይሞትም አይደል?! እኔም ማስታወሻዋን ተደብቄ ሳነብ፣ ያገኘኋት፣ የዳበስኳት፣ መስሎ ይሰማኛል፡፡ አሁንም ቢሆን እወዳታለሁ! አዎ! አብዲ ቢረሳትም እኔ እና ኡምቤርቶ ሁሌም እናስታውሳታለን፡፡ ሰው እንዳያይሽ እያለ መከራዋን ሲያሳያት የነበረው ሰውዬ፣ በሞተች በወርዋ ትዳር መስርቶ ቁጭ ማለቱስ አይገርምም? ኡምቤርቶ ግን እድሜ ልኩን ሴት የሚባል የሚቀርብ አይመስለኝም፡፡ ልቡን እምሮት ይዛው ተቀብራለች፡፡

የኤሚ ማስታወሻ ደብተር ላይ ሦስት ባዶ ገፆች ስላገኘሁ ነበር የታዘብኩትን መፃፍ የጀመርኩት፡፡ ግን አንድ በጣም ማስፈር የምፈልገው ነገር አለ፡፡ ማርኮ እና ትዕግስት ሲፈራረሙ የሚሰማኝን ስሜት የኤሚ ማስታወሻ ላይ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፡፡ ፍቅረኛዬ የነበረ ሰው ሲያገባ ሚዜው እንድሆን ተፈረደብኝ፡፡ ሚዜ አልሆንም እንዳልል ከአልቤርቶ ጠቀም ያለ ገንዘብ ተቀብያለሁ፡፡ ብሩን እንዳልመልስ አጥፍቼዋለሁ፡፡ አማራጭ የለኝም! የፊርማው ስነስርዓት የሚፈፀመው ነገ ስለሆነ የተሰማኝን ስሜት በቀረችው አንድ ባዶ ገፅ ላይ መፃፍ የምችለው ነገ ማታ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የጠቆረውን ሰማይ ተገትሬ ስመለከተው አመሸሁ፣ ከከዋክብት ሌላ ምንም ነገር ሊያሳየኝ አልቻለም፤ እግሬ ሲዝል ጋደም ብዬ የኤሚን ማስታወሻ አገላበጥኩት፡፡ እኔን የሚጠብቅ አንድ ባዶ ገፅ አለ፡፡ ስለፌርማው ስነስርዓት መፃፍ ጀመርኩ፡፡

ጉድ እና ጅራት...

ከየት ልጀምር? እሺ!... ሱፌን ገጭ አድርጌ፣ ከኡምቤርቶ እና ከአብዲ ጋር ከማርኮ ጎን ፊቴን ዘፍዝፌ ተገትርኩ፡፡ ትእግስት ቬሎዋን ለብሳ፣ ሚዜዎቿን ከጎኗ አሰልፋ፣ ትፍለቀለቃለች፡፡ የትእግስት ጓደኞች፣ የአብዲ ጓደኞች፣ ብቻ በአጃቢ ተከበናል፡፡ ማርኮ ድንገት ትእግስትን ተሰናብቶ ከአዳራሹ ውልቅ አለ፡፡ አይኔን ጨፍኜ ገለጥኩት፡፡ ማርኮ የለም፤ ትዕግስት እራሷን ስታ በሚዜዎቿ ተከባለች፤ አጃቢዎች ይንጫጫሉ፤ ቅዠት እንጂ እውነት አይደለም እያልኩ ከራሴ ጋር ተሟገትኩ፤ ግን እውነት ነው! ምን እንደተሰማኝ በትክክል አላውቅም፡፡

አሁን ከምሽቱ 5:00 ሆኗል፡፡ ትእግስት እና ማርኮ እስካሁን ወደ ቤት አልተመለሱም፡፡ ድንገት ማርኮ በሩን ከፍቶ ገባ፡፡ ተመስገን! የት እንዳመሸ ስጠይቀው፣ ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ አቅፎ ጭምቅ አደረገኝ፡፡ አይኖቹ በስስት ተመለከቱኝ፡፡

«አንድ ምስጢር ብነግርህ ለማንም አትናገርም?» አለኝ፡፡

«እመነኝ!... ለማንም አልናገርም፡፡» አልኩት፡፡

«እንደነገርኩህ ቢያውቅ ይገለኛል!... ኡምቤርቶ እና ወንድሙ ከአብዲ ጋር እርቅ አውርደው እየኖሩ መሆናቸውን ታውቃለህ፡፡ ግን....



- አብዲ የሌሰኝነተሽ ፈውስ ነው! ለበቀል የምትፈልጊው እና እንደሰይጣን የምትፈሪውም ሰው ነው:: ሕምቤርተ ግን እያፈቀርሽው የምትሸሺው ... ነው:: ሕምቤርቶን ታፈቅሪዋለሽ! ከአብዲ የምትፈሲጊው ወሲብ ነው! ... እራስ ነብር እያደረገ የአብዲን ገላ የሚያዘለዝልሽ በአብዲ ውስጥ የምታያች... የደፈራሽ ወንዶች እንጂ የአብዲ የወሲብ ክህሎት አይደለም:: አንቺ ከወሲብ ጋር የተዋወቅሽው በስቃይ ነው:: ለዛነው አብዲ እያሰቃዩ ሲጋልብሽ የምትደሰቺው አልፎተርፎም በፍቅሩ የተነደፍሽ መሰለሽና ለሕምቤርተ ጀርባሽን ሰጠሽው:: ግን... ልብሽ ውስጥ ያለው ሰው ሕምቤርተ መሆኑን አንቺ ሳትሆኚ ልብሽ ያውቀዋል:: እውነቱ ይሄ ነው!!

* * * * * *

ፍቅር በእራሱ ዓለም፣ በእራሡ ኃይል የሚኖር፣ በመረጣቸው ሰዎች ልብ ገብቶ የሚያብረከርክ፣ በኃይል የተሞላ፣ በኃይል የተገነባ ንጉስ ነው:: ፍቅር በአይን አይታይም:: ልብሽ ውስጥ የገባ ቀን ግን ታዳምጪዋለሽ:: እኔ ልብ ውስጥ ... ባሳየውም እያዳመጥኩት ነው:: በፍቅር መንግስት ውስጥ አይን ያለው ... የሌለው እኩል ነው:: የፍቅር ዕርስት አይን ሳይሆን ልብ ነውና!! ... የማንረዳውን ነገር ፍቅር እያስተማረን ነው:: የምናየው በአይናችን እየ... እንሸወዳለን:: ማነው ልቡ የወደደውን ትቶ አይኑ ያየውን የመረጠ? አይ... ሳይሆን ልብሽ ካየኝ መቼም ቢሆን አንቺ የእኔ እና የእኔ ብቻ ነሽ::

Design: ... Printing
Mob: 09...
International Leadership Institute Printers 0111 24 99 97